በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2008/2009 ኦዲት ዓመት
የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት
አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ግንቦት / 2009
አዲስ አበባ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2008/2009 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም

1. **መግቢያ**

የዋና ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የህገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55/1 እና አንቀጽ 101/4 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

1.1. <u>የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ስርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤

- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌድራል መንግስት መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመ/ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያድረግ ይችላል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እንዳአስፈልጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤
- አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ ይህን ሂሳብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፤ መዘክሮች፤መዝገቦች ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥ ነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፤
  - የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አያያዝ፤አጠባበቅ፤ የሂሳብ አያያዝና ንብረት አስተዳደር በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈከለጊውን ምክር ይሰጣል፤
  - ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ጋር የፌዴራልና ክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤
  - ከክልል የኦዲት መ/ቤቶችና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

1.2. <u>የሪፖርቱ ዓላማ</u>

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 በአንቀጽ 13/1 እስከ 4 መሠረት በ2008/2009 የኦዲት ዓመት ባከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2008 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና

ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ የ2008/2009 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች መሰረት ያደረጉት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የ2008 በጀት ዓመት ሒሳብ፣ የአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግስት በገባው ውል መሠረት በብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤትና በመ/ቤታችን የተከናወኑ የልዩ ኦዲት ሥራዎችን ነው፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሣቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ስራም የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፤ የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት መሠረት በማድረግ እና በኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2008/2009 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የ2008/2009 የኦዲት ዓመት

የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፣ ዋና ዋና የስራዎች ክንውን ሪፖርት፣ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፣ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ ቀርቧል።

በሁለተኛው ክፍል የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የአካባቢና የክዋኔ ኦዲት፣ እንዲሁም መንግሥት ከዓለም ባንክ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሣብ ተከታታይ ኦዲትና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን ሂሳብ ኦዲት ውጤት ያጠቃልላል፡፡

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ የልማት ድርጅቶችና በመንግስት የልማት አጋራች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የኦዲት ውጤትን የሚመለከት ይሆናል፡፡

2. የ2008/2009 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ አምስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፣ የካቲት 1/2008 እስከ ጥር 30/2009፣ የ158 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና 48 የቅርንጫፎች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ በተያዘው መሠረት የ158 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና የ44 ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን የ158 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችና አንድ የመንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ የኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የተላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት

ከ2007/2008 ኦዲት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት	
	2007	2008
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	36	27
ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	66	73
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	6	5
የጎላ ችግር ያለባቸው፣ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	37	53
ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ/ሪፖርት ያልወጣ/	1	-
ድምር	**146**	**158**

2.2 <u>የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ ክትትል ተደርጓል፡፡

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከሐምሌ/2007 እስከ ጥር /2009 ዓ.ም አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ(ቀደም ሲል እስከ ሰኔ 30 የደረሱትን ብቻ ነበር ሲናቀርብ ነበር፣የበለጠ ወቅታዊ ለማድረግ እስከ ጥር 30/2009 ያለው ተካቷል) ሪፖርታቸው

ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 113 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 192 በድምሩ 305(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው የልማት ድርጅቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 258 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.3 <u>የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ</u>

የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል በመወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታተቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ይከናወናል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2008-2009 የኦዲት ዓመት (Audit Calendar) በሁለቱ ክዋኔ ኦዲት ደይሬክቶሬቶች ከየካቲት/2008 እስከ ጥር 30 የሚጠናቀቁ 18 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 8 /ስምንት/ የክዋኔ ክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች አፈጻፀም ሲታይ በእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው የ18 ለማከናወን በታቀደው ላይ አንድ ተጨምሮ የ18 ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላኩና ሲሆን፡ አንድ ስራው ተጠናቆ ኦዲት ሪፖርቱ በዝግጅት ላይ፣ ሲሆን፤ በ 7 ቀደም ባሉት ክዋኔ ኦዲቶች ላይ የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር ላይ የክትትል ኦዲት ተደረጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት የክትትል ኦዲቱ ሲጨመር ከ100% መሆኑን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 18 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶችና 7 የክትትል ኦዲት ሪፖርቶቹ ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶች በአጭሩ ቀጥሎ ከገጽ 69 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.4 <u>አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት</u>

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡

2.5 <u>የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት</u>

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተም የ2008/2009 ኦዲት ዓመት በ305 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ደረጃ)፣ ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋዊ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በኦዲት ዓመት የ238 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ተልኳል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅድ ወቅት ያልታወቀና በዕቅድ ያልተያዘ ነገር ግን ለመንግሥት ለሚደረገው የገንዘብ ፍሰት የኦዲት ሪፖርታችንን መሠረት የሚያደርገው በፍትሃዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮገራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services-ESPES, Program for Result) የገንዘብ ፍሰት አመልካቾችን የማረጋገጥ ሥራ (Verfication) በ64 ወረዳዎች በመከናወኑ አጠቀላይ ክንውኑን 302 ወረዳዎች ወይም የዕቅዱ 99.02% መፈጸም ተችሏል፡፡

2.6 **ልዩ ኦዲት**

መ/ቤታችን በዕቅድ ከያዘው የኦዲት ስራዎች በተጨማሪ በፍ/ቤትና በተለያዩ አካላት የተጠየቁ 8 የልዩ ኦዲት ስራዎችን አከናውኖ ለሚመለከታቸው ጠያቂ አካላት ሪፖርት አቅርቦል፡፡

2.7 **የኦዲት ጥራትና ሌሎች የኦዲት ሥራዎች**

የኦዲት ጥራትና ቁጥጥር በመ/ቤቱ የሚከናወኑ የኦዲት ሥራዎች በጥራት እና ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ዕገዛና ድጋፍ ለማድረግ የተዋቀረ ሲሆን ታቅደው የተከናወኑ ሥዎች ኡንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም ለበጀት ዓመቱ የታቀደ ካለፉት ዓመታት የዞሩ 10 የጥራት ማረጋገጥ ሥራዎች፣ 8 በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀዱ የድህረ ኦዲት እና 12 በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀዱ ቅድመ ኦዲት (ፕሪኢንጌጅመንት) የጥራት ማረጋገጥ ሥራዎች እና ከሪፖርት በፊት የስትራቴጂክና የዝርዝር ዕቅድ የጥራት ማረጋገጥ ሥራ በ15 መ/ቤቶች ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሲሆን ከሪፖርት በፊት የጥራት ማረጋገጥ ሥራ በ3 መ/ቤቶች ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን 3 መ/ቤቶች ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል

ተ.ቁ	መግለጫ	ዕቅድ	አፈጻጸም	ምርመረ
1	ከለፉት ዓመታት የዞረ ከመስክ እስከ ሪፖርት ጥራት ማረጋገጥ	10	10	
2	በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀደ የድህረ ኦዲት	8	8	
3	በበጀት ዓመቱ የታቀደ ቅድመ ኦዲት (የፕሪ ኢንጌጅመንት ስራዎች)	12	12	
4	የስትራቴጂክና የዝርዝር ዕቅድ ሥራ ጥራት ማረጋገጥ (ከሪፖርት በፊት)	15	15	
5	ከመስክ እስከ ሪፖርት ጥራት ማረጋገጥ(ከሪፖርት በፊት)	6		በ3 መከናወን ላይ
	ድምር	51	48	3

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የኦዲት ጥራት ሥራን በተሻለ ለማገዝ ለመ/ቤቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ለመ/ቤቱ ያልደረሱ ደንቦችና መመሪያዎች ለሠራተኞች ተደራሽ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም የመ/ቤቱን የኦዲት ጥራት ከፍ ለማድረግ የዓለም ባንክ አማካሪዎችን ለመቅጣርና ለመደገፍ ጨረታ ወጥቶ በሂዳት ላይ ያለ ይገኛል፡፡ የ2008/09 የኦዲት ዕቅድ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ የኦዲት ጥራት መሆኑ፤ እያንዳንዱ ኦዲት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ኦዲቱን ስለማከናወኑ የሚያረጋግጥበትን በዕቅዱ ውስጥ አካቶ እንዲያከናውን ከስምምነት ተደርሷል፡፡

3. ሌሎች ዋና ዋና የዕቅድ ክንውኖች

3.1 የመ/ቤቱን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ

የመ/ቤቱ ፋ/ግ/ንብረት አስተዳደር ቀልጣፋና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ መፈጸም፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ሂሳቦችን /ሰነዶችን/ በፍጥነት ማወራረድ እንዲሁም ክፍያ የተፈፀመባቸውን ሰነዶች መዝግቦና አደራጅቶ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ማስመርመርና ከኦዲተሮች ለሚነሳ ጥያቄ ምላሽ መስጠት፣ሁሉም ግዢዎች በመንግሥት የግዢ አዋጅና ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈፀሙ በማድረግ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው የግዢ ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣ የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የግዥ እቅድ አዘጋጅቶ ለግዥ ኤጀንስ እና ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ማቅረብ፣ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በሚፈለገው ጥራት መጠንና ተመጣጣኝ በሆነ ወጪ ገዝቶ በወቅቱ ማቅረብ፡ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ የፋይናንስና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት እና በየወሩ የዜሮ ሚዛን እንቅስቃሴ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ማቅረብ፣ የመ/ቤቱን ንብረት አጠቃቀምና አያያዝ እንደዚሁም ቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር፣ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ማከናወን፣ ዋንኛዎቹ ሥራዎች ናቸው፡፡

3.2 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

በ2008/2009 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አሠራር መሠረት የመ/ቤቱ የኦዲት ዓመት (በጊዜያዊነት የተስተካከለ) ከየካቲት 1/2008 - ጥር 30/2009 ቢሆንም፤ የ2008 በጀት ዓመት የተስተካከለውና ሥራ ላይ የዋለው በጀት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

ተ.ቁ	የወጪ አርዕስት	የበጀት ኮድ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ ያልዋለ	በመቶኛ
1.	ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች	6100	35,220,107.10	34,903,600.16	316,506.94	99.1
2.	ለአላቂ እቃዎች	6200	7,815,480.00	6,142,526.24	1,662,683.84	95.2
3.	ለቋሚ ንብረቶችና ግንባታ	6300	922,665.59	922,665.59	0.00	100
4.	ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ	6400	191,360.00	173,315.22	18,044.78	90.6
	ድምር		44,149,612.69	42,142,107.21	2,007,505.48	95.4

በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የበጀት አፈፃፀሙ 95.40% ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ሂሳቡም በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በተመደቡ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጓል፡፡

በሌላም በኩል 2009 በጀት ዓመት ለመ/ቤቱ ሥራ በአጠቃላይ ተፈቅዶ የጸደቀው በጀት ብር **66,598,550.00** ሲሆን ከተመደበው በጀት ውስጥ በ9 ወራት ውስጥ ሥራ ላይ መዋል የነበረበት ዕቅድ ብር **49,776,412.50 ሲሆን አፈጻጸሙም** ብር **71,878,576.34** ወይም **144.40% በጀት** ሥራ ላይ ውሏል፡፡

የበጀት አጠቃቀሙ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	የ9 ወራት ዕቅድ	የ9 ወራት አጠቃቀም	የ9 ወራት ከወጪ ቀሪ	አፈጻም በ%
6100	55,897,932.00	41,923,449.00	40,977,136.39	946,312.61	98
6200	10,307,290.00	7,730,467.50	5,086,709.57	2,643,757.93	66
6300	12,854,880.00	9,641,160.00	4,343,833.00	5,297,327.00	45
6400	230,000.00				
ድምር	**79,290,102.00**	**59,295,076.50**	**50,407,678.96**	**8,887,397.54**	**85**

ማስገንዘቢያ፡- ለ9 ወራት ከታቀደው በላይ አጠቃቀሙ ከፍ ያለበት ምክንያት በጀቱ ተፈቅዶ ከመጠ በኃላ በርካታ ሠራተኞች በመቀጠራቸው ምክንያት የተከፈለ የደመወዝ ክፍያ መሆኑን፡፡

በሌላ በኩል የመ/ቤቱን የ2009 በጀት ዓመት ግዥን በዕቅድ ለመምራት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ የተዘጋጀ ሲሆን ዕቅዱም በግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ በማስገምገምና በማጸደቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተልኳል፡፡ በመሆኑም ግዢዎችም በፀደቀው ዕቅድ መሠረት እንዲፈጸም በማድረግ እና በመንግሥት የግዢ አዋጅና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት እንዲፈፀሙ በማድረግ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው የግዢ ሥርዓት መኖሩን በማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል፡፡

ጠንካራ የንብረት አያያዝ፤ አጠቃቀም እንዲሁም አወጋገድ ሥርዓት፣ የንብረት አጠቃቀምና አያያዝ በተመለከተ የቋሚና አላቂ ንብረት ምዝገብ በማዘጋጀትና ምዝገባ በማከናወን፤ ዓመታዊ የአላቂና ቋሚ ንብረት ቆጠራ በማካሄድ ከመዝገብ ጋር በማስታረቅ የንብራት አስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓት ለማጠናከር ተገቢው እርምጃ ተወስዷል፡፡

3.3 <u>የመረጃ አስተዳደርና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ</u>

የመ/ቤቱን ሥራዎች በማገዝና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና በዘመናዊ ዘዴ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመገንባት ደህንነቱ የተጠበቀና የተደራጀ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግና ሠራተኛውን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም በማብቃት የሥራ አካባቢን በመፍጠር በተቋም ደረጃ የተቀረጹ ዓላማዎች፣ ግቦችንና ራዕይን ማሳካት፣ የመ/ቤቱ አጠቃላይ መረጃዎችና የመረጃ ማዕከሉ ሲስተሞች ኮንፊጌሬሽን ፋይሎች በተገቢው ሁኔታና መንገድ መያዛቸውን የማረጋገጥ መከታተል ሥራዎች በመሥራት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱን ማዕከላዊ የመረጃ ቋት (Integrated Centralized Database Management System) ለማደራጀት እና የኦዲት ግኝቶችን በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ማሰባሰብና ክትትል ማድረግ የሚችል ሥርዓት (Audit Recommendation and Tracking System) ለመዘርጋት በDFID ፕሮጀክት አማካኝነት መጠናቀቅ

የነበረበት ቢሆንም በዕርዳታ ሰጪው ድርጅት የአሰራር ሂደት ምክንያት ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣የመረጃ መዕካሉ ሥራ በአሁኑ ወቅት ዕቃ አቅራቢዎቹ የተለዩ በመሆኑ የግዥ ሂዳቱ በቅርቡ የሚጠበቅ መሆኑን፣ፕሮጀክቱም ሙሉ በሙሉ ሲተገበር የመ/ቤቱ መረጃ አያያዝና አሠራር ሥርዓት በመሠረታዊነት እንደሚለውጥ ይጠበቃል፡፡ የዳታ ማዕከሉ ባይጠናቀቅም በአሁኑ ሰዓት Corporate E-Mail System ተዘጋጅቶ ለሁሉም ሠራተኛ አድራሻ እንዲያገኝ መደረጉን፣ በተቋሙም ወረቀት የማተም ሥርዓት እንዲቀንስ በታቀደው መሠረት ሥርዓቱን በማጠናከር Paper less Office concept ለመተግበር ሰፊ ሥራዎች የተሠሩ ይገኛል፣

ለመ/ቤቱ የሚያስፈልጉ የመረጃ ቴክኖሎጂ መጠቀሚያ መሳሪያዎች፣ ሲስተሞችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ለማድረግ የጥናትና የሰነድ ዝግጅት ማድረግ፣ አጠቃላይ የኦዲት ግኝቶችን በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ማሰባሰብና ግኝቶች ላይ ክትትል ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት (Audit Recommendation and Tracking System) ለመዘርጋት የተለያዩ ጥናቶችን የማከናወንና የፍላጎት ዝርዝር መግለጫ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፣

የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ቀጣይነት እና ከአደጋ ማገገሚያ (Business Continuity and Disaster Recovery Plan) እቅድ ማዘጋጀት፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ፖሊሲን (IT Policy) እና የደህንነት ፖሊሲን (IT Security Policy) የመከለስ ሥራ ተሰርቷል፣ የመ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች የሥምሪት አሠራራቸውንና ቁጥጥሩን ለማገዝ የሚረዳ ሥርዓት (Fleet Management System (GPS)) ለመዘርጋት የተለያዩ ጥናቶችን የማከናወንና የፍላጎት ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት፣ በመ/ቤቱ ውስጥ የመረጃ ቴክኖሎጂ ኦዲት (IT Audit) የማቋቋም ሥራ መሥራት፣ በመረጃዎች ላይ ለሚደርስ ድንገተኛ አደጋ መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል በርቀት ያለ ተጨማሪ ቦታ (Disaster Recovery Site) የማደራጀት ሥራ መሥራት፣ የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተለያዩ ሥርዓቶች ለውጥ አስተዳደር (Change Control Policy and Procedures) ሥርዓት ሰነድ ማዘጋጀትና መሥራት ተችሏል፡፡

3.4 <u>አደረጃጀትና የሰው ሀይል አቅም ግንባታ በተመለከተ</u>

የሰው ሀብት ሥራ አመራር እና አቅም ግንባታ አንጻር በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አጠቃላይ ተቋማዊ ለውጥ መርሃ ግብር በተካሄደው ጥናት መሠረት የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም ሙሉ በሙሉ ማሳደግ፤ ለሠራተኞች ምቹ □ሥራ አካባቢ መፍጠር፣ የሰው ሀብት ዕውቀትና ክህሎት እንደዚሁም ሥነ-ምግባርና አመለካከት የሚያሳድጉ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች መንደፍ፣ በዋነኛነት የሠራተኛውን አመለካከትና ቁርጠኝነት በማሳደግ በሙሉ አቅሙ ለተልዕኮው ስኬት እንዲረባረብ የሚያግዘው ዋነኛው መሣሪያ ነው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቱ የተሰጡትን የሥራ ኃላፊነትና ተግባራት በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለውን የሰው ኃይል አቅርቦትና ብቃት ለማሳደግ ያልተቋረጠ ጥረት በማድረግ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 645 እና ለድጋፍ ሰጪ 314 በድምሩ 959 ሲሆን፣ በየካቲት ወር 2008 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 268 ኦዲተሮችና 145 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 413 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 156 ኦዲተሮችና 89 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 245 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ ከድጋፍ 1 እና ከኦዲት 3 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 1

በሞት የተለዩ 3 በዲሲፒሊን ቅጣት፣ 42 አዲተሮችና 25 ድጋፍ ሰጪ 29 በድምሩ 54 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን በአጠቃላይ በኦዲት ዓመቱ 71 ሰው ኃይል ከመ/ቤቱ ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 265 ወንዶችና 135 ሴቶች በድምሩ 400፣ የድጋፍ ሰጪ 89 ወንዶችና 115 ሴቶች በድምሩ 204 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአጠቃላይ 604 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 355 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ እነኚህ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሙለት መ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ጥረት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በመ/ቤቱ ውስጥ 37 ሰርቪስና ጥገና የሚያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ገብተው ሰርቪስና ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ፣ 25 መኪናዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በኩል የተገዙ አራት ተሽከርካሪዎችን በመረከብ የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙና የሠሌዳ ቁጥር እንዲሠጣቸው ተደርጎ ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

በሌላ በኩል የመ/ቤቱን የሰው ሀብት፤ የቤተ-መጽሀፍትና መዝገብ ቤት ሥራዎችን በመረጃ ቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራዎች ተጀምረው መረጃዎችን ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ እስከ አሁን በተደረጉ ጥረቶች የመ/ቤቱ የሰው ሀይል እየተጠናከረ የመጣ ቢሆንም ከፍተኛ የብቃት ችግር የሚታይ በመሆኑ ቀጣዩ ሥራና ትኩረት እየተደረገ ያለውን የሥልጠና ማዕከል ሥራ በመፋጠን የሠራተኛውን ብቃትና ክህሎት በመገንባት አቅሙን በማሳደግ የመፈፀም አቅሙን ከፍ የማድረግ ሥራ ይሆናል፡፡

3.5 ከውጭና ህዝብ ግኙኙነት አንፃር

የውጭና የሕዝብ ግንኙነት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ተልዕኮ፤ ራዕይና ዓላማዎችን ለማሳካት በሚደረገው ርብርብ ሁሉን አቀፍ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም የውስጥና የውጭ ኮሚኒኬሽን ተግባራትን በማከናወን የተቋሙን

መልካም ገፅታ ለመገንባት፣ ወቅታዊና ትክክለኛ የተቋሙን መረጃ ለሠራተኛው፣ ለባለድርሻ አካላትና ለህብረተሠቡ እንዲደርሳቸው በመስጠትና በማሳወቅ በኦዲት ውጤቶች ላይ የጋራ መግባባት በመድረስ ተግባራዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችል የህዝብ ግንኙነት ሥራ ተሰርቷል።

በቋሚነት በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የወጡ ዜናዎችንና ጽሁፎችን በተመሳሳይም በኤሌክትሮኒክ ሚድያዎች ሞኒተር የማድረግ ስራ መስራት፣ የ5 ዜናዎችን ሞኒተር የማድረግና ዳውን ሎድ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት የመላክ ስራ ተሰርቷል።

ለመፅሔት የሚሆኑ 7 የተለያዩ አርቲክሎችና ሁለት ቃለመጠይቆች፣ በመ/ቤቱ የተከናወኑ 15 ዜናዎች በዜና መጽሄቶች እንዲወጡና በሰሌዳ ላይ እንዲለጠፉ፣ የመ/ቤቱን የተመለከቱ ጉዳዮችን ዙሪያ መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል። ፐብሊክ ሒሪንግ የተካሔደባቸው 3 ዜናዎችና 1 ልዩ የግብረመልስ መድረክን የተመለከቱ 4 ዜናዎች የተዘጋጁ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 3ቱ የፐብሊክ ሒሪንግ ዜናዎች በአውትሉክና በዌብ ሳይት ላይ ተጭነዋል።

ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ለመጡ 76 ተማሪዎች እንዲሁም ከተቋማት ለመጡ 9 ባለጉዳዮች መረጃ ተሰጥቷል። በውጭ ኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ ውስጥ ያሉ የኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። በተቋሙ የተከናወኑና ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያላቸውን 15 ዜናዎች እንዲሁም የሚዲያ ፖሊሲ በተሟላ መንገድ መተግበር (የሚዲያ ፖሊሲውን ለሚዲያ አካላት በድረ-ገፅ እና ፌስቡክ ላይ በመጫን እንዲገነዘቡት ማድረስ ተችሏል።

በቻይና በተደረገው የእንግሊዝኛ ተናጋሪ የአፍሪካ ሀገራት ዓለም አቀፍ የኦዲት ሴሚናር ላይ በመገኘት ከተለያዩ ሀገራት የኦዲት ሀላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ግንኙነት የመፍጠርና ልምድ የመለዋወጥ ሥራ ተሰርቷል። የ2007 በጀት አመት የኦዲት ሪፖርት መጽሄት ለተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች በማሰራጨት የመ/ቤቱን አርማ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል።

3.6 የለውጥ ሥራ አመራርና መልካም አስተዳደርን በተመለከተ

በመ/ቤቱ የሚታዩና በተለያየ መንገድ የሚገለጹ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመለየት የሥራ አመራሩ በጋር በመሆን ችግሮችንና መገለጫዎቻቸውን የለየ ሲሆን ይህንኑ ለአጠቃላይ ሠራተኛ በማቅረብ ግልጽና ዝርዝር ውይይት በማድረግ ችግሮች በሁሉም ተሳትፎ መፈታት እንደሚኖርባቸው ከስምምነት ተደርሶ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የራሱን ዕቅድ እንዲያዘጋጅ በማድረግ ሥራዎች በዕቅዱ መሠረት ማከናወን፣ በመልካም አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅት ላይ የምክር እና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣ የዉጤት ተኮር ዕቅድ፣ ኦፐሬሽናል ፕላን በማዘጋጀት.../ ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ መስጠት፣ ውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት ለመተግበር ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የሚሉት ዋና ዋና የተከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የBSC ጥናት ሰነድ በማዘጋጀት የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ተግባራት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ የመስጠት ሥራ ለሚመለከታቸው ተሰርቷል፡፡ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ስኮርካርድ በማዘጋጀት እስከ ግለሰብ ድረስ በማውረድ ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የሥራ ክፍሎችም በየሳምንቱም ሥራው በታቀደው መሠረት መከናወኑን መገምገም የጀመሩ በመሆኑና ከዚህ በፊት ሲያጋጥሙ የነበሩት ችግሮች እየተፈቱ መምጣታቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሰነድ ላይ በቀጣይ ሁሉም ፈፃሚዎች በስኮር ካርዱ መሠረት እንደሚመዘኑና የሥራ አፈፃፀሙም እንደሚለካ አስፈላጊውን ግንዛቤ በመፍጥር ሁሉም የሥራ ክፍሎች ከአሁን ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባቸው የማሳወቅ ሥራ ተሠርቷል፡፡፣

3.7 የመ/ቤቱ ህግ ጉዳዮች በተመለከተ

መ/ቤቱ በሚከሰስባቸውም ሆነ በሚከስባቸው ጉዳዮች ላይ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በመከታተልና አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ፣ በፍ/ቤት የሚገኙትን የፍ/ብሔር ክርክሮችን እና በዲሲፕሊን ኮሚቴ ክስ የቀረበባቸውን ጉዳዮች ተከታትሎ ከግብ ማድረስና ይግባኝ የሚቀርብባቸው ላይ ክትትሉን አጠናክሮ

መቀጠል፣ ከመ/ቤቱ ከሁሉም የሥራ ክፍሎች ለሚቀርቡ የቃልም ሆነ የፅሑፍ ጥያቄዎች የህግ አስተያየትና ምክር መስጠት፣ መ/ቤቱ ከውጭ አካላትና ግለሰቦች ጋር ለሚያደርጋቸው ስምምነቶች የውል ሰነድ ማዘጋጀት የሚጠበቁ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

በመሆኑም መ/ቤቱ በመደበኛ ፍ/ቤት ላይ ባሉ አስራ አንድ የፍ/ብሔር ክርክሮች በቀጠሮው በመገኘት በየደረጃው ተገቢውን የሕግ መከራከሪያ በማቅረብ ክርክር ተደርጓል፡፡ መዝገቦቹም በተለያዩ አጀንዳ በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ የመ/ቤቱ ማሻሻያ ማቋቋሚያ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በኩል አዋጅ ቁጥር 982/2008 ሆኖ በመጽደቅ በስራ ላይ ውሏል፡፡ የተሻሻለውን ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በማድረግም የመ/ቤቱን ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ በማርቀቅ እና የመ/ቤቱን የተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀትና ማቅረብ ታችሏል፡፡

በሶስት የምዕራብ ወኪል መ/ቤት ሠራተኞች የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ባቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ ላይ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ ሲሆን ተከሳሾችም የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተው መዝገቡ ለምርመራ ተቀጥሮ ይገኛል፡፡ ከኦዲተሮች እጅ የጠፋ ላፕቶፖችን በተመለከተ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ወንጀለኞች እንዲያዙና ንብረቶቹ እንዲመለሱ ፖሊስ ጣቢያ የከሳሽነት ቃል በማስመዝገብ ተገቢውን ክትትል ተደርጓል። በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች መብትና ግዴታ እንዲሁም ተጠያቂነት ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ እንዲጨብጡና መብትና ግዴታቸውንም ለይተው በማወቅ የተሻለ ሥራ እንዲሰሩ የሚያስችል የመተዋወቂያ ሥልጠና በመ/ቤታችን ለተቀጠሩ አዳዲስ ሠራተኞች ተሰጥቷል፡፡

በመ/ቤታችን ከሁለት ቀደም ሲል የመ/ቤቱ ሰራተኞች የነበሩት ላይ ክስ መስርቶ በፍ/ቤት በተሰጠው ብይን አንደኛው ተከሳሽ ብር 16,610.63 (አስራ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አሥር ብር ከስልሳ ሦስት ሳንቲም) እና ሁለተኛው ተከሳሽም 256 ፓውንድ በቀን 26/03/2009 ዓ.ም በሚኖረው የፓውንድ ምንዛሬ ተመን መሠረት፤እንዲሁም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ ውሳኔው

ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለመ/ቤታችን እንዲከፍሉ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

3.8 ዘርፋ ብዙ ጉዳዮች ሴቶችና ወጣቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ስርዓተ ጾታ ዙሪያ

የመ/ቤቱን ሠራተኞች ሴቶችና ወጣቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ስርዓተ ጾታ ዙሪያ በቂና አስተማማኝ የሆነ መረጃ በማዘጋጀት በተቋሙ ውስጥ ሰፋ ያለ ግንዘቤ እንዲፈጠር ማድረግ ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የመ/ቤቱን ሠራተኞች የፆታ እና የዕድሜ መረጃ ዝርዝር ማዘጋጀት፣ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ የሴቶች ቀን፣ የፀረ-ጾታ ቀን እንዲሁም የሴቶችን ፎረም በሚመለከት ዓላማዉንና አስፈላጊነቱን የያዘ ብሮሸር በማዘጋጀት በአዉትሉክ በማሰራጨት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የመ/ቤቱን ስትራቴጅክ ዕቅድ ከስርዓተ -ጾታ አንጻር እንዲቀኝ ተደርጓል፡፡ የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች ፎረም ረቂቅ የፎረም መተዳደርያ ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡

ማርች 8/ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን የሴቶች ማረፊያ ልማት ማህበር በመሄድ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ጉብኝትና የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ስራዎች ተሰርቷል፡፡

የአፈጻጸም ሪፖርቶች ከስርዓተ ፆታ አንፃር በመገምገም ግብረ መልስ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ የመ/ቤቱ ሠራተኞች መረጃ በመውሰድ በማጠናከር ለሚመለከተው አካል ተደራሽ የማድረግ ስራዎች ተሰርቷል፡፡

በሌላ በኩል አነስተኛ የገቢ ምንጭና ዝቅተኛየትምህርት ደረጃ ላላቸዉ የመ/ቤቱ 30 ሴት ሰራተኞች በመሰረታዊ የንግድ ክህሎት፣በግማሽ ክፍያና ነጻ የርቀት ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተቋማትን በማፈላለግ ለ9 ሴት እና ለ5 ወንድሠራተኞች በዲፕሎማ፣ለ11 ሴት እና ለ3 ወንድ ሠራተኞች በዲግሪ እንዲሁም ለ5 ሴት ሠራተኞች ከ5ኛ-7ኛ ክፍል እና ለ1 ሰራተኛ የግማሽ ክፊያ እና ሁለት ሠራተኛ የነፃ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በአጠቃላይ ብር 105,150.00 ለሠራተኞች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

3.9 **የውስጥ ቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ**

የመ/ቤቱ ሀብትና ንብረት ከምዝበራ፣ ከማጭበርበር፣ ከስርቆት፣ አላግባብ ከመጠቀምና ከብልሽት መጠበቁን፣ የሚዘጋጁት የፋይናንስ መግለጫዎች ትክክለኛና ተአማኒነት ያላቸው መሆኑን፣ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በኦዲት በማረጋገጥ እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በመፈተሸ፣ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን በማጣራት እንዲሁም የመ/ቤቱ አመራሮች፣ሠራተኞችና ሌሎችም የሚጠይቁትን ሙያዊ የምክር አገልግሎት በመስጠትና በማገዝ የመ/ቤቱ ዓላማ፣ ተልዕኮና ግብ እንዲሳካ ጥረት በድረግ ከፍተኛ ሚና እየተጨወተ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ለውስጥ ኦዲት ያወጣቸውን ደረጃዎች ህጎችና ደንቦች፣ መመሪያዎችን ተከትሎ የኦዲት ሥራዉን ለማከናወን ሐምሌ1/2008 እስከ ታህሳስ 30/2009 በጀት ዓመት ከሣጥንና ከባንክ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ የዋለው የመደበኛ የገቢና የወጪ ሂሣብ እንቅስቃሴና አፈጻጸም ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን ለማረጋገጥ የኦዲት ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን በተገኙ ግኝቶች ላይ ተመርማሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተልኳል፡፡ የ2008 በጀት ዓመት የመ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀም ማመዛዘኛ ተዘጋጅቷል፡፡

የደቡብ ወኪል መ/ቤት የፋይናንስና ንብረት ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ የ2008 በጀት አመት ከወጪ ቀሪ ቆጠራ መሰረት ፈሰስ መደረግ የሚገባቸው ሂሣብ ለ/ገ/ኢ/ት/ሚ/ቀርቧል፡፡ የአላቂና ቋሚ ንብረት ቆጠራ በደንብና መመሪያ መሰረት መሆኑን ተረጋግጦ የአላቂ እቃዎች ማመዛዘኛ ተሰርቶ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ሙያዊ የሥራ ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ለሚፈልጉ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ሐምሌ 1/2007 እስከ ሰኔ 30/2008 በጀት ዓመት ከሣጥንና ከባንክ ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ የዋለው የመደበኛ የገቢና የወጪ ሂሣብ እንቅስቃሴና አፈጻጸም ደንብና መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን የማረጋገጥ ስራ በድጋሚ ተሰርቷል፡፡ የ2008 በጀት አመት የነደጅ ከሽ ኩፖን አጠቃቀም ልዩ ኦዲት ተደርጓል፡፡

4. መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፤ በሥራ ሂደት እየተፈታተኑን ከሚገኙ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ሁሉም መ/ቤቶች ሂሳባቸውን የበጀት ዓመቱ እንዳለቀ እስከ መስከረም 30 ዘግተው ሂሳቡን ለኦዲት ማቅረብ ቢኖርባቸውም 72 መ/ቤቶች ወይም 46.83% (ዝርዝሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ) የሚሆኑት ሂሳባችውን ከመስከረም 30/2007 በኋላ ከጥቅምት1/2009 እስከ ጥር 24/2009 ዓ.ም ድረስ አዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ በመሆኑ፤ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በታሰበው ጊዜ ማጠናቀቅ አለስቻለንም፡፡ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሂሳቡን ዘግተናል ብለው ከሰጡን መ/ቤቶችም ውስጥ የማይናቅ ቁጥር ያላቸው አልዘጉም ተብሎ ስማቸው እንዳይነሣ እንጂ መረጃዎችን በሚገባ አሟልተው ባለመሆኑ ሥራችንን በወቅቱ በዕቅዳችን መሠረት እንዳናጠናቅቅ ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርጎብናል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር መሻሻል ያሳየ ቢሆንም፤ አሁንም አልፎ አልፎ የሥራ ቦታ ያለማመቻቸትና ማስረጃ ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፤ ኦዲተሮች ሥራቸውን አጠናቀው የመውጫ ስብሰባ አድርገው ከወጡና ወደ ሌላ ሥራ ከተሰማሩ በኃላ በኦዲት ወቅት ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት መ/ቤታችን ድረስ ይዘው የማምጣት፣ በመጀመሪያው የመውጫ ስብሰባ ላይ ባለመገኘት ድጋሚ እንዲደረግ መጠየቅ፤ ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ በጣም ብዙ በኦዲቱ ወቅት ሊቀርቡ ይችሉ የነበሩ ማስረጃዎች የማቅረብ ሁኔታዎች የሚታዩ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህ ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን በተገቢው ጊዜ ሊወጡ ይገባል፡፡

5. ማጠቃለያ

በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት የተደረጉ በመሆኑ የፋይናንስና ህጋዊነት

ኦዲት ዕቅዱን መቶ በመቶ መፈጸም የተቻለ ከመሆኑም በላይ ባለፉት ዓመታት የተረጋገጠውን የ100.00% የኦዲት ሽፋን አፈጻጸም ለማስቀጠል ተችሏል፡፡

የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምም ቢሆን 18 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲትና 8 የክትትል ኦዲት በማከናወን 26 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 18 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲትና የ7 ክትትል ኦዲት ሪፖርቶችን ጨምሮ 25 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርጓል፡፡ በቀሪው 1 የክትትል ኦዲት ምትክ ሌላ አዲስ የክዋኔ ኦዲት ተጀምሮ የተጠናቀቀ ሲሆን የመውጫ ስብሰባ ብቻ ባለመደረጉ ሪፖርቱ ወጪ አልሆነም፡፡ ይህን ሣይጨምር የዕቅድ ክንውኑ 96.15% ነው፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ305 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ238 (78.00%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅድ ወቅት ያልታወቀና በዕቅድ ያልተያዘ ነገር ግን ለመንግሥት ለሚደረገው የገንዘብ ፍሰት የኦዲት ሪፖርታችንን መሠረት የሚያደርገው በፍትሃዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮገራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services-ESPES, Program for Result) የገንዘብ ፍሰት አመልካቾችን የማረጋገጥ ሥራ (Verfication) በ64 ወረዳዎች በመከናወኑ አጠቀላይ ክንውኑን 302 ወረዳዎች ወይም የዕቅዱ 99.02% መፈጸም ተችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት ሁሉም የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በየዓመቱ ኦዲት እየተደረጉ በየተቋመቱ የሚታዩ የፋይናንስ አስተዳደርና የንብረት አጠቃቀም ክፍተቶች እየተለዩ ቢሆንም በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ እርምጃ በበቂ ደረጃ ባለመወሰዱ ከሞላ ጎደል በየዓመቱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ግኝት ሆነው በመታየት ላይ ናቸው፡፡ በቂ ትኩረት ቢሰጣቸው ኖሮ እነዚህ ጉድለትና ክፍተቶች ሊታረሙ የሚችሉ ናቸው፡፡

ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ የተጠናከረ ክትትል ሊያደርጉና ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱና ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ24 ጥራዝ

ተዘጋጅቶ ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላከ በመሆኑ ሪፖርቶቹን በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ተመርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በዚህም ምክንያት እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በ2008 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲትም ወቅት የውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት የግንባታዎች ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በወቅቱና በተያዘላቸው በጀት ያለመጠናቀቅ፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፣ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች አሁንም ዋንኛ ግኝቶች ሆነው ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም እነኚህን ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ሊያቃልሉ እንደሚችሉ የታመነባቸው የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁሟል፡፡

ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ የመጀመሪያው እርምጃ አዳዲስ ውዝፎች እንዳይፈጠሩ ጥብቅ የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶና መ/ቤቶች ሀላፊነት ወስደው እንዲፈጽሙ ማድረግና ሥርዓቱንም ለበጀት ጥያቄ እንደቅድመ ሁኔታ መጠቀም፡፡

የቆዩ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ ጊዜ ገደብ ተቀምጦ በተቀመጠው አሠራር መሠረት እንዲሰበሰብ ወይም እንዲከፈል ወይም እንዲወራረድ ወይም ከመዝገብ እንዲሠረዝ እንዲደረግ፡፡ ነገር ግን በዚህ መሠረት መፍትሄ ማምጣት ካልተቻለ ለምን በተቀመጠው አሠራር ሂሳቦቹን መሰብሰብ ወይም መክፈል ወይም ማወራረድ ወይም ከመዝገብ መሠረዝ እንዳልተቻለ ዝርዝር መረጃ ተሰብስቦና ተጣርቶ ሌሎች አማራጭ እርምጃዎችን መውሰድ፣

ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ በጅምር ላይ ያሉ የቴክኖሎጂ አመራጮችን በማስፋት የታክስ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት ማዘመን፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ማሳደግ፣ ያለደረሰኝ የሚደረጉ ግብይቶች በደረሰኝ ብቻ የሚሆኑበትን ሥርዓት አስገዳጅ ማድረግና መተግበር፣ ወደ ግብር መረብ ያልገቡትን ማስገባት፣ ህጋዊ ያልሆኑ ንግዶችን ከንትሮባንድን ጨምር ቀጠይነትና ዘላቂ በሆነ

ሥርዓት መቆጣጠር፤ በቀጣይነት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ላይ መሥራት፤ የገቢ ሰብሳቢ ተቋመትን አቅም መገንባት፤

ከግንባታ ጋር ተያይዞ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡ ሊሆን የሚገባው የመጀመሪያው እርምጃ ለፕሮጀክቶች በጀት ከመፈቀዱ በፊት በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረቱ፤ የተሟላና የተረጋገጠ ዲዛይን ያለቸው፤ እንዲሁም ግልፅና ተጨባጭ የትግበራ መርሀ ግብር የተዘጋጀላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ብቻ በጀት ሊፈቀድ ይገባል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ጥብቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ኖሮአቸው ሊመሩ ይገባል፤፤ በሦስተኛ ደረጃ በማንኛውም የመንግሥት ግንባታ (በፌዴራልም ይሁን በክልል) ላይ የሚሳተፉ ተቋራጮችና አማካሪዎች አፈፃፀም (ከጥራትና ጊዜ ጭምር) በማዕከላዊ የዳታ ቋት ተቀምጦ አዳዲስ የግንባታ ኮንትራት ለመስጠት እንደ አንድ መሠረታዊ መስፈርት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር አሁን በግንባታ ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚታዩትን ችግሮች በማቃለል ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ዕቃና አገልግሎት ለማቅረብ ውል ገብተው በተባለው ጥራትና ጊዜ የማያቀርቡትን አቅራቢዎች ለመቅጣት የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ቢኖርም በብዙዎቹ የመንግሥት መ/ቤቶች ባለመተግበሩና አደገኛም በመሆኑ ይህን በማይተገብሩ መ/ቤቶችና ሀላፊዎች ላይ ተገቢው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አሁን የሚታየውን ችግር ከመፍታት አንፃር ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ከመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ጋር ተያይዞ ስታንዳርድ ያልወጣለት በመሆኑ መንግሥትን ከፍተኛ ወጭ እያስወጣ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ምን ዓይነትና ደረጃ ያለቸው የመስተንግዶ አገልግሎቶች በየትኛው ደረጃ ይስተናገዱ የሚለውን በተመለከተ ደረጃ ቢወጣለቸውና የግዥ ዘዴውም ጭምር በተለየ ሁኔታ ቢዘረጋ በየዓመቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ክፍተቶች ለማረም የሚያስችል ይሆናል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ ለበርካታ ኦዲት ግኝት እምብርት የሆኑት በተቋማቱ ከሚከናወኑት ግንባታዎች፤ የዕቃና የአገልግሎት ግዢዎችን በተመለከተ ሌሎች አማራጮች ቢፈተሹና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በመማር መስተማርና ምርምር ሥራ ላይ ብቻ አትኩረው እንዲሠሩ ቢደረግ፡፡ በሌላ በኩል

ግልፅ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ወይንም በሚመለከታቸው አካላት የጋራ ስምምነት ባለመደረሱ በየዓመቱ የሚታዩ የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ የትምህርት ሚኒስቴር፤ የፐብሊክ ሠርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር ሆነው በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲበጅለት ቢደረግ፡፡

የመንግሥት ንብረት አያያዝን በተመለከተ መጠነኛ መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የንብረት አወጋገድ ግን አሁንም ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አወጋገድ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ባለቤትም ኖሮት እየተሠራ አይደለም፡፡ የተለያዩ ኬሚካሎችም ከኤሌክትሮኒክስ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሌሎችም ዕቃዎች ቢሆኑ በግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትና በተቋማቱ መካካል አንዱ በአንዱ ላይ በማሳበብ ንብረቶቹ ሳይወገዱ ከፍተኛ ክምችት በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ መ/ቤቶች ይታያል፡፡ ስለሆነም የአገልግሎቱን አቅም በማሳደግ ወይም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ተቋማቱ ራሳቸው ንብረቶቹን በሽያጭ የሚያስወግዱበት ሰፋ ያለ የሥልጣን ውክልና የሚሰጥበት ሁኔታ መታየት ይኖርባታል፡፡

በየአመቱ ባደረግናቸው ኦዲቶች ያላግባብ የፈጸሙትን ክፍያ እንዲያስመልሱና ከተዘረጋው የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ውጭ እየተፈጸሙ ያሉ ተግባራት እንዲያቋርጡ በተደጋገሚ አሳስበን ያልፈጸሙ ተቋሚትና በየደረጀው ያሉ ሀላፊዎቻቸው ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በፍጥነት ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አሁን የጀመረውን በጎ ጅምርና ጥረት ሊጠናከር ይገባል፡፡ በሌሎች አካላትም ተጨበጭ እርምጃዎች ሊወሰድ ይገባል

መሻሻል ሲገባው አሁንም ያልተሻሻለው የባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብን በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ዘግቶ ለኦዲት ያለማቅረብ ጉዳይ በአንክሮ ሊታይና ተገቢው እርምጃ የሚያሻው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ጉዳይ የፋይናንስ፤ግዢና ንብረት ተግባራትን ከሚያከናውኑ ሠራተኞችና ሀላፊዎች አቅምና አቅርቦትም ጋር የሚያያዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ይህ ሁኔታ በዚህ መልክ ሊቀጥል ስለማይገባ በመካከለኛና በረጅሙ ጊዜ አቅም የመገንባትና አቅርቦቱን የማሻሻል ጉዳይ

ትኩረት ተሰጥቶት የሚመለከታቸው አካል ሊሠሩበት ይገባል፡፡ በአጭሩ ጊዜ ግን ይህ ጉዳይ የኦዲት ጥራትና ጥልቀቱም ላይ ተፅዕኖ እያመጣ በመሆኑ በም/ቤቱም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተገቢው አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የሚደረገው ኦዲት የአሠራር ክፍተቶችን በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግና እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ያላግባብ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ እንዲመለስ፤ ከተዘረገው አሠራርና ሥርዓት ውጭ በመሆናቸው እንዲቋረጠ የተባሉት ተግባራት በፍጥነት እንዲቆሙ፤ አሠራርና ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው የተባሉት እንዲፈጸሙ ሁሉም የሚመለከተው አካል ተገቢውን ግፊትና ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

<u>የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት</u>

<u>ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች</u>

መ/ቤታችን በ2008/2009 የኦዲት ዓመት በ158 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና በ48 ቅ/ጽ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ ባቀደው መሰረት የ158 መ/ቤቶችና የ44 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን በኦዲቱ የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ክፍል የሚነሱ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች አብዛኞቹ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

<u>ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች</u>

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 144,716.56 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 3 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ2 መ/ቤቶች ቆጠራው

በብር 2,445,827.16 በመብለጥ የሚታይ ሲሆን፣ በ5 መ/ቤቶች ብር 379,390,668.85 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-3/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች</u>

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-4/ሀ-ሰ ተመልክቷል፡፡/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ3 መ/ቤቶች ብር 913,704.66፤
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ4 መ/ቤቶች ብር 2,558,981.76 መገኘቱ፣
- በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 18,892,132.52 በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው፣
- ለተለያዩ ድርጅቶች በባንክ በኩል ክፍያ ለተፈጸመው የባንክ አድቫይስ/ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ሳይያያዝ የተገኘ በ2 መ/ቤቶች ብር 80,073,363.23፤

- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ2 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 69,939,618.96 መገኘቱና በ1 መ/ቤት ብር 665,031.96 በማነስ የሚያሳይ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ ላይ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፤ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2 <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ113 መ/ቤቶች እና በ23 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 5,262,272,848.29 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	119,432,359.04
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,917,783,011.16
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	684,135,065.76
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,084,093,170.28
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	224,833,495.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	231,995,746.39
ጠ/ድምር	ብር	<u>5,262,272,848.29</u>

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 134,153,964.72 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 3,174,764,464.42 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 372,936,870.76 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 196,565,227.12 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,442,462,508.41 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለና ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ ብር 375,557,284.38 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቢው ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 2,388,942,192.66፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 720,056,723.48፤ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 461,024,828.37፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 352,267,320.48፣ የሀገር መከለከያ ሚኒስቴር ብር 172,017,623.31፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 122,357,333.28፤ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት 7 ተጠሪ ተቋማት ብር 120,806,110.43፤ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 119,048,306.24፤ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 108,320,687.31፤ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 82,078,962.89፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ሶስት ተጠሪ ተቋማት ብር 57,915,537.72 እና ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 55,650,002.47 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም

ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ለተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ያልተዘገጀ በዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 654,583.29 መገኘቱ ፤
- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ7 መ/ቤቶች ብር 28,905,615.31 መሆኑ፣
- በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ በፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ብር 438,902.91 መገኘቱ፣
- በሁለት መ/ቤቶች ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 11,155,949.90 መኖሩ፤

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ መ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ /እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,137,991,342.68፤በሌሎች በ30 መ/ቤቶች ብር 5,920,743.20 በድምሩ ብር 1,143,912,085.88 የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣

የተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/፣ ቅድመ ግብር (withholding tax)፣ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ፣ እና በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 19 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 226,318,955.97 ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በተፈራመው የውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት በሶስት መ/ቤቶች ብር 6,157,838.84 እና በሁለት መ/ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ገቢ በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ- 9 እና 9/1 እና 9/2 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	137, 991,342.68
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	136,813.59
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	225,013.49
የከፍተኛ ትምህርት ት	"	299,910.67
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	2,923,765.19
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,335,240.26
ጠ/ድምር	ብር	1,143,912,085.88

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 725,157,433.77፣ በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 239,105,787.51 ፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 55,660,066.90 ፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,602,011.26 ፣ በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 20,474,305.24፣ የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,595,253.19 ሲሆን፣ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 2,334,379.40 እና ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 1,512,791.25 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፊያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች 5 መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 4,009,579,782.80 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመሰጠቱ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በ2

ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ግብር፣ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 3,534,374,123.04 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 8 እና 8/1 ተመልክቷል/

በተጨማሪም ከሰጡት አገልግሎት ሽያጭ ላይ ውዝፍ ሂሳብ /የዱቤ ሽያጭ ከነወለዱ/ በ4 መ/ቤቶች ብር 758,441,552.94 በወቅቱ /በአባሪ- 8/2/ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ውዝፍ ገቢ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,568,784,786.96፣ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 221,873,831.48፣የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 82,614,496.40 ፣የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 53,030,155.76፣ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 49,103,485.09 እና ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 36,468,864.32 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 621,050,644.38 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ እስከ 8 ዓመታት የቆየ) ይገኝበታል፡፡ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር፣148 በድርጅቶች/ተግልጋዮች/ በመመሪያው መሰረት ቅሬታቸው በወቅቱ ባለመታየቱ ወይም ውሳኔ ባለመሰጠቱ ከ14/01/2007 እስከ 26/04/2009 የቆየ መሆኑ እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፣ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አምስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 36,807,405.88 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም የተሰበሰበባቸው 170 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ተጠይቀው ያልቀረቡ በመሆኑ፤በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤ አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፤የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ 119 ግብር ከፋዮች፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 27 ግብር ከፋዮች እና ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ ያለሳወቁ 11 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን፤ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም ፤ ስለመክፈላቸው/ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ11 መ/ቤቶች ብር 196,400,089.47 እና በሌሎች ሁለት መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-11 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	167,457,520.57
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,187,238.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	14,563,698.31
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	12,191,632.32
በድምር	ብር	196,400,089.47

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ

ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 8,250,112.36 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ /ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈስስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.6.1 በገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 15(1-5) እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 ክፍል 5 ቁጥር18(2) መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ወደ ሀገር ሲገባ የያዘው የውጭ ምንዛሪ የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዲክላራሲዮን ላይ መመዝገብ እንደሚኖርበት እና ተመልሶ ለመውጣት ሲፈልግ ገንዘቡን ያስመዘገበበት ዲክለራሲሆን ካላቀረበ በስተቀር መልሶ ለማውጣት እንደማይችል ይገልጻል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

- በውጭ ዜጎች ባለቤትነት በቀን 22/05/2008 ሊወጣ ሲል በፍተሻ የውጭ ምንዛሬ በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.0 በወቅቱ

ባለው የሀገር ውስጥ ምንዛሬ ሲመነዘር ብር 4,876,186.20 እና 4.336 ኪ.ግ ወርቅ የግለሰቦቹ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሳይኖር እና የገንዘቡ ህጋዊነት በአግባቡ ሳይረጋገጥ ለግለሰቦቹ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑን፣

- በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2ሀ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀፅ 13 ላይ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን በሚለው ከንዑስ አንቀፅ 1-4 ድረስ በተዘረዘሩት መሰረት የኢንቨስትመንት የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አሰራር ላይ ክትትል እየተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- እያንዳንዱ አስመጪ ድርጅት ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በሚያስገባበት ወቅት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ለኢንቨስትመንት እንዲገቡ ደብዳቤውን በቀጥታ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚጽፍ በመሆኑ እና በዋና መ/ቤት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት አውቆት ክትትል የማይደረግበት መሆኑ፣
- አስመጪ ድርጅቶች ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ሲጀምሩ በሚያስገቡበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያስገባ የተፈቀደለትን የዕቃዎችን ብዛትና ዓይነት ለማወቅ የሚያስችል አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ከአንዳንድ የተሰረዙ የኢንቨስትመንት ፍቃዶች እና የህግ ማስከበር ሂደቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሀብቱ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ዕቃ ለታለመለት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስራ በትክክል ስለማዋሉ፣ በስራ ላይ ስለመሆኑ፤መብቱን ያለአግባብ አለመገልገሉን፤ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍቃዱ ሲሰረዝ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል እንዲቻል እና ግዴታዎቹን ሳይወጣ ከሀገር

እንዳይወጣ የቅርብ ጊዜ ትክክለኛ አድራሻ በመያዝ ቁጥጥሩን ሊያጠናክር የሚችል የተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ትክክለኛና ወቅታዊ የሆነ መረጃ የመቀባበል ልምድ እና አሰራር የሌለ መሆኑን፤

- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 791,195.26 በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ በብልጫ ተቀናሽ ወይም ተመላሽ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ መገኘቱ፤

- በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 66/1/ሀ/ እና በገቢ ግብር ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ19/1 ና 2 መሰረት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ቢኖርም ባይኖርም በየዓመቱ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት የሂሳብ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 6 ቅ/ጽ/ቤቶች፡-

- በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 ክፍል 1 አንቀጽ 38 በተቀመጠው የግብር አስገቢው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት ፣ የደንበኞች አገልግሎት እንቅስቃሴ አላቸው ብሎ ከያዛቸው ግብር ከፋይ በናሙና ከተመረጡት መካከል፡-

በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት

- ዶንዷ ኤምፔክስ ሰርቭስ የግብር መለያ ቁጥር /0000388195/ ከ2007 ዓመት ጀምሮ አራት (4) ዓመታት ወደኋላ ተሂዶ ሲታይ ኪሳራ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡ በመሆኑ እና የታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን የስራ ሂደት በኩል ስጋት አለባቸው ተብለው ከቀረቡት ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ያልተያዘ መሆኑ፤

የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- ጂሮው ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0015445634 ከ2003 እስከ 2007 በጀት ዓመት በንግድ ትርፍ ግብር ዜሮ እያሳወቀ መሆኑ እና በታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን በታክስ ኦዲት እንዲታይ የተመረጠ ቢሆንም ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤
- መሀመድ አብዱላሂ ኦክሰዴ የንግድ ስራዎች ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0004978176 ከ2001 እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ ኪሳራ እያሳወቀ በመሆኑ የስጋታቸውን ምንጭ በመጥቀስ የስራ ክፍሉ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ኦዲት ወይም ክትትል እንዲደረግባቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡

3.6.2 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

በጅማ ዩኒቨርሲቲ፤

- በጅማ ሆስፒታል የመድሃኒት ሽያጭ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እና በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት ሳምፕል በታዩት ብቻ ለAPTS የብር 14,276,899.61 የመድሃኒት ግዥ ከመደበኛ በጀት የተገዛ ሲሆን ከመድሃኒቱ በመልሶ ሽያጭ የተገኘ ገቢ በበጀት ዓመቱ በቀረበ የሂሳብ ሌጀር መሠረት ብር 5,401,390.44 እንደሰበሰበ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ የመድሃኒት መልሶ መሸጥ ገቢዎች የተገኘ ብር 28,977,861.37 ሲሆን መድሃኒቱ ከመደበኛ በጀት ግዥ የተፈፀመ በመሆኑ ሂሳቡ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገንዘቡ ብሎክ ተደርጎ እንዳይወሰድ ለሆስፒታሎች በተፈቀደ የማይዘጋ ሂሳብ

አካውንት ቁጥር 1000166208819 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ መሆኑ፤

በመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ፤

- ከተከታታይ ትምህርት (Extension, Weakened and Summer) እና ከድኅረ-ምረቃ ለሚሰበሰበው ገቢ ከእያንዳንዱ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን ለይቶ የሚያመለክት ተቀጽላ የሂሳብ ቋት (Subsidiary ledger) የሌለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ ማመንጫ የሥራ ክፍል በዳይሬክቶሬት ደረጃ ቢኖረውም ከተከታታይ ትምህርት፤ ከድኅረ-ምረቃ፤ ከእርሻ ምርት ሽያጭ፤ የተለያዩ አገልግሎት ከሚሰጡ ሱቆች ኪራይ፤ ከመዝናኛ ክበቦች እና ከሌሎች የተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡ ገቢዎች በዝርዝር የሚያሳይ መከታተያ የሌለው መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሱቆች፤ መዝናኛ ክበቦች እና የጀበና ቡና አቅራቢዎች በአብዛኛው ውላቸው የተጠናቀቀ /ያልታደሰ/ መሆኑ፤

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፤

- የክፍያ ትዕዛዙ በጥቅሉ በክረምት መርሃ- ግብር የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን ያስተማሩበት በሚል ሂሳቡ ከመደበኛ በጀት የተከፈለው ብር 979,976.00 በክረምት የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን፣ በሌሎች የመንግስት መ/ቤቶችና በግላቸው ከፍለው የሚማሩ ተማሪዎች በግልጽ ተለይቶ የተያዘ ባለመሆኑ ከመደበኛ በጀት መከፈል የሌለበትን እና ከክረምት ድህረ-ምረቃ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ መከፈል ያለበትን ሂሳብ ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፤

በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤

- (GIZ) ለፈጸማቸው የዕቃና አገልግሎት ግዢዎች ሂሳቡ ሲወራረድ በወጪ ሰነዶቹ ላይ የተመለከቱት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳቦች (2%) በራሱ ስም በታተመ የቅድመ ዊዝ ሆልዲንግ ደረሰኝ መሰብሰቡን ከማመልከቱ በቀር ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ሂሳቡ ሲወራረድ ማስረጃ የማይቀርብ መሆኑ፤
- የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 345,009.00 መገኘቱ፣
- በ6 መ/ቤቶች ከመንግስት በጀት በተሰሩ ወይም በተዘጋጁ ገቢ ማስገኛዎች ህጋዊ ሥልጣን ባልተሰጠው አካል ገቢ ስለመሰብሰቡና ተጠቅመው ስለመገኘቱ፤
- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች 10 ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ ብር 791,195.26 በብልጫ ተቀናሽ ወይም ተመላሽ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ መኖሩ፣
- በሁለት መ/ቤቶች ስድስት ሰራተኞች የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ባልተወጡ መምህራንን ላይ በገቡት ግዴታ መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ/አባሪ-30 ይመልቱ

በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ አንዳንዶቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3.7 የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ፡- ብር 11,771,351,616.51(23%)

ለ/ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 21,287,645.55(18%)

ከዕቅዱ በታች መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ15 መ/ቤቶች ብር 36,725,016.96 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	2,576,852.24
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	10,885,892.93
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	14,936,002.43
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	6,981,886.20
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	8,326,269.36
በድምር	ብር	36,725,016.96

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው፤የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 12,660,000.00፣

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 8,179,060.00፣ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,873,851.63፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 4,366,013.47 ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 2,359,106.93 እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ብር 2,276,002.43 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ59 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 236,452,502.91 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	430,691.53
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	1,070,878.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	334,587.65
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	56,960,784.04
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	132,739,577.83
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	44,915,983.86
በድምር	ብር	236,452,502.91

ሆኖ ተገኝቷል ።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 47,697,409.60 ፣ የአሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 25,870,747.59፣ የፌዴራል ፖሊስ

ኮሚሽን ብር 21,125,500.00 ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንንት አገልግሎት ብር 20,951,955.77 እና አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,538,683.00 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ91 መ/ቤቶችና በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 98,768,151.60 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	4,758,723.09
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	139,648.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	24,677,392.76
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	56,059,377.29
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	4,452,559.33
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	8,680,450.93
በድምር	ብር	98,768,151.60

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,626,212.78፤ ደብረታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 13,324,499.96 ፤ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 10,149,481.18፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,279,127.30፤ ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,845,492.87፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,544,216.00 እና ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,880,610.00 ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም ፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ ለውጭ ጉዞ ከወሰዱት የውሎ አበል ሂሳብ በመመሪያው መሰረት መመለስ ሲገባቸው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም ፤ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት ባሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ በ8 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 7,633,947.38 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጠይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር

የተፈጸመ ክፍያ እና በ11 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 58,364,234.32 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-9/1 እና 9/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ18 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 19,512,255.86 እና በ25 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,431,888.97 በጠቅላላው ብር 29,944,144.83 እና በ1መ/ቤት $2,500.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገቢው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግና በድጋሚ መመዝገብ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ79 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 324,950,102.20 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	15,802,727.15
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	774,051.89
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,282,333.69
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	98,796,196.46
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	163,811,204.22
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	32,483,588.79
በድምር	ብር	324,950,102.20

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡-ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር185,413,357.21፤መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 30,659,951.58 ፤የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 42,915,658.54 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 65,961,134.87 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 69,476,518.45 ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,606,609.47፤የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 22,809,928.86፤ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,294,981.03፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,720,591.17 ፤አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,037,410.63 ፤ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 10,105,118.59 ፤ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,109,599.15 መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,701,853.51 እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር

8,935,793.76 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ በ6 መ/ቤቶች የብር 49,599,091.24 መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ14 መ/ቤቶች በብር 21,416,544.15 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች ብር 2,674,478.09 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1 ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	361,180.22
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	10,833,260.25
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	3,199,525.00
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,022,578.68
በድምር	ብር	<u>21,416,544.15</u>

ከዚህም ውስጥ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 6,433,032.76፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 4,743,664.81 ፤ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ

ዩኒቨርሲቲ ብር 4,302,552.26 ፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,184,000.00 እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ብር 1,073,235.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፣ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብር 1,496,954.03 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 918,758.32 ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 99,645,132.99 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 27 ተመልክቷል/

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ64 መ/ቤቶች ብር 134,338,778.71 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	ብር	56,562,154.04
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	31,381,529.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	38,662,041.49
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,733,054.13
በድምር	ብር	<u>134,338,778.71</u>

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 29,703,434.00 ፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 22,322,164.80 ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 13,025,029.57 ፣የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብር 8,879,767.20 ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 7,296,089.99 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,582,659.52 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 106,539,302.53

የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2008 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	20,462,380.02
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	5,098,656.18
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	80,650,516.33
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	327,750.00
በድምር	ብር	106,539,302.53

ሲሆን፤ ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ12 መ/ቤቶችና ሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,427,854.32 እና በአንድ ዩኒቨርሲቲ እና አንድ ሆስፒታል በገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤</u>

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለትና በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ9 መ/ቤቶች ብር 140,384,732.80 ፤ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ በ3 መ/ቤቶች ብር 66,383,236.25 በድምሩ በብር 206,767,969.05 ተከፍሎ መገኘቱ፤
- ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው ያልታደሰ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከግንባታ ክፍያው ላይ ያልተቀነሰ መሆኑ፤ ለግንባታው ሥራ የተገዙ የተለያዩ ማቴሪያሎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤ የውል ሰነድ እና የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የሚያሳይ ዝርዝር ሁኔታ ሳይቀርብ እንዲሁም የግንባታ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይኖር ለGIZ የተከፈለ…..ወ.ዘ.ተ) የግንባታ ክፍያዎች፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 37,909,666.37 መፈጸሙ፤
- በተጨማሪም በ20 መ/ቤቶች ብር 133,631,062.49 ከግንባታ ፕሮጀክቶች ጋር የተያያዘ በመጀመሪያ ከተከፈላቸው የቅድሚያ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ሳይደረግ የቀረ ሂሳብ መኖሩ፤
- በ8 መ/ቤቶች ብር 260,989,864.26 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርትፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤

- በ3 መ/ቤቶች ብር 23,130,699.31 በተከፋይነት ያልተያዘ ፤ በጀት ሳይፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ መከፈሉ ተረገግጦል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- አባሪ-20/1 እስከ አባሪ-20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከሪያ ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን፤ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 28,627,001.52 ፤ በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 7,074,728.79 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ እና በሁለት መ/ቤቶች የወጪ ሂሰብን ማዘጋጀት፤ ማረጋገጥና መፍቀድ ተግባራት ተደርቦ በአንድ ሰራተኛ የተከናወነ ክፍያ ብር 230,737.61 መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ-26/2 ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

4.13 <u>ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች</u>

4.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

- በዩኒቨርሲቲው በርካታ የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩም የፕሮጀክት ሂሳቦቹ ዝርዝር መረጃ ማለትም የፕሮጀክቱ ስም፣ የፕሮጀክቱ ዓላማ፣ ፕሮጀክቱ የጀመረበት ጊዜ፣ ለሂሳብ ምዝገባው እና ለሪፖርት ዝግጅት የሚጠቀመው የኤሌክትሮኒክስ ምዝገባ ዓይነት፣ በሂሳብ አካውንት ላይ የሚታይ የገንዘብ መጠን ሰኔ 30/2008፣ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት እንደሚዘጋጅ፣ የፕሮጀክት ሂሳቡ ኦዲት ለመደረጉ እና ላለመደረጉ ከተደረገ በማን እንደተደረገ የሚገለፅ ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ሪፖርት ለማቅረቡ የሚገልፅ ማስረጃ በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ኦዲቱ ከተጀመረ ጀምሮ የተጠየቀ ቢሆንም መረጃው በዩኒቨርሲቲው ያልቀረበ መሆኑ፤

በመቱ ዩኒቨርሲቲ

- በትምህርት ሚኒሰቴር እና በመቱ ዩኒቨርሲቲ መካከል በ2005 ዓ.ም የግንባታ ሥራዎች በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነትና ሃላፊነት እንዲካሄድ ከትምህርት ሚኒሰቴር ወደ ዩኒቨርሲቲ ያስረከባቸዉ ስራ ተቋራጮች ርክክብ ሲደረግ ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ በትክክል ታውቆ ወደ ዩኒቨርሲቲ ባለመተላለፉ በወቅቱ ዩኒቨርሲቲው ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ መዝግቦ ያልያዘ መሆኑና አሁን ያለዉ የህንጻ ተቋራጮች የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳየው ዩኒቨርሲቲው ግንባታውን ተረክቦ ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ በኃላ ያለው ሂሳብ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

➢ ኒሐም ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የብር 14,699,675.00 ፒፒስ ሲሚንቶ ለማቅረብ ውል የተገባ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ *30% (14,699,675.00*30%)= ብር 4,409,902.50 ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ሲገባ ብር 14,699,675.00 ሙሉውን ጠቅላላ የውሉን ዋጋ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

➢ ቀደም ሲል ትምህርት ሚኒስቴር ክትትል እየተደረገባቸው የነበሩ እና GIZ በተባለው ድርጅት ተይዘው ሲሰሩ የነበሩ የዩኒቨርሲቲው የህንፃ ግንባታዎች እና የመሰረተ ልማት ግንባታ እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታን በተመለከተ ለማወቅ የሚያስችሉ፣ የተደረጉ የሰነድ ርክክቦች፣ ማለትም፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚያ የተከፈለው ጥሬ ገንዘብ፣ ተመላሽ የተደረገው እና ያልተመለሰ ቅድሚያ ክፍያ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በዓይነት የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች /Material Advance/ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብና እና ያልተመለሰ፣ቀሪ ዕዳ፣እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ለሚያከናውናቸው ግንባታዎች በመያዣነት ገቢ ያደረገው የመልካም ስራ ዋስትና ገንዘብ እንዲሁም ግንባታ ክፍሉ ከGIZ-IS የተረከባቸው ሰነዶቹ ለሂሳብ ክፍል ተላልፈው በእያንዳንዱ የህንጻ ስራ ተቋራጭ ስም ሂሳቡ እንዲመዘገብ ስለመደረጉ፣ እንዲሁም ስራው የደረሰበት ደረጃ፣ ያቋረጡ ካሉ በእነሱ ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ፣ ከስራ ተቋራጮቹ የሚፈለገውን የተሰብሳቢ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳይ ተቀጽላ ሌጀር ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብና እየተደረገ ስላለውም ክትትል ለማወቅ የሚያስችል በቂ ምላሽ የሚሰጥ አካል ባለመገኘቱ የሂሳቡን ሁኔታ ማጣራት አለመቻሉ፤

የጅማ ዩኒቨርሲቲ

- የላብራቶሪና ወርክሾፕ ግንባታ በብር 355,925,389.92 በቀን 07/06/03 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 07/06/05 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤
- የሪሰርች ሴንተር እና ኮንፈረንስ ሆቴል ግንባታ በብር 227,919,070.43 በቀን 9/9/2002 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 01/4/2004 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ4 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤
- የእስታዲየም ግንባታ በብር 144,323,492.00 በቀን 6/8/2007 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 25/1/2008 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀና ስራው ያለበት ደረጃ 23.35% መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው በ13/07/2003 ሁለት ቢሮዎች (አንድ ቢሮ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ግቢ ውስጥ እና ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ቤተ-መጻህፍት) እና ከዋናው ግቢ ወደ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የሚያስተላልፍ ድልድይ ለማሰራት ከአፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግ.ማ ጋር በ48.7 ሚሊዮን ብር ውል የገባ ሲሆን በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ግቢ መገንባት የነበረበት ህንፃ ሙሉ በሙሉ ያልተሰራ መሆኑ፤

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

- በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በውሉ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 8 የህንጻ ተቋራጮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት አሰራሮች እንዲስተካከሉ የተጀመሩት ግንባታዎች በጊዜያቸው እንዲጠናቀቁና በውል በተቀመጠው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው የደረሰው የጉዳት ካሳ እንዲጠየቅበት አሳስበናል፡፡

5 <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ73 መ/ቤቶችና በስምንት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,880,499,977.09 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	375,652,461.94
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	666,574,340.47
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶ	"	77,632,748.48
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	536,771,014.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	188,583,502.76
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	35,285,908.57
ድምር	ብር	1,880,499,977.09

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፣ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 104,587,943.58፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 374,727,888.39፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 20,043,052.99 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 23,675,570.61 ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,357,278,582.92 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ፣ ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ በ8 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 833,811,806.31 በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ለማን እንደሚከፈል፣ መቼ እንደተከሰተ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 419,956,203.21፤በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 342,950,209.55 ፣በአዲስ አበባ ምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 308,074,556.05 ፤የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 285,468,377.01 ፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 159,561,189.14 ፤ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር 79,227,247.16፣ የአ.አ. ሳይንስና ቴክ. ዩኒቨርስቲ ብር 39,760,785.78፣ በምዕ/አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,577,225.60 ፤አዲስ አበባ ኤርፖርት ብር 26,163,220.64 እና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 15,923,663.20 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ያልተመዘገበ የግንባታ የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በሁለት መ/ቤቶች ብር 51,470,989.29 እና የመያዣ ተከፋይ ሂሳብ ያልተመዘገበ በ3 መ/ቤቶች ብር 109,539,434.01 መገኘቱ፤
- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 6,000,000.00 መገኘቱ፤
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ3 መ/ቤቶች ብር 20,611,102.35 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 1,496,469.73 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ52 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 177,327,518.45 እና ከካፒታል በጀት ብር 92,432,012.04 በድምሩ ብር 269,759,530.49 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	5,947,483.52
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤቶች	"	7,230,416.01
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶ	"	49,404,867.46
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	195,875,731.29
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		9,178,686.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,122,345.34
ጠ/ድምር	ብር	269,759,530.49

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 83,491,831.42 ፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 46,964,205.09 ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 15,798,465.73 ፣ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,212,410.76፣

ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,013,561.17 እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,793,868.48 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ5 መ/ቤቶች ብር 24,654,548.49 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች እና በ3 መ/ቤት ለስራው በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈረም ወጪ የማድረግ አሰራር የሚከተሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት

ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ142 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 3,331,577,013.49 እና ካፒታል ብር 1,725,145,215.92 ብር 5,056,722,229.41 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	596,704,850.36
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	754,901,868.91
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	352,069,616.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	1,000,512,214.44
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	681,814,885.93
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	1,497,856,757.95
ጠ/ድምር	ብር	5,056,722,229.41

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 754,901,868.91፤ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 424,278,500.86፤ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 403,331,824.91፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 221,777,718.77፤ትምህርት ሚኒስቴር ብር 215,916,040.78 ፤ የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 198,236,163.67፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 142,012,434.17፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 128,805,410.23፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 115,280,256.32 እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 110,230,389.22 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል፡፡/

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	38 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	39 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	19 መ/ቤቶች
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	17 መ/ቤቶች
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	28 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	72 መ/ቤቶችና 14 ቅ/ጽ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	22 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	10 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው:- 243 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 11 ሞተር ብስክሌቶች	10 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ 26 ላፕቶፕና ሌሎች ዕቃዎች	2 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	4 መ/ቤቶች
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	1 መ/ቤት
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	17 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤቶች

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ

ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ27 መ/ቤቶች	170 ተሽከርካሪዎችና 14 ሞተር ብስክሌቶች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ32 መ/ቤቶች	453 ተሽከርካሪዎችና 18 ሞተር ብስክሌቶች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ6 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	በ8 መ/ቤቶች	182 ተሽከርካሪዎች
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	በ2 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	በ3 መ/ቤቶች	182 ተሽከርካሪዎችና 2 ብስክሌቶች
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	በ3 መ/ቤቶች	17ተሽከርካሪዎች
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ	በ5 መ/ቤቶች	

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ሸ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ55 መ/ቤቶች እና 19 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየዘርፉና በየመ/ቤቶቹ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላም በኩል በ2008 ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሣብ መሠረት መርሃ ግብር እንዲያዘጋጁ ከተጠየቁት 129 መ/ቤቶች ምላሽ የሰጡት 50 (38.75%) ሲሆኑ ለክዋኔ ኦዲት ደግሞ 1 መ/ቤት ብቻ ነው፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ 39 ተመልክቷል/

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9 ልዩ ልዩ ፤

9.1 ከውል ውጪ የተፈቀደ ሴሌክትድ ማቴሪያል፤

በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል እና የሆለታ የአስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያን የውስጥ ለውስጥ አስፋልትና ለጠጠር መንገድ ለማሰራት ማዕከሉ ከኃሽሪም ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጋር የውል ስምምነት የፈጸመ ሲሆን፣ ድርጅቱ ለመንገድ ሥራው የሚሆን ሴሌክቲቭ ማቴሪያል ከሆለታ የአስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ቆፍሮ ለመጠቀም ይችል ዘንድ እንዲፈቀድለት ሰኔ 2 ቀን 2007 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር HVT/540/07 ማዕከሉን በጠየቀው መሰረት፡-

- ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር እንዳይበልጥ፣
- ለሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ፣
- የግጦሽ ቦታን ሳይጎዳ በአንድ መንገድ እንዲጠቀም፣

የተፈቀደ መሆኑን የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ገልጸዋል፡፡ ሆኖም፡-

➢ በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ቢሆንም፤ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ የተጠቀመ በመሆኑ ገንዘቡ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ ከተቀመጠው ላይ ተቀናሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያሉን ከሆለታ ጣቢያ ቆፍሮ እንዲጠቀም ሲፈቀድለት፡-

- የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር ሳይበልጥ የተፈቀደ ቢሆንም በተባለው መሰረት የተፈጸመ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ በተባለው መሰረት ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያል አዘጋጅቶ ቦታው ላይ ያላደረሰ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም የመንገድ ሥራው በውሉ መሰረት ካልተፈጸመ፡-

- ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለማይሆን፤

በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ሆኖ ሳለ ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መጠቀሙ አግባብ ስላልሆነ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ የተቀመጠው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

9.2 ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት እየተቀጠፉ የሚገኙ የወተት ላሞችን በተመለከተ፤

የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብና ንብረት ኦዲት በተደረገበት ወቅት በሆለታ በሚገኘው አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ግንቦት 10 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ወጥቶባቸው ከተገዙት 300 የሆሊስቴይን ፍሬዢያ ላሞች 84 ብቻ የቀሩ መሆኑ ተገልጾ ለቀረበው ግኝት ማዕከሉ ኮርማዎቹን ለአባለዝር ምርት ለማዋል ወይም ለማስወገድ ከብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ቴስት የሚያደርግ ኪት ከውጭ አገር በማስገባት ሂደት ላይ እንደሆነ እና ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በቅርብ ጊዜ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን በወቅቱ በሰጠው ምላሽ ላይ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ኦዲት ወቅትም ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2007 በጀት ዓመት ወደ 2008 በጀት ዓመት በቆጠራ የዞሩ የወተት ላሞች ብዛት 475 ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ 127 ወደ ጣቢያው የገቡት ተደምረው 602 ላሞች የደረሱ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ 179 ላሞች ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት በሆነው አይቢአር (IBR) (Infection Bovinerino Tricitits) ቫይረስ መሞታቸውና በህይወት ያሉትም በዚህ መድኃኒት በሌለው ቫይረስ የተጠቁ በመሆኑ የሞሞቻ ጊዜአቸውን እየተጠባበቁ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ማዕከሉ የቫይረሱን ስርጭትና ተጋላጭነት ፍተሻ አድርጎ የመፍቴህ አቅጣጫ ካላስቀመጠ፡-

- ✓ ላሞቹን እየፈጀ በሚገኘው ቫይረስ ላይ ተገቢው ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ካልተደረገ በቀሪዎቹ ላሞች ላይም ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤
- ✓ ቫይረሱ በቀላሉ ወደ አካባቢው ገበሬዎች ቀንድ ከብቶች ሊዛመት እና ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፤

ለወተት ላሞቹ አስፈላጊው የጤና ምርምራ ተደርጎላቸው ጤነኞቹ በበሽታው ከተጠቁት እንዲለዩ እንዲደረግ እና ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት አሰፈላጊው እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

9.3 **<u>በአደራ የተቀመጠ የጅማ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ንብረቶችን በተመለከተ፤</u>**

ግንቦት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ጅዩ 92/738 ጅማ ዩኒቨርስቲ በሰበታ ከተማ በብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል አጠገብ ለግንባታ መሬት የተሰጠው መሆኑን ገልጾ በቦታው ላይ ግንባታ ሲጀመር አገልግሎት ላይ የሚውሉ በርካታ አሸዋ፣ ብረትና ጠጠር በማዕከሉ ቅጽር ግቢ ውስጥ በአደራ ለጥቂት ወራት ለማስቀመጥ ፍቃድ የጠየቀና ያስቀመጠ ቢሆንም ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

መሆኑም ንብረቶቹ በቶሎ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ካልተደረጉ ለብልሽት ሊጋለጡ ስለሚችሉ ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ስለሆኑና ሥራ ላይ ሳይውሉ ለብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ በቶሎ ሥራ ላይ ይውሉ ዘንድ ሁኔታውን ለዩኒቨርስቲ ማሳሰብ እንዳለበት አስገንዝበናል፡፡

9.4 **<u>በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የጤና ጠንቅ እያስከተለ የሚገኘውን የማይፈለጉ የህክምና ቁሳቁሶች ቃጠሎን በተመለከተ፤</u>**

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ቀጥለው የተመለከቱት የህክምና ቁሳቁሶች ይኸውም፡-

- ✓ ሲሪንጅ ከነመርፌው በሴፍቲ ቦክስ፣
- ✓ የተለያዩ አይነት ግላሶች፣
- ✓ ከደም ጋር ንክኪ ያላቸውና ደም የነካቸው ፎጣዎች፣ ጨርቆች፣ ባንዴጆች፣

✓ የወንዶች ኬር የተሰራባቸው ማቴሪያሎች፣

የመሳሳሉት በሆስፒታሉ ለህክምና የማይፈለጉ ማንኛውንም ነገሮች በሜዲካል ኮሌጁ ግቢ ውሰጥ እንዲቃጠሉ የሚደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ ሁኔታ በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ መሆኑ በሬዲዮ ፋናም ጭምር አስተያየት የተሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም ሁኔታው እስከአሁን እንዲስተካከል ባለመደረጉ ችግሩ መቀጠሉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ሁኔታው በአስቸኳይ እንዲስተካከል ካልተደረገ ሽታው በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ላይ የጤና ተጽዕኖ ሊያሳድር የአካባቢውን አየርም ሊበክል ስለሚችል ሜዲካል ኮሌጁ የጤና ተጽዕኖ እያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ ለሚገኘው ቃጠሎ ሌላ መፍቴህ በአስቸኳይ በመፈለግ ህብረተሰቡን ካልተፈለገ ሽታ መታደግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

II. <u>የክዋኔ/አካባቢ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

1. **በውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት የውሃ ልማት ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደርን በተመለከተ**

ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል /ፕሮፋይል/ ስለማዘጋጀቱ፣

1. ጽ/ቤቱ ወጭን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሰረተ የረዥም ጊዜ ብድር ለመስጠት እንዲቻል ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው መዋቅር /የዜጎች ቻርተር/ መሰረት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚሆን የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ክትትል በማድረግ ፋይናንስ ሊያፈላልግ ይገባል፡፡
2. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያላቀረበና ለዚህ አገልግሎት የሚሆን ፋይናንስ የማፈላለግ ሥራ ያልሰራ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ምዝገባ በተመለከተ፤

3. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን ገንዘብ የመንግስትን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በጠበቀ ሁኔታ በወቅቱ ተከታትሎ ሊመዘግብ ይገባል፡፡

4. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች መሰብሰብ ያለበት የፕሮጀክት መዋጮ መካከል የአመዘጋገብ ልዩነት (ሁለት የተለያየ መግለጫ መቅረብ) መኖሩ፣ ጽ/ቤቱ የፈንዱ ሂሳብ በመንግስት ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ሂሣቡን መዝግቦ በመያዝ ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት እየሰራ ለሚመለከተው አካል ስለማቅረቡ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

የፈንዱን ሂሣብ በውጭ ኦዲተሮቸ ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፣

5. ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሳብ የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት በየአመቱ ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሪፖርቶቹ ለቦርዱ እንዲቀርቡ ማድረግ አለበት፡፡ በቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በሚሰጡ አስተያየቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረትም ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረግ አለበት፡፡

6. ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ማስደረግ ያለበት ቢሆንም የፈንዱ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ጽ/ቤቱ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመሪያ አዘጋጅቶ በቦርድ በማጸደቅ ብድር የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፤

7. ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመሪያ በማዘጋጀት በቦርድ እንዲጸድቅ ማድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም በቦርዱ በጸደቀው የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መሰረት ጽ/ቤቱ ለውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ሥራ አገልግሎት የሚሆን በያመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም ለተበዳሪዎች ብድር መስጠት አለበት፡፡

8. ጽ/ቤቱ ብድር ለመስጠት የሚያገለግል ረቂቅ መመሪያ በሚያዝያ ወር 2001 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ረቂቅ መመሪያው በቦርድ እንዲጸድቅ ባለመደረጉ ባልጸደቀ ረቂቅ መመሪያ ለተበዳሪ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት ጽ/ቤቱ ብድር እየተሰጠ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

9. የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

10. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀት እና የልውውጥ ሥርዓት ቢኖርም ተግባራዊ ባለመደረጉ በክፍያ ሰነዶች ላይ የመረጃ አያያዝ ችግር በመኖሩ የክፍያ መጓተት መፈጠሩን፣ የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም መረጃዎች፣ ለክትትልና ግብረ መልስ ሥራዎች በአግባቡ ያለመቀበል እና አደራጅቶ የመያዝ ችግሮች መኖራቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው እንዲቀርቡ የተጠየቁ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility Study) እና የፕሮጀክት ግምገማ ሪፖርት (Appraisal report) ሰነዶች እንዲሁም የብድር ዋስትና የተያዘበት ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አንዳንዶቹ ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

በመሆኑም

- ጽ/ቤቱ መዋቅር /በዜጎች ቻርተር/ ላይ ለመተግበር ቃል በገባው መሰረት የረዥም ጊዜ ብድር ለከተሞቹ እና የመስኖ ማህበራት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት ወጭን በማስመለስ መርሆ ላይ ተመስርቶ ለመስጠት እንዲችል አስፈላጊ የሆኑ አጋዥ ደንብ እና መመሪያዎች በማዘጋጀት እና በሚመለከታቸው አካላት በማጸደቅ የፕሮጀክት ፕሮፋይል እያዘጋጀ እና በቦርዱ እያጸደቀ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የፈንዱን ገንዘብ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በወቅቱ ተከታትሎ ሊመዘግብና ሂሣቡን በወቅቱ ሊዘጋ ይገባል፡፡
- ፈንዱ ከተቋቋመ ጀምሮ ኦዲት ባለመደረጉ አስፈላጊ ምዝገባዎችን እና ሰነዶችን በማዘጋጀት በፍጥነት የፈንዱ ሂሳብ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት

ሊደረግ እና ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በቀረቡት ሪፖርቶች መሰረትም ተገቢ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረግ አለበት፡፡

- ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት ተዘጋጅቶ በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመሪያ የሚመለከታቸውን አካላት በማወየያት እና ለቦርዱ አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ጽ/ቤቱ ዘመናዊ የሆነ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች አደራጅቶ በመያዝ ለተለያዩ ተጠቃሚዎችና ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ድረ-ገፅ (ዌብ ሳይት) ሊጠቀም እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

አገልግሎቱ የአሸናፊ ድርጅቶችን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግም ስለመሆኑ፣

11. አገልግሎቱ አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

12. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ እቃ ለማቅረብ ጨረታውን የአሸነፉትን አቅራቢዎች ከመወሰኑ እና ከአሸናፊ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት የአቅራቢዎችን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቷል፡፡ ነገር ግን የተዘረጋው ሥርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውስጥ

አንዳንድ አቅራቢ ድርጅቶች በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ ከማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም አገልግሎቱ በውሉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን ይልቁንም በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008- 2010) የማዕቀፍ ውል ስምምነት ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

አገልግሎቱ አቅራቢዎች የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት በቂ አቅም ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ፣

13. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ለማቅረብ ተወዳድረው ጨረታ ያሸነፉ አቅራቢዎች ጋር የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት አሸናፊዎቹ ለማቅረብ የተወዳደሩትን እቃዎች በተፈለገው ጥራት፣ ጊዜና፣ መጠን ወዲያውኑ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ አቅም (ክምችትን ጨምሮ) ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ አቅራቢዎቹም በውሉ መሰረት በተፈለገው ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

14. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ የመንግስት መ/ቤቶች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በግዥ ትዕዛዝ (purchase order) የጠየቁት እቃ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እየቀረበላቸው እንዳልሆነ፤ በማዕቀፍ ዕቃዎችን ለማቅረብ ጨረታ ከአሸነፉት አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ በናሙና ከታዩት አቅራቢዎች ውስጥ አንዳንዶቹ በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እቃዎችን እያቀረቡ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡

አገልግሎቱ ግዥ ለሚፈጸምላቸው ተጠቃሚ መ/ቤቶች ውል ከመግባቱ በፊት የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ ማሳወቁን በተመለከተ

15. አገልግሎቱ ግዥ ለሚፈጸምላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ለእያንዳንዱ ዕቃ አቅራቢዎቹ እናቀርባለን ያሉትን ዕቃ ጥራት አስቀድሞ በላብራቶሪ መረጋገጥ ያለበትን በላብራቶሪ፣ በባለሙያ መታየት ያለበትን በባለሙያ በማረጋገጥ ይህንኑ የሚያሳይ ናሙና ወይንም በቴክኒክ መግለጫ /specification/ መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን አረጋግጦ ሊልክ ይገባል፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎችም የሚገዟቸውን ዕቃዎችና ንብረቶች

በተላከላቸው ናሙና እና ቴክኒክ መግለጫ /specification/ መሰረት መሆኑን አረጋግጠው ሊረከቡ እና አገልግሎቱም ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

16. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ የማዕቀፍ ውል ለተዋዋለላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የቴክኒክ መግለጫ /specification/ በሲዲ የሚልክ ሲሆን ናሙና ግን እየላከ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ተጠቃሚ መ/ቤቶች በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ስለመኖሩ በሚጣራበት ጊዜ፡-

- የአገልግሎቱ የ2007 እና የ2008 በጀት ዓመታት እቅድ አፈፃፀም ላይ እቃዎቹ በአግባቡ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች በወቅቱ መድረሳቸውን ያለመከታተልና በሚፈለገው ደረጃ ማስተዳደር አለመቻሉ፣
- አገልግሎቱ አቅራቢዎች ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት /የተጣጣመ/ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑን፣
- ተጠቃሚ መ/ቤቶች ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እቃዎች በስተቀር በማዕቀፍ ግዥ የተገዙ እቃዎችን ሲረከቡ በውሉ ላይ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽንና ናሙና መሰረት ስለመሆኑ በአገልግሎቱ በአልፎ አልፎ ዘዴ እንኳ የማይረጋገጥ መሆኑን፣
- አገልግሎቱ በማዕቀፍ ውል የተገዙ እቃዎችን በውሉ ላይ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽንና ናሙና መሰረት በባለሙያ ተረጋግጦ መረከባቸውን የማረጋገጥ ስራ በዓመታዊ እቅድ በማካተት ያልሰራ መሆኑን፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች እቃዎችን በወቅቱ ማቅረባቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ

17. አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በሰፔስፊኬሽን እና በናሙና

መሰረት በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 2 አገልግሎቱ አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል እንዳለበት ቢገለጽም አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ማዘዣ (purchase order) ሲደርሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

በገቡት የማዕቀፍ ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃ በተመለከተ

19. አገልግሎቱ በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎችን በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ ለተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የአቅርቦት ችግር ሲገጥማቸው የአቅራቢ ለውጥ እንዲያደርጉ በደብዳቤ ከማሳወቅና ለአንድ ጊዜ በራሳቸው እንዲገዙ ከማድረግ በስተቀር በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙትን አቅራቢዎች በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለገዟቸው ዕቃዎች በወቅቱ ክፍያ መፈጸማቸውን በተመለከተ

21. የመንግስት መ/ቤቶች እና የዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ ሊፈጽምላቸው ይገባል፡፡ አገልግሎቱም በገባው ውል መሰረት አቅራቢዎች ላቀረቡት ዕቃ በውሉ መሰረት ክፍያ ስለመከፈሉ አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

22. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን ከሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲረከቡ በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ የማይፈጽሙ መሆኑን እና

አገልግሎቱም አቅራቢዎች ክፍያ እንዳልተፈፀመላቸው ሲያሳውቁ ብቻ ተጠቃሚ መ/ቤቶችን እንዲከፍሉ በደብዳቤ ከማሳወቅ በስተቀር ክፍያው መፈፀሙን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን እና ክፍያ የሚያዘገዩ መ/ቤቶችን በተመለከተ ክፍያ በማዘግየታቸው ስለሚወሰነው ቅጣት በማዕቀፍ ውል ላይ ያልተጠቀሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

23.በመሆኑም

- አገልግሎቱ ከአሸናፊ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት አቅራቢው ውሉን ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እና የፋይናንስ አቅም ስለመኖሩ ሊያረጋግጥና የአቅራቢውን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አሸናፊ አቅራቢዎች እናቀርባለን ያሉትን እቃ በሚፈለገው ጥራት መሆኑን ለማረጋገጥ በላብራቶሪ መፈተሽ ያለባቸውን በላብራቶሪ በማስፈተሽ እና ሌሎቹንም በጨረታ በተጠቀሰው ስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎችም እቃዎቹን ሲረከቡ በስፔሲፊኬሽን በተገለፀው መሰረት የቀረበ መሆኑን በላብራቶሪና በባለሙያ በማረጋገጥ ሊረከቡ ይገባል፡፡ አገልግሎቱም መስፈርት በማዘጋጀት እና መርሃ ግብር በማውጣት የማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች እቃዎችን በሚፈልግበት ጊዜ፣ መጠንና አይነት እንዲሁም በስፔስፊኬሽኑ መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥበት እና የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ የማዕቀፍ እቃ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የግዥ ትዕዛዝ (purchase order) ሲደርሳቸው በ 7 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን በመደበኛነት የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች የማዕቀፍ ስምምነት ውልና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን ክትትል በማድረግ

ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ሊያደርግና በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎች ላይ እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

- ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ የመንግስት መ/ቤቶች እና ለዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶች እቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ሲያስረክቡ በውሉ መሰረት በአምስት ቀናት ውስጥ ክፍያ መፈፀሙን አገልግሎቱ ክትትል ማድረግ እንዳለበት

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ</u>

የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ጸድቀው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣

24. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥን የሚመለከቱ አዋጆችን ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስፈፃሚ አካላት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 691/2002 ለቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 27/መ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተሰጠውን ስልጣን ተከትሎ የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ደንብ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልወጣም፡፡ ነገር ግን ማስፈጸሚያ ደንቡ ሳይወጣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መመሪያ ቁ.19 (የባለሙያዎችና የሥራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ እና 22 (የአማካሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ) ያዘጋጀ ሲሆን እስከ 2008 ዓ.ም መመሪያዎቹ ከመፅደቃቸው በፊት የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ያላቸውን ሃሳብ/አስተያየት እንዲሰጡ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

26. በተጨማሪም የቀድሞው የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሳያጸድቅ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ መመሪያ በማዘጋጀት እየተጠቀመበት ሲሆን የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ በአዋጅ ከተቋቋመ በኋላ በህዳር ወር 2009 ዓ.ም ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለባለድርሻ አካላት ለውይይት ያቀረበ ቢሆንም ያልፀደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና እድሳትን በተመለከተ፣

27. ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ፣ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (የመሳሪያ፣ የተሽከርካሪና የሰው ኃይል) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት፣ በእድሳት ወቅትም በሰነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የመጡ ስራ ተቋራጮች፡-

- የሚያቀርቧቸው እና መሟላት ያለባቸውን መሳሪያዎችና ተሸከርካሪዎች በሰነድ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በተመለከተ ግን ፈቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲያሳድሱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ሥራ ተቋራጮች በሰነድ ያቀረቡት የሰው ኃይል (Minimimum man power requirement) የስራ ውል ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ በሰነድ ላይ ያቀረቡት የሰው ኃይል ስራ ላይ ስለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ሥራ ተቋራጮች ፍቃድ ለመውሰድ በ Minimimum requirement ያስመዘገቧቸውን መሳሪያዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳያሳውቁ እያከራዩ መሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞችን በተመለከተ፣

29.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

30.ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የብቃት ደረጃ ከሚወስዷቸው የግንባታ ኮንትራቶች እና ሰራተኞቹን ከሚያሠሯቸው ተግባር ጋር ተመጣጣኝ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ማሳደሳቸውን መቆጣጠርና መከታተልን በተመለከተ፣

31.ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃድ ያሳደሱ መሆናቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር፣ ያላሳደሱትን በተቋራጭነት ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ለማድረግ ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

32.በኦዲቱ ወቅት የሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማደሳቸውን የማይከታተልና የማይቆጣጠር በመሆኑ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ከ11,912 ስራ ተቋራጮች ውስጥ 5,321 ስራ ተቋራጮች ፈቃድ ያላሳደሱ ሲሆን ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በተመለከተ፣

33. የሥራ ተቋራጮች በወሰዱት ፈቃድ ብቻ ሊሰሩ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮች የሚጠየቁበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልት አልተዘጋጀም፡፡

የፌዴራልና የክልሎች የኮንስትራክሽን ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

35. በፌደራል እና በክልሎች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራል እና በክልሎች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ያለው ቢሆንም ተግባራዊነቱ ላይ ልዩነት ያለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ እና በአዲስ አበባ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣

37. በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ/ባሉበት ቦታ ወይም በቅርበት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን በተመለከተ፣

39.ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተይዘው ማህደር ውስጥ እንዲያዙና በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ እንዲገኙ በሚያስችል መልኩ ሊደራጁ ይገባል፡፡

40.ይሁን እንጂ ፈቃድ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ማህደር በጥንቃቄ የማይያዙ እና የሚፈለጉ መረጃዎች በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበትና በቅደም ተከተል (chronological order) መልኩ የማይቀመጡ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ፋይሎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

41.በመሆኑም

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምዝገባና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ሥራ ላይ ለመዋል ለወጡ አዋጆች ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ደንቦች በፍጥነት ተዘጋጅተውና በሚመለከተው አካል ሊጸድቁ ይገባል፡፡ ደንቦቹንም ለማፈጸም ሚረዱ መመሪዎያዎችም በተጓዳኝ ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ፣ ከዚህ በፊት የወጡ መመሪያዎችም ከደንቡ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ እና በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ለማሳደስ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እነዚሁ የሥራ ተቋራጮቹ የሚወስዷቸው የኮንትራክት ፕሮጀክቶች ተገቢውን የሙያ ብቃት ደረጃ ያሟሉ የሰው ኃይል በየፕሮጀክቱ ማሰማራታቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የሚረጋገጥበት አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ የእድሳት ጊዜያቸውን ጠብቀው ያላሰደሱ የሥራ ተቋራጮች ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግና ፈቃዳቸውን ያደሱ ሥራ

ተቋራጮችን ዝርዝር የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣ፣ ዌብሳይት .... ወዘተ) በመጠቀም ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት፣ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሰራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫውን ለማግኘት ያስመዘገቧቸውን (የሰው ኃይል፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች) ለተባለለት ዓላማ/ሥራ እየዋሉ መሆናቸውን በየዓመቱ በእቅድ ይዞ በማረጋገጥ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችለውን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ በወጣው ስታንደርድ መሰረት ከክልሎች ጋር ወጥ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በቅንጅት መስራትእና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ብቻ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን በያሉበት እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመክፈት ካለሆነም ሌላ አማራጭ በማጥናት ተግባራዊ በማድረግ ተገልጋዮች ለአላስፈላጊ ለሆነ የገንዘብና ወጪ እና የጊዜ ብክነት እንዳይጋለጡ ማድረግ አለበት፡፡
- የስራ ተቋራጮችን የሚመለከቱ ማንኛውም ሰነዶች ዘመናዊ በሆነ የመረጃ አያያዝ ዘዴ በመጠቀም ሊያደራጃቸው እና ጥንቃቄ ሊደረግላቸው እና በተገልጋዮች ሲፈለጉ በቀላሉ ሊገኙ እንዲችሉ ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ እንዲቀመጡ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን የተቀላጠፈ ማድረግ እንደሚጠበቅበት

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ፣ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እና በየጊዜው የሚገመገም መሆኑን በተመለከተ፤

42. የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት አስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ለማከናወን የትግበራ መርሃ ግብር ያልወጣለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

44. የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት (ግንባታዎቹ በምዕራፍ ተከፋፍለው መቼ እንደሚሰሩ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ፣ ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች የት እንደሚቋቋሙ፣ ለካሳ ክፍያ የተያዘው ወጪ፣ ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ወጪዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚናቸው መለየቱን…) የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ በመሪ ዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ቢዘጋጅም የግንባታ ግብዓት ሆነ የላብራቶሪና የመጽሐፍት ግዥ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑ በተመለከተ፣

46. የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የዕቅድ ትግበራ መርሃ

ግብር ተዘጋጅቶ በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ኘሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ እንዳልተደረገ እና ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ያልተቀመጠ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. በተጨማሪም የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት በየካቲት 30/2009 ዓ.ም የመጀመሪያው የምዕራፍ ግንባታ መጠናቀቅ እንደነበረበት እና የግንባታው ሂደት ያለበትን ሁኔታ እስከ የካቲት 25/2009 ዓ.ም ድረስ የተደረገው ግምገማና ያሉበትን ደረጃ ከ 38 ከመቶ (ቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ) እስከ 78 ከመቶ (የጂንካ ዩኒቨርሲቲ) ድረስ ሲሆን የኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታው ጭራሹ አለመጀመሩ ታውቋል፡፡ ዝርዝር ሰንጠረዡ ተያይዞ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ዩኒቨርሲቲ	ግንባታው ያለበት ደረጃ በፐርሰንት
1	ደባርቅ	69.36%
2	እንጅባራ	66.29%
3	መቅደላ አምባ መካነሰላም	60%
	ቱሉ አዋሊያ	55%
4	ሰላሌ	48.68%
5	ደምቢ ዶሎ	75.44%
6	ራያ	67.48%
7	ቦንጋ	55.36%
8	ወራቤ	64.39%
9	ጂንካ	78.02%
10	ቀብሪ ደሃር	37.73%
11	ኦዳቡልቱም	ግንባታው እስከ 25/06/09 ዓ.ም አልተጀመረም፡፡

በግንባታው ምክንያት ለሚነሱ ተነሽዎች የተያዘው በጀት በበቂ ጥናት ላይ አለመመስረቱ፣ የሚከፈል የካሳ ክፍያ እና የካሳ ክፍያ መዘግየቱን በተመለከተ፤

49. ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ ሊከፈል ይገባል፡፡ ካሳ የተከፈላቸው ተነሽዎች የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኋላ ከቦታቸው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መነሳት አለባቸው፡፡

50. ይሁን እንጂ ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታው ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነ እና ካሳ የተከፈላቸውም የአካባቢ ነዋሪዎች በተቀመጠው ቀነ ገደብ ከቦታው ያልተነሱ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም፡-

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ቀሪ ሂደቱ ዋነኛው መሪ ዕቅዱ (Master Plan) መሰረት በማድረግ እና የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዘገዩ ስራዎች የሚካካሱበትን መንገድ በመቀየስ በዕቅዱ መሰረት የተማሪዎች ቅበላ የሚከናወንበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የፕሮጀክት እቅድ ትግበራው ሂደቱ ገና በጅምር ላይ ስለሆነ ለአንደኛውም ሆነ ለቀሩት የግንባታ ምዕራፎች በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ በዘላቂነት እንዳይቀጥል ሊከሰቱ የሚችሉ ሥጋቶች ተለይተው እንዲቀመጡ እና እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችም ሊሰሩ ይገባል፡፡
- ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነላቸው ነዋሪዎች በህጉና በመመሪያው መሰረት እንዲከፈል እና ለካሳ ክፍያ ተብሎ በጥቅል የተላኩ ሂሳቦች

እንዲሁም እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም ያልተወራረዱ ሂሳቦች በአስቸኳይ ሊወራረዱ እና በካሳ ምክንያት ያላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተጣርቶ በአስቸኳይ የሚመለስበት ሁኔታ ሊመቻች እንዲሁም ወደፊትም የሚከፈሉ የካሳ ክፍያዎች በካሳ አዋጁ፣ ደንብ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊፈጸሙም እና ከህግ ውጭ እንዲከፈል የተደረገው ሂሳብ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር የወረዳ ኔት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

51.የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

52.ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት ክፍያ እንዳይከፈሉ ክትትልና ቁጥጥር መኖሩን በተመለከተ፤

53.የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እንዳይከፍሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

54.ይሁን እንጂ የወረዳ ኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም እየፈጸሙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡

የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት አገልግሎት መሰጠታቸውን እና ከወረዳኔት አገልግሎት የተገኘ ፋይዳን በተመለከተ፡

55. ዝርጋታቸው የተጠናቀቀ የቪድዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የወረዳኔት አገልግሎት ለመዘርጋት የወጣው ወጪ እና አገልግሎቱ በመሰጠቱ የተገኘው ፋይዳ ሊጠና እና ውጤቱም ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ በርካታ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ዝርጋታቸው ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ በየክልሉ መኖራቸውን እና የወረዳኔት አገልግሎት በማግኘታቸው ከገንዘብ ፋይዳ አንጻር ተመዝግቦ እንዳልተያዘ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በተመለከተ፣

57. ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ ሊታወቅና ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በትክክል ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ተመዝግቦ ያልተቀመጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

59. ጠቅላላ በወረዳኔት በኩል የሚተላለፉና የሚያዙ መረጃዎች የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ የሚመለከት ህግ (National Data Protection Law) ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡

60. ይሁን እንጂ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ በረቂቅ ደረጃ ያለና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤት ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. በመሆኑም፡

- በረቂቅ ደረጃ ያለው የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ እና በባለድርሻ አካላት ተገምግሞ በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ሊሸጋገር ይገባል፡፡

- ለወረዳኔት አገልግሎት ከተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ የሚፈጸመው ክፍያ በአስቸኳይ ተጣርቶ ለተጠቃሚዎች ተመላሽ በማድረግ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ምክንያቱ በአስቸኳይ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድና አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- መንግስት ለወረዳኔት አገልግሎት ያወጣው ወጪ በመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት መሰረት ተመዝግቦ ሊያዝ እና መረጃ ፈላጊ ለሆኑ አካላት ሊያገኙት የሚገባና ሂሳቡ እየተዘጋ በየጊዜው ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
- የቴክኖሎጂ መረጃዎች ወንጀል እና ስርቆት(Cybercrime) እንዳይስፋፉ ለመከላከል የሚስችል የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>የኢትዮጲያ ኢነርጂ ባለስልጣን የኢነርጂ ብቃት(Energy Efficiency) እና ቁጠባ(Energy Conservation) አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

62. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ላይ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ (Energy Efficiency and conservation) ደንብና መመሪያዎች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

63. በኦዲት ወቅት አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጣባን የሚመለከቱ የኢነርጂ ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency and Conservasion Rule and Regulations) በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ቢሆንም አለመጽደቃቸው ታውቋል፡፡

ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡

64. ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መሆኑን ሊቆጣጠር ይገባል::

65. በኦዲት ወቅት ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) አለመውጣቱ ታውቋል፡፡

የኢነርጂ ፈንድ ተቋቁሞ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

66. የኢነርጂ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 23 መሰረት ሊቋቋምና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

67. በኦዲት ወቅት የኢነርጂ ፈንድ ባለመቋቋሙ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ማቋቋማቸውን በተመለከተ፤

68. ባለስልጣን መ/ቤቱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡ ድርጅቶቹም ይህ ክፍል እንዲያቋቁሙ ለማድረግ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል።

69. በኦዲት ወቅት ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም፡-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency and Conservation Rule and Regulation) በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ እና ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡

- ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት ያላቸው መሆኑን የሚለይበት የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) አውጥቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::
- ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ኃይል አባካኝ የሆኑ እና ብቃት የሌላቸው የኢነርጂ መጠቀሚ ቴክኖሎጂዎች በኃይል ቆጣቢና ብቃት ባላቸው ለመተካት እንዲችሉ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ በአዋጁ መሰረት የኢነርጂ ፈንድ ሊያቋቁም እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዲያቋቁሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በስፋት ሊሰራ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርትአሳስበናል።

7. <u>የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸም</u>

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከውድመት መከላከሉን በተመለከተ፡-

70. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

71. በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች ሥር በሚገኙ ወረዳዎች፣

   - በተለያዩ ምክንያቶች መሬት መቦርቦርና አፈር መሸርሸር እየጨመረ መምጣቱ፣
   - በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ ከተራራማ ቦታዎችና ከተቦረበሩ መሬቶች አሸዋ እየወጣ ያለ መሆኑ፣
   - የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997ን በሚቃረን መልኩ ተዳፋትነታቸው ከ60 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ተራራማ ቦታዎች የሚታረሱና ለልቅ ግጦሽ እየዋሉ መሆኑን፣ እንዲሁም በዝዋይ ሻላ ተፋሰስ ውስጥ በሚገኙ 469 ንኡስ ተፋሰሶች

ውስጥ 57,505 ሄክታር የተጎዳ መሬት (በጣም ገላጣ አካባቢዎች፣ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ቦሮቦሮች እና ገደላ ገደል የበዛባቸው፣ አፈሩ እየተሸረሸረ ወደ ሀይቆችና ወንዞች የሚገባ) መሆኑ፣

ለማሳያ ያህል እ.ኤ.አ. ከ2000 - 2011 ዓ.ም ድረስ፡-

- የላንጋኖ እና የአብጃታ ሐይቅ በቅደምተከተላቸው 4.0 ኪ.ሜ^2 እና 38.3 ኪ.ሜ^2 የቀነሱ መሆኑ፣ በሁለቱም ሐይቆች አከባቢ የጥቅጥቅ ደን ሽፋን በ9.0 ኪ.ሜ^2 መቀነሱ፣ በተቃራኒው የእርሻ፣ የሳር እና የግጦሽ መሬት በላንጋኖ 43.0 ኪ.ሜ^2 እና በአብጃታ122.5 ኪ.ሜ^2 መጨመሩ፣
- የዝዋይ ሐይቅ በአማካይ ጥልቀት ከ2007 ዓ.ም በፊት 4 ሜትር የነበረው ሲሆን አሁን በአማካይ 2.5 ሜትር ጥልቀት ያለው መሆኑ፣
- የጨለለቃ ሐይቅ ከሐዋሳ ሐይቅ ጋር አንድ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ የግጦሽና አሸዋ የማውጣት ሥራ የሚከናወንበት መሆኑ፣ እንዲሁም በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ የወይጦ ወንዝ በታችኛው ተፋሰስ እና በሎካ አባያ ወረዳ ቡኪቶ በሚባል ቀበሌ 2500 ሄ/ር መሬት በላይ ለኢንቨስተሮች በመሰጠቱ ደን በከፍተኛ ሁኔታ የተጨፈጨ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰስ አካባቢዎች ጥበቃ በተመለከተ፡-

72.ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰሱ አከባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ሊያጠና እና በጥናቱ መሰረት ጉዳት የደረሰባቸውን አከባቢዎች ሊለይ ይገባል ፡፡ የተለዩት አካባቢዎች ግልጽ የሆነ የመመረጫ መስፈርት በማዘጋጀት እንደጉዳታቸው መጠን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት የማልማትና የማንከባከብ ስራ ሊከናወንባቸው ይገባል፡፡

73.በባለሥልጣኑ በሶስት ንዑስ ተፋሰሶች (ሀዋሳ ፣ዝዋይ ሻላ እና አባያ ጫሞ ላይ ንዑስ ተፋሰሶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ መሰረት የተለያዩ ጉዳት አይነትና መጠን ያላቸው እና ከሐይቆች ወይም ከውሃ አካላት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው

አካባቢዎች ለማልማትና ለመንከባከብ ቅድሚያ ለመስጠት ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ እና ከሀይቁ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እና ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ሳይሆኑ ሌሎች አካባቢዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ለእንክብካቤ እየተመረጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

74.በኦዲቱ ወቅት በባለሥልጣኑ የተለያዩ እንክብካቤና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ በቱላ ክፍለ ከተማ እና በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የተለያዩ ጉዳት ዓይነትና መጠን ያለውና ከሀዋሳ ሀይቅ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ተብሎ በ2008 በጀት ዓመት ከተለዩት ውስጥ፡-

- በቱላ ክ/ከተማ በሀበላ ወንዶ ቀበሌ በጫራ ማይክሮ ተፋሰስ ውስጥ ቀጥታ ወደ ሀይቁ የሚፈስና ከፍተኛ ጥልቀትና ስፋት ያለው በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እያደረሰ ያለው ቦሪቦሪ /ገሊ/ ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ሥራ ያልተደረገለት መሆኑ፣
- በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ በጋሎ አርጌሳ ቀበሌ ከፉኬሳ ሱኬ፣ መቅባሳ ቆርኬ፣ ኦዶ ወጣጤ ቀበሌዎች የሚነሳ ጎርፍ ሞሌ በሚባል ቦታ ተገናኝቶ ቀጥታ ወደ ሀይቁ የሚገባ እና ጎርፉ የፈጠረው ገሊ በግምት 20-30 ሜትር ስፋት እና 5-10 ሜትር ጥልቀት ያለው ቢሆንም ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ያልተደረገለት መሆኑ፣
- በዝዋይ ሻላ ንዕስ ተፋሰስ በዝዋይ ዱግዳ፣ በጥዮ፣ በኣዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ፣ በአርሲ ነገሌ ወረዳዎች የተለያዩ ጉዳት ዓይነትና መጠን ያላቸውና ከሀይቆች (ዝዋይ፣ አብጃታና ሻላ) ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ተብሎ በ2008 በጀት ዓመት የተለያዩ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራዎች የተከናወኑባቸው ቀበሌዎች ቢኖሩም፤
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ በበሺራ ጫፋና በሂሬራ ቀበሌዎች መካከል የሚገኝ በሳቀላ ተፋሰስ ከተለያዩ አካባቢዎች በሚመጣ ጎርፍ የተፈጠሩ ትላልቅና ሰፋፊ ቦርቦርዎች ያሉና ደለልን ይዞ ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገቡ ቢሆንም ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣

- በጥዮ ወረዳ ብዙ ምንጮች የሚፈልቁበትና በአካባቢው ህብረተሰብ ጉዳት እየደረሰበት የሚገኘው ጭላሎ ተራራ ላይ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣
- በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ አባዬ ደነባ ቀበሌ ከፍተኛ ጥልቀትና ስፋት ያለው ገሊ /ቦሪቦሪ/ ከዝዋይ ሀይቅ ጋር ቀጥተታ ግንኙነት ያለው ቢሆንም ከፍተኛ ወጪ ያስፈልጋል በሚል የ2008 በጀት ዓመት ፕሮጀክት ውስጥ ያልተካተተ መሁኑ፣ እንዲሁም
- በአርሲ ነገሌ ወረዳ በሻላ ቢላ ቀበሌ በፍቄ ንዑስ ተፋሰስ ፍቄ ከሚባል ተራራ በሚነሳ ጎርፍ የተፈጠረው ገሊ/ቦርቦሪ/ ስፋቱ በግምት 15-20 ሜትር የሚሆን እና ጥልቀት ያለው ሲሆን ከፍተኛ ደለልን ወደ አብጃታ ሀይቅ የሚወስድ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት የተቀረጸው ፕሮጀክት ውስጥ አለመካተቱ፣

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖረው መደረጉን በተመለከተ፡-

75. በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የሚሰሩ የልማትና የእንክብካቤ ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ዘላቂነታቸው በተረጋገጠ መልኩ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ሥራዎቹም የተቀናጀና ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በየጊዜው ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን መከታተል/መገምገም ይኖርበታል፡፡

76. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተፋሰሱ ውስጥ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍ የተሰሩ የስነ አካላዊ (physical structures) እና የስነ ህይወታዊ (biological conservation) ስራዎች በቅንጅት እንዲደጋገፉ አለመደረጉ እንዲሁም ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑን በሀዋሳና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ ተመርጦ በታዩ በወንዶ ገነት፣ በጥዮ፣ በዝዋይ ዱግዳ፣ በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻና በአርሲ ነገሌ ወረዳዎች እና በሀዋሳ ከተማ፣ በቱላ ክፍለ ከተማ፣በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ለአብነት፡- በሐዋሳ እና ዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች፡-
- አገልግሎት መስጠት እንደጀመሩ የፈረሱ መሆኑ፣

- የክትር (ጋቢዮዎን) ስራዎች የጎርፍ ግፊት መጠን /discharge rate/ ሳይጠና የተሰሩ አካላዊ ስራዎች ርቀታቸውን /interval/ ጠብቆ አለመሰራታቸው፣
- በተሰራው ጋቢዎን አልፎ የሚፈስ ውሃ የሚያርፍበት ቦታ /Apron/ ያልተሰራ በመሆኑ ተጨማሪ መሬት መቦርቦር እያስከተለ መሆኑ፣
- እንዲሁም በየጊዜው የችግኝ ተከላ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚከናወን ቢሆንም በአብዛኛው የማይጸድቁ (low survival Rate) መሆኑን ለምሳሌ በወረዳዎች የችግኞች ተከላ ውጤታማ ነው እየተባለ በሪፖርት የሚገለጸው በአካል ሲታይ ችግኞቹ የጸደቁ አለመሆናቸው መታየቱ እና
- በአርሶ አደሩ ተሳትፎ በተፋሰሱ ውስጥ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በየዓመቱ የሚታረሱና የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩ፣

ታውቋል፡፡

በተፋሰሱ የውሃ አካላትን፣ ሐይቆቹንና የብዝሀ ሕይወቱን ሕልውና ከብክለት መከላከልን አስመልክቶ፡-

77.ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የተፋሰሱን አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ ማዘጋጀትና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞችና ሐይቆች ከመልቀቃቸው በፊት ቆሻሻዎቹ መታከማቸው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ሀይቆቹንና የብዝሀ ህይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተጽኖዎችን የመለየት፣ የመቀነስና የመከላከል ስራን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

- ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ወንዞች ከመለቀቃቸው በፊት ከባለሥልጠኑ አክሞ ለመልቀቅ ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው ቢሆንም፤ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ
- በናሙና የታዩ ድርጅቶች ከብ.ጂ.አይ (BGI) ኢትዮጵያ ፒ.ኤል.ሲ (ሀዋሳ ቢራ ፋብሪካ)፣ ኢታብ ሳሙና ፋብሪካ፣ ታቦር ሴራሚክ ፋብሪካ፣ ሞሃ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ እና ከሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከምርት ክፍሎች የሚወጣው ብክለት ያለው ፍሳሽ በጨፌ ረግረጋማ መሬት

አማካኝነት በጥቁር ውሃ ወንዝ በኩል ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚገባ መሆኑን፣ በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ እና ዝዋይ ሐይቅ ላይ ህጋዊም ሆነ ህገ ወጥ የአሳ አስጋሪዎች የሚበዙና የአሳዎች ተረፈ ምርት መልሶ ወደ ሐይቆቹ የሚጣል መሆኑ፣

- ዝዋይ ሻለ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ በናሙና የታዩ በዝዋይ ከተማ ከመስኖ እርሻ ማሳ እና ከአበባ ልማት ድርጅቶች ሼር ኢትዮጵያና በሼር ኢትዮጵያ ቅጥር ግብ ውስጥ ከሚገኙ Herburg Roses Plc, AQ Roses, Zway Roses የሚወጣ ፍሳሽ ኬሚካል ቆሻሻ ሳይታከም ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባ መሆኑ፣
- በአዳሚ ቱሉ ጅዶ ኮምቦልቻ ወረዳ በዝዋይ ሐይቅ ዙሪያ ከፍተኛ የመስኖ ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን የተለያዩ ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን ስለሚጠቀሙ በዝናብ ወቅት በጎርፍ እና በመስኖ ቦይ አማካኝነት ኬሚካሉ ወደ ሐይቁ የሚገባ መሆኑን እንዲሁም
- በምስራቅ ዝዋይ ማይክሮ ተፋሰስ ውስጥ ከአሰላ ከተማ የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻዎች የሚደፉበት ቦታ ምቹ ባለመሆኑ ቆሻሻዎች በዝናብ ወቅት በተለይ በክረምት ወልኬሳ ወደ ሚባል ወንዝ ገብቶ የካታርን ወንዝ በመቀላቀል ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባና የሚበክል መሆኑ እና
- ከዝዋይ እና ከመቂ ከተሞች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች የሚደፉበት ቦታ ምቹ ባለመሆኑ ቆሻሻዎች ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባና የሚበክል መሆኑ፣
- ለባቱ (ዝዋይ) ከተማ ለመጠጥ ውሃ ሲያገለግል የነበረው የዝዋይ ሀይቅ በነዚህ ችግሮች ምክንያት በመበከሉ የከተማው ነዋሪዎች የከተማውን ውሃ መጠቀም ማቆማቸው፣

በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የአከባቢ ተጽኖ ግምገማን እና የግንዘቤ ሥራን በተመለከተ፡-

78. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የሚያከናውኑዋቸውን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ አስተያየት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በሚከናወኑት የልማት

ሥራዎች እና ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ ሊያደርሱ የሚችሉ ተጽዕኖች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

79.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች በሚያሰጡኑዋቸው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ የውሃ አካላቱን ደህንነት በዘላቂነት የተጠበቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሆነው መጠናታቸውን እንዲያረጋግጥ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት አስተያየት እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በሐይቆችና በረግረጋማ መሬቶች አካባቢ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እና ግንዛቤ ያልሰጠ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ስለመደረጉ፡-

80.ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ ይገባል፡፡

81.ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት

- በሁሉም ወረዳዎች በባለስልጣኑ በጀት ድጋፍ ለሚከናወኑ ስራዎች በጀቱ በጊዜ የማይለቀቅ መሆኑ፣
- በሀዋሳ ከተማ በቱላ ክፍለ ከተማ የክትር /ጋቢዎን/ ስራዎች በ2008 በጀት ዓመት ለማከናወን ድንጋይና ሽቦ ተገዝቶ ሳይሰራበት ለቀጣይ በጀት ዓመት የተላለፈ መሆኑ፣
- በሶስቱም ንዑስ ተፋሰሶች ውስጥ የችግኝ ተከላን በተጎዱ ቦታዎች፣ በተሰሩ እርከኖች እና በሌሎች ቦታዎች ላይ ለመትከል 19.5 ሚሊዮን ችግኞች ታቅዶ 4.48 ሚሊዮን ችግኞች (23%) ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣

- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ በሄሬራ ቀበሌ እና በወንዶ ገነት ወረዳ በ3 (አባዬ፣ ወተራ ቀጨማ፣ ዩዎ) ቀበሌዎች በ2008 በጀት ዓመት ለመስራት የታቀዱ ስራዎች ያላለቁ መሆኑ፣
- በፕሮጀክት አፈጻጸም በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ ጨንቻ እና አባያ በመካከለኛ፣ አ/ምንጭ ከተማ፣ በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ- ቱላ ክፍለ ከተማ እና ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ፣ በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ- አርሲ ነጌሌ፣ ሁልባረግ እና ቆሬ ወረዳዎች ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ መሆኑ፣
- በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ሀይቁ ዙሪያ ያለው ህብረተሰብ ከሀይቁ ጥገኝነት ለማላቀቅ ሲባል ስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች የፕሮጀክቱ አካል በማድረግ ቀጣይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን በወረዳው የተሰራጨው የንብ ቀፎና የከብቶች መኖ ግን ሀይቁ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው እና ለስራ አጦች ሳይሆን የተሻለ ኑሮ ላላቸው ሰዎች የተሰጠ መሆኑን፣ እንዲሁም በቱላ ክፍለ ከተማ በ2008 በጀት ዓመት ለስራ ዕድል ፈጠራ ተብሎ የተገዛ የንብ ቀፎ እስከ መስከረም 2009 ዓ.ም ድረስ ለሚመለከታቸው ያልተሰራጨ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

የረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና የሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

82. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ረግረጋማ መሬቶችና የሐይቆች ዳርቻ በመከለል፣ ወሰኑን የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት፣ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደርና የሀይቆች ዳርቻ ክልልን የሚመለከት ጥናት ያልተካሄደ እና የሀይቆች ዳርቻ ክልል (Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች በሚያካልሉዋቸው ወረዳዎች

- በሁሉም የሀይቁ ዳርቻ ክልል ያልተከለለ በመሆኑ ከሀይቁ 5 ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ የሚታረስ እና ከብቶች የሚሰማሩበት መሆኑ፣
- በአርሲ ዞን በጥዩ ወረዳ ጨፌ ሚሶማ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ረግረጋማ መሬት ለባለሀብት ተሰጥቶ እየታረሰ መሆኑ፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ 4130 ሄክታር የሚሆን አምስት ረግረጋማ መሬቶች (ሼተ-ማታ-ወደ 300 ሄ/ር፣ ጥኖ- 3000ሄ/ር፣ ወንበራ- 400ሄ/ር፣ ገኖ 30 ሄ/ር እና ዋራቤ- 400ሄ/ር) የሚሆኑና ሁሉም ረግረጋማ መሬቶች ተከልለው ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ ያልሆኑ መሆኑ፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳው ሼሌም፣ ውሺቲ እና ዱግዳ አባቱ ቀበሌዎችን የሚያዋስነው ሼተ-ማታ ረግረጋማ መሬት ጥኖ ከሚባል ረግረጋማ መሬት ጋር ተያይዞ ያለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እየታረሰ መሆኑ እና ሼተ-ማታና በአራጣ ቀበሌ ጥኖ ረግረጋማ መሬት አካል የሆነ መሬት ለባለሀብት በመሰጠቱ ለመታረስ ዝግጅት ላይ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-

84. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን ፍትሃዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የክልልና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡ የውሃ አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተፋሰሱ በሶስቱ ንዑስ ተፋሰሶች (በሀዋሳ፣ በዝዋይ ሻላ እና በአባያ ጫሞ) ውስጥ የውሃ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ በላይኛውና በታችኛው ተፋሰስ ላይ በሚገኙ ተጠቃሚዎች መካከል የአጠቃቀም ግጭት መኖሩ፣ ለአብነት፡-

- በሻሸመኔ ወረዳ በመስኖ ልማት ስራ እና በመጠጥ ውሃ አጠቃቀም ላይ ግጭቶች ያሉ መሆኑ፣
- በጊዳቦ ተፋሰስ በዳራ ወረዳ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ፍትሃዊ ባለመሆኑ ግጭቶች መኖራቸውን፣ በሎካ አባያ ወረዳ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች

በተለይም በብላቴ ወንዝ ላይ በእርሻ ስራ ላይ በተሰማሩ ኢንቨስተሮችና አርሶ አደሮች መካከል ፍትሀዊ የውሃ አጠቃቀም ላይ ግጭቶች ያሉ መሆኑ፣

- በምዕራብ ዝዋይ ንዑስ ተፋሰስ በወንዞች ላይ የሚካሄዱ የመስኖ ተግባራት ፍትሀዊ ባለመሆናቸው በላይኛዉ ተፋሰስና በታችኛዉ የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች መካከል አለመግባባት የሚስተዋል መሆኑ፣
- በቡልቡላ ወንዝ፣ ወርጋ ወንዝ፣ መቂ ወንዝና ለመቂ ወንዝ ገባር የሆኑ ሌሎች ወንዞች ላይ በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ አለመግባባት የሚስተዋልባቸው መሆኑን እና በአርሲ ነገሌ ወረዳ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ ግጭት (conflict) ያለ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በተፋሰሱ ውስጥ የሚካሄደውን ውሃ አጠቃቀምን መጠን እና ክፍያ እንዲሁም የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ሥርዓት መዘረጋቱን በተመለከተ፡-

86.ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ውሃ ነክ ስራዎች ለመስራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት፣ የሚጠቀሙት የውሃ መጠን እና የክፍያ ተመን አወሳሰን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

87.ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ለተለያዩ ሥራዎች ውሃን ለሚጠቀሙ የአጠቃቀም ፈቃድ ሊሰጥና በየዓመቱ ፈቃዱን ሊያድስ ሲገባ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች በተፋሰሱ ውስጥ ውሃን የሚጠቀሙ ስለመሆኑ ባለሥልጣኑ ከሰበሰበው መረጃ 319 የውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥ

- የውሃ አጠቃቀም ፈቃድ የሰጠው ለ14 መሆኑን፣ ፈቃድ ለማውጣት በሂደት ላይ ያሉት ይህ መረጃው እስከ ተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ 5 ብቻ መሆናቸውን እና ሌሎቹ 300 የውሃ ተጠቃሚዎች (94%) የውሃ ፈቃድ ሳይወስዱ ውሃን የሚጠቀሙ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ አጠቃላይ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚዎች (የመስኖ፣ ፋብሪካዎች፣ ሪዞርቶች…) ብዛት እና የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን ለይቶ የማያውቅ መሆኑ፣

- በተፋሰሱ ላይ ለተለያየ ሥራ የተተከሉ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ብዛታቸው እና አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ ባለስልጣኑ መረጃ የሌለው መሆኑን እና
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚያውቃቸው 319 ውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥ 86 ተጠቃሚዎችን ብቻ የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን (የሜትር ኪዩቢክ ውሃ) የሚያውቅ መሆኑ፣

88.በተጨማሪም በውሃ ክፍያ ላይ

- የአከፋፈል ታሪፍ መመሪያ አለመኖሩ፣
- በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የውሃ ሀብት የሚጠቀሙ ድርጅቶች የቢ.ጂ.አይ (BGI) ኢትዩጵያ ሀዋሳ ቢራ ፋብርካ፣ የኢታብ ሳሙና ፋብሪካ፣ የሞሃ ለስላሳ ፋብሪካ፣ የሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ የኤልፎራ አግሮ ኢ/ኃ/የተ/የግል/ማ፣ የካስትል ዋይነሪ ኃላ/የተ/የግል/ማ፣ ሼር ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግል/ማ፣ ሰላም የተፈጥሮ የታሸገ የማዕድን ውሃ ፋብሪካ ወዘተ…) ለሚጠቀሙት ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ የሌለ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውሃ ተጠቃሚዎቹ ለሚጠቀሙት ውሃ የክፍያ ታሪፍ ረቂቅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያላቀረበ መሆኑ፣

ባለሥልጣን መ/ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ እየፈሰሰ ስለመሆኑ ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡-

89.ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኙ ወንዞችን ተፈጥሯዊ የፍሰት ሁኔታ አለመዛባቱን የሚከታተልበት ሥርዓት በመዘርጋት መከታተልና መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች ሥር በሚገኙ ወረዳዎች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ በመከታተል አቅጣጫ የቀየሩ ወንዞችን ወደ መደበኛ ፍሰታቸው እንዲመለሱ እየተከታተለ አስፈላጊውን መፍትሄ የማይሰጥ መሆኑ፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ ካታር ወንዝን በመቀላቀል ዝዋይ ሀይቅ ሲገባ የነበረው ጬፋ ወንዝ በአራጣ ቀበሌ ጌኖ በሚባል ቦታ አቅጣጫውን

በመልቀቅ ወደ 40 ሄክታር የሚሆን የአርሶ አደሩ መሬት ላይ በመተኛት በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣

- በኮንሶ አካባቢ የሚገኘው የወይጦ ወንዝ እና በአባያ ጫሞ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኘው የብላቴ ወንዝ አቅጣጫ የቀየረ መሆኑ፣ እና
- የወንዞች ፍሰት የሚቆጣጠር መሳሪያ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሌለ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-

90.ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ወሳኝ የሆኑ በቀጥታ የውሃ ሀብት አስተዳደር የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ለማቀድና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የትስስር ፎረም መመስረት፣ በጋራ ማቀድና የስራ አፈፃፀምን በጋራ መገምገም አለበት፡፡

91.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የተፋሰስ ልማት እንክብካቤ ሥራዎችን በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት (የክልል፣ የዞን እና ወረዳ መሬት አስተዳደር፣ የመስኖ ልማት፣ ኢንቨስትመንት፣ ማዕድን እና ኢነርጂ ጽ/ቤቶች…) ጋር የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ለማቀድ፣ ለመጠቀም፣ ለመንከባከብ እና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የምክክር መድረክ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በቅንጅት መሰራታቸውን በተመለከተ፡-

92.በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡ ቅንጅቱም ተፋሰሱ ከሚገኝባቸው እና የተጎዱ አካባቢዎች ከሚገኙ የወረዳ አካላት እና የውሃ ተጠቃሚዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

93.ይሁን እንጂ በሀዋሳ እና ዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ውሃ ተጠቃሚ ድርጅቶች ባሉበት አካባቢ በሀይቆችና በውሃ አካላት ዙሪያ የተጎዱ አካባቢዎችን ለማልማትና ለማንከባከብ ፍላጎት

ያላቸው ቢሆንም የተጎዱ አካባቢዎች ያሉበትን ቦታ፣ የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና ማልማት የሚቻልበትን ሁኔታ በማመቻቸት የሚያስተባብር አካል አለመኖሩ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክት ቀርጾ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን /physical structures/ ያከናወነባቸው ቦታዎች ላይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ሙሉ በሙሉ በሥነ ህይወታዊ /biological/ ሥራዎች በጋራ መሰራት ሲገባቸው ያልተሰሩ/ ያልተደገፉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-

94. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡

95. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን (ወቅታዊ የሆነ የውሃ መጠንና ጥራትን፣ የወንዞች የፍሰት መጠን፣ የሀይቆች ከፍታና ዝቅታ መጠን፣ የወንዞች እና የሀይቆች የደለል መጠን፣ እንዲሁም የውሃ ተጠቃሚዎች አይነትና ብዛት) መረጃው የሌለ መሆኑ፣ በተለያዩ አካላት (በተማሪዎችና በተመራማሪዎች) ስለተፋሰሱ የተጠኑ ጥናቶችን የማይሰበሰቡና የማይተነተኑ መሆኑ፣ እንዲሁም ሌሎች ከተፋሰሱ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር እና በመተንተን መረጃዎችን አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የሚለዋወጥበትና የሚይዝበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩ፣

96. በተጨማሪም ባለሥልጣን መ/ቤቱ፡-

- በተፋሰሱ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜትሮዋሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብና ለማደራጀት የሚረዳ የመረጃ ቋት (Data Base) አለመኖሩ፣

- በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎችን ከውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተረከበ ቢሆንም ነገር ግን አብዛኛዎቹ መሳሪያዎች አገልግሎት የማይሰጡ፣ አስፈላጊው ጥገናም ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ያልተፈተሹ (calibration Test) ያልተደረገላቸው በመሆኑ መረጃዎችን በተገቢው መልኩ መስጠት አለመቻላቸው፣
- የሀይድሮሎጂ መሳሪያዎች አዲስ ተተክለላቸው የተቋቋሙትም ጣቢያዎችና መሳሪያዎቹ ወደ አገልግሎት ያልገቡ እና የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የሚሰበሰቡትን መረጃ በማዕከል ሆኖ ለማሰባሰብ የሚያግዝ ኔትዎርክ ያልተዘረጋላቸው መሆኑ፣
- በሻላ ንዑስ ተፋሰስ ዉስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ሁሉም የመለኪያ ጣቢያዎች (hydrological stations) የሌሉባቸዉ አካባቢዎች መሆኑን እና በንዑስ ተፋሰሱ ዉስጥ ያለዉ የከርሰ ምድር ውሃ መጠን (ground water potential) የማይታወቅ መሆኑ እንዲሁም
- ካታር ወንዝ ከ25 በላይ ገባር ወንዞችና ጅረቶች ቢኖሩትም የወንዞቹን የፍሰት መጠን የሚለካበት የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎች በወንዞቹ ላይ ባለመኖራቸው መረጃዎችን ማሰባሰብ አለመቻሉ

ታውቋል፡፡

በመሆኑም፤-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የተጎዳን መሬት መልሶ ለማልማትና ስነ- ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በተመረጡ ስፍራዎች የተከለለ መሬትን ከሰውና ከእንስሳ ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ፣ በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች ከፍተኛ የአካባቢ መራቆት የሚታይባቸውን በጥቃቅን ተፋሰስ (micro watershed) በመለየትና በደረጃ ሊያስቀምጥ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡

- የተለያዩ ልማት ሥራዎች ሲከናወኑ የተፋሰሱን ስነምህዳር ለመጠበቅና ጉዳቶችን ለመከላከል ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ጋር ተያይዞ ያሉ የመንግስት ፖሊሲዎችን ባማከለ መልኩ በማንኛውም ልማት ድርጅት ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ወጥ የሆነ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ሐይቆች እና ወንዞች ያለባቸውን የስህነምዳር እና የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ በማጥናት እና በጥናቱ መሰረት እየደረሰባቸው የሚገኘውን ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችል የመፍትሄ እርምጃ መውሰድና የተጀመሩ ሥራዎችን በመደገፍ ማጠናከር አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር የተፋሰሱ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን (Buffer Zones) የሚከለልበት የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት እና ለከፍተኛው የተፋሰስ ምክር ቤት አቅርቦ እንዲጸድቅ በማድረግ በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ እጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ፣ የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ፣እና ሌሎች ዳርቻዎቹን የሚጎዱ ተግባራት እንዳከናወኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በሀይቆች አካባቢ የሚገኙ ረግረጋማ መሬቶች እንዳይታረሱ እንዲከለል ሊያደርግ፣ (delineation of the wetlands)፣ ለባለድርሻ አካላትና በተፋሰሱ ውስጥ ለሚኖረው ህበረተሰብ በተፋሰሱ ልማትና እንክብካቤ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሀይቆችን ለማስተዳደር እና ለመንከባከብ የሚያስችል የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክትን በሁሉም ሐይቆች ዙሪያ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ወጥና በጥናት ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ መምረጫ መስፈርት በማውጣት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት የፕሮጀክት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተፋሰስ በመለየት የፕሮጀክት ዶክመንት ማዘጋጀት፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸትና ስነ አካላዊ እና የስነ- ህይወታዊ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራን እንደ አስፈላጊነቱ የአፈር ካብ፣ የጋቢዮን ክትር፣ የድንጋይ ክትር፣ የእንጨት ክትር፣ ማይክሮ ቤዝን፣ ውሃ ማስረጊያ ጉድጓድ፣ የህብረተሰብ ኩሬ እና የቤተሰብ ገንዳ፣ ችግኝ ጣቢያዎችን የማስተካከል ሥራ፣ የተለያዩ የችግኝ ዝርያዎችን የማፍላት፣ የችግኞችን ጉድጓድ አዘጋጅቶ መትከልና በማንከባከብ የተፋሰሱን የተፈጥሮ ሃብት ልማትና እንክብካቤ ሥራችን በማከናወን በመራቆት ላይ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት መልሶ እንዲያገግም በማድረግ አርሶ አደሩ የሚጠቀማቸው ማዳበሪያና ሌሎች ኬሚካሎች በዝናብና ጎርፍ ታጥበው ወደ ውሃ አካላት እንዳይገቡ እና የደለል መጠን እንዲቀንስ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን የስነ-ሕይወታዊና ስነ- አካላዊ ስራዎች ሲከናወኑ በአብዛኛው ሥራ በህብረተሰቡ ጉልበት ተሳትፎ የሚሰራ በመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል በማደረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በወቅቱ በመልቀቅ እና ከወረዳዎቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ ውሃ የሚጠቀሙ አካላት በሙሉ የውሃ ሀብት ለመጠቀምና ውሃ ነክ ስራዎችን ለመራት የሚያስችል ፍቃድ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ በውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ 197/2000 እና ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 115/2005 ዓ.ም መሰረት ፈቃድ በመውሰድ እንዲሰሩ ሊደረግ እና ፈቃድ ያላወጡ አካላት ከውሃ መጠቀም እንዳይችሉ የሚያደረግበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በተጨማሪም ማናቸውም ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎችን የባለሥልጣኑን ፈቃድ ሳያገኙ ማናቸውም አካላት በተፋሰሱ ሥር ወደሚገኙ የውሃ አካላት ለመልቀቅ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ መውሰዳቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፤ የሚለቀቀውም ፍሳሽ ታክሞ ስለመለቀቁ ባለሥልጣን መ/ቤቱ

በየጊዜው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ ካለፈቃድ ውሃ የሚጠቀም እና ሳይታከም ቆሻሻዎችን ወደ ውሃ አካላት በሚለቁ ማናቸውም አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እና የህግ እርምጃ ባለሥልጣኑ ሊወስድ ይገባል፡፡

- የመስኖ አጠቃቀሙን ዘመናዊ ማድረግ (Drip and sprinkler irrigation syatems)፣ የሐይቁን ዙሪያ በመከለልና ኬሚካልን በሚቋቋሙ ዕጽዋቶችን በማልማት ጎርፉንና ብክለቱን መከላከል እና የውሃ ሀብት እንዳይበከል እና ለጤናና ለአካባቢ የጤና ጠንቅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ሀይቆችንና ብዝሀ ህይወቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በመለየት፣ ሀይቆችና ላይ በሚፈጥሩት ተፅዕኖ መሰረት ችግሮቹን መቅረፍ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ሀይቆችና ብዝሀ ህይወቱ ላይ የሚፈጠረውን ተጽዕኖ መቀነስና መከላከል ይኖርበታል፡፡
- የውሃ ሀብትን ለማልማትና ህዝቡን የልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ፈቃዶች አካባቢንና ህዝብን ማዕከል ያደረጉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ በመመርመር እና የሚመለከታቸውን አካላትን እና ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተሳተፈበት መሆን አለበት፡፡ ፈቃዱ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ስራዎችም ፍቃድ በወሰዱት መሰረት መተግበራቸውን ባለሥልጣኑ ሊቆጣጠርና ተገቢውን የቴክንክ ድጋፍ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር እድሸጋገሩ፤ ባለሥልጣኑ በጀትን በወቅቱ ሊለቅና አስፈላጊ በሆኑ ኮዶች ላይ ሊመደብ፣ ፕሮጀክቶቹ ያሉባቸው ወረዳዎች መረጃና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በየጊዜው እንዲቀርብ ሊያደርግ፣ ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጀመሩ ሊያደረግ፣ የፕሮጀክቱን ተግባራት የሚያከነውኑ አካላቶች በገቡት ውል መሰረት የፕሮጀክት ስራዎችን አጠናቀው እንዲያስረክቡ ክትትል ሊያደርግ እና የድንጋይና ጋብዮንም ሆነ የሌላ ቁሳቁሶች ግዥዎች በወቅቱ ሊፈጸም ይገባል፡፡

- በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ሀብት በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳዳር ስር በማዋል የተፋሰሱን ስነ- ምህዳር የጠበቀ፣ ዘላቂና ፍትሐዊ እንዲሁም ከብክለት ነፃ የሆነ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ መጠንን ማወቅና መለየት እንዲሁም በተገኘው የውሃ አቅም ጥናት ውጤት /የተፋሰሱን ውሃ ፍላጎትና ያለው ውሃ መጠን ባገናዘበ መልኩ/ መሰረት ፍትሃዊ የውሃ ምደባ ሊያካሂድ፣ የውሃ ተጠቃሚዎችን በመለየት ፈቃድ እንዲያወጡ ሊያደርግ፣ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ለማስቀረት ለመፍታት የሚረዳ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣኑ በተፋሰሱ ውሃ ተጠቃሚዎች ለሚጠቀሙት ውሃ መጠን ክፍያ እንዲከፍሉ የሚያስችል ታሪፍ የሚወሰንበት የሕግ ማዕቀፍ እና ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የወንዞችን ፍሰት ሁኔታ በመከታተል በክረምት ወቅት አቅጣጫቸውን ስተው ጉዳት በማህበረሰቡ ላይ እዳያደርሱ በቅድሚያ ከሚመለከታቸው የክልልና ወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት ስነ- አካላዊ እና የስነ- ህይወታዊ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣኑ በተፋሰስ ደረጃ የአየር ሁኔታን እና የተፋሰሱን ዓመታዊና ወቅታዊ የዝናብ መጠንና ስርጭት በመለየት ለዓመታዊ የወንዝ ፍሰት ያለውን አስተዋፅዎ በመተንተን፣ ተፈጥሮአዊ የወንዞች ፍሰትን የሚያስተጓጉሉ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮችን ሊከታተልና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውሃ ሀብት ጋር ቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው አካላት ጋር የቅንጅትና የትስስር ፎረም በመመሰረት ስለ ውሃ ሀብት መረጃ መለዋወጥ፣ መመካከር፣ ማቀድና መወሰን፤ ሁሉንም አጋር አካላት የሚያሳትፍ የተቀናጀ ስራን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ፤ ወጥና ተከታታይነት ያለው የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና የግምገማ ስርዓት መዘርጋት፤ የእቅድ ክትትልና ግምገማ

ስርዓት ማስፈጸሚያ ስልት መቅረጽ እንዲሁም ግልጽና አሳታፊ የሆነ የእቅድ ክትትልና ግምገማ ስርዓትን መተግበር አለበት፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውሃ ተጠቃሚዎችን በመለየት በየዓመቱ የሚጠቀሙትን ውሃ መጠን መረጃ መያዝ፣ በተፋሰሱ ዙሪያ በተለያዩ አካላት የተጠኑ ጥናቶች በማሰባሰብ ሊይዝ ፣ በጥናቶቹ ላይ የተቀመጡ መፍትሄ ሃሳቦችን ተግባራዊ ሊያደረግ፣ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ኃብት በተለይ ውሃ ሀብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜቲሮሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማደራጀት የሚረዳ መረጃ ቋት ሊያቋቁም ይገባል፡፡
- ባለሥልጣኑ ከዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን በተፋሰሱ እየታዩ ያሉ ችግሮችን በቅደም ተከተል የመለየትና መፍትሄ የማስቀመጥ ተግባራትን ማከናወን፣ የምርምር ስራዎችን አጠናክሮ ለመቀጠል የላቦራቶሪ ማዕከላትን ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ደርጅቶች ጋር በመሆን የማደራጀት፣ የሃይቆቹን ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ባህላዊ እና ስነ- ህይወታዊ ጠቀሜታዎችን በማጉላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰራዎች ለመስራት እና ለደህንነታቸው ስጋት የሆኑትን ነባራዊ ችግሮች ለማወቅ በተለያየ መልኩ ጥልቅ የሆነ ጥናት (Research) ሊደረግ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8. <u>በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

ዝርያ ማሻሻያ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና እስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-

97.አገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ የእንስሳት የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች የሚመሩበት እና ሊደረስበት የታሰበውን አቅጣጫ የሚያመላክት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና ተመርጠው በታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልል (የኦሮሚያና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች)ና ዞንና ወረዳዎች እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ለመረዳት እንደተቻለው የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚያስችል ፖሊሲ (ስትራቴጂ) ተቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ ታውቋል፡፡

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ እቅድ አዘገጃጀትን በተመለከተ፡-

99. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን ለማከናወን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን አገር አቀፍ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

100. በሚኒስቴር መ/ቤቱ (የቀድሞው የግብርና ሚኒስቴርን ጨምሮ) ከ 2006 - 2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አመታዊ የእንስሳት የዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ የሚዘጋጅ ቢሆንም የሚዘጋጀው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ የአርብቶ አደሩ፣ የከፊል አርብቶና የአርሶ አደሩን የእንስሳት ዝርያ ፍላጎት ላይ የዳሰሳ ጥናት በማከናወንና የእንስሳት ዝርያ ፍላጎትን በማሰባሰብ የማይዘጋጅ መሆኑ፣ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላቱም ዕቅድ የሚያዘጋጁት ማዕከላዊ እስታትስቲክስ የሚያወጣውን የእንስሳት ብዛት መግለጫን መሰረት በማድረግ እንጂ ከአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩ እንዲሁም የግል ባለሀብቶችን የዝርያ ፍላጎት የሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ የማያቅዱ መሆኑ ታውቋል፡፡፣

ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን የምርመራ መስፈርቶች ትግበራ እና የኳራንታይን አገልግሎትን በተመለከተ፡-

101. ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ እና ወደ ሀገር የሚገቡትም ሆነ ከሀገር ውስጥ የሚሰበሰቡትም እንስሳት ላይ የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት አስፈላጊው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

102. ማናኛውም ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) ወደ አገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን 6 የምርመራ መስፈርቶች (Bovine Tuberculosis, Brucellosis, Bovine viral diarrhea-mucosa disease (BVD-MD), Bovine Venereal Trichomoniasis, Infectious Bovine Rhinotrachitis (IBR), and Campylobacter fetus) እንዲያሟሉና በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው (GUIDELINES FOR IMPORT AND EXPORT ANIMAL AND ANIMAL GENETIC MATERIAL) መግባት እንዳለባቸው የሚገልጽ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡፣

103. በኦዲቱ ወቅት የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ከኔዘርላንድ ሀገር በ2005 ዓ.ም ለገቡት 300 ክበድ ላሞች

- የተሰጠው ሰርተፍኬት የእንስሳቱን የጤና ሁኔታ የማይገልጽ መሆኑ፣
- ክበድ ላሞቹ ሲገቡ ከ3 እስከ 7 ወራት እርግዝና የነበራቸው ቢሆንም ከውጭ ሀገር ገብተው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሽታ ምልክት ያሳዩ እና ውርጃ የታየባቸው መሆኑ፣
- በአጠቃላይ 300 ክበድ ላሞቹም ሆነ ሌሎች ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር ውስጥ በሚሰበሰቡት እንስሳት ላይ የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት ተላላፊ የእንስሳት በሽታዎችና በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተህዋስያን ወደሌሎቹ በመተላለፍ ተጽዕኖዎች እንዳይፈጠሩና ያሉትም ዝርያዎች እንዳይጠፉ የሚደረገው የመከላከል ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣ የኳራንቲን ሥራውም በተቀናጀና ለአገልገሎቱ በሚያስፈልጉ ግብአቶች የተሟሉ አለመሆናቸው

ታውቋል፡፡

አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመሆን የምርምር ሥራ መከናወኑን በተመለከተ፡-

104. ዝርያዎችና ዘሮችን በመለየት አገሪቱ ያላትን የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻልና የአገሪቱን የእንስሳት ሀብት በአይነት፣ በጥራትና በብዛት ለማሳደግ

የሚረዳ ዝርያዎች በሳይንሳዊ ምርምር ውጤት እንዲገኝ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብነት ካላቸው የምርምር ተቋማት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

105. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ ተቀናጅቶ የማይሰራ መሆኑን፣ ከእነዚህ ተቋማት ዝርያ ማሻሻያን አስመልክቶ የሚወጡ የምርምር ውጤቶች ሚ/ር መ/ቤቱ በሥሩ ለሚያስተዳድረው የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት እንዲደርስ እና የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥም ስለሚያጋጥሙ ምርምር የሚሹ ችግሮችን ለግብርና ምርምርና ኢኒስቲትዩት እና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማሳወቅ የምርምር ተግባራት እንዲከናወንባቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡

ለዝርያ ማሻሻል ለሚመረጡ እንስሳት የጤና አገልግሎት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-

106. ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ እንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል፣ የስጋት ትንተና ለማካሄድና መጠኑን ለመለየት፣ በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

107. የዝርያ ማሻሻል ሥራን ለማከናወን ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም

- በ2005 ዓ.ም ከኔዘርላንድ ከገቡት 300 ክበድ ላሞች ውስጥ በበሽታ ምክንያት እስከ ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም ድረስ በህይወት ያሉት 34 ብቻ መሆናቸው፣
- የሰበታ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ በሪፖርት ቁ.322/16 በ16/09/16 በተጻፈ በሆለታ አስኳል የእናቶች መንጋ ማዕከል ለሚገኙ 220 እንስሳት ላይ ምርመራ አድርጎ ሁሉም በመተንፈሻ አካል በሽታ (IBR) የተጠቁ መሆናቸው ያረጋገጠ ሲሆን በመተንፈሻ አካል (IBR) በሽታ የተጠቁ እንስሳቶች በዘር (genetic) አማካኝነት በሽታን እንደሚያስተላልፉ የሰበታ የእንስሳት የጤና ላቦራቶሪ በ ቁ.322/16 በ16/09/16 በተጻፈ ሪፖርት ቢያሳውቅም ችግራቸው እየታወቀ ከነዚህ

ላሞች የተወለደ ኮርማ ለዝርያ ማሻሻያ ሥራ ከሆለታ አስኳል መንጋ ማዕከል ተመርጦ በቃሊቲ ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ዘሩ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ መደረጉ፣

- የአገሪቱን የእንስሳት ዝርያዎች ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል በወቅቱ እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ የእንስሳት ጤና ሁኔታዎች ሲከሰቱ የስጋት ትንተና በማካሄድና መጠኑን በመለየት ድንገተኛ የእንስሳት በሽታዎች በተከሰተባቸው የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ቦታዎች (ክልሎች) በመገኘት ስለደረሰው ጉዳት እና መንስኤ ጥናት በማድረግ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉ፣
- በብሄራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ማዕከል እና በሆለታ አሰኳል መንጋ የእናቶች ዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ውስጥ ለዝርያ ማሻሻል ተግባር ተይዘው የሚገኙ የወተት ላሞች፣ ኮርማዎች እና ጥጆች በክትባት መደኃኒት አቅርቦት እጥረት እንዲሁም የምርመራ ባለሙያ አቅም ውስንነት ምክንያት በተደጋጋሚ በቆዳ ጉርብርብ፣ ቲቢ፣ የጡት በሽታ በመጠቃት ለሞት የተዳረጉ መሆኑ ለዝርያ ማሻሻያ የሚቀርቡት አንዳንድ የክትባት መደኃኒቶች ውጤታማ አለመሆናቸውን ለማዕከላቱ ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፤ ለምሳሌ፡-
- ለዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት የቀረበ የቆዳ ጉርብርብ ክትባት ለአመት ያገለግላል ተብሎ ለእንስሳቱ ቢሰጥም በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ አብቅቶ /Fail አድርጎ/ እንስሳቱ በበሽታው ምክንያት የሞቱ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ነባርና ዘራቸው እየመነመነ ያሉ የእንስሳት ዝርያዎች መጠበቃቸውን በተመለከተ፡-

108. ነባር እና አዳዲስ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

109. የሚ/ር መ/ቤቱ በወተት ዳልጋ ከብት ላይ ብቻ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን የሚያከናውን ቢሆንም

- የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑት የሸኮ ና አቢጋር ዝርያዎች እየተባዙ ባለመሆናቸው ዝርያዎቹ ወደ መጥፋት ደረጃ እየተቃረቡ መሆኑ፣
- በዳልጋ ከብት ላይ በሀገር ውስጥ የቦረና፣ የበጋይት፣ የፎገራ፣ የሆሮ፣ የሸኮና አቢጋር ዝርያዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለዩ ቢሆንም እነዚህን ዝርያዎች በመጠበቅና በማባዛት ማሰራጨት አለመቻሉ፣
- በተጨማሪ በማዕከል ደረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከዳልጋ ከብት ውጪ በሌሎች የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ በሚችሉ ፍየል፣ በግ፣ የሥጋ ዳልጋ ከብት፣ ፈረስ ወ.ዘ.ተ. ላይ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑ አለመደረጉ፣ የሀገር ውስጥ ዝርያን በማሻሻል ሌሎች ሀገራት ከደረሱበት በማድረስ (Export standard) የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት አለመቻሉ፣

ታውቋል፡፡

የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ጥገና እና ስርጭትን በተመለከተ፡-

110. ለዝርያ ማሻሻያ የተመረቱ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች መደበኛ የጥገና ፕሮግራም (Service) በማዘጋጀት በፕሮግራሙ መሰረት እንዲከናወን እና የፈሳሽ ናይትሮጂኑ ምርት በተጠቃሚዎች ፍላጎት መሰረት እንዲሰራጭ ሊደረግ ይገባል፡፡

111. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትና ሥርጭት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ክልሎች በዓመት በታቀደው መጠን

መሰረት ማግኘት አለመቻላቸውን በናሙና የታዩ ተጠቃሚዎች የገለጹ መሆኑ፣

- አገሪቱ ውስጥ የሚገኙት የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ብልሽት ሲያጋጥማቸው በወቅቱ ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማይደረግ መሆኑ፣
- ለዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ማንዋሉ በሚያዘው መሰረት (8000 ሰዓት ከሰራ በኋላ) መደበኛ ጥገና (service) የማይደረግላቸው መሆኑ፣
- እንዲሁም በተደጋጋሚ የማምረቻ ማሽን ብልሽት የሚደርስባቸው ስለሆነ መሳሪያዎቹን ለመጠገን በናሙና ከታዩት ክልሎች ያለውድድር ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከ2006-2008 ባለው ጊዜ ሁሉንም በክልሉ የሚገኙና በናሙና በታዩት የናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላትን ፍቼ፣ ሻሸመኔ እና ነቀምት ለሚገኙ ማዕከላት ብር 2,935,859 (ሁለት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አምስት ሺ ሰምንት መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር) የደቡብ ህዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች በሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በ2008 ዓ.ም ብቻ ብር 6,657,688 (ስድስት ሚሊየን ስድስት መቶ ሀምሣ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር) በድምሩ ብር 9,593,547 (ዘጠኝ ሚሊየን አምስት መቶ ዘጠና ሦስት ሺ አምስት መቶ አርባ ሰባት ብር) ወጪ ተደርጎ እንዲጠገን መደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ የፈሳሽ ናይትሮጅን ማምረቻ ማዕከላት፣ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልልና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤት ጋር በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣
- አገሪቱ ውስጥ ለሚገኘው የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽን የጥገና አገልግሎት የሚሰጠው በአንድ ብቸኛ ባለሙያ መሆኑ፣ የፈሳሽ ናይትሮጂን የማምረቻ ማሽን የመለዋወጫ እቃ እጥረት መኖሩ፣

ማሽኑንም በብቸኛነት የሚያቀርበው በአገሪቱ አንድ ድርጅት ብቻ መሆኑ

ታውቋል፡፡

የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ሥርጭትን በተመለከተ፡-

112. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ሊሰራጩ ይገባል፡፡

- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እንደ ግብዓት የሚሆኑ ኮርማዎችን የሚያዘጋጀው የሆሎታ አስኳል መንጋ የእናቶች ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ ኮርማዎችን ማከፋፈል አለመቻሉ፣ በብሄራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ማዕከልም ከ2006-2008 ዓ.ም. ድረስ 5,360,000 አባላዘር ለማምረት ታቅዶ በዚሁ ከላይ በተገለጸው 3 ዓመታት ውስጥ የተመረተው አባላዘር ብዛት 2,422,616 (45%) ብቻ መሆኑ፣
- የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፣
- በናሙና በታዩ ወረዳዎች የሚከናወኑ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች (Artificial Insimination Services) ሲሰሩ የዘር እጥረት በመኖሩ ላሞቹ ፍላጎት ባሳዩ ጊዜ ወቅቱ ተጠብቆ ዘር እንዲሰጣቸው ባለመደረጉ ላሞቹ እርግዝና ሊይዙ አለመቻላቸው፣

ታውቋል፡፡

በድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትን በተመለከተ፡

113. በእንስሳት ዝርያ የማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) በመጠቀም የተዳቀሉ እንስሳት ጤናማ ጥጃና ጊደር በመውለድ ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደረግና ውጤታቸውም በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡

114. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትን በተመለከተ በየጊዜው ግምገማ እየተከናወነ የግምገማ ሪፖርት የሚቀርብ ቢሆንም በቀረበው የግምገማ ሪፖርት መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣ አብዛኛው የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን በመጠቀም በአርሶ አደሩ/ አርብቶ አደሩ የተዳቀሉ እንስሳት ውጤት ወደ እርግዝና መሸጋገራቸውን እና ጤናማ ጥጃ/ጊደር መውለዳቸውን በየማዕከሉ መረጃው ተጠናቅሮ አለመያዙ፣ በህብረተሰቡ ዘንድም በሆርሞኖች ስርጭት ምክንያት የተገኘውን ለውጥ ለማወቅ ጥናት የማይደረግ በመሆኑ ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከላት መቋቋማቸውን በተመለከተ፡-

115. የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ለማከናወን ማዕከላት ለዋነኛ ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ አድርጎ በአመቺ አካባቢዎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላት ጋር በመናበብ ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የማዕከላቱን የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

116. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የእንስሳት የብዜትና የስርጭት ማዕከል ለአብዛኛው ተጠቃሚዎች አመቺ በሆኑ አካባቢዎች ያልተቋቋሙ መሆኑ፣
- በየክልሉ ከ2006 ዓ.ምና ከዚያ በፊት በመንግስት ይተዳደሩ የነበሩ እና የእንስሳት ዝርያን የሚያሻሽሉ፣ የሚያባዙና የሚጠብቁ ማዕከላት (ሀበርኖሳ፣ ጎቤ፣ አንዳሳ፣ ፣ ዲዳ ጥያራ፣ በጌ፣ አኖ …) ወደ ግሉ ዘርፍ ከተዘዋወሩ በኋላ ከእንስሳት ዝርያ ጋር የተያያዘ ሥራን የማያከናውኑና በሌላ ሥራ ላይ የተሰማሩ መሆኑ፣
- በግልም ሆነ በመንግሥት ሥር የሚገኙ ዝርያን በማሻሻልና በመጠበቅ ሥራ ላይ የተሰማሩ በክልል የሚገኙትን ተቋማት የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ግብረ መልስ እንዲሰጥ አለመደረጉ፣
- ከ2006 ዓ.ም በፊት ጊደሮች እና ኮርማን ለተጠቃሚዎች ያሰራጩ የነበሩ የመንግሥትና የግል ማዕከላት ሥርጭት ያቆሙ መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዝርያን በማባዛት ሊያሰራጩ የሚችሉ (የግል ወይም የመንግሥት) ማዕከላትን እንዲቋቋም አለማድረጉ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2017 ዘመናዊ የእንስሳት ኢንዱስትሪ በመገንባት ሀገራችን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ፣ በአፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የእንስሳት ሀብት ምርት አቅራቢ እንድትሆን ለማድረግ የያዘውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ የአገሪቱ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር የሚመራበትና አቅጣጫ በማስያዝ ሥርዓት ባለበት መንገድ ሥራን ለማከናወን የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀትና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በረቂቅ ደረጃ ላይ አለ የተባለው የርቢ ፖሊሲ በተቻለ ፍጥነት የሚመለከታቸው እንዲመክሩበትና እንዲያዳብሩት በማድረግ ጸድቆ ወደ ተግባር ሊሸጋገር ይገባል፡፡
- ከውጪ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት ዝርያዎች (ለዘር በቁም፣ በአባላዘር፣ በሽል ወይም በማንኛውም መልኩ) በሚገቡበት ጊዜ በአግባቡ ታውቀውና ተመዝግበው እንዲሁም ፍተሻ ተደርጎባቸው እንዲገቡ ቁጥጥር በማድረግ ወደ አገሪቱ እንዲገቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለኳረንቲን የተሟላ ምርመራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ግባቶች ተሟልተው አገልግሎቱን በመስጠት ጤናማ ዝርያዎችና ዘሮች ብቻ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥ የተሻለ ውጤት የሚያመጡ ዝርያዎችና ዘሮችን ለመለየትና ጥቅም ላይ ለማዋል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ካሉ የምርምር እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡
- በዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትና በተሰራጩ ዝርያዎች ምክንያት በሚገኙ እንስሳት ላይ ስለሚያጋጥም የበሽታ ክስተት መረጃው እየተጠናቀረ

የሚያዝበት እና ለወደፊት ለፖሊሲ ውሳኔዎች እና የምርምር ሥራዎች በሚያግዝ መልኩ እየተተነተነ በሀገራዊ የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) በማዘጋጀት እንዲያዝ ሊደረግና ተጠቃሚዎች የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በአገሪቱ ያሉ ነባር የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች እየተባዙ የሚሰራጩበት እና ወደ መጥፋት እየተቃረቡ ያለቸውንም ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በልዩ ክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ለማከናወን ማዕከላት ለዋነኛ ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን ታሳቢ አድርጎ በአመቺ አካባቢዎች የመንግስት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ማዕከላት እንዲጠናከሩና የግል ማዕከላት በስፋት እንዲቋቋሙ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት የሚውል የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻዎችና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የጥገና ፕሮግራም በማዘጋጀት በፕሮግራሙ መሰረት እንዲጠገን በማድረግ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ለዝርያ ማሻሻያ የተመረቱ አባላዘሮችን ለማስቀመጥ የሚጠቅም የፈሳሽ ናይትሮጂን ምርት እንደዚሁም የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ለአርብቶ አደሩ፣ ለአርሶ አደሩ እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት መጠን እንዲሰራጩ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የፈሳሽ ናይተሮጅን መሳሪያዎችን በብዛት እንዲቀርቡ ለማድረግ ሆነ የተበላሹ የፈሳሽ ናይትሮጅን መሳሪያዎች ጥገና በፍጥነት እንዲከናወን ለማድረግ መሳሪዎቹን በአገር ውስጥ የሚመረቱበት ወይም መንግስት ሌላ አማራጭ የሚፈልግበት ስትራቴጂ በመንደፍ ለሚመለከተው አካል በማስወሰን ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከፍተረኛ ትምህርት ተቋማት እና ከግብርና የቴክኒክ ኮሌጆች ጋር በመመካከር መሳሪዎቹን የሚጠግኑ ባለሙያዎቹ የሚፈሩበትን መንገድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- በዝርያ ማሻሻል ሥራ የድራት ማጎልበቻ ሆርሞን (በሲንክሮናይዜሽን ሰርቪስ) የተዳቀሉ እንስሳት ውጤታማነትና፣ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ብዜትና ሥርጭት ማዕከላትን የሥራ እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ በመገምገም የሚመለከታቸው አካላት እርምጃ እንዲወስዱበት ግብረ መልስ ሊሰጥ እና ለተግባራዊነቱም አስፈላጊው ድጋፍ ሊሰጥ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

9. <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት አፈጻጸም በተመለከተ</u>

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ፡-

117. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙበት ወጥ የሆነ /Standardized/ በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያን ሊያዘጋጅና በስሩ ላሉ ልማት ድርጅቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም መመሪያ ከየወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እየተጠና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

118. ይሁን እንጂ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በስሩ ያሉ የልማት ድርጅቶች የሚመሩበት ወጥ የሆነ /Standardized/ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ ቁጥጥር እና የአስተዳደር መመሪያን ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ የሚያዘጋጁ መሆኑን በተመለከተ፡-

119. ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለተሽከርካሪዎቹ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር በጥናት ላይ በመመስረት ዕቅድ ሊያዘጋጁ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የሚዘጋጀውም ዕቅድ ያሏቸውን ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና ማሽነሪዎች ብዛት፣ አይነት እና ያላቸውን

የቴክኒክ ብቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው አጠቃቀም እንዲኖር የሚያደርግ ሊሆን ይገባል፡፡

120. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር፣ የተፈጥሮ ሙጫና የደን ውጤቶች ምርትና ገበያ እና አርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በየዓመቱ የነዳጅና የቅባት ፍጆታ ዕቅድ የሚያዘጋጁ ቢሆንም የሚያዘጋጁት ዕቅድ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ (የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን ብዛት፣ ዓይነትና የቴክኒክ ብቃት ከግምት ያላስገባ) እና ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው አጠቃቀም እንዲኖር የሚያደርግ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

የነዳጅ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓትን በተመለከተ፡-

121. የእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ያላቸው የነዳጅ መያዣ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን አስቀድሞ በማወቅ ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች በሊትር/ በሰዓት ምን ያህል ነዳጅ እንደሚጠቀሙ መስፈርት /Standard/ ሊወጣ እና የተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ በመስፈርቱ መሰረት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከአሰላ ብቅል ፋብሪካ እና ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ከዋና እና ከቃሊቲ ቅ/መ/ቤት ወደ መስክ ስራ የሚላኩ ተሽከርካሪዎች በስተቀር ሁሉም የልማት ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን የማይታወቅና ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፣ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ነዳጅ መቅዳት የሚችሉት ምን ያህል ሊትር ነዳጅ በሰልባቶዮ/በታንከራቸው ውስጥ ሲቀራቸው እንደሆነ የተቀመጠ መስፈረት /Standard/ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የነዳጅ ዲፖ ያላቸው የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፡-

123. የነዳጅ ዲፖ ያላቸው ድርጅቶች ነዳጅ ሲገዛም ሆነ ወደ ዲፖ ሲገለበጡ ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የነዳጅ ማደያ መሳሪያውም በየአመቱ ካሊቢሬት ሊደረግ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የነዳጅ ማጠራቀሚና ማደያ ዴፖ ያላቸው

- በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣
  - የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች በ1972 ዓ.ም የተገነቡና ለረጅም ጊዜ እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
  - የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎቹ በትክክል አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ (calibration test) በየወቅቱ አለመደረጉ፣
  - የነዳጅ መቅጃ የመጠን መቁጠሪያቸው (counter) የማይሰራ ዴፖዎች መኖራቸው
  - በነዳጅ ማደያ ዲፖዎቹ የእሳት አደጋ መከላከያ (Fire extinguisher) አለመኖሩ፣
  - በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ
  - በስሩ ያሉት ዴፖዎች የሚመሩበት የነዳጅ ዲፖ አስተዳደር መመሪያ የሌለው እና የቁጥጥር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን
  - ማጠራቀሚያ ታንከሩ በ1998 ዓ.ም የተተከለና ከዛ በኋላ እድሳትና (calibration test) ያልተደረገለት መሆኑ፣
- በአብዛኛዎቹ የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች የነዳጁን ጥራት አረጋግጠው የሚረከቡበት መሳሪያ የሌላቸው መሆኑ፣ ነዳጅ ለብክነት እንዳይጋለጥ ለማድረግ የነዳጅ የማራገፊያ ሰዓት ያልተወሰነላቸው መሆኑ

ታውቋል፡፡

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትን በተመለከተ፡-

125. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት በሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ ሊቀመጥላቸውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

126. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት

- ከአሰላ ብቅል ፋብሪካ እና የኬሚካል ኮርፖሬሽን በስተቀር የሁሉም ልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት የሌላቸው መሆኑ፣ ሁሉም በናሙና የታዩ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዳዲስ ተሽከርካሪዎቻቸው ከአምራች ኩባንያው በሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የማያነፃፅሩና ልዩነቱንም ከምክንያት ጋር የማያስቀምጡ መሆኑ፣ የልማት ድርጅቶቹ ለሚጠቀሙባቸው እያንዳንዱ ጄነሬተር፣ ትራክተር፣ ኮንባይነር እና የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ (በኪሎ ሜትር ወይም በሰዓት ምን ያህል ነዳጅ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ) የሌላቸው መሆኑ እና አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም በየዓመቱ እየተከለሰ ወይም በእርጅና መጠናቸው ወቅታዊ እየተደረገ ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ ለእያንዳንዱ ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት (harmonization rate) ሳይዘጋጅ ነዳጅ ያለገደብ ለአሽከርካሪዎች የሚቀዳ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ትንተና እና ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ፡-

127. በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ጭምር በየደረጃው ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

128. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ዋና መ/ቤትና ሻሸመኔ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪና የስራ መሳሪያዎች በሰሌዳ ቁጥር ተለይተው የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት/ሰዓት ጋር በማነጻጸርና በመተንተን በሪፖርት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

የልማት ድርጅቶቹ ነዳጅ አጠቃቀም ላይ በሚከሰቱ ግድፈቶችና ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፡-

129. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ግድፈቶችና ክስተቶች ሊለዩ ይገባል፡፡ በተከሰቱት ችግሮችና ግድፈቶች ላይም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

130. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት

- በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን

ድርጅት የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል፣ ቁጥጥር፣ የግምገማ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን በፕሮጀክት ያሉ መሳሪያዎች አንድ አይነት የነዳጅ ፍጆታ፣ የስራ ጫና እና የስራ ሰዓት ኖሯቸው ሰፊ የነዳጅ አጠቃቀም ልዩነት ያላቸው እንዲሁም ትንሽ ሰዓት የሰሩ መሳሪያዎች ብዙ ከሰሩት የነዳጅ ፍጆታቸው የሚበልጥ መሆኑ፣
- በተጨማሪም በ2009 ህዳር ወር ላይ መገጭ ግድብ ፕሮጀክት ላይ ተሸከርካሪዎች (ታርጋ ቁጥር፡- 3-28741፣ 3-47223፣ 3-78119፣ 3-78120፣ 3-28895፣ 3-58108፣ 3-30157፣ 3-62554፣ 3-24056፣ 3-26952፣ 3-68770፣ 3-73057) የሰሩበት ሰዓት ሳይኖር 4,722 ሊትር ናፍጣ እንዲሁም ማሽነሪዎች (መለያ ቁጥር፡- 3334፣ 031467፣ 1635፣ 21023፣ 18745) የሰሩበት ሰዓት ሳይኖር 5,888 ሊትር ናፍጣ በአማካይ ብር 88,320 ነዳጅ የተጠቀሙ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን በቀድሞው የአርዳይታ ምርጥ ዘር እርሻ ልማት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለእርሻ መሳሪያዎች በመስክ ላይ በቦቴ ነዳጅ በሚታደልበት ወቅት ቦቴው ነዳጅ መቅጃ ቆጣሪ (counter) የሌለው በመሆኑ የሚቀዳው የነዳጅ መጠን ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ እና የማይመዘገብ መሆኑ

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ በጥናት ላይ በመመስረት ሊያዘጋጁ እና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚ/ር የልማት ድርጅቶቹ የሚጠቀሙበት ወጥ /Standardized/ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ ሊያዘጋጅ፣ መመሪያውም በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደርን አስመልክቶ ጥናት ሊያካሂድ እና በጥናቱ በተለዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሃሳብ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የነዳጅ ዲፖ ያላቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ነዳጅ ሲገዛም ሆነ ወደ ዲፖ ሲገለበጡ ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶቹ ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የተሞላው ነዳጅ ምን ያህል ሲቀረው መሆን እንዳለበት የሚገልጽ መስፈርት /Standard/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የእያንዳንዱ የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲየ) የሚይዘው የሊትር መጠን አስቀድሞ በማወቅ ተመዝግቦ ሊያዝ እና በዚሁ አግባብ ስለመሞላቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- እያንዳንዱ የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል እና እያንዳንዱ ማሽነሪ በሰዓት ምንያህል የነዳጅ መጠን እነደሚጠቀም መስፈርት ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለአንድ ተሽከርካሪ ነዳጅ ከመሙላቱ በፊት በነዳጅ ማጠራቀሚያው ውስጥ ያለው ነዳጅ እና የተጠቀመው ነዳጅ ታውቆ ከተወሰነለት ኮታ ጋር የሄደበት ኪ.ሜ. ርቀት በማነጻጸር በተፈቀደለት ኮታ ብቻ ስለመጠቀሙ ሊረጋገጥና የነዳጅ ቅጽ ፈቃድ ሊሞላ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ አዘጋጅተው በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ኪሎ ሜትር ቆጣሪው፣ ጌጅ የሚሠራ መሆኑ በየጊዜው መረጋገጥ አለበት፡፡
- አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታቸው ስለሚጨምር የነዳጅ ኪሎ ሜትር አጠቃቀም በየዓመቱ ለቁጥጥር ተግባር በሚመች

ሁኔታ ተለክቶና ተረጋግጦ ሊመዘገብ እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የልማት ድርጅቶቹ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሚጠቀምበትን ነዳጅና የሚጓዝበትን ኪሎ ሜትር ከአምራች ኩባንያው ከሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሊነጻጸር እና ልዩነቱንም ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ሊገለጽ ይገባል፡፡
- በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ በሚ/ር መ/ቤቱ ወይም በድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ሊወሰድ እንደሚገባ

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10. <u>የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚር</u>

የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም እና በክልል ክልላዊ አተገባበር ኮሚቴ እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም የተዘጋጀውን የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም ለመከታተል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰብሳቢነት የተቋቋመው ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ በመርሃ ግብሩ መሰረት ስለመፈፀሙ የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን እንዲልኩ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ በተጨማሪም ይህን በማይፈፅሙ ተቋማት ላይ የሚጠየቁበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በክልልም ክልላዊ አተገባበር ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ተግባር እንዲገባ በማስተባበር ድጋፍ ሊያደርግና አፈፃፀሙንም ሊከታተል ይገባል፡፡

132. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም የወጣውን ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ በማፅደቅ በሚመለከታቸው ጉዳይ መሰረት ለመፈፀም የተለያዩ አካላት ኃላፊነት የወሰዱ ቢሆንም የኮሚቴው አባላት በተደራጀ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው ማቀዳቸውን እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸው የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህን በማይፈፅሙ ተቋሚት የሚጠየቁበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

133. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የክልል ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ሶስት ክልሎች ውስጥም ክልላዊ የአተገባበር ኮሚቴ እንዳልተቋቋመ እና በስራ ላይም እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡

ስለ የአካል ጉዳተኞች በአዋጆችና በኮንቬሽን የተገለፁ መብቶች በስራ ላይ እንዲውሉ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲወጣ ማስተባበሩን በተመለከተ

134. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ ጁን 2010 የተፈረመውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 የተሰጠውን ሥልጣን በተቀላጠፈ፣ ተደራሽና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣትና ለመተግበር የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ሊያዘጋጅ እንዲሁም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ተቋማቱም በየበኩላቸው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

135. ይሁን እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአካል ጉዳተኞችን በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ያላወጣ መሆኑ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አገሪቷ የፈረመችውን ኮንቬንሽን እና ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት መደራጀቱን በተመለከተ

136. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅና በመዋቅር እንዲካተት አስፈላጊውን ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና ተፈፃሚ እንዲሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

137. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ስራ እንዳልተሰራ ታውቋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች መብቶች የሚከበሩና የሚተገበሩ መሆናቸው በተመለከተ፣

138. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና የአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል

ድርጅቶች አካል ጉዳተኞች በቅጥር ምልመላ፣ ጊዜያዊና ቋሚ ቅጥርን፣ በቋሚ ስራ ላይ መቀጠልን፣ የሙያ እድገትና፤እኩል ዋጋ ላለው ስራ እኩል ዕድሎች ሆነ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ ለቅሬታዎች የመፍትሄ ምላሽ ማግኘት፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታዎች መኖሩን፣ ማንኛውም ረዳት ለሚያስፈልገው አካል ጉዳተኛ ሥራውን ለመሥራት ወይም ሥልጠናውን ለመከታተል እንዲችል ረዳት የተመደበለት መሆኑን እና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከጉዳት አልባዎች ጋር በእኩል ደረጃ ምቹ የስራ ሁኔታ የማግኘት መብት መኖሩን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

139. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ እና በአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስለመከበራቸው የሚረጋገጥበት እና አፈፃፀሙንም የሚገመገምበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረጋቸውን በተመለከተ

140. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ሊሰራ ይገባል፡፡

141. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና

አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል ሥራዎችን አለመሰራቱ ታውቋል፡፡

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ

142. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከክልል አካላት ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የኦርቶፔዲክ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን፣ የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ስትራቴጂ ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ፤ እንዲሁም በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲያገኙና በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

143. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ስትራቴጂ በ2003 ዓ.ም የተቀረፀ ቢሆንም ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል አለመደረጉ፣ እንዲሁም የኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን ያልተቀረፀ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

እንዲሁም አንዳንድ ማዕከላት ምርቶችና ግብዓቶች የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የሚያወጣውን ስታንዳርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም መሳሪያዎቹና በመሳሪያዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ በየጊዜው የሚፈተሸበት አግባብ /ስታንዳርድ/ አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

144. በተጨማሪም የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ስር የሚገኘው የብሄራዊ ተሀድሶ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በማስተባበርና በመቀናጀት በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽኖች፣ ኦክዩፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት

በጠቅላላ ስልጠና፣ ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያና የተግባር ስልጠና እንዲያገኙና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ቢደረግም የሚሰለጥኑት የባለሞያ ቁጥር በሀገሪቱ ያለውን የባለሞያ ፍላጎት ለመሙላት የሚያስችል አለመሆኑ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሞያዎችን ቁጥር በማሳደግ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚደረገው ድጋፍ በቂ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት እንዲስፋፉ እና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ

145. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በተቋቋመባቸው ክልሎች የሚጠናከሩበት፣ ባልተቋቋመባቸው ደግሞ እንዲቋቋሙ የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን በማውጣት እንዲተገበሩ የማስተባበር ስራዎችን ሊሰራና የቴክኒክና ሙያ ድጋፍ ሊያደርግ፤ በተመሳሳይም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር አገልግሎቱ ተደራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

146. ይሁን እንጂ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸው ክልሎች በተለያየ አቅምና ደረጃ ያሉት ሲሆን፣ በአብዛኛው በከተማ አካባቢ ላይ የሚገኙ በመሆኑ በገጠር የሚኖሩ ዜጎች አገልግሎቱ ተደራሽ አለመሆኑ፤እና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲጠናከሩ ባልተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲቋቋሙ በቂ የሆነ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር ማለትም (ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች) ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች(rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም ስራዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ

147. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና ህዝቦችን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ተደራሽ የሆነ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞች በስትራቴጂክና በአመታዊ ዕቅድ በማካተት የሚተገበር መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

148. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ ስለመሆኑ በእስትራቴጂክ ሆነ በአመታዊ ዕቅድ በማቀድ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ ስለመሆኑ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል በተመለከተ

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው ከመዘጋጀት ጀምሮ እንደጉዳታቸው አይነት ተስማሚ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች እና የሰለጠኑ መምህራን ወዘተ

ዝግጅትና አቅርቦት መደረጉን የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

150. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአካል በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ መሆኑን ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው ከመዘጋጀት ጀምሮ እንደጉዳታቸው አይነት ተስማሚ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች እና የሰለጠኑ መምህራን ወዘተ ዝግጅትና አቅርቦት መደረጉን የሚከታተልበት ስርዓት በመዘርጋት ክትትል ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

151. እንዲሁም ማየትና መስማት በጣምራ ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርግ ካሪኩለም ያልተቀረፀ መሆኑ፤ አካል ጉዳተኞች ወደ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታ መምጣት የሚችሉበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣ በተጨማሪም የመጣውን የለውጥ ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን በመያዝ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ስለመከናወናቸው ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

አካል ጉዳተኞች በሚገነቡ ሕንፃዎች እና ለህዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ

152. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚገነቡ ህንፃዎች ከዲዛይን ጀምሮ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ መሆኑን፤ ማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና ሌሎች መገልገያ ተቋማት ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበር ለመንቀሳቀስ የሚገደዱትንና መራመድ የሚችሉ ሆኖ ደረጃ መውጣት የሚሳናቸውን ጨምሮ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በሚመች መልኩ የተዘጋጁ ስለመሆኑ፣

ሊደርሱባቸው የሚችሉ በቂ መጠን ያላቸው መፀዳጃ ቤቶች መዘጋጀቱን እንዲሁም በህንፃዎች ውስጥ የሚገጠም አሳንሰር ማየት ለተሳናቸው የአካል ጉዳተኞች አመች በሆነ መልኩ የበር መዘጋትና መከፈት እና የወለል ከፍታን በድምፅ የሚገልፅ መሳሪያ የተገጠመለት እና የውስጥና የውጭ መጥሪያ ደወል የብሬል ፅሁፍ ያለበት ስለመሆኑ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ተደራሽ ስለመሆናቸው በቅንጅት ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

153. ይሁን እንጂ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. በተቀመጠው መሰረት የሚገነቡ ህንጻዎች ከዲዛይን ጀምሮ፣ በትግበራ ላይ ክትትል በማድረግ እና በርክክብ ወቅት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ባደረገ መልኩ እየተገነቡ ስለመሆኑ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ ቅንጅታዊ የክትትል ስራ የሚከናወንበት ስርዓት ተዘርግቶ ክትትል እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

አካል ጉዳተኞች ለማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ውስጥ ተደራሽ በሆነ መልኩ መረጃ የሚገልፁ ወይም የሚያስተላልፉ መሆናቸውን በተመለከተ

154. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው የተዘጋጁ መሆኑን ፤ በግልፅ የሚታዩ ምልክቶችን፣ ብሬሎችንና በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ቅፆችን፣ የቀጥታ ድጋፍ ዓይነቶችንና መሪዎችን፣ አንባብያንንም ሆነ የምልክት ቋንቋ አጠቃቀም የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን፣ መሪ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የድምጽ መረጃ የሚሰጡ መሣሪያዎችን የሚያስቀምጡ ወይም የሚያቀርቡ ስለመሆኑ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በመስጠት፣ ተግባራዊ መሆኑን የሚከታተልበት ሥርዓት በመዘርጋት ድጋፍ እና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

155. ይሁን እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሰረት ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂና ውጤት የሚያመጣ የግንዛቤ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡

156. እንዲሁም በፌዴራልም ሆነ በክልሎች በግልና በመንግሥት የተሠሩ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ለምሳሌ ባንክ፣ የሕዝብ ማህበራዊ ጉዳዮች መስጫ ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የማምለኪያ ቦታዎች---ወዘተ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆናቸው እና ይህን ለማስተካከል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞችን ኮንቬንሽን፣ በሥራ ስምሪት አዋጅና በሌሎች አዋጆች ማስተዋወቃቸውን በተመለከተ

157. ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ በአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን፣ በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና በሌሎች አዋጆች፣ ደንቦች አካል ጉዳተኞችን መብቶች በሚያስከብሩ ጉዳዮች ሁሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሊሰራ እና በህብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች ያለውን ግንዛቤ ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተጠቃሚነታቸውን እንዲረጋገጥ በቅንጅት ሊሰራና በግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የመጡትን ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማዘጋጀት የመጣውንም ለውጥ ሊገመግሙ ይገባል፡፡

158. በኦዲት ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳዎች መሠረት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በዕቅድ አየያዙ ተግባራዊ ሲያደርግ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጡት የግንዘቤ ማስጨበጫዎች በተለይም የአካል ጉዳተኞችን እኩል ዕድል ተጠቃሚነትና የስራ ስምሪት መብታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስለመሰጠቱ ሲገመገም የሚከተሉት ጉዳዮች ታይተዋል፡፡

- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የሚሰጠው ግንዛቤና ስልጠና በማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ውስጥ በጥቅል የተቀመጡ በመሆናቸው ስለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ የግንዛቤ ማስጫበጫዎች፣ የተሰጠበት ርዕስ፣ ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንደተሳተፉ በዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣
- የሚሰጡ ድጋፎች በጥቅል የሚቀመጡ በመሆኑ ለየትኛው ጉዳይ ምን አይነት ድጋፍ እንደተሰጠ እና ድጋፉ ማንን ተጠቃሚ እንዳደረገ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚሰጡ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ያስገኙት ውጤት ውጤታማነት ከግቡ አንፃር እየተመዘነ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- በሴክተሩ የሚከናወኑ የግንዛቤና የስልጠና ሥራዎችን ስታንዳርድ አውጥቶ ያስገኙትን ውጤት እየመዘኑ የማህበራዊ ችግሮችን በመከላከልና ህብረተሰቡን በማሣተፍ የተፈለገውን ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ ተከታታይ ስራዎች አለመስራታቸው፣
- የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚያሰችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫና ስልጠና ለመስጠት የሚታቀደው ከሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ጋር በጅምላ መሆኑ እና አፈፃፀማቸውን ለይተው በቁጥር ቢገልጹም ለአካል ጉዳተኞች ተለይቶ ስለመታቀዱ በዕቅድ ሪፖርቶች ላይ የማያሳዩ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

11. <u>በስኳር ኮርፖሬሽን በነበር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች ውጤታማነትን አስመልክቶ በተደረገ የክዋኔ ኦዲት</u>

<u>ወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ</u>

159. ለስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ሥራ የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን፣ የመለዋወጫ አቅርቦት፣ የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ/የሙከራ ፍተሻ/ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና የዲይዛን ግምገማ ሊሰራ ይገባል፡፡

የፋብሪካ ግንባታ ዝርዝር ዲዛይን ክትትልና ግምገማ

- በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በኮንትራት ውል ሰነድ 1ቢ /Volume- 1B/ እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 የጨረታ ሰነድ ስምምነት ሰንጠረዥ ተ.ቁ 9 ላይ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጅነሪንግ ፓኬጅ ተቋራጩ ጨረታውን እንዳሸነፈ ለቀጣሪው ድርጅት ማስረከብ ያለበት መሆኑን፤ ይህም እንደ ዋና ኢንጅነሪንግ አመልካች ዳታ ሆኖ በኢንፎርሜሽን ሰጪነት ማገናዘቢያ እንደሚያገለግል የተገለፀ ቢሆንም፤ተቋራጩ በውሉ መሰረት የሚያስፈልጉ የፋብሪካው ንድፎችን/Drawing/ እና ማንዋሎችን ሙሉ ለሙሉ ያላስረከበ መሆኑ፤

የመለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ

160. የመለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ እ.ኤ.አ መጋቢት 8/2008 በድርጅቱ እና በተቋራጩ በተፈረመው የኮንትራት ውል ላይ ተቋራጩ ለቀጣሪው ድርጅት በቀን 6,250 ቶን ማምረት የሚችል ፋብሪካ፣ የእንፋሎት ሃይል አመንጪ እስከ መለዋወጫው ዝርዝር ሁኔታው በውል በሰነድ 2/Volume-2/ በተገለፀው መሰረት የሚያቀርብ መሆኑ የተመለከተ ቢሆንም፤ በቃለ-ጉባኤ ቁጥር 049 በቀን እ.ኤ.አ 26/02/2013 የወንጂ/ሸዋ አዲስ ፋብሪካን በተመለከተ በተደረገ የማኔጅመንት ውይይት የፋብሪካ መለዋወጫን አስመልክቶ ተቋራጩ ዝርዝር እስፔስፊኬሽን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን በማሳወቁ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ አቅራቢነት የመለዋወጫ አቅርቦት ለማግኘት መነጋገርና በቀጣይ የሚስተካከልበትን መንገድ

መፈለግ የሚል ውሳኔ የተቋራጩን ፍቃደኛ አለመሆን እና የድርድር ሀሳብ የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ መመልከት የተቻለ መሆኑ፤

የሲቪል ግንባታ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒንግ

161. የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 በቀጣሪው ድርጅት እና በተቋራጩ በተፈረመው ኮንትራት ውል እስፔሻል ኮንዲሽን/ልዩ ሁኔታ/ በንዑስ ቁጥር ጂሲሲ/GCC 27.6.1/ ላይ በተመለከተው መሰረት የፋብሪካው የሥራ ዋስትና ፍተሻ/Guarante Test/ ሶስት ጊዜ በሚከናወንበት ወቅት ማንኛውም የፋብሪካው አካል /Equipment/ ውጤታማ ካልሆነ ጥገና ሳያስፈልገው በተቋራጩ ዋስትና አዲስ ተተክቶ የዋስትና ማረጋገጫውም ለአንድ ዓመት እንደሚራዘም የተመለከተ ቢሆንም፤የወንጂ/ሸዋ አዲሱ የማስፋፊያ ፋብሪካ እ.ኤ.አ ሐምሌ 11/2009 መጠናቀቅ የሚገባው ሆኖ በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ሥራው እስከ እ.ኤ.አ ግንቦት 2013 የተራዘመ ሆኖ ሥራ እንዲጀምር የተደረገው ተቋራጩ የሥራ ብቃት ፍተሻ/ Commissioning/ ሳያደርግ መሆኑ፣

የስኳር ፋብሪካ ግንባታው በታቀደው ጊዜና በተመደበ ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

162. የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ ሥራውን በአማካሪነት የተከታተለው ጄ.ፒ ሙከርጂ/JP MUKHERJI/ የተባለ ካምፓኒ ሲሆን፤የመነሻ ውል እ.ኤ.አ ግንቦት 19/2005 ተፈርሞ የኮንትራት ውሉ ሥራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ነሀሴ/2005 ሆኖ የመነሻ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ እ.ኤ.አ የካቲት 2/2008 ቢሆንም ውሉ ለ 8 ጊዜ ተራዝሞ እስከ እ.ኤ.አ መጋቢት 23/2017 እንዲቆይ በመደረጉ ለዘጠኝ ዓመት የዘገየ ሲሆን፣እንዲሁም የውል መነሻ ዋጋ እ.ኤ.አ ግንቦት/2005 ዩሮ 558,350/Firm Price/ እና ዩሮ 929,750/Budgeted Price/ ሲሆን 8 ጊዜ የውል ማሻሻያ በመደረጉ ከመነሻ ኮንትራት ዋጋው በድምሩ ዩሮ <u>4,648,860</u> ተጨማሪ ክፍያ የሚያመለክት መሆኑ፣

ለሸንኮራ አገዳ ልማት እርሻ መሬት የመስኖ ጥናት እና ግንባታ በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

163. ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚውል የመስኖ ግንባታን በታቀደው ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በማረጋገጥ ርክክብ ሊከናወን ይገባል፡፡

164. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማት ማስፋፋትን በተመለከተ በመስኖ ግድብና አውታር ግንባታ አማካሪ ሆኖ የሰራው ድርጅት የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሲሆን የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 1/2010 ለ 24 ወራት የሚያገለግል እና እንደ አስፈላጊነቱ የሚታደስ ሆኖ የመነሻ ኮንትራት ዋጋ ብር 17,427,728.99/አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ከ ዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም/ ውል የፈረመ ቢሆንም፤ የመጀመሪያው የመነሻ ኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ሐምሌ 30/2012 የተጠናቀቀ በመሆኑ እና በመነሻ ኮንትራት ውል በተቀመጠላቸው ጊዜ ሥራዎች ባለመጠናቀቃቸው አራት ጊዜ ውሉ የታደሰ በመሆኑ በድምሩ የአራት ጊዜ ውል መራዘም ብር 30,489,214(ሰላሳ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ አስራ አራት) /74.95%/ ከመነሻ ዋጋ ተጨማሪ ክፍያ የሚያመለክት መሆኑ፣

ግዥዎች ተጠያቂነት ባለው አግባብ የሚፈፀሙ መሆኑን በተመለከተ

165. ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ውጤታማነት፤ ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በአግባቡ ሊፈፀሙ ይገባል፡፡

የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በ 2007 በጀት ዓመት ወደብ የደረሱ እቃዎችን ወደ ፋብሪካ አጓጉዞ ለመውሰድ ባለመቻሉ ለኮንቴይነር ዲሜሬጅ/በወቅቱ ባለማንሳት የሚከፈል ክፍያ/ እና ለመጋዘን ኪራይ ብር 393,231.33/ሶስት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አንድ ከሰላሳ ሶስት ሳንቲም/ የከፈለ መሆኑ፣

በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የኢታኖል ፋብሪካን በተመለከተ

ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት እና የማሽነሪ፣

የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ

ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ዘመናዊ የማሽነሪዎች ጥገናና እድሳት አገልግሎት እንዲተገበር፣እንዲሁም የማሽነሪ፣ የግብዓትና የምርት ትስስር ድጋፍ /ሀብትን አዛውሮ በመጠቀም/ ለፋብሪካና ለእርሻ የሚሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ እንዲቀርቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የመተሐራ ኢታኖልፕላንት በ2008 በጀት ዓመት እስከ ግንቦት ወር ድረስ ከመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ማግኘት በሚገባው የእንፋሎት ሃይል እጥረት ምክንያት ለ 111.67 ቀናት ምርት ሳያመርት የቆመ በመሆኑ፤ ከፕላንቱ ቡድን መሪ በተገኘ መረጃ መሰረት በቀን 40,000 ሊትር ሬክቲፋይድ ስፕሪት ጥቅል/የመጀመሪያ ደረጃ ምርት/ ቢመረትና ወደ ማምረት አቅም ቢቀየር በ 95% የጊዜ አጠቃቀም፡-= ብር 61,487,735 ማግኘት ይቻል እንደነበረ መታወቁ፣
- በ2008 በጀት ዓመት በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የታንደም ቢ ወፍጮ ቁጥር 1 ተርባይን በእርጅና ምክንያት ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ መሥመር በመውጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ አዲስ የተርባይን ግዥ በ EI 13- 7630 ተጠይቆ የግዥ ሂደቱ በዩሮ 420,007.20 ከፋይቭስ ኮይል /FIVES CAIL/ ካምፓኒ ተከናውኖ /የተርባይኑ ዙሪት/አዟዟር ከወፍጮ ዙሪት ጋር አንድ ሆኖ ባለመገኘቱ የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በሙሉ አቅሙ ባለመሥራቱ ለኢታኖል ፕላንቱ በበቂ ሁኔታ የእንፋሎት ሃይል መስጠት ያልቻለ መሆኑ፣

ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ወጪ

ቆጣቢ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን በተመለከተ

166. ግዥዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሊፈፀሙ እና የግዥ ፈፃሚ አካላት ከግዥ ጋር ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ኃላፊና ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊደረግ እንዲሁምከእቅራቢዎች ጋር ለሚመሰረት ዘላቂ ግንኙነቶች ግብዓት እንዲሆን የገበያ ጥናት ሊከናወን ይገባል፡፡

- በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በግዥ/ቁጥር MSD/1509 3700 Normal Overhaul /የሰራተኞች ዩኒፎርም/ እንዲገዛ ተጠይቆ በግልፅ ጨረታ በመውጣቱ በቀን 24/12/2005 የተከፈተ ሆኖ አስበሞ ኢንደስትሪል ኃ/የ/ግ/ማህበር ቫትን ጨምሮ በብር 705,266.25/ሰባት መቶ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ስድስት ከሃያ አምስት ሳንቲም/ ያቀረበ ቢሆንም በወቅቱ ግዥው ባለመከናወኑ በሌላ ጊዜ ከአዳማ ጋርመንት ቫትን ጨምሮ በብር 1,178,635.00/አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት/ እንዲገዛ በመደረጉ ድርጅቱ በተመሳሳይ ግዥ ላይ ብር 437,368.75/አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ስድሳ ስምንት ከሰባ አምስት ሳንቲም/ ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣
- በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ አዲስ ተገዝቶ የተተከለ ቦይለር ፊድ ዋተር አናላይዘር /ለእንፋሎት ሃይል ማመንጫት የሚያስፈልገውን ውሃ የሚያጣራ/ ብር 1,906,362/ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት/ ለግዥ፣ለመጓጓዣና ለተለያየ ወጪ የተከፈለበት ከነባሩ ቴክኖሎጂ ጋር ባለመግጠሙ ምክንያት ከተተከለበት ቀን አንስቶ እስከ ኦዲቱ ወቅት ሰኔ/2008 ዓ.ም ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የተቀመጠ መሆኑ፣

በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የተገኙ

ለስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ የጨረታ ሂደትና ድርድር መደረጉን በተመለከተ

167. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ግንባታ የጨረታ ሂደትና ድርድር ሁሉም ተጫራቾች ቅድመ ግንዛቤ ባገኙበት ሁኔታ ሊያከናውን ይገባል፡፡

- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላን በተመለከተ በተደረገ የተናጠል ጨረታ ውድድር ኢፒሲ/EPC/ የተባለው ተቋራጭ ከሌሎች ጋር የማሸነፍ እድል አግኝቶ በጨረታ ውድድር ወቅት ባልተገለፀ ሁኔታ ሌሎቹ የጨረታ አሸናፊዎች በእሱ ስር /Sub- Contractors/

ሆነው የጨረታው ዋጋ ጭማሪ በማያሳይበት/Fixed Price/ እንዲሰሩ በቀጣሪው ድርጅት የተወሰነ በመሆኑ፣ በዋናነት እንዲመራ የተደረገው ኢ.ፒ.ሲ /EPC/ ተቋራጭ እያንዳንዱ የጨረታ ተወዳዳሪ የአስተዳደር ክፍያ እንዲከፍለው በመጠየቁ ጭቅጭቅ ተነስቶ በሁለት የጨረታ ተወዳዳሪዎች ክስ በመመስረቱ የ ኢ.ፒ.ሲ/EPC/ የኮንትራት ውል እ.ኤ.አ ጥር 2008 የተፈረመ ቢሆንም ሥራ ላይ ሊውል የቻለው ከ 18 ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ሀምሌ 17/2009 መሆኑ፣

ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ መፈፀሙን እና የማሽነሪ አቅርቦት በማሟላት የመሬት ዝግጅት መደረጉን በተመለከተ

168. ኮርፖሬሽኑ ለነባር ስኳር ፋብሪካዎች ለሸንኮራ አገዳ ተክል ልማት የመሬት ርክክብ ሊፈፅም፣ የማሽነሪ አቅርቦት እንዲሟሉ ሊያደርግ፣ ለአገዳ ልማቱ የመሬት ዝግጅት የማለስለስ/Fine Level/ ሥራን ሊደግፍ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የግርድፍ መሬት አቅርቦትን ለማዘጋጀት በ 2007 በጀት ዓመት 22 ዶዘሮች የነበሩት ቢሆንም ፤ 16ቱ የመለዋወጫ ችግር የገጠማቸው በመሆኑ 6ቱ ብቻ በሥራ ላይ በመዋላቸው እና ዶዘሮቹ የሰርቪስ ኪት የሚፈልጉ በመሆናቸው በግርድፍ የሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማት መሬት ሥራ አቅርቦት ላይ ለዝቅተኛ አፈፃፀም አስተዋፆ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን፣ እንዲሁም የውሃ ገብ መሬት 10,521 ሄክታር ለመረከብ ታቅዶ ክንውኑ 2,654/25.23%/ሄክታር መሆኑ፣

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ መጠናቀቁን በተመለከተ

169. ኮርፖሬሽኑ የክትትልና ቁጥጥር አሰራር ስርዓትን በመዘርጋት እና ተግባራዊ በማድረግ የፋብሪካ ግንባታ በታቀደለት ጊዜና በተመደበለት ወጪ እስከ ኮሚሽኒንግ ሥራ በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክትን ለማማከር በጄፒ ሙከርጂ እና በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመነሻ ውል እ.ኤ.አ መስከረም 2006 በመነሻ

ዋጋ ዩስዲ 1,328,030 በመፈራረም ሥራው ከ እ.ኤ.አ ህዳር 22/2006 ተጀምሮ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 23/2009 እንዲጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም፤ውሉ 3 ጊዜ በመራዘም ወደ ዩስዲ 7,250,160 በመድረሱ ከመነሻ ኮንትራት ዋጋ ዩኤስዲ 5,922,130/81.68%/ ጭማሪ ያሳየ መሆኑ፣

- ለተንዳሆ የአገዳ እርሻ ልማት በመሰረታዊነት እንዲያገለግል ታስቦ የተሰራው የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት በቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ድርጅት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የውሃ መሰረተ ልማት ኮንስትራክሽን ዘርፍ የፕሮጀክቱ ግንባታ በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም በብር 840,254,270.70/ስምንት መቶ አርባ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ከ 70/100/ የውል ስምምነት ተፈፅሞ በ24 ወራት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ታስቦ ግንባታው የተጀመረ ሲሆን፤ በነሀሴ 2007 ዓ.ም የተጠናቀቀ ሆኖ በ 2003 ዓ.ም የውለታ ማሻሻያ ተደርጎ የኮንትራት ዋጋውም ወደ 4.15 ቢሊዮን ከፍ እንዲል የተደረገ መሆኑ፣
- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታና ተከላ እ.ኤ.አ ከሐምሌ 17/2009 እስከ እ.ኤ.አ ሰኔ 2016 ድረስ የመጀመሪው ምዕራፍ 94.80% የደረሰ ሆኖ ሁለተኛው ምዕራፍ 31.39%/ የደረሰ ሆኖ ከማጠናቀቂያ ጊዜ ለ 4 ዓመት የዘገየ መሆኑ፣

የተንዳሆ ማስፋፊያ ስኳር ፋብሪካ የሠራተኞች መኖሪያ ቤት ግንባታ የጨረታ ሂደትን በተመለከተ

170. ኮርፖሬሽኑ በነባር ስኳር ፋብሪካዎች ማስፋፊያ ስር ለሰራተኞች መኖሪያ የተገነቡ ቤቶች የጨረታ ሀደት የተከናወነባቸው ሠነዶች ተሟልተው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

- በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የሰራተኞች መኖሪያ 499 ህንፃ ብሎኮች ለመሥራት የተሰማሩ ከ 300 በላይ ተቋራጮችም ሆነ አማካሪዎች የህንፃ ብሎኮቹን ግንባታ ለመሥራትም ሆነ የምክር አገልግሎት ለመስጠት በምን ያህል ዋጋ ሥራ እንደ ጀመሩና መቼ ለማጠናቀቅ

ውል እንደ ገቡ፤እንዲሁም በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ በተሟላ መልኩ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ፣

12. <u>በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከጉምሩክ ስነ ሥርዓት አፈጻጸም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት</u>

171. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚታወቁ የጉምሩክ ትራንዚት ዓይነቶች ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት በመመሪያው የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟሉ ስለመሆናቸው ፤በትራንዚት የተመዘገበ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከመጀመሩ በፊት የጉምሩክ ትራንዚት ስነ ሥርዓት መፈጸሙን እና የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታዎች ወይም ጣቢያዎች የእቃውን ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ የትራንዚት ፈቃድ አዘጋጅቶ በመስጠት ትራንዚቱ እንዲጀምር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

- የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ላይ በቃሊቲ ጉምሩክ የዘርፍ አስመጪነት ፍቃድ ሳይኖራቸው የባንክ ፈቃድ አግኝተው ቀረጥ እና ታክስ ከፍለው እቃ ወደ ሀገር ለማስገባት የሚጠየቅበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት (ንግድ ሚኒስቴር እና ብሄራዊ ባንክ) ጋር ውይይት ተደርጎ እልባት እንዲኖረው አለመደረጉ እና የዘርፍ አስመጭነት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያስከተለ መሆኑ ያለዘርፍ አስመጭነት እቃዎችን ያስመጡ 34 አስመጭዎች መገኘታቸው፡፡ በተጨማሪም ነዳጅ ጭነው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ተሸከርካሪዎች ዲክላራሲዮን እና የመንገድ ወረቀት (T1) አይዘጋጅም፣ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፣የወጪ ትራንዚት እቃ ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግ እና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ ትራንዚቱ እንዲጀምር የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

172. ባለስልጣን መ/ቤቱ ታሽገውና ሳይታሸጉ የሚጓጓዙ የትራንዚት እቃዎችን በጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተቀመጠው

መስፈርት መሰረት በመለየት መታሸግ የሚገባቸው እቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸጋቸውን እና በታሸጉበት ሁኔታ መድረሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- በሀገር ውስጥ ተመርተው ወይንም እሴት ተጨምሮባቸው ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች የሚታሸጉበት ደረጃውን የጠበቀ የጉምሩክ ማሸጊያ /ሲል/ ባለመኖሩ ህገ ወጥነትን ለመቆጣጠር በማይቻልበት መንገድ በሽቦ ብቻ እየታሰሩ ወደ ውጭ እየተላኩ የሚገኙ መሆኑ፣

173. የትራንዚት እቃዎች በተነሱበት ሁኔታ እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የደረሱ ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ እና በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን እቃዎች በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ (Reconciliation) ስራ በመስራት በጊዜ ያልደረሱትን ወደ ህግ ማስከበር በማስተላለፍ ክትትል እንዲደረግባቸ ሊያደረግ ይገባል፡፡

- በመልቲሞዳል ስርዓት ተጓጉዘው ወደ አገር የገቡ ጭነቶች ቃሊቲ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መድረስ የነበረባቸው ከ2006-2008 ዓ.ም 1,365 ኮንቴይነሮች እና ሞጆ ገቢዎች እና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ከተጀመረበት ጀምሮ መግባት የነበረባቸው ጭነቶች 2,647 ኮንቴይነሮች በድምሩ 4,021 በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ፣በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2016 በሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 1,576፣አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 279፣ሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 9፣ጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 28 እና መቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 239 በድምሩ 2,131 የመልቲ ሞዳል ጭነቶች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ መድረሳቸው በሲስተም ቫሊዴት አለመደረጉ ፣

174. በባለስልጣኑ የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡

- ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት (Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) ለመዘርጋት ከሀይ.ጅ.ቴክ ካምፓኒ ጋር ጥር 7/2003 ዓ.ም በ2,500,000.00(በሁለት ሚሊየን አምስት መቶ ሺ.ህ የአሜሪካን ዶላር) የውል ዋጋ እና ከውሉ ሁለተኛ

አመት ጀምሮ እስከ አምስተኛው ዓመት በየአመቱ ለስራ ማስኬጃ ወጪዎች በሚከፈል 289,000 የአሜሪካን ዶላር ውል ተፈራርሞ በቀጣዮቹ አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ በትንሹ 10,000 ተሽከርካሪዎችን ወደ ስርአቱ በማስገባት ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገባ የውል ስምምነቱ ቢገልጽም እስከ 2008 በጀት አመት መጨረሻ 312 (3%) ተሽከርካሪዎች ብቻ የካርጎ ትራኪንግ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑ እና የተዘረጋው የካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ከኢትዮጵያ መግቢያ በር ጋላፊ ጀምሮ ሲሆን ከጅቡቲ ወደብ እስከ ጋላፊ ባለው ስፍራ በውሉ መሰረት ስርአቱ ያልተዘረጋ መሆኑን፣

175. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ ወደቦች ፣ በወሰን አካባቢዎች ፣ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ሊፈትሽና የጉሙሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ወደ አገር የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ለማጠናከርና አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ ሥርዓት ለመዘርጋት ባለስልጣን መ/ቤቱ በስምንት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች (ሞያሌ፣ሞጆ፣ ሁመራ፣ ቶጎጫሌ፣ ያቤሎ ፣መተማ፣ ጋላፊ እና ጅግጅጋ) ላይ ለኤሌክትሮኒክስ ካርጎ ፍተሻ መሳሪያ (Scanning machine) ተያያዥ የቤትና የአስፋልት ግንባታ በ53 ሚሊዮን ብር በሶስት ወራት ውስጥ አጠናቆ እንዲያስረክብ ከኢትዮጵያ ብረታብረት እና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የካቲት 1/2003 ዓ.ም ውል ተፈራርሞ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም ከስምንቱ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ የያቢሎ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ለሞያሌ ቅርብ ስለሆነ መገንባቱ አስፈላጊ አይደለም ግንባታው ወደ ቃሊቲ ይዛወር ተብሎ መቅረቱን፣ ነገር ግን ቃሊቲም ላይ ግንባታው አለመከናወኑ ፣የጋላፊ መቆጣጠሪያ ጣቢያን በተመለከተ ግንባታው ተጠናቆ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ አገልግሎት ወደ ስራ ቢገባም በመንገዱ ፣በህንጻው ላይ በታዩ የግንባታ ችግሮች ምክንያት የመጨረሻ ርክክብ አለመደረጉንና በመንገዱ ላይ የታየው ችግር በገለልተኛ አካል እንዲጠና ተደርጎ የተሰራው ስራ ከዲዛይኑ ጋር

የማይመሳሰል መሆኑ መረጋገጡ፣ሞያሌን በተመለከተ የቤት ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የነበረ ቢሆንም በኢትዮ-ኬንያ (One Stop Border Post) የመንገድ ስራ ምክንያት በመፍረሱ አገልግሎት እንደማይሰጥ፣ ሞጆን በተመለከተ ስራው 64% ከተጠናቀቀ በኂላ አሁን ካለው የደረቅ ወደብ የፍተሻ ጣቢያ የራቀ እና ለፍተሻ የማያመች በመሆኑ ግንባታው ባለበት ሁኔታ ቆሞ ርክክብ መፈጸሙን ፣የመተማ እና ሁመራ ስካኒንግ ማሽን ጣቢያዎች ግንባታ ተጠናቆ ግንቦት 15/2008 ጊዜያዊ ርክክብ መደረጉን እና በጅግጅጋ እና ቶጎጫሌ ሳይቶች ቀሪ ስራዎችን ለማጠናቀቅ ሂደት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ መቻሉ፤

- በኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የአየር በአየር በ190 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ እቃዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድ እቃዎችን ለማን እንዳስረከባቸው፤ መቼ እንዳስረከባቸው ዝርዝር መረጃ የተጠየቀ ቢሆንም አየር መንገዱ በ83 የማስጫኛ ሰነዶች ለመጡ እቃዎች ብቻ የእቃዎቹ ባለቤት ናቸው የተባሉትን ማረጋገጫ የሰጠ ሲሆን በ107 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ ዕቃዎች ማረጋገጫ ያላቀረበ መሆኑ፣ በተጨማሪም ከመጋዘን አየር በአየር ከወጡ ዕቃዎች በግምታዊ ዋጋ ብር 101,932,491 ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ መጠየቁ፣የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት አጓጓዥ ድርጅቶች ወደ ሀገር ለሚያስገቧቸው እቃዎች የእቃ መግለጫዎችን (manifest) የሚያገኙበት አሰራር ኂላ ቀር እና አጓጓዥ ድርጅቶች ካላቸው ሲስተም ጋር የተጣጣመ እንዳልሆነ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

176. ባለስልጣኑ የገቢ፣የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ እና የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶች እና የሚከናወኑ የቁጥጥር ስርዓቶች በመረጃ በተደገፈ መመዘኛ የገቢ ፣ የወጪ እና የተላላፊ ዕቃዎችን የስጋት ደረጃ በመለየት የአገልግሎት አሰጣጡን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ መከናወን ይገባዋል፡፡

- በባለስልጣኑ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 6(4) መሰረት መ/ቤቱ የገቢ፣ የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ እንዳላወጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በባለስልጣን መ/ቤቱ በ2008 በጀት ዓመት በሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ በተደረገው ማሻሻያ ከአጠቃላይ የሥጋት ደረጃ ከተስተናገዱ 136,931 ዲክላራሲዮኖች ውስጥ የቀይ የሥጋት ደረጃ 35 በመቶ፣ የቢጫ የሥጋት ደረጃ 50.7 በመቶ፣ የአረንጓዴ የስጋት ደረጃ 13.70 በመቶ እና በሰማያዊ የስጋት ደረጃ 0.06 በመቶ ሽፋን ሲኖራቸው የቀይ የሥጋት ደረጃ 20 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ አለመሳካቱ፣እንዲሁም በ2007 በጀት ዓመት በስጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ላይ በተደረገው ማሻሻያ ከአጠቃላይ የሥጋት ደረጃ ከተስተናገዱ 139,330 ዲክላራሲዮኖች ውስጥ የቀይ የሥጋት ደረጃ 40.02 በመቶ ሽፋን የነበራቸው ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቀይ የሥጋት ደረጃን ወደ 31 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እንዳልተሳካ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

177. ባለስልጣኑ እቃዎች በመጋዘን ውስጥ የሚቆዩት በጉምሩክ አዋጅ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ እና ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በአዋጁ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግስት ጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል እስከ እስከ ሰኔ 30/ 2008 ዓ.ም በሞጆ ደረቅ ወደብ ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት 967 እና ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 213 ኮንቴይነሮች በድምሩ 1,180፤ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ደረቅ ወደብ ከሁለት ወር በላይ የቆዩ 54 ኮንቴነሮች ፣መጋዘን ቁጥር አንድ 29፣መጋዘን ቁጥር ሁለት 28 ፣ መጋዘን ቁጥር አምስት 21፣ መጋዘን ቁጥር ስድስት 19፣ መጋዘን ቁጥር ሰባት 16፣መጋዘን ቁጥር አስራ ሁለት 18 የተለያዩ እቃዎች እና በክፍት መጋዘን 3 ኮንቴነሮች ከሁለት ወር በላይ በመጋዘን የቆዩ መገኘታቸው፤
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ በሚገኙ መጋዘን ቁጥር አንድ 29፣መጋዘን ቁጥር ሁለት 28 ፣ መጋዘን ቁጥር አምስት 21፣ መጋዘን ቁጥር ስድስት 19፣ መጋዘን ቁጥር ሰባት 16፣መጋዘን ቁጥር አስራ ሁለት 18 የተለያዩ እቃዎች እና በክፍት የፍተሻ መጋዘን 3 ኮንቴነር ከሁለት ወር በላይ በመጋዘን የቆዩ መኖራቸው፣

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ የተደረጉ እና የቆይታ ጊዜያቸውን ያሳለፉ የተለያዩ እቃዎች ለማሳያነት ያክል 11 ኮንቴነር ፣ በቁጥር 489 ልዩ ልዩ የመኪና ጎማዎች፣ባለ 25 ኪ.ግ 2,616 ከረጢት ሩዝ፣ 783 ካርቶን ኮስሞቲክስ እና 385 ካርቶን እስክርቢቶ ወደ ውርስ መጋዘን ሳይተላለፉ ጊዜያዊ እቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

178. ባለስልጣኑ የወጪ እና ገቢ እቃዎችን በሚመለከት የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና የፋይናንስ ተቋማት በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

179. ባለስልጣኑ ስራዎቹን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመደገፍ እና የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው ከInvestment Climate for Africa(ICF)፣አለም ባንክ (IFC) እና ከመንግስት በተገኘ የፕሮጀክት በጀት 7.3 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም የፕሮጀክት ስምምነት በመፈረም በአስራ ስምንት ወራት ለማጠናቀቅ በይፋ ስራውን የጀመረ ቢሆንም ፕሮጀክቱ ሲጀመር በቂ ዝግጅት ባለመደረጉና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በዋናነት (የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ) ያላሳተፈ በመሆኑ፣ ኤጀንሲውን ለማሳተፍ ረዥም ጊዜ በመውሰዱ፣በዝግጅት ጊዜ መከናወን የነበረባቸው የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች አለመከናወናቸው፣ ከመንግስት የሚጠበቅ ውሳኔ በወቅቱ አለመገኘት፣የፕሮግራሙ ከፍተኛ አመራሮች ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች በመሆናቸው በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች የነበራቸው ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ ውሳኔዎችን በወቅቱ አለማግኘት፣የፕሮግራም ጽ/ቤቱ በተገቢው ደረጃ አለመደራጀት እና የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ባለመያዙ ምክንያት ወደ ትግበራ ምእራፍ መግባት እንዳልቻለ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

13. <u>በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር መ/ቤት የተቀናጀ የከተሞች ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ስርአትን በተመለከተ</u>

<u>የከተሞች ጽዳት ውጤታማ ለማድረግ ስታንዳርዶችና ማንዋሎች ስለማውጣቱ እና የትግበራ ድጋፍና ክትትል ስለማድረጉ ፡-</u>

180. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጽዳት ዙሪያ ለሚያጋጥሙ ችግሮችና ለሚከሰቱ አዳዲስ ክስተቶች አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ስታንደርዶችን ሊያወጣና የወጡ ስታንዳርዶችና ማንዋሎች በማሻሻል ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች ጽዳት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ስታንዳርዶች እና ማንዋሎች በማውጣት ስራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግና በአፈጻጸም ወቅት የትግበራ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጽዳት ዘርፉ ለሚያጋጥሙት ችግሮች እና ለሚከሰቱ አዳዲስ ክስተቶች አስፈላጊውን ጥናት በማጥናት የወጡ ስታንዳርዶች እና ማንዋሎች በማሻሻል ተግባራዊ እንዲሆኑ የስራ አፈጻጸምን አስመልክቶ የክትትልና ድጋፍ ግምገማ ስርአት በመዘርጋት እና ግብረ መልስ በመስጠት የዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ይኖርበታል፡፡

182. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች እና ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞችን ጽዳት በአግባቡ ለመምራት እና ውጤታማ ለማድረግ አጸድቆ ስራ ላይ ማዋል የሚጠበቅበት ኃላፊነቶች መካከል የሚከተሉትን ማለትም በጽዳት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲቻል የአረንጓዴ ልማት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስትራቴጂ ሐምሌ 2006 ዓ/ም፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ስታንዳርድ የትግበራ ማንዋል በየካቲት 2007 ዓ/ም፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ የዜጎች ቻርተር ስታንዳርድ በየካቲት 2007 ዓ/ም፣ ወጪ ቆጣቢ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግንባታ የአሰራር መመሪያ ጥር 2003 ዓ/ም፣ አደጋን የሚቋቋም አረንጓዴና ተደራሽ የከተሞች ልማት ፖሊሲ ግንቦት 2005 ዓ/ም አዘጋጅቶ ስራ ላይ ማዋሉ ይታወቃል፡፡ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች

ጽዳትን የሚመለከቱ ጥናቶች ማለትም የክልሎችና የከተሞች ሞዴል የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አደረጃጀት የጥናት ሰነድ ጥር 2007ዓ/ም፣ ለአየር ንብረት ለውጥ አይበገሬ የከተሞች ጽዳት እና አረንጓዴ ልማት ቢ.ፒ.አር ጥናት መጋቢት 2007 ዓ/ም፣ በማጥናት ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ስልጠና እየተሰጠ መሆኑ፡፡ ለአብነትም፡- በ2007 ዓ.ም ለ7400 የከተማ አመራር በቪዲዮ ኮንፈረንስ እና በ2008 ዓ.ም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመሩት ለ2300 ከፍተኛ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት በሰነዶቹ ላይ ሥልጠና በመስጠት ወደ ትግበራ እንዲገባ ማድረጋቸውን፤ከዚህ በተጨማሪ ያልጸደቁና በሂደት ላይ የሚገኙ የተለያዩ ጥናቶችን ለአብነትም፡- የወጭ ማካካሻ ፣ የጽዳት ሞዴል አደረጃጀት፣ የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ፣ በግል ለተሰማሩ ማህበራት/ የግል ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ፣ የሰፈር ውድድርና ሽልማት፣ ቆሻሻን ከምንጩ የመለየት፣ የመልሶ መጠቀምና የመልሶ ዑደት፣ የኮምፖስት አዘገጃጀት እና የኮምፖስት ስታንዳርድ ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ስራ አመራርና አስተዳደር /Land fill operation and management/ እና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግንባታ /Land fill construction/ ጥናቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

183. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ ላይ ያዋላቸው ስታንዳርዶች መንዋሎች እና የጥናት ሰነዶች አፈጻጸምና ውጤታማነትን አስመልክቶ ኦዲት ሲደረግ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ ከተሞችና ጉዳዩን አስመልክቶ በተከለሱ መረጃዎች መሰረት በየከተሞቹ የነበረው አፈጻጸምና ውጤታማነት አጥጋቢ እንዳልነበረና በጽዳት ዘርፉ የነበሩ ችግሮች በሚጠበቀው ደረጃ እንዳልተሻሻሉ ታውቋል፡፡ የወጡ ስታንዳርዶችን፣ ማንዋሎችንና ጥናቶችን ከአከባቢያቸው ሁኔታ ጋር በማጣጣም የመፈጸም ኃላፊነት የክሎችና የከተሞች መሆኑ ቢታወቅም እ.ኤ.አ እስከ 2015 ባለው መረጃ ከ**1606** የኢትዮጵያ ከተሞች አፈጻጸማቸው በመከታተል ድጋፍ የተደረገላቸውና ግብረ መልስ የተሰጣቸው ከተሞች ብዛት በ2006 ዓ/ም **15 ከተሞች /0.93 %/** ፣ በ20007 ዓ/ም **16 ከተሞች / 1%/** እና በ2008 ዓ/ም **27 ከተሞች /1.68%/** ብቻ መሆናቸው ከኢትዮጵያ ከተሞች ብዛት አንጻር የተደረገው ድጋፍና ክትትል አነስተኛ እና

የተሰጠው ግብረ መልስ ያመጣው ውጤትም የማይገመገም መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀውን ስታንዳርድ ክልሎች እና ከተሞች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው ያላዘጋጁና ተግባር ላይ ያላዋሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡

<u>በከተሞች አካባቢን የሚበክል አካል ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍል የማድረግና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን ክትትልና ድጋፍ ማደረጉን በተመለከተ፡-</u>

184. ሚኒስቴር መ/ቤቱ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች በከተሞች አካባቢን የሚበክል አካል ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍል የማድረግና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን በማስፈን አገልግሎቱ የራሱን ወጪ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍን የሚያደርግ ስርአት በመዘርጋት እየተገበሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

185. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን የስራ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ከዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች መሰረት፡-

- በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት በሀረር እና በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት በጂግጂጋ ከተሞች አካባቢን የሚበክሉ አካላት ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍሉ የማይደረግና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን በማስፈን አገልግሎቱ የራሱን ወጪ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍን እየተደረገ አለመሆኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ገልፀዋል፡፡
- በከተሞች በከፍተኛ ደረጃ አደገኛ ቆሻሻ በአግባቡ የማይሰበሰብና የማይወገድ መሆኑ፤ እንዲሁም አካባቢን የሚበክሉ አካላትና ተቋማትን ተጠያቂ አድርጎ የሚያቀርብ የአደረጃጀት ስርአት አንዲሁም የህግ ማእቀፍ አለመኖሩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

186. ስለጉዳዩ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ ችግሩን

ለመፍታት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረገው ድጋፍና ክትትል እንዲሁም የተሰጠው ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ በቂ አለመሆኑና የተሰጠው ግብረ መልስ ያመጣው ለውጥ ባለመገምገሙ የመጣ ችግር መሆኑ ታወቆ አፋጣኝ መፈትሄ ካልተፈጠረ ችግሩ እየሰፋና እየተባባሰ እንደሚመጣ ገልጸዋል፡፡

<u>በገበያ ቦታዎች የሚመነጭ ቆሻሻ ከተሞች በመነጨበት ቀን ወዲያውኑ እንዲሰበሰብ እያደረጉ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን በተመከተ፡-</u>

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከገበያ ቦታዎች የሚመነጭ ቆሻሻ በአብዛኛው በተፈጥሮዋዊ ሂደት የመበስበስ ባህሪ ስላለው መጥፎ ሽታ እንዳያመጣና የተለያዩ ነፍሳትና የእንስሳት መዋያ እንዳይሆን እንዲሁም ከቆሻሻ የሚመነጨው ጥቁር ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ውስጥ የሚሰርግና ከፍተኛ ዝገትና ብልሽት የሚፈጥር በመሆኑ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ ቆሻሻ በመነጨበት ቀን ወዲያውኑ እንዲሰበሰብ እያደረጉ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

188. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን የስራ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳ፣ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ከዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የመስክ ምልከታዎች መሰረት፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ በገበያ ቦታዎች የሚመነጭ ቆሻሻ በመነጨበት ቀን ወዲያውኑ እንዲሰበሰብ እያደረጉ ስለመሆናቸው የመከታተል፣የመደገፍ እና አስፈላጊውን ግብረመልስ የመስጠት ስራ ያልተጠናከረ እና አፈፃፀሙ አጥጋቢ እንዳልነበረ እንዲሁም የተሰጠው ግብረ መልስ ያመጣው ውጤት የማይገመገም መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመርካቶ እህል በረንዳ አካባቢ የገበያ ቦታ ሳይሆን የቆሻሻ መድፊያ ቦታ /Landfill/ እስኪመስል ድረስ ቆሻሻ በየቦታው

ተከምሮና ተዝረክርኮ የሚገኝ በመሆኑ፣ የአከባቢው ነጋዴዎች ችግሩ መፍትሄ እንዲያገኝ በሐምሌ 05/ 2009 ዓ/ም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ በግልባጭ ለወረዳው አስተዳደር፣ለአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ፖሊስ ጣቢያ እና ለወረዳው ጽዳት አስተዳደር ቢሮ ቢያመለክቱም የኦዲት መስክ ምልከታ እስከተደረገበት ቀን ችግሩ ያልተፈታ መሆኑ፡፡ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአስኮ አዲስ ሰፈር፣ በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ቀፊራ ዋና የገበያ ቦታ፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር እና በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ጂግጂጋ ከተሞች የሚገኙ የገበያ ቦታዎች ቆሻሻ በመነጨበት ቀን ወዲያውኑ የማይሰበሰብ እና ቆሻሻው ለሺያጭ በተቀመጡ የአትክልትና ፍራፍሬ ፣ የአዝርእትና ጥራጥሬ አይነቶችና ሌሎች ሰው የሚገለገልባቸው ቁሳቁሶች ዙሪያ ተዝረክርኮ የሚገኝ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ የገበያ ቦታዎች ቆሻሻ የማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ ተሸከርካሪዎች አናሳ በሚሆኑበት ጊዜ እና ለጥገና ጋራዥ በሚገቡበት ወቅት አገልግሎቱ የሚቆራረጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ በየካ ክ/ከተማ ካለው የገበያ ስፋትና ከሚያመነጨት ደረቅ ቆሻሻ አንፃር ሲታይ ተደራሽነቱ ያልተሟላ መሆኑ፣ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ በንግድ ቦታዎቹ ላይ የተዘጋጀ የቆሻሻ ማቆያ ቦታ ስለሌለ በኮልፌ፣ በመርካቶ፣ በመሳለሚያ አካባቢ ደረቅ ቆሻሻ በየቦታው ተዝረክርኮ የሚጣልና በወቅቱ የማይነሳ መሆኑ እንዲሁም በጂማ፣ ጂግጂጋና አዋዲ ከተሞች ቁልፍ ችግር የገበያ ቦታዎች የቆሻሻ አሰባሰብ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ **<u>የአደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር ሳይቀላቀል ለብቻው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ታክሞ ለብቻው በተከለለት ቦታ በአካባቢ ላይ ተፅእኖ በማያመጣ መልኩ እንዲወገድ እየተደረገ ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፡-</u>**

189. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የአደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር ሳይቀላቀል ለብቻው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ በሚገባ ታክሞ ለብቻው በተከለለት ቦታ በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ ተፅእኖ በማያመጣ መልኩ እንዲወገድ እየተደረገ ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

190. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን የስራ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳ፣ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ከዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የመስክ ምልከታዎች መሰረት፡-

- በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ቢሾፍቱ፣ አወዳይ፣ ባሌ ሮቤ እና በአማራ ብ/ክ/መንግስት ቡሬ ከተሞች አደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ የሚለይበት ስርአት ያለመኖር፤ በተለይም ከጤና ተቋማት የሚወጣ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር ሳይቀላቀል የማስወገድ እውቀትም ሆነ አቅም ውስን በመሆኑ አደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ እየተቀላቀለ የሚወገድ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሽታ አስተላላፊ /infectious/ እና በሽታ አስተላላፊ ያልሆነ /non infectious// ቆሻሻ በአግባቡ የመለየት አገልገሎት ያለመኖር፣ አብዛኛዎቹ ሆስፒታሎች ቆሻሻን የመለየት ልምድ የሌላቸው መሆኑ፣ ያለምንም ቅድመ ጥንቃቄ የጤና ተቋማት ቆሻሻ እንደማንኛውም ቆሻሻ ተቀላቅሎ የሚሰበሰብና ሚጓጓዝ መሆኑ፣ አደገኛ ቆሻሻ አደገኛ ካልሆነ ቆሻሻ ተለይቶ የሚሰበሰብበት፣ የሚጓጓዝበትና የሚወገድበት ስርአትም ሆነ ቴክኖሎጂ የሌለ መሆኑ፣ አብዛኛዎቹ የግል ክሊኒኮች ባዮ ሚዲካል ቆሻሻዎችን የማከሚያ ቴክኖሎጂ የሌላቸው መሆኑ፣ ፒት እየተባለ የሚጠራው የፕላሴንታ ማስወገጃ ጉድጓድ ከመሰራቱ በፊት ያለምንም ጥንቃቄ በክፍት መጓጓዣ ክፈት በሆነ የማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ በሚወገድበት ስፍራ ይወገድ የነበረ ሲሆን ፒት እየተባለ የሚጠራው የፕላሴንታ ማስወገጃ ጉድጓድ ከተገነባ በኂላም ወደታችና ወደ ጎን ስርገት ያለው በመሆኑ የአለም የጤና ድርጅት ስታንዳርድ ያሟላ አለመሆኑ፣ ከኤሌክትሮኒክና ኤሌትሪክ ነክ ከሆኑ ዕቃዎች የሚመነጭ አደገኛ ቆሻሻ በመነጨበት ቦታ በአይነቱ ተለይቶ የማይቀመጥ መሆኑ እና እነደማንኛውም ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚወገድ መሆኑ፣ በአዲስ አበባ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የተለያዩ አይነት አደገኛ እና ስለታማ የሆኑ ደረቅ ቆሻሻዎች የመሰብሰብ የማጓጓዝና

የማስወገድ ስራ የሚከናወነው አደገኛ ካልሆኑ ደረቅ ቆሻሻዎች ጋር ተቀላቅሎ መሆኑ፣

- በድሬደዋ ከተማ አስተዳደርና በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ሻሸመኔ እና ቢሾፍቱ ከተሞች ከጤና ተቋማት እና መድሃኒት ቤቶች የሚመነጨው አደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር የሚቀላቀልበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር እና በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ጂግጂጋ ከተሞች ከነሐሴ 2008 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ/ም በተደረገ የመስክ ምልከታ /በቼክ ሊስት/ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ፣ቂርቆስና ልደታ ክ/ከተሞች በቀረበው መጠይቅ መሰረት የአደገኛ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ቆሻሻ ጋር የሚቀላቀል መሆኑ፣ ለብቻው በአግባቡ በመያዝ በሚገባ ታክሞ በተከለለለት ቦታ በማህበረሰብ፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ ተፅእኖ በማያመጣ መልኩ እንዲወገድ እየተደረገ አለመሆኑ፣
- በአዲስ አባባ ከተማ በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል አጥር ጥግ በተቀመጠው ገንዳ እና በዙሪያው አደገኛ ይሁኑ አይሁኑ ያልተለዩ ቆሻሻዎች እንደ የምግብ ትርፍራፊ የእንስሳት አጥንት የመሳሰሉት ተዝረክርከው እንደሚገኙ እና ይህም በሆስፒታሉ ሰራተኞች እና በታካሚዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን ጳጉሜ 2008 ዓ/ም የሚመለከታቸው ባለሞያ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡
- ከጳጉሜ 2008 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባ ጋንዲ መታሰቢያ እና ለፖሊስ ሆስፒታሎች፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ለሀረር ጆጎል ሆስፒታል፣ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ለድል ጮራ እና ለሳቢያን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ለሚመለከታቸው ባለሞያዎችና ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የመስክ ምልከታ መሰረት እስካሁን ድረስ ቆሻሻ ታክሞ እንዲወጣ የሚያገለግል መሳሪያ ስለሌለ በሆስፒታሎች ግቢ ውስጥ በሚገኝ የቆሻሻ ማቃጠያ /ኢንሲሊኔተር/ እና በተቆፈረ ክፍት ጉድጓድ እንዲቃጠል የሚደረግ መሆኑ ገልጸዋል፡፡
- መስከረም 2009 ዓ/ም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለዘጠኝ ፅዳት ማህበራት በቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት በከተማው ያሉ የግል ክሊኒኮች አደገኛ

ቆሻሻዎችን ሚቶ በሚባል መናኻሪያ መሻገሪያ አካባቢ ሜዳ ላይ እንደሚጥሉ እንዲሁም በሀረር ከተማ ለፅዳትና ውበት ኤጀንሲ በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት ሀረር ቢራ፣ ሀማሬሳ ዘይት ፋብሪካ፣ ባቢሌ የውሃ ማዕድን፣ ሀረር አጠቃላይ ሆስፒታል፣ አማጅ ሆስፒታል፣ ኢማም ክሊኒክ፣ ኦዳ ክሊኒክ፣ አራተኛ ጤና ጣቢያ፣ ጀጎል ሆስፒታል፣ ሂወት ፋና ሆስፒታል እና ፖሊስ ሆስፒታል፣ ቆሻሻ አክመው እንደማያስወግዱ እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ቆሻሻ ታክሞ እንዲወገድ እና አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያደርስ ለማድረግ የሚያስችል ስርአት ያልዘረጋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ከመስከረም እስከ ህዳር 2009 ዓ/ም አዲስ አበባና በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር እና በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ጂግጂጋ ከተሞች ለከተማ ፅዳት ኤጀንሲ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት የጤና ተቋማት የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሸ አክመው ያስወግዱ አያስወግዱ የሚቆጣጠሩበት ስርአት የሌላቸው መሆኑን፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ድጋፍና ክትትል አለመኖሩ ገልጸዋል፡፡

<u>የጤና ተቋማት እና ኢንዱስተሪዎች በሚያመነጩት ቆሻሻ የተከሰተ የጤና ችግር እና ቆሻሻ ሲያዝ፣ ሲያክሙ እና የማስወገድ ተግባራት ሲያከናውኑ በአካባቢ የተፈጠረ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው በማረጋገጥ እየተገበሩ ስለመሆናቸው ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡-</u>

191. ሚኒስቴር መ/ቤቱ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የጤና ተቋማት እና ኢንዱስተሪዎች በሚያመነጩት ቆሻሻ የተከሰተ የጤና ችግር እና ቆሻሻ ሲያዝ፣ ሲያክሙ እና የማስወገድ ተግባራት ሲያከናውኑ በአካባቢ የተፈጠረ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው በማረጋገጥ እየተገበሩ ስለመሆናቸው ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

192. በ2006 ዓ/ም በወጣው ለአረንጓዴ ልማት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የከተሞች የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብ እና አወጋገድ ስትራቴጂ እና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣አሰባሰብና አወጋገድ ስታንዳርድ ማንዋል ቁጥር 06/2007 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ

ቤቶች/ የጤና ተቋማት እና ኢንዱስተሪዎች በሚያመነጩት ቆሻሻ የተከሰተ የጤና ችግር እና ቆሻሻ ሲያዝ፣ ሲያክሙ እና የማስወገድ ተግባራት ሲያከናውኑ በአካባቢ የተፈጠረ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው በማረጋገጥ እየተገበሩ ስለመሆናቸው የክትትልና ድጋፍ ስራ በማከናወን ግብረ መልስ መስጠትና ግብረ መልሱ ያመጣውን ውጤት መገምገም ይኖርበታል፡፡

193. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን የስራ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳ፣ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ከዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የመስክ ምልከታዎች መሰረት፡-

- ከጳጉሜ 2008 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባና በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር እና በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ጂግጂጋ ከተሞች የተደረገ የመስክ ምልከታ እና ለሆስፒታሎች እና የጽዳት ማህበራት በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት በአጠቃላይ የጤና ተቋማት በሚያመነጩት ቆሻሻ የተከሰተ የጤና ችግር ስለ መኖሩና አለመኖሩ እንዲሁም ቆሻሻ ሲይዙ፣ ሲያክሙ እና የማስወገድ ተግባራት ሲያከናውኑ በአካባቢ የተፈጠረ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያስከትል መልኩ እየተገበሩ ስለመሆናቸው በክልልም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ ክትትልም ሆነ ድጋፍ ተደርጎላቸው እንደማያውቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በ14 ከተሞች /መቀሌ፣ ሰመራ፣ ደብረማርቆስ፣ ባህርዳር፣ አምቦ፣ አዳማ፣ ጂግጂጋ፣ አሶሳ፣ ይርጋለም፣ ዲላ፣ አዋሳ፣ ሀረር፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች 90 በመቶ የሚሆኑት የማይታከሙ መሆናቸው፣
- ከጳጉሜ 2008 ዓ/ም እስከ ህዳር 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባና ድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር፣ በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ጂግጂጋ እና በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር ከተሞች በተደረገ የመስክ ምልከታ /ቼክ ሊስት/ እና ለጽዳት አገልግሎት ኤጀንሲ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት ኢንዱስትሪዎች የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሸ አክመው ያስወግዱ

አያስወግዱ የሚቆጣጠሩበት ስርአት የሌላቸው መሆኑና ከኢንዱስትሪም ሆነ ከሌሎች ተቋማት የሚመነጭ ቆሻሻ ከመወገዱ በፊት የማይታከም መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በጳጉሜ 2008 ዓ/ም በአዲስ አበባ መስተዳድር በንፋስ ስልክ ላፍቶ እና የካ ክፍለ ከተሞች በቀረበ መጠይቅ መሰረት ከኢንዱስትሪና ከሌሎች ተቋማት የሚመነጭ ቆሻሻ ታክሞ የሚወገድበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡
- ከጳጉሜ 2008 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል እና ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ድል ጮራ ሪፈራል ሆስፒታል እና ሳቢያን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል እና በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት በሀረር ጀጎል ሆስፒታል በተደረገው የመስክ ምልከታ እና በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት አደገኛ ቆሻሻ የሚያክሙበት ቴክኖሎጂ እንደሌላቸው እንዲሁም በቆሻሻ ማቃጠያ /ኢንስሊኔተር/ እና በተቆፈረ ጉድጓድ እንደሚያቃጥሉት ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በህዳር 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለኢልኮ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ እና ለሆራይዞን አዲስ ጎማ ፋብሪካ በተደረገ ቃለ መጠይቅ መሰረት የደረቅ ቆሻሻ ማከሚያ መሳሪያ እንደሌላቸው እና በአይነት ለይተው በቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቦታ ሄዶ ይወገዳል እንጂ የሚያክሙበት ስርአት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡
- እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ድጋፍና ክትትል ውስንና ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል ውጤት የሚያመጣ አለመሆኑ በመስክ የታዩ ከተሞች የሚመለከታቸው የዘርፉ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

<u>የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /Landfill/ በየከተሞቹ ፈርጅ መሰረት የወጣውን የምድብ ደረጃ ስታንደርድ ያሟላ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል በተመለከተ፡-</u>

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /Landfill/ በየከተሞቹ ፈርጅ መሰረት የወጣውን የምድብ ደረጃ ስታንደርድ ያሟላ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

195. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን የስራ ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳ፣ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ከዘርፉ የስራ ኃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የመስክ ምልከታዎች መሰረት፡-

የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (landfill) ሊያስተዳድር የሚችል በመዋቅሩ መሰረት ብቃት ያለው የሰው ኃይል አለመኖሩ፣ አመራሩ በሰው ኃይል አመዳደብ ለጽዳት ዘርፍ ትኩረት አለመስጠቱ፣ በግምገማ ከቦታቸው የተነሱ ባለሞያዎች እና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው አመራሮች በዘርፉ እንዲመደቡ የሚደረግ መሆኑ፣

196. ሰንዳፋ የተገነባው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /Landfill/ ፡-

- ለስራ ደጋፊ እና ምቹ የሆኑ መገልገያዎች የልተሟሉለት መሆኑ ለምሳሌ ካፊቴሪያ፣ ክሊኒክ፣ ማሽኖች ከፀሀይና ከዝናብ ሊከላከልላቸው የሚያስችል መጠለያ ያልተሟሉለት መሆኑ፣
- ከኢንዱስትሪዎች የሚወጣ ያልታከመ አደገኛ ቆሻሻ የሚወገድበት መሆኑ፣
- በስታንዳርዱ መሰረት ለማስወገጃ ቦታው የሚያስፈልግ ሞተር ግሬደር የሌለው መሆኑ፣
- ቦታው ከከተማ የራቀ ቢሆንም ከማስወገጃ ስፍራው አጥር ከስታንዳርዱ በታች በሆነ ርቀት የመኖሪያ ቤቶች እና የእርሻ ማሳዎች በቅርበት የሚገኙ መሆኑ፣
- የተገነባው የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ነፋሻማ ቦታ ላይ ከመሆኑም ባሻገር ለእርሻ አገልግሎት ሊውል የሚችል ለም መሬት ላይ መሆኑ፣
- ከቆሻሻው የሚመነጨው ጥቁር ፈሳሽ ማጠራቀሚያ እና ማከሚያ ስፍራው ክፍት በመሆኑ ዝናብ የሚገባበት ሲሆን የሚታከመውን ጥቁር ፈሳሽ ሂደቱን ሳይጨርስ ወደ ውጭ ሊፈስ ስለሚችል ገፀምድር የመበከል እድል እንደሚኖረው እና በሚወጣው መጥፎ ሽታ የአካባቢውን አየር በመበከል በዙሪያው የሚኖሩ ገበሬዎች ጤና ላይ ችግር ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፣

197. እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ ረጲ የሚገኘው የቀድሞው ክፍት የቆሻሻ መድፊያ ቦታ የሚያመነጨው መርዛማ ፈሳሽ አካባቢውን እየበከለ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም በህዳር 2009 ዓ/ም የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የመልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ስራ አስኪያጆች በጋራ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቆሻሻ ማስወገጃው መረጣና ግንባታ ዙሪያ ያላገዛቸውና በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥበት የዳሰሳ ጥናት ሰነዱን ቢልኩለትም ምላሽ አለመስጠቱ እንዲሁም የተገነባው ዘመናዊ የቆሻሻ መድፊያ ቦታ እንዲጎበኝላቸው ጥሪ ቢያደርጉለትም ያልጎበኘላቸው መሆኑ ገልጸዋል፡፡

198. በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /Landfill/ ፡-

- በስታንዳርዱ መሰረት ከቆሻሻው የሚመነጭ ጥቁር ፈሳሽ /lecheate/ ለመከላከል እና ለማከም የሚያስችል የኦክስዴሽን ኩሬ የሌለው መሆኑ፣
- ተከታታይ የስርገት ቁጥጥር እንደማይደረግለት፣ ስራው በስራ አመራሩ እቅድ መሰረት ካለመሰራቱም ባሻገር ጎማዎች፣ የህክምናና ሌሎች አደገኛ ቆሻሻዎች፣ የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እንዲሁም የግንባታ ፍርስራሾች በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ እየተወገደ መሆኑ፣
- ወደ ማስወገጃ ቦታ በሚደርሱ የቆሻሻ አይነቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል ከፍተኛ የብቃት ደረጃ ያለው የስራ አመራር አለመኖሩ፣
- የማስወገጃ ቦታ የሚጠቀጥቅ ማሽን ተንቀሳቃሽ ሎደር፣ ተንቀሳቃሽ ዶዘር፣ ፊቱ ላይ መዛቂያ የተገጠመለት ሎደር፣ ገልባጭ መኪና፣ ሞተር ግሬደር(ማረሻ)፣ የውሃ ቦቲ የሚጭን (የሚጎትት መኪና) አለመኖሩ፣
- ህብረተሰቡ በቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ አጠገብ የመኖሪያ ቤት እና የኤሌክትሪክ ፖል ማምረቻ ተቋም ግንባታ እያከናወነ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በፍተኛ ወጪ የተገነባው ደረጃው የጠበቀ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አስፈላጊ ማሽነሪዎች ባለመሟላታቸው ወደ ክፍት የቆሻሻ መድፊያ ቦታ የተቀየረ መሆኑ ለመረዳት ተችለዋል፡፡ በተጨማሪ የቀድሞው

የቆሻሻመድፊያ ቦታ ለአየር ንብረት ለውጥ በሚያግዝና ለአይን በሚስብ መልኩ ወደ አረንጓዴ ቦታነት እንዲቀየር መደረጉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

199. በሀረሪ ብ/ክ/መንግስት ሀረር ከተማ ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማሰውገጃ ቦታ እየተገነባ መሆኑ ነገር ግን አሁን ባለበት ሁኔታ በስታንዳርዱ መሰረት ደረጃው የጠበቀ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እንደማይቻል፤ ነባሩና አገልግሎት መስጠት ያቆመው የቆሻሻ መድፊያ ቦታ ወደ አረንጓዴነት ለመቀየር እንቅስቃሴ መጀመሩ ከባለሞያው ከተገለጸው ውጪ ስራው ብዙ የሚቀረው መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

200. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለኢልኮ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ በቀረበ ቃለ መጠይቅ መሰረት የሰንዳፋ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲገነባ ኢንዱስትሪዎችን ማዕከል ያደረገ ባለመሆኑ ከኢንዱስተሪው ቆሻሻ በሚሄድበት ወቅት ከኢንዱስትሪ ለሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻዎች ማከሚያ ስርአት ስለሌለን አንቀበልም የሚባሉበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

201. እንዲሁም፡-

- በአማራ ብ/ክ/መንግስት ባህር ዳር ከተማ ከደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚመነጨው መርዛማ ፈሳሽ /Leachate/ አካባቢውን እየበከለ መሆኑ፣
- በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች አለመሟላት፤
- በአዳማ ከተማ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታው ስራ አመራር የላላ በመሆኑ ወደ ክፍት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ /Open landfill/ መቀየሩ፣
- በቡታጅራ፣ ቁሊቶ እና ዲላ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ያልተከለለና ያልታጠረ ከከተማው ፈርጅ ስታንዳርድ በታች መሆኑ፣
- ደብረታቦር ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታው ያልታጠረ ከመሆን ባለፈ አካባቢው በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የተካሄደበት፣ የንፋስ አቅጣጫውም ወደ ከተማው መሆኑ እና የቤት እንስሳት የሚሰማሩበት መሆኑ፣
- በደሴ ከተማ በአገልግሎት ላይ ያለው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በተፈጥሮው ገደላማ ቦታ መሆን እና ለአያያዝ አመቺ አለመሆኑ እንዲሁም

ከደረቅ ቆሻሻ የሚመነጨው ፈሳሽ /Leachate/ በአካባቢው የሚገኘውን ወራጅ ወንዝ ሊበክል የሚችል መሆኑ፣

- በጂግጂጋ ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አለመኖሩ አሁን ያለው ጊዜያዊ ማስወገጃ የከርሰ ምድር እና የወንዝ ውሃን እየበከለ መሆኑ፣
- በጋምቤላ ከተማ ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ የተመረጠው ቦታ ከከተማ 7 ኪ/ሜ እርቀት ላይ ቢሆንም ለደረቅ ቆሻሻ ማስወጋጃ በሚሆን መልክ ቦታው በአግባቡ ያልተመረጠና ያልተዘጋጀ ግልፅ ሜዳ ስለሆነ ከቤትና ዱር እንስሳት እንዲሁም ከሰዎች ንክኪ የተከለለ አለመሆኑ፣
- በአሶሳ ከተማ አዲስ ጊዚያዊ ማስወገጃ ስፍራም ለከተማው በጣም ቅርብ (ከመሀል ከተማ 1.5 ኪ.ሜ ርቀት) እና ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃነት የተጠና ስፍራ አለመሆኑ እንዲሁም ለተሽከርካሪም ምቹ እንዳልሆነ ለመረዳት ተችለዋል፡፡
- በጎንደር ከተማ የሚወገድ ደረቅ ቆሻሻ በቀጥታ እንደሚቀበር ሊመነጭ የሚችለው አደገኛ ፈሳሽ /Leachate/ የሚወገድበት ሁኔታ እንደሌለ ለመገንዘብ ተችለዋል፡፡
- በቢሾፍቱ ከተማ አገርአቀፍ የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስታንዳርዱን የሚያሟላ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ (landfill) ከታቀደላቸው በበሀገሪቷ ካሉት ጥቂጥ ከተሞች ውስጥ አንዷ ብትሆንም ከሁለት አመት በፊት ከወርልድ ባንክ የከተሞች ዕድገት ፕሮግራም በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ግንባታ የተናቀቀ ቢሆንም ለቦታው የሚያስፈልጉ ቁሳቆሶችን ለማሟላት የሚያስፈለገው ገንዘብ ስላልተለቀቀ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ እና እንደተለመደው ከከተማዋ የሚሰበሰበው ቆሻሻ በፊት በነበረውና የእርሻ ቦታ በሆነው ቦታ ላይ እየተጣለ መሆኑ፤
- በጅማ፣ ወለወዲያ፣ ውልቂጤ፣ ባሌሮቤ፣ ዲላና ወሊሶ ከተሞች የሚገኝ የቆሻሻ መድፊያ ቦታ የአካባቢ፣ የቦታ፣ የመሳሪያ፣ እና የባለሙያ ቁጥጥር የማይደረግበትና ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዳልሆነ፤ አወዳይና ቡሬ ከተሞች ከአከባቢ ጥበቃ አንጻር ትክክለኛና ስታንዳርዱ ያልጠበቀ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የውቅሮ ከተማ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ በዋና መንገድ አጠገብ መሆኑ ለመረዳት ተችለዋል፡፡

- በጂግጂጋ ከተማ 4 ሄክታር የሚሸፍን ከከተማዋ 7 ኪ.ሜ የሚርቅ ዋና የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ያለ ቢሆንም ለ12 አመት ያገለገለ እና ያልተከለለ መሆኑ፣ ቦታው በመኖሪያ ቤት አካባቢ በመሆኑ ለ24 ሰአታት ቆሻሻው እንዲቃጠል ስለሚደረግ የአየር ብክለት ከማስከተሉም በላይ ለነዋሪዎች የጤና ጠንቅ ሊሆን የሚችል መሆኑ፣ አስተዳደራዊ ቁጥጥር የማይደረግበትና ስታንዳርዱን ያላሟላ መሆኑ ታውቋል፡፡

202. በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (landfill) ችግር ለመፍታት የሚያስችል ያደረገው ድጋፍና ክትትል አነስተኛና የሚጠበቀውን ውጤት የማያስገኝ መሆኑ በመስክ የታዩ ከተሞች የሚመለከታቸው የዘርፉ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ገልጸዋል፡፡

14. <u>የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን</u>

የዩኒሞዳል ገቢ ዕቃዎችን እንቅስቃሴ አፈጻጸምን በተመለከተ

203. ባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ መጠን ጭነትን (Bulk Shipments) በተመለከተ ከአስመጪዎች መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን በየበጀት ዓመቱ የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) አመጣጥ መረሃ-ግብር ረቂቅ ዕቅድ በማዘጋጀት ከአስመጪዎች፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

204. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከከፍተኛ መጠን ጭነት አስመጪዎች (ከስኳር ኮርፖሬሽን፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን፤ ከግብርና ምርት ማሳደግያዎች አቅርቦት ዘርፍ እና ከአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትና ከሌሎች አስመጪዎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት) የከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብር ዕቅድ ለመዘጋጀት የሚያስችል ማስረጃዎችን ወጥና አግባብ በሆነ መልኩ በደብዳቤ ስለመሰበሰቡ ተጠይቀው የ2006 ዓ.ም እና የ2007 ዓ.ም ብቻ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቀሪው የ2008 ዓ.ም ማስረጃ ያልቀረበ እና የ2009 ዓ.ም ደግሞ ጊዜው ካለፈ በኋለ/ በጀት ዓመቱ ከገባ ከስድስት ወር በኋለ የተሰበሰበ መሆኑን፤

እንደዚሁም ባለስልጣኑ በየበጀት ዓመቱ ተዘጋጅቶ ጸድቋል የተባለው የከፍተኛ መጠን ጭነት አመጣጥ ብሔራዊ ዕቅድ መረሃ- ግብር /Schedule/ ዝግጅት ላይ ከአስመጪዎች፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር በማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሰዋል የተባለ ቢሆንም ይህ ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ በኦዲት ወቅቱ ያልቀረበ መሆኑ፤

205. ባለስልጣኑ መ/ቤቱ በየወቅቱ የገቢ ከፍተኛ ጭነት አፈጻጸም ግምገማን በተመለከተ ከአስመጪዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

206. ባለስልጣኑ በተዘጋጀው ዕቅድና አፈጻጸም መርሃ ግብር መሰረት አፈጻጸሙ ላይ በየደረጃው ግምገማ በማድረግ እና ወቅታዊ ጉዳዮችና በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከአስመጪዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቋሚ በሆነ መልኩ ውይይት በማድረግ የግምገማውን ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ-መልስ በጽሑፍ አዘጋጅቶ የማይላክ መሆኑ፤

207. ባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቀውን የብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና መረሃ-ግብር መሠረት ለሚያስገቡ አስመጪዎች፤ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተገቢውን ግምገማ በማድረግ ዕውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

208. በብሔራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት ዕቅድ እና በመርሃ-ግብሩ መሠረት ከባህር ወደብ በወቅቱ ዕቃዎቻቸውን ወደ ሀገር ለሚያስገቡ አስመጪዎች፤ የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተለይተው ተገቢው ግምገማ በማድረግ በባለስልጣኑ ዕውቅና የማይሰጥ መሆኑ፤

209. ባለስልጣኑ አሰፈላጊ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ማዕከል (on line data base) ሊያደራጅ ይገባል፡፡

210. በባለስልጣኑ ደረጃ ከሚመለከታቸው የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃን በየዕለቱ ለማሰባሰብና በአንድ ማዕከል ለመያዝ የሚያስችል ዳታ ሲይሰተም (Data system) ባለመኖሩ አሰፈላጊና ወቅታዊ የሆኑ የሎጂስቲክስ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው አካላት (መርከብ ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በቀላሉ ለማሳራጨት አለመቻሉን፤

211. ባለስልጣን መ/ቤቱ ሀገራዊ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር (ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፤ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ወኪሎች) በባህር ወደብ ላይ የተከማቹ የገቢ ዕቃዎችን መጠን፤ ዓይነት፤ የቆይታ ጊዜ እና በኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት መረጃዎቹን ሊያጠናቅር ይገባል፡፡

212. በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሀገራዊ የሆነ የማሪታይም ሎጅስቲክስ መረጃ ሥርዓትን በተመለከተ በኢ-ሜይል በየቀኑ ከተለያዩ ዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች ለባለስልጣኑ ሲላክ የነበረው በ2006 ዓ.ም መ/ቤቱ ሥራ ላይ አውሎት የነበረ ሶፍትዌር የገቢና ወጪ ዕቃዎችን ኦፕሬሽን ሙሉ መረጃ ከዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች ተቀብሎ እና አጠናቅሮ ለባለስልጣኑ የሚያሳውቅ የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ተዘርግተው የነበረ ቢሆንም ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራው ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ መሆኑ፤

213. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ ዕቃዎችን የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻቸውን ለይተው መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በባለስልጣን መ/ቤቱ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ የቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚገቡ የገቢ ዕቃዎችን በተመለከተ ማስረጃዎቹ ለመጠናከርና ዕቃዎቹ የቆዩበትን ምክንያትና ችግሮቻችውን ለመለየት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤

ባለስልጣን መ/ቤቱ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረገ አካልን በመከታተልና መረጃ በመሰበሰብ ተጠያቂ

የሚሆኑበት የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ሊያቀርብ ይገባል፡፡

214. ባለስልጣኑ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ላይ ሀገሪቱን ለዲመሬጅ ክፍያ የዳረጉ አስመጪዎች፣ ዕቃ አስተላለፊዎች፣ መርከብ ወክሎችና ሌሎች አካላትን መረጃ አጠናቅሮ የማይያዝና ድርጅቶችን ተጠያቂ የሚያደርግበት የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፤

215. በ2006 ዓ.ም የከፍተኛ መጠን ገቢ ጭነት አገባብ ኦፕሬሽናል ዕቅድ በሚል በተዘጋጀ ዶክሜንት መሠረት የስቶሬጅና ተዛማጅ የወደብ ክፍያዎችን በተመለከተ እ.አ.አ ከጥር 2012 እስከ ሰኔ 2013 የከፍተኛ መጠን ጭነት ብቻ 38,522,598.11 የአሜሪካን ዶላር የተከፈለ ሲሆን የፕሮጅክት ካርጎ ደግሞ 4,120,246.10 በድምሩ 42,642,844.21 የአሜሪካን ዶላር ቢሆንም በችግሩ ዙሪያ ትንታኔ በመስጠት ውጤቱን በሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግስት አካላት ያልቀረበ መሆኑ፤

216. በ2008 ዓ.ም የደረቅ ብትን ጭነት ሎጅስቲክስ ፕሮግራም በሚል በቀረበው ጥናት የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት ለመርከብ ዲመሬጅ ብቻ በበጀት አመቱ ዝቅተኛ ስሌት ቢያንስ 5.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን በአጠቃለይ የመንግሥት የደረቅ ብትን ጭነት የሎጅስቲክስ ወጪ ዓመታዊ አማካኝ 257.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይም 5.6 ቢሊዮን ብር መሆኑን ያሚያስረዳ ቢሆንም የተካሄደውም ጥናት በጥቅል የቀረበና አላግባብ የወጣውን ወጪ በማን እንደሆነ ዝርዝር መረጃው ያልያዘ በመሆኑና በወቅቱም ለትራንስፖርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ለመንግሥት አካላት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤

217. በተጨማሪም በ2008 ዓ.ም በዩኒሞዳል በሚጓጓዙ የጀነራል ካርጎ ጭነት ላይ የብትን ጭነት ኦፕሬሽን ባስከተለው ጫና ምክንያት ለተጨማሪ ብር 162.1 ሚሊዮን አላግባብ ወጪ መሆኑ፤

218. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ድጋፍ ተደርጎላቸው በባህር ወደብ ላይ እቃዎችን በ30 ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት የማያነሱ አስመጪዎችን መረጃ በየወቅቱ በማጠናከር እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት በማድረግና በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

ባለ-ሥልጣኑ በባህር ወደብ ላይ በወቅቱ ወይም ከዕፎይታ ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ የሚቆዩ በዩኒሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የገቡ የገቢ ዕቃዎችን መረጃ በማጠናከርና በመተንተን ውጤቱን ውሳኔ ለመስጠት በሚያመች መልኩ በሪፖርት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለመላኩ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

ባለስልጣን መ/ቤቱ የተተዉ እቃዎች በወቅቱ ዝርዝር መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ለሚመለከታቸው አካላት በጊዜው ማሳወቅ እና እቃዎቹ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

219. በባህር ወደብ ላይ የተተዉ እቃዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎችን ከ2006 ዓ.ም እስከ 2009 ግማሽ ዓመት የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከ2010 እስከ 2015 እ.አ.አ ብቻ ያልተሟላ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያቀረቡ ሲሆን የተሰበሰበው መረጃ ሙሉና ወቅታዊ ባለመሆኑ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ ተተንትኖ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሪፖርት አለመደረጉ እና ከ2016 እስከ 2017 ግመሽ ዓመት ያለው መረጃ ግን ያልተሰበሰበና ለሚመለከታቸው አካላትም እንዳልቀረበ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

220. ባለስልጣን መ/ቤቱ የገቢ ዕቃዎች እና የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) የትራንዚት ትራንፖርትን በተመለከተ ባበህር ወደብ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር፤ ምክክር እና የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት በማድረግ ሊከታተልና ሊያሻሽል ይገባል፡፡

221. በ1994 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 284/94 የጸደቀው የኢትዮ-ጅቡቲ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት፣በክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት ሁለቱም

ሀገራት ካርጎ/ዕቃ በባህር ወደብ ከተራገፈ ጊዜ ጀምሮ ለ30 ቀናት ብቻ ለገቢ ዕቃዎች ያለምንም ክፍያ /30 days are Grace period for Import Transit Cargo/ በባህር ወደብ መቆየት እንደሚቻል ቢገልጽም በአሁኑ ወቅት የባህር ወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሻሻያ ያልቀረበ እና የገቢ ዕቃዎች ያለክፍያ በባህር ወደብ መቆየት የሚችሉት ወይም የእፎይታ ጊዜ እስከ 8 ቀናት (8 days are Grace period for Import Transit Cargo) በመሆኑ አገሪቷ ከ8 ቀናት በላይ በባህር ወደብ ለቆዩ ዕቃዎች ዲመሬጅ እየከፈለች መሆኑ፤

15. **<u>በኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት አዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞች በቅደም ተከተላቸው መሰረት እየተስተናገዱ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

222. ድርጅቱ አዳዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞችን መዝግቦ ሊይዝና በቅደም ተከተላቸው መሰረት ሊያስተናግድ ይገባል፡፡

223. በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 9 የሚጠበቅባቸውን የምሶሶ ክፍያ ከፍለው የኤሌክትሪክ ኃይል ከሚጠባበቁ ደንበኞች ቅደም ተከተል ዝርዝር ውስጥ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 13 ድረስ ያሉ ኃይል ተጠባባቂ ደንበኞች የውል ቁጥሩ 843430 ከሆነ በቀን 16/10/2007 ዓ.ም. ክፍያ ፈፅሞ አገልግሎቱን በመጠባበቅ ላይ ካለ ደንበኛ ከ 5 ወራትበኋላ በ2008 በጀት አመት ክፍያቸውን የፈጸሙ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሰውን የኃይል ፈላጊ ደንበኛ በወረፋ ቀድመው እንዲመዘገቡ መደረጉ፤

224. በናሙና ከታዩት 6 ሪጅኖች እና 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን በስተቀር በተቀሩት አምስት ሪጅኖች እና በ15ቱም አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ደንበኞችን ያለቅደም ተከተላቸው እንደሚያስተናግዱ ከማዕከላት በተሰጠን መረጃ ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኙ ደንበኞች ወደ ክፍያ ስርዓት እንዲገቡ ማድረግን በተመለከተ፣

225. ድርጅቱ አዲስ የኃይል አገልግሎት ያገኙ ደንበኞችን በሁለት ወር ውስጥ ወደ ክፍያ ስርዓት የሚገቡበት ስርዓት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

በምዕራብ፣ ሰሜን፣ ከደቡብ እና ምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን እንዲሁም ምስራቅ እና የጅጅጋ ሪጅን ቢዝነስ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ አዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኙ ደንበኞች በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ክፍያ ስርዓት ሊገቡ የሚገባ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶቹ ከዚህ በላይ ጊዜ እንደሚወስድባቸው የገለጹ መሆኑ

በተጨማሪም በሰኔ ወር 2008 በጀት አመት ደንበኞች በወቅቱ ወደ ሲስተም መግባትና ያለመግባታቸውን ለማረጋገጥ በአገልግሎቱ የውስጥ ኦዲት በናሙና ከተወሰዱ አስራ አንድ ደንበኞች ማለትም በንብረት ቁጥር (000787፣0003023፣ 1091468፣1091110፣ 00004141፣ 1076859፣ 0007317፣ 000648፣ 000648፣ 0004137፣ 00005415 እና 0000503) ሲስተም ውስጥ ሳይገቡ እና ምንም አይነት ክፍያ ሳይፈፀሙ እየተጠቀሙ ያሉ ደንበኞች እንደነበሩ የተገለፀ ሲሆን፣ ኦዲቱ ከተደረገ ከስድስት ወር በኃላ በ27/04/2008 ዓ.ም. በክዋኔ ኦዲቱ በተደረገው ማጣራት ከአንድ ደንበኛ ማለትም (የንብረት ቁጥር 1091110) ውጪ ሌሎቹ ደንበኞች ወደ ሲስተም ያልገቡ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ድርጅቱ ለሰጠው አገልግሎት በወቅቱ ክፍያ መሰብሰቡን በተመለከተ፣

226. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለደንበኞች የሰጠውን አገልግሎት ክፍያ በወቅቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

ተቋሙ ከተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ግለሰብ ደንበኞቹ ከ10 ዓመታት በፊት ጀምሮ ክፍያ ሳይፈጸምባቸው በየበጀት ዓመታቱ ተንከባሎ የመጣ ብር 132,352,369.89 በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ያልሰበሰበ መሆኑ፣

የአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር ጅጅጋ ቅርንጫፍ ቆጣሪ ወስዶ የኤሌክትሪክ ኃይል በመጠቀም አንድ አመት ከስድስት ወር በላይ ቢሆነውም እስከ ቀን 24/01/2009 ዓ.ም. ቆጣሪው ተነቦ የአገልግሎት መስጫ ማዕከሉ ወደ ክፍያ ስርዓት እንዲገባ ባለማድረጉ የተጠቀመበትን የአገልግሎት ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑን ከባንኩ ከቀረበልን መረጃ ለማወቅ የተቻለ መሆኑን፣

በሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን በሚገኙ ማዕከላት ደንበኞች ላይ በሰኔ 2008 ዓ.ም. በተደረገው የውስጥ ኦዲት በወቅቱ ወደ ሲስተም ባለመግባታቸው የተጠቀሙበትን የአገልግሎት ክፍያ ስለመክፈላቸው በናሙና ከተወሰዱ አስራ አንድ ደንበኞች ማለትም በንብረት.ቁጥር (0007871፣ 0003023፣ 1091468፣ 1091110፣ 00004141፣ 1076859፣0007317፣ 000648፣000648፣ 0004137፣ 00005415፣ 0000503) በተደረገው ማጣራት ሲስተም ውስጥ ሳይገቡ እና ምንም አይነት ክፍያ ሳይፈፅሙ እየተጠቀሙ ያሉ ደንበኞች እንደነበሩና ኦዲቱ ከተደረገ ከስድስት ወር በኃላ 27/04/2008 ዓ.ም. በክዋኔ ኦዲቱ በተደረገው ማጣራት ከአንድ ደንበኛ ማለትም(1091110) ውጪ ሌሎች የተጠቀሙበትን የአገልግሎት ክፍያ ያልፈፀሙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች የቤት ለቤት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ፣

227. የድርጅቱ የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞችን ምቹ የሆነ የቤት ለቤት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በኦዲቱ በናሙና በታዩት 6 ሪጅኖች ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች key account በመፍጠር የቤት ለቤት አገልግሎት እየሰጡ ያለመሆኑን፤

በኦዲቱ በናሙና ተለይተው መረጃ ከተሰበሰበባቸው 6 ሆቴሎች፤ 8ባንኮች፣4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፤ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎችእንዲሁም 1ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በድርጅቱ በኩል ምንም

አይነት የቤት ለቤት አገልግሎት እያገኙ አለመሆኑን በኦዲት ስራው ወቅት ካቀረቡት የጽሁፍ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ክፍያቸውን በአግባቡ በማይፈጽሙ ደንበኞች ላይ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ፣

228. ድርጅቱ ለደንበኞች አገልግሎት ሰጥቶ ክፍያውን በወቅቱ በማይፈፅሙ ደንበኞች ላይ ተገቢውን እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በኦዲት ስራው ወቅት በሰሜን አዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ ዲስትሪክቶች ስር የሚገኙ የአገልግሎት ቁጥር 2800626፣ 2800608 እና 1841702 ደንበኞች ውዝፍ የፍጆታ ሂሳብ ብር 270,747.30፣ ብር 218,287.30 እና ብር 69,249.85 በአጠቃላይ ብር 558,284.45 ያልተሰበሰበ መሆኑን መረጃ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በድርጅቱ ካሉት 15 ሪጅኖች ውስጥ 97 የሚሆኑ የተለያዩ የአገልግሎቱ ደንበኞች ማለትም ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ኤምባሲዎች እና ግለሰቦች ከ1999-2008 በጀት አመት ለተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 80,927,531.81 ለመፈጸም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው በተቋሙ ምንም አይነት እርምጃ እንዳልተወሰደባቸው በኦዲት ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ስለመዘርጋቱ በተመለከተ፣

229. ድርጅቱ ከደንበኞች የሚነሱትን ቅሬታዎች የሚፈታበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

230. በምዕራብ አዲስ አበባ ሪቴል ቢዝነስ ቁጥር 6 አገልግሎት መስጫ ማዕከል በሁለት ኮፒ የሚዘጋጅና አንደኛው ኮፒ ቅሬታ አቅራቢ ክትትል ሊያደርግበት የሚያስችል የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ የተዘጋጀ መሆኑን በተደረገው ማጣራት የሚከተለው ተገኝቷል፣

- ✓ በምስራቅ አዲስ አበባ ሪቴል ቢዝነስ ቁጥር 5 አገ/መ/ማዕከል ደንበኞች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት ቅጽ የቢል ሂሳብ ማረሚያ/ማስተካከያ/ የሚነሱ ቅሬታዎችን ብቻ ለመፍታት የተዘጋጀ ቅጽ መሆኑን፤
- ✓ በሰሜን አዲስ አበባ ሪቴል ቢዝነስ ቁጥር 4 አገልግሎት መስጫ ማዕከል ደንበኛው ቅሬታውን ሊከታተልበት የሚያስችል ቀሪ የሌለው ሲሆን ቅሬታውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና የስራ ኃላፊነት ሊጠቀስ የሚችልበት ቦታ ያለመኖሩ፤
- ✓ በሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 6 የቅሬታ አቅራቢው አድራሻ የሚሞላበት ቦታ የሌለ እና ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን የሚከታተልበት ቀሪ ኮፒ ያልተዘጋጀለት መሆኑን፣
- ✓ ደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማእከላት ቁጥር 7፤ 9 እና አዱላላ፤ምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማእከል ቁጥር 4 እና ሀረር ሪጅን ቁጥር 1 አገልግሎት መስጫ ማእከላት የደንበኞች ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ ከዚህ በተጨማሪም ለሪፖርት ፍጆታነት እንዲውል ብቻ በሚመስል ሁኔታ የደንበኞች ቅሬታ ሪፖርቶች የሚወጡበት ሁኔታም አለ ለመጥቀስ ያክል በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን የደብረዘይት አገልግሎት መስጫ ቁጥር 1 የደንበኞች ቅሬታ እና የተፈቱ ቅሬታዎች ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ከመጋቢት 24 እስከ ሚያዚያ 20 2008 ዓ.ም. የዋጋ ትመና ያልተደረገላቸው ደንበኞች የወሩ ቅሬታ ብዛት 896 መሆን ሲገባው 19 ተብሎ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ከሚያዚያ 21 እስከ ግንቦት 19 2008 ዓ.ም. ሪፖርት ላይ ያለፈው ወር ያልተፈታ ቅሬታ ዝርዝር ውስጥ የዋጋ ትመና ቅሬታ ብዛት 896 ተብሎ

መመዝገብ ሲገባው 535 ተብሎ ሪፖርት መደረጉ ከቀረበልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በናሙና ከታዩ 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የቅሬታ መቀበያ ፎርም ከማዕከል ማዕከል እንደሚለያይና አንድ ወጥ የሆነ የቅሬታ መቀበያ ፎርም የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላቱም በተጠናከረ መልኩ የደንበኞች ቅሬታን በማይሰበስቡበት ፤ የቀረበው ቅሬታ ስለመፈታቱ የሚያሳይ መረጃ በሌለበት ሁኔታ በየወሩ ለሪጅን ቅሬታ (ግሪቫንስ) ቢሮ ከደንበኞች የተነሳ እና የተፈታ ቅሬታ ሪፖርት አዘጋጅተው የሚልኩበት ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በውስጥ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ድርጅቱ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ፣

231. ድርጅቱ በሚያከናውነው የውስጥ ኦዲት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚመለከተው አካልም የእርምት እርምጃውን ስለመውሰዱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

232. በአዲስ አበባ 4 ሪጅኖች በኢትዮ ቴሌኮም የማስፋፊያ እቅድ መሰረት 404 አዲስ ቆጣሪዎችን ማስገባትና የመስመር ዝረጋታ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ተሰርቶ ብር 62,515,317.00(ስልሳ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ሶስት መቶ አስራ ሰባት ብር) የአገልግሎት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

በ2007 በጀት አመት በተደረገው የውስጥ ኦዲት ሪፓርት ምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ለአስር የከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን በፕሮሚሰሪ ኖት እንደሚከፍሉ ከተሰማሙ በኃላ ከጠቅላላ ሂሳቡ ከብር 1,207,543.49 ውስጥ ብር 434,866.60 ብቻ የተከፈለ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 772,676.89 ክፍያው ያልተፈፀመ መሆኑ፣

በመቀሌ ሪቴል ቢዝነስ የመስቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለሚያከናውነው የማስፋፊያ ስራ ከተጠቀመው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከጠቅላላ ክፍያው ብር 10,120,000.00 ውስጥ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 302888 ብር 9,776,367.28 የተከፈለ ቢሆንም፣ ቀሪ ብር 343,632.72 የአገልግሎት ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑን በውስጥ ኦዲት ሪፖርት ላይ ለማወቅ የተቻለ መሆኑን፣ አገልግሎቱ ጉዳዩን በተመለከተ በመውጫ ሰብሰባ ወቅት ባቀረበው መረጃ እ/ኤ/አ ደብዳቤ ቁጥር ms/636/1/0/17 በቀን 09/03/2017 የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለአገልግሎቱ በጻፈው ደብዳቤ መሰረት ቀሪው ክፍያ በአገልግሎቱ በኩል መሰራት ሲገባው በሲሚንቶ ፋብሪካው በኩል የተሰራ በመሆኑ የዚህን ቀሪ ክፍያ ብር 343,632.72 ተቀናሽ ስለማድረጉ የገለጸ ቢሆንም፣ በፋብሪካው የተሰራ የተባለው ቀሪ ስራ የተገለጸውን ያህል ወጪ ስለማስወጣቱ በአገልግሎቱ በኩል ምንም አይነት ማረጋገጫ ያልቀረበለበት መሆኑ፣

233. በአዲስ አበባ ከተማ ለተከናወነው የቀላል ባቡር ግንባታ ስራ ለሚያስፈልገው የኤሌክትሪክ አገልግሎት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን እና በኢትዮጵያ ቀላል ባቡር ኮርፖሬሽን በኩል በቀረበው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ጥያቄ መሰረት ለጠየቁት ኃይልና መስመር ዝረጋታ በምዕራብ፣ በምስራቅ እና በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅኖች በኩል ለተፈጸመው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር **24,275,656.31** በአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በኩል ያልተከፈለ መሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን በኩል ለተከናወነው የቀላል ባቡር ግንባታ ስራዎች የአገልግሎት ክፍያ ከተጠየቀው ጠቅላላ ሂሳብ ብር 117,001,280.50 ውስጥ ብር 116,755,989.59 ብቻ የተከፈለ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 245,290.91 ያልተከፈለ መሆኑ፣

አዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ለአዲስ አበባ የመንገድ መብራት አገልግሎት በደቡብ፣ በሰሜን እና በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን ከሰኔ 2005

ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 2006 ዓ.ም ያልተከፈለ የመንገድ መብራት ውዝፍ ክፍያ ብር 5,510,232.71 መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም፣ በቀን 13/03/2009 ዓ.ም. ብር 382,974.86 በኢትዮጵያ ምድር ባቡር በኩል ለሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን ገቢ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ በመውጫ ስብሰባ ወቅት የቀረበ ሲሆን፣ ቀሪው የአገልግሎት ክፍያ ብር 5,127,257.85 ስለመከፈሉ የሚያሳይ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

ምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ሪቴል ቢዝነስ የ193 የመንገድ መብራት ቆጣሪዎች ቢል የማይወጣላቸው መሆኑንና በዚህም ምክንያት በድርጅቱ ብር 4,353,610.00 ያልተሰበሰበ የአገልግሎት ክፍያ መኖሩ ፣

በምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን ከ176 የመንገድ መብራት ቆጣሪዎች ላይ 25,891,706 Kw ወይም ብር 12,539,353.00 ያልተሰበሰበ መኖሩ፣

የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች ላይ የማሻሻያ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፣

234. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የማከፋፈያ መስመሮች እና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸው ተጠብቆ የማሻሻያ ስራዎች እንዲሰራላቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

በ15 ሪጅኖች ያሉት የማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸውን ጠብቆ በእቅድ ላይ የተመሰረተ የማሻሻያ ስራዎች ያልተሰራ መሆኑ፣

በ15 ሪጅኖች ያሉት የማከፋፈያ ጣቢያዎች ከደንበኞች ፍላጎት ጋር በተናበበ ሁኔታ አስቀድመው እንዲሻሻሉ አለመደረጉ፣

በአገልግሎቱ ስር ካሉት ትራንስፎርመሮች ውስጥ 40% ያህሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች (አሬስተር እና ድሮፕ አውት ፊውዝ) ባለመኖሩ ምክንያት በ2007 በጀት አመት 1029 ትራንስፎርመሮች በጭነት ምክንያት የተቃጠሉ መሆኑ፣

በተጨማሪም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የተቋሙ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች ኃይል በመቆራረጡ ምክንያት የሚሰጡትን አገልግሎት እንዳይቋረጥ በጄነሬተር ስራው እንዲቀጥል የሚያደረጉ መሆኑን እና ከድርጅቶቹ በጽሁፍ በቀረበው መረጃ መሰረት ከ2006-2008 ዓ.ም. ባሉት የበጀት ዓመታት ለጄነሬተር ያወጡት ወጪ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡-

- ✓ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብር 39,693,639.13፣
- ✓ አባይ ባንክ ሳቢያን ቅርንጫፍ ብር 5984.80፣
- ✓ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ ሐረር ቅርንጫፍ ብር 34,431.85፣
- ✓ ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሐረር ቅርንጫፍ ብር 20,000 ፣
- ✓ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ብር 42,066,737 ፣
- ✓ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል ብር 16,000 ፣
- ✓ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብር 2,557,196.81 ፣
- ✓ ጳውሎስ ሆስፒታል ብር 1,104,666.78 ብር፣
- ✓ ካዲስኮ ሆስፒታል ብር 145,619
- ✓ ሚሲዮኒግ የክርስቲያን ህክምና ማዕከል ብር 1,062,000፣
- ✓ የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብረካ ብር 184,800፣
- ✓ ቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብረካ ብር 218,173፣
- ✓ ኢንተርኮንትኔታል ሆቴል ብር 1,569,658.70፣
- ✓ ጊዮን ሆቴል ብር1,381793.05 ፤
- ✓ የኢትዮጵያ ሆቴል ብር 204,620.00 እና
- ✓ ኢሊሊ ሆቴል ብር 344,220 መሆኑን ከቀረበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞችን በተቀመጠው ስታንደርድ ማስተናገዱን በተመለከተ፣

235. የድርጅቱ የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞች የኃይል መቋረጥ ካመለከቱበት ጊዜ አንስቶ በ4 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በናሙና ከታዩት አራት ሪጅኖች አስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞችን በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት የማያስተናግዱ መሆኑን የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ መልስ የሰጡ መሆኑን፤

236. የኦዲት ቡድኑ መረጃ ከሰበሰበባቸው በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የድርጅቱ ከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች (ማለትም 6 በሆቴል አገልግሎት የተሰማሩ፤8 ባንኮች፤ 4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፤ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች እና 1 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ኃይል በሚቋረጥበት ወቅት በስታንደርዱ መሰረት ምላሽ የሚሰጥበት ሁኔታ አለመኖሩን ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ መልስ የሰጡ መሆኑን፤

237. በድሬደዋ የምግብ ካምፕሌክስ የሚመረቱት ምርቶች ዳቦ፣ ማካሮንና ፓስታ እየተመረቱ ባለበት ሁኔታ ኃይል ተቋርጦ የድሬደዋ የጥገና ክፍል አፋጣኝ ምላሽ ባለመስጠቱ ምክንያት ምርቶቹ በመበላሸታቸው ድርጅቱ ብር 36,288,522.51 ኪሳራ እንደደረሰበትና፤ በተመሳሳይ ሁኔታ የድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በኃይል መቆራረጥ አፋጣኝ የጥገና አገልግሎት ባለማግኘታቸው ምክንያት የደረሰ ኪሳራ ብር 12,224,293.73 መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ቀርቦ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ መተሳሰርን በተመለከተ፣

238. በድርጅቱ ስር የሚገኙት የአስቸኳይ ጊዜ የጥሪ ማዕከላት እና የአስቸኳይጊዜ ጥገና ክፍል በመረጃ ኔትወርክ ሊተሳሰሩ ይገባል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ማዕከል ከአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል የሚገናኙበት የመረጃ ማስተላለፊያ ስርዓቱ ፈጣንና ቀልጣፋ ባለመሆኑ ጥሪዎቹ ወደ አስቸኳይ ጥገና ማዕከላት መተላለፋቸውንና መስመሩ መስራት አለመሰራቱን ደንበኞች የሚያውቁበት መንገድ የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

239. ከአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ማእከላት ወደ አስቸኳይ ጥገና ክፍል የሚመጣውን ቅሬታ ምን ያህሉ እንደተፈታና ምን ያህሉ ደግሞ እንዳልተፈታ የሚያሳይ ሪፖርት ሲስተሙ የማያወጣ መሆኑን፣ እንዲሁም በአስቸኳይ ጥገና ስራ በምን መንገድ እየተሰራ መሆኑን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና አመታዊ የተዘጋጀ ሪፓርት ያለመኖሩን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩት የሰሜን እና የደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን የአስቸኳይ ጊዜ የጥገና ክፍል በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ (ኮምፒውተሮች) ያልተሟሉበት ሁኔታ መኖሩን፤ ከጥሪ ማዕከላትም ሆነ በአካል ደንበኞች መጥተው የሚያስመዘግቡት ቅሬታዎች የተፈቱ ስለመሆኑ እና ያልተፈቱም ከሆነ ያልተፈቱበት ምክንያት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የማይመዘገብ መሆኑን በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

16. <u>የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር እና ቁጥጥር አፈፃፀምን በተመለከተ</u>

240. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያዘጋጅና ሊሰጥ፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀቱን ሊያድስ፣ ሊያግድና ሊሰርዝ ይገባል፡፡

241. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ቢሰጥም፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር

ወረቀታቸውን ባለማደሱ፣ ባለማገዱ እና ባለመሰረዙ 3 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች በወቅቱ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የተገኙ መሆኑ፣

242. እንዲሁም 6ቱ ደግሞ በቅጣት እድሳት የሚፈፅሙበት ጊዜ ያለፈ ቢሆንም ባለስልጣኑ እድሳት የፈፀመላቸው መሆኑ በተጨማሪም 7 መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጭ ድርጅቶች የፈቃድ እድሳት ክፍያ አለማከናወናቸውና 3ቱ የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች ደግሞ ፈቃድ ያወጡበት የአገልግሎት ክፍያ ያልፈፀሙ መሆኑ፣

- ሌሎች 3 የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች እና 5 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደግሞ እድሳት እንዳላከናወኑና ባለማሳደሳቸውም እንደተሰረዙ ይቆጠራሉ በማለት በባለስልጣኑ የወሰደው እርምጃ የሌለ ሲሆን ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በኦዲቱ ወቅት ሲሰራ የተገኘ ድርጅት መኖሩ፣
- ከዚህም ሌላ 3 የእንስሳት መኖ አምራች / ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የማምረት አቅማቸው ከፍተኛ ቢሆንም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ እንዳልወሰዱ እንዲሁም 2 የመድኃኒትና የክትባት አምራች ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይሰጣቸው እየሰሩ መሆኑ፤

243. ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ሊመዘግብ እና ሊቆጣጠር፣በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች ፣ እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ሊመዘግብ፣ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ሊያድስ፣ ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት በየ5 ዓመቱ ሊያዲስ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 3 የእንስሳት መድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ 3ቱም ድርጅቶች አስገምግመው ሳያስመዘግቡ ተመርተው የሚሸጡ መድኃኒቶች መኖራቸው እንዲሁም በአንድ

አስመጪ እና በአንድ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ያልተመዘገበ መድኃኒት ሲሸጥ መገኘቱ በተጨማሪም በ3 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ድርጅት ውስጥ በተደረገው ድንገተኛ ኢንስፔክሽን በባለስልጣን መስሪያቤቱ ያልተመዘገበ መድኃኒት የተገኘ መሆኑ ከዚህም በተጨማሪ 5 ድርጅቶች በባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችን ሳያስመዘግቡ ከውጭ ሀገር ያስመጡ ቢሆንም በድርጅቶቹ ላይ ምንም ዓይነት የፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛ አለመደረጉ፣

- በተጨማሪም ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በክፊል በየ5ዓመቱ ቢያድስም በራሱ የምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀትና አፀድቆ እየሰራበት አለመሆኑ እና በቀድሞ ጊዜ በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የሚሰራ ቢሆንም በተሟላ መልኩ በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት የማይሰራ መሆኑ፣
- ከባለስልጣን መ/ቤቱ በእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪነት ፈቃድ ከወሰዱ እና እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም በባለስልጣኑ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ከተካተቱ ወደ 30 ከሚሆኑ ድርጅቶች ውስጥ 16 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪ ድርጅቶች የመድኃኒት ሴሪትፍኬት ጊዜያቸው አብቅቶ ለዕድሳት በሂደት ላይ ያሉ 63 ዓይነት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም መድኃኒቶች የሴሪትፊኬት ጊዜያቸው ካበቃ ከ5 ወር እስከ 6ዓመት ቢሆንም ጊዜያዊ ሴሪትፍኬት እስኪሰጣቸው ድረስ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር አስገብተው በመሸጥ ላይ እንደነበሩ እና በኦዲቱ ወቅትም በመሸጥ ላይ መሆናቸውና ሌሎች ደግሞ እድሳት ቢያደርጉም የመድኃኒቶቹ ናሙና በላብራቶሪ ታይቶ አለመሆኑ ፡፡

244. ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣ መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ ይገባል፡፡

245. ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ያላዘጋጀ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ያልመደበ መሆኑ ፣

246. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

247. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት በተሟላ መልኩ ስልጠና አለመስጠቱ እና በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 12 የመድኃኒት አስመጪ፣6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና 3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ ለ7 መድኃኒት አስመጪ፣ ለ1 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት እና ለ3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች እንዲሁም በመድኃኒት አያያዝና አከመቻቸት እንዲሁም አጓጓዝ ዙሪያ ስልጠና እንዳልተሰጣቸው እንዲሁም በናሙና ለታዩት ለ 5 መኖ አምራች እና ለ2 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝን አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ሰጥቷቸው የማያውቅ መሆኑ፤

248. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

249. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተሟላ መልኩ በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣

ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት በወቅቱ ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

250. ባለስልጣኑ ከውጭ ሀገር መድኃኒት ለሚያስገቡ ለ21 እንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ ለ280 ዓይነት መድኃኒቶች ጊዜያዊ ፈቃድ በመስጠት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረጉና ይህም ጉዳይ ኦዲቱ እስከተጠነቀቀበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ መሆኑ፡፡.

251. ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማድረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊፈቅድ ይገባል፡፡

ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ያላደረገ መሆኑ፡፡

252. ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተስራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተስራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 15የመድኃኒት አስመጪና አምራች ድርጅቶች ውስጥ 15ቱም ድርጅቶች የእንስሳት መድኃኒት በባለስልጣኑ ያስመዘገቡ ቢሆንም ባለስልጣኑ መድኃኒቶቹ ከተሰራጩ በኃላ ምንም ዓይነት የድህረ ገበያ ጥናት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና ድርጅቶቹም የፋርማኮቪጅላንስ ማስረጃም ለባለስልጣኑ አቅርበው የማያውቁና ባለስልጣኑም ጠይቋቸው የማያቅ መሆኑ፣

253. ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች አወጋገድን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎና አከባቢን በማይበክል መንገድ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት የታዩት 5 የእንስሳት መድኃኒቶች አስመጪ፣ 1ጅምላ አከፋፋይ እና 2 አምራች ድርጅቶች መጋዘን ውስጥ ከ2006 ዓም ጅምሮ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆኑ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በቁጥጥር ጊዜ ቢያዩም በተጨማሪም ፎርም ቀርፀው በዝርዝር አሳውቁን ብለው ያሳወቁአቸው ቢሆንም ባለስልጣኑ የአወጋገድ መመሪያ እስኪያወጣ ድረስ ተለይተው እንዲቀመጡ ከማድረግ ውጭ

በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ አለመደረጉ እንዲሁም ፡በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 7 የመኖ አምራች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ 3ቱ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ንጥረ-ነገር እና መኖ ያላቸው ሲሆኑ እንዲሁም 4 ድርጅቶች ያስወገዱበት ሁኔታ ቢኖርም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ባለስልጣኑ ያልተቆጣጠረ መሆኑ ፡፡

254. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች እንዲሁም የእንስሳት መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች እና የእንስሳት መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብና ተከታትሎ በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲውል ያላደረገ መሆኑ፡፡

255. ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ መኖ በባለስልጣኑ የተሰጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት፡፡

ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ አውጥተውና ሳያወጡ በተደጋጋሚ መኖና የመኖ ግብዓት ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ለእንስሳት መኖዎች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት እንዳልጀመረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

256. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ እና መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ ሊይዝ እንዲሁም ባለስልጣኑ ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

257. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ያልዘረጋ እና

መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ የማይዝ መሆኑ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፡፡

258. በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 12 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ከ6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች፣ከ3 አምራች ድርጅቶች ውስጥ 6መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች 3ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር የእንስሳት መድኃኒትን እና የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ የሚኖሩትን ወቅታዊ መረጃዎች የሚለዋወጥበት ስርዓት የሌለው መሆኑ፡፡

259. ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን ሊከታተል ይገባል፡፡

260. ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች መድኃኒትን በተመለከተ ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን በተሟላ መልኩ እንደማይከታተልና መኖን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ የማይከታተል መሆኑ፡፡

261. ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፣ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

262. ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፣ መከማቸቱንና መጓጓዙን በተሟላ መልኩ እየተቆጣጠረ እንደማይገኝ ታውቋል፡፡

263. በኦዲቱ ወቅት የታዩት ሁሉም የመኖ አምራች ድርጅቶች ማለትም 9ኙም መኖን ለማምረት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የመኖ ግብዓቶች ከተገኘበት ቦታ ሁሉ በመግዛት መኖ የሚያመርቱ ቢሆንም የመኖ

ድህንነትንና ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲያስችል አምራቾች ጥራቱን የተጠበቀ የመኖ ግብዓት ስለመጠቀማቸው እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች/ግለሰቦች/ ድህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ስለማቅረባቸው እና የመኖ አምራች ድርጅቶችም ደህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ከታወቀ ድርጅት ስለመግዛታቸው ባለስልጣኑ ክትትል እያደረገ አለመሆኑ

264. ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ ተጠንቶ የጥናቱ ሪፖርት የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ከግብዓት አቅራቢዎች ጀምሮ ወጥነትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ባለመስራቱ መነሻው ፈንገስ ወይም ሻጋታ የሆነ አፍላቶክሲን የተባለ መርዛማ ኬሚካል በወተት ላይ እንደተፈጠረ ማሳየቱ እንዲሁም ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር በማያያዝ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ዙሪያ ስራውን መስራት ባለመቻሉ ይህ አፍላቶክሲን የተባለው መርዛማ ኬሚካል ሊከሰት እንደቻለ፣በተጨማሪም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መኖ እና የወተት ናሙና ተወስዶ ሁሉም ናሙናዎች በአፍላቶክስን እንደተጠቁ ጥናቱ እንደሚያሳይ በተለይም ደግሞ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ችግሩ እንደከፋና ወተት ላይ የታየውም ምንጩ የሚመገቡት መኖ እንደሆነ በጥቅምት/2008ዓ.ም ለባለስልጣኑ ያሳወቀ መሆኑ፣

265. ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ ለሚያከፋፍሉ፣ ለሚያስተዋውቁ፣ መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡና ወደ ውጭ የሚልኩ አካላትን እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን ሊቆጣጠር እና በተቆጣጠረውም ላይ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡

266. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 12 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ 6 ጅምላ አከፋፋዮች፣3የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች እንዲሁም 6 መኖ አምራች ድርጅቶች እና 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ውስጥ 10 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ

ድርጅቶች ፣ 2 የመድኃኒት አምራቾች   እንዲሁም 6 የመኖ አምራች ድርጅቶችና 2የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ባለስልጣኑ ቁጥጥር ቢያደርግባቸውም በየዓመቱ ለቅድመ ፈቃድ እድሳት ቁጥጥር እንደሆነና አልፎ አልፎም የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በራሳቸው ፕሮግራም ሳያሳውቁ ድርጅቶቹ ድረስ በመምጣት ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግም መደበኛ በሆነ መልኩ የማያደርግ እና በተቆጣጠረውም መሰረት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

17. **<u>በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት መርሐ ግብርና የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በማንዋሉ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲያቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣</u>**

267. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የታቀዱ ውጤቶችና ግቦች መሳካታቸውን ለመደበኛ እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመከታተል በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ባለበጀት መ/ቤቶች የድርጊት መርሐ ግብራቸውንና የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

268. በወቅቱ መርሃ ግብራቸውንም ሆነ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን የማያቀርቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣ የተሟላ ሪፖርት የማያቀርቡ ማለትም በፋይንሻል አፈጻጸም ላይ ብቻ የተመሰረተ ሪፖርት /የፊዚካል እና የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡ/ የሚያቀርቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣ እንዲሁም የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል ገጽ 73 ላይ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተዘጋጀው መርሃ-ግብር መሠረት የየሩብ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት መዘጋጀት እንደሚኖርበት የሚገልጽ ቢሆንም ከመርሐ ግብሩ ውጭ ወይም መርሃ ግብርን መሰረት ያላደረገ ሪፖርት የሚያቀርቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣

269. በ2008 ዓ.ም. አብዛኛው መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈፃፀም ሪፖርት የክትትል ዓላማን የማያሟላ/ማለትም የፊዚካል

አፈጻጸም የቀረበላቸውም በአብዛኛው በሪፖርቱ የተጠቀሰው የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እንጂ የውጤቶች እና የፕሮጀክቶች አፈፃፀም አለመሆኑ፣

የፕሮግራም በጀትን ተግባራዊ ያደረጉ ባለበጀት መ/ቤቶች በመርሃ ግብራቸውመሠረት ሥራ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤

270. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለበጀት መ/ቤቶች የታቀዱት ግቦች የደረሱበት ደረጀና አፈጻጸም ካስቀመጡት መርሃ ግብር አንጻር በየጊዜው ክትትል በማድረግ እና በተገኙ ልዩነቶች ላይ በወቅቱ ማሻሻያ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

271. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመ/ቤቶችን አፈጻጸም የሚከታተለው በሪፖርት ሲሆን ከ2006-2008 ዓ.ም. በየሩብ ዓመቱ የመ/ቤቶችን ሪፖርት ግምገማ ማካሄድ ቢኖርበትም በ2006 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 53 በሁለተኛ ሩብ ዓመት 45 ባለጀበት መ/ቤቶች፣ በ2007 ዓ.ም. የመጀመሪያና ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶች በመኖራቸው ከ155 ባለበጀት መ/ቤቶች በተከታታይ የ55 እና የ47 መ/ቤቶች እና በ2008 ዓ.ም ከ165 ባለበጀት መ/ቤቶች ውስጥ የ41 መ/ቤቶች አፈጻጸማቸው ላይ ግምገማ ያልተደረገባቸው ሲሆን በሦስቱም በጀት ዓመት የሦስተኛ ሩብ ዓመት ማለትም የ9 ወር የመ/ቤቶች አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት በወቅቱ አለመዘጋጀቱ፣

272. በተጨማሪም አፈጻጸማቸው የተገመገመ መ/ቤቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጽሁፍ ግብረ መልስ አለመሰጠቱ እና መ/ቤቶችን ተጠያቂ ከማድረግ አንጻር የግምገማ ውጤት ለውስጥ አሰራር ከመጠቀም ውጭ ለሚንስትሮች ምክር ቤት የማይቀርብ መሆኑ፣

273. በናሙና በታዩት ባለበጀት መ/ቤቶች/ትምህርት ሚኒስቴር፣ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ፣ ሀዋሳ፣ ዲላና አዳማ ዩኒቨርስቲዎች/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ

ከመርሐ ግብር አንጻር አፈጻጸማቸው እየተገመገመ ባለው ልዩነት ላይ በቃል እንጂ በዝርዝርና በጥልቀት በጽሑፍ ግብረ መልስ የማይሰጣቸው መሆኑን፤ በቃል የሚነገራቸውም ግብረ መልስ አልፎ አልፎ እንጂ ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመሆኑንና በመርሐ ግብሩ መሰረት መሄዳቸው ያለው የክትትል ሥርዓት ዝቅተኛ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መቤቱ መ/ቤቶችን የመስክ ጉብኝት •እና ቅኝት ለማድረግ መርሃ ግብር በማዘጋጀት በመርሃግብሩ መሰረት መከታተሉን በተመለከተ፤

274. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸምን አስመልክቶ ወቅታዊነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ በድንገት ወይም በተወሰነ ጊዜ ክትትል ለማድረግ መርሃ ግብር ሊያዘጋጅና በመርሃግብሩ መሰረትም ጉብኝት •እና ቅኝት በማድረግ ሊከታተል፣ በወቅቱ የታዩ የአሠራር ድክመቶችና ጥንካሬዎች በመለየት የእርምት እምርጃዎችን ሊወስድና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

275. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006 እና በ2007 ዓ.ም. የድርጊት መርሃ ግብር ያላዘጋጀ ሲሆን በ2006 ዓ.ም. የመስክ ክትትል ስለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ አልተገኘም፡፡ በ2007 በጀት ዓመት ከ155 ባለበጀት መ/ቤቶች በሦስቱ ማለትም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከ250 ፕሮጀክቶች በ9ኙ /.04%/፣ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ከ50 ፕሮጀክቶች ውስጥ በመስኖ ግድቦች በሁለቱ ላይ /.04%/፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ10 ፕሮጀክቶች ውስጥ በሦስቱ 30% ላይ ብቻ የመስክ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ2007 ዓ.ም. በፊትም ሆነ በኋላ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስክ ጉብኝት አልተደረገም፡፡

276. በ2008 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ተግባራዊ ካደረጉ 165 ተቋማት በ5ቱ ላይ ብቻ ማለትም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ፣ በግብርና ዘርፍ፣ በፌዴራል ፖሊስ፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር /በመስኖ

ግድቦች ግንባታ ላይ/ በጠቅላላው 23 ፕሮጀክቶች ለማየት የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጀ ቢሆንም በመርሐ ግብር ከያዛቸው ከአምስቱ በሦስቱ መ/ቤቶች አምስት ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ የመስክ ክትትል ያደረገ ሲሆን የመስክ ጉብኝት ካደረገባቸው ተቋማት ካላቸው የፕሮጀክቶች ብዛት አንጻር አፈጻጸሙ ሲገመገም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ካሉት 250 ፕሮጀክቶች በሁለቱ /.008%/ ላይ ብቻ፣ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ካሉት 50 ፕሮጀክቶች በሁለቱ /.04%/ላይ ብቻ፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ካሉት 4 ፕሮጀክቶች በአንዱ/25%/ ላይ ብቻ የመስክ ጉብኝት ያደረገ ሲሆን በተቀሩት መ/ቤቶች ግን ትኩረት ሰጥቶ የመስክ ጉብኝት አያደርግም፡፡

<u>**የፕሮጀክቶች አፈጻጸም መ/ቤቶቹ ባቀረቡት መርሐ ግብር መሰረት መሆኑን በተመለከተ፤**</u>

277. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባለበጀት መ/ቤቶች ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ማለቃቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በፌዴራል ደረጃ መንግስት ከፍተኛ በጀት የሚመድበው በካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በመርሐ ግብራቸው መሰረት ያለው የክትትል ሥራ አነስተኛ በመሆኑ በናሙና ከታዩት የ8 መ/ቤቶች (የአዲስ አበባ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የዲላ ዩኒቨርስቲዎች፣ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የመንገዶች ባለስልጣን፣ የማረሚያ ቤቶች እና የትምህርት ሚኒስቴር) ፕሮጀክቶች በመርሐ ግብራቸው መሰረት ስለማለቃቸው በተደረገ የኦዲት ምርመራ፡-

- መንገዶች ባለስልጣን በመጀመሪያው የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሊሰሩ የታሰቡ ከ20 በላይ ፕሮጀክቶች ወደ 2008 ዓ.ም. በመሸጋገራቸውና ነባር ፕሮጀክቶች በመኖራቸው ምክንያት አዲስ ፕሮጀክት አለመጀመሩ፣ በተጨማሪም በናሙና ከታዩት ሦስት ፕሮግራሞች ውስጥ የዋና መንገዶች ማጠናከር ፕሮግራም ካሉት 12 ፕሮጀክት 7ቱ በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ ሲሆን ሁለቱ በ2005፣ ሁለቱ በ2006፣ ሦስቱ ደግሞ በታህሳስ፣ በሰኔና በሐምሌ 2007 ዓ.ም.

መጠናቀቅ የነበረባቸው ቢሆንም ከአንድ እስከ ሦስት አመት ዘግይተው በ2008 ዓ.ም. መጠናቀቃቸው፣

- እንዲሁም የዋና መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ፕሮግራምን በተመለከተ ካሉት 9 ፕሮጀክቶች ውስጥ አምስቱ ሐዋሳ ጭኮና ይርጋ ጨፌ፣ ይርጋጨፌ ሀገረማርያም፣ በደሌ - መቱ/ሎት 1/ እና በደሌ - መቱ/ሎት 2/ የካቲትና ሚያዚያ 2008 ዓ.ም. ማለቅ ቢገባቸውም አፈጻጸማቸው ግን ደካማ /50% በታች/መሆኑ፣
- አገናኝ መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ፕሮግራም በተመለከተ 51 ፕሮጀክቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በ2008 በጀት ዓመት ከተጠናቀቁት 14 ፕሮጀክቶች 11ዱ በወቅቱ ያልተጠናቀቁ ሲሆን ከሰኔ 2006-ሚያዚያ 2007 በተለያየ ወር ማለቅ የሚገባቸው ቢሆንም በ2008 መጠናቀቃቸው፣
- በዲላ ዩኒቨርስቲ ካሉት 28 ፕሮጀክቶች ውስጥ አሥራ ዘጠኙ /68/ በመቶ በተያዘላቸው ጊዜ ያላለቁ ሲሆን ከተገለጹት ውስጥ በ2008 ዓ.ም በመጠናቀቅ ላይ ካሉትና ከ80 በመቶ በላይ አፈጻጸም ያሳዩት የተማሪዎች ማደሪያ፣ ካፍቴሪያ፣ መማሪያ መጋዘን እና የምድረ ግቢ ሥራ በ2002 ዓ.ም.፣ የአጥር ግንባታ በ2006 ዓ.ም.፣ የተማሪዎች የሰራተኞችና የመምህራን የመማሪያና የማደሪያ ብሎኮች በ2006 ዓ.ም.፣ የትሪትመንት ፕላንት እና የተማሪዎች ማደሪያ ካፍቴሪያ በ2007 ማለቅ ቢኖርባቸውም ከ1 እስከ 5 አመት ቆይተው በ2008 ዓ.ም. መጠናቀቅ ላይ መድረሳቸው፣
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ካሉት አስር ፕሮጀክቶች ዘጠኙ ፕሮጀክት በጊዜ ሰሌዳቸው መሠረት ያልተጠናቀቁ መሆኑ እና በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በናሙና ከታዩት 41 ፕሮጀክቶች ውስጥ 34 የሚሆኑ ፕሮጀክቶች በመርሐ ግብሩ መሰረት ያልተጠናቀቁ መሆናቸው፣
- በተጨማሪም በውሃ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ከመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልገሎት አሰጣጥ አንፃር ከፍተኛ ግብ የተጣለባቸውና ከፍተኛ በጀት

የተመደበላቸው የመስኖ ልማት፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የውሃ ሀብት አስተዳደርና የኢነርጂ ልማት ኘሮግራሞች ከተቀመጠው መርሃ ግብር አንጻር ካሉት 50 ኘሮጀክቶች ሃምሳውም ፕሮጀክቶች በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት ያልተጠናቀቁ እና ከዚህ ውስጥ 17 ፕሮጀክቶች ፊስካል አፈፃፃማቸው ከ50% በታች መሆኑ፣

278. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመለከታቸው መ/ቤቶች የሚቋረጡ ኘሮጀክቶች መኖራቸው፣ ከነዚህም ውስጥ፤

- በአዳማ ዩኒቨርስቲ በሐብታሙ ኢንተርናሽናል የንድፍና ምህንድስና ምክር አገልግሎት ኃላፊነቱ የተ.የግ.ማህበር የሚገነቡ የስብሰባ አዳራሽ፣ የማዕከላዊ አስተዳደር ህንፃዎችና የስፖርት አካዳሚ ኘሮጀክቶች ሰኔ 2005 ዓ.ም. ተጀምረው ሰኔ 2008 ዓ.ም. የሚጠናቀቁ እና ፊዚካል አፈጻጸማቸውም 74 በመቶ ቢሆንም የሥራ ተቋራጩ በገባቸው ውሎች መሰረት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱና ከውሉ ውጭ ተጨማሪ ብር በመጠየቁ በሐምሌ ወር የግንባታ ሥራው እንዲቋረጥ መደረጉ፣
- እንዲሁም የአሰላ የጤና ሳይንስ መማሪያ አዳራሽ፣ የላብራቶሪ ህንጻዎች ኘሮጀክትና የአሰላ 1ኛ ደ/ት/ቤት የተጨማሪ መማሪያ ክፍሎች ግንባታ በሰኔ 2004 ተጀምሮ መስከረም 2007 መጠናቀቅ ቢኖርበትም እስከ 2008 በጀት አመት ያልተጠናቀቀ፣ ለመገንባት ውል የገቡ ተቋራጮች በውላቸው መሰረት ባለመስራታቸውና በታቀደው ጊዜ መሰረት ሥራቸውን ባለማገባደዳቸው ኘሮጀክቶቹ መቋረጣቸው፣
- በተመሳሳይ መልኩ በዲላ የኮንዶሚኒየም እና የምድረ ግቢ ሥራ ብር 18,768,263.04 የተመደበ እና በ8/8/07 ተጀምሮ በ20/03/08 የሚያልቅ ሲሆን እስከ ሚያዚያ 8/2008 ያላለቀና 35 በመቶ ብቻ አፈጻጸም ያለው ወይም ከ13 ብሎክ ውስጥ 3 ብሎክ ብቻ የተሰራና የኦዲት ቡድኑ ለኦዲት በሄደበት ወቅት ኮንትራክተሩ ማህበራዊ ችግር አጋጥሞታል በሚል ሥራው መቆሙ፣ በተጨማሪም 5 ኪ.ሜ. ዩኒቨርስቲዎችን የሚያገናኝ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ ሥራ ብር

93,715,287.47 የተመደበለት ቢሆንም ለ8 ወር ወደ ሥራ መግባት አለመቻሉ፣

- መንገዶች ባለሥልጣን የዋና መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ፕሮግራም ውስጥ ሁለት ፕሮጀክቶች መካከል ሐዋሳ ጭኮ 66 ኪሎ ሜትር መንገድ፣ ሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ተጀምሮ በሚያዝያ 2008 መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም. የፊዚካል አፈጻጸሙ 23.5 ሲሆን የኦዲት ቡድኑ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመገምገም በተንቀሳቀሰበት በሐምሌ/2008 ዓ.ም. ሥራው እንዲቋረጥ መደረጉ፣
- በተመሳሳይ ጭኮ ይርጋ ጨፌ ፕሮጀክት በሚያዝያ 2005 ዓ.ም ተጀምሮ በሚያዝያ 2008 ዓ.ም. ማለቅ የሚገባው ቢሆንም እስከ 2008 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ 24.3 ከመሆኑም በላይ ሥራው መቋረጡ፣

<u>የፕሮግሞች ውጤት ከግብ ስኬት አንጻር መገምገሙን በተመለከተ፤</u>

279. ሚኒስትር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት ዘመን ከተጣለው የግብ ስኬት አንጻር በእያንዳንዱ የፕሮግራም በጀት ዓመት የተገኘው ዓመታዊ የግብ ስኬት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም ይኖርበታል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ማንዋል መሰረት በእያንዳንዱ የፕሮግራም በጀት ዓመት የተገኘው ዓመታዊ የግብ ስኬት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም ቢኖርበትም በየዓመቱም ሆነ በየሦስት ዓመቱ /ከ2004-2006 በጀት ዓመት/ የመ/ቤቶች ፕሮግራሞች ከግብ ስኬትና ከመጀመሪያው ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንጻር ያመጡት ውጤት አለመገምገሙ፣

በመ/ቤቶች ከፕሮግራም ወደ ፕሮግራም የሚደረግ የበጀት ዝውውር አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

280. በፕሮግራሞች ወይም በፕሮጀክቶች እና በመደበኛ ዋና ተግባራት መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና በፋይናስ ደንብ እንዲሁም በፕሮግራም በጀት የበጀት ዝውውር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡

281. በፋይናንስ የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10/1-ሐ ላይ አንድ የመንግሥት መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል በጀት በሥራ ኘሮግራሙ መሠረት የማይጠቀምበት ሆኖ መገኘቱ ሲያረጋግጥ እጥረት ወዳለበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ማዘዋወር ይችላል የሚልና ዝውውር የሚደረግ ቢሆንም መ/ቤቶች የያዙትን በጀት ያልተጠቀሙበትን ምክንያት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይጠየቅ፣ የመ/ቤቶች የዕቅድ ክፍተት መኖሩን እና ለማይሰሩት ሥራ በጀት መያዛቸውን የሚያሳይ እንዲሁም በጀት የተያዘባቸው የኘሮግራሞች ውጤት ላይ የሚያመጣው ክፍተት የኘሮግራም በጀት መርህን /በጀትን ከውጤት ጋር ማስተሳሰር/ የሚጻረር ሲሆን ለማሳያ ያህል፤

- ሰኔ 13 ቀን 2008 ዓ.ም. ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከተቀናጀ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር ኢንፎርሜሽን ኘሮጀክት ከተያዘው በጀት በጠቅላላ ብር 27,907,119.82 /ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባት ሺ አንድ መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም/ለዲላ ዩኒቨርስቲ ለመኖሪያ ሕንጻዎች ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት ግንባታ ዝውውር የተደረገ ቢሆንም ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ለምን ኘሮጀክቱ እንዳልተፈጸመ የተገለጸ ማብራሪያ አለመኖሩ፣ በተመሳሳይ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከዲጂታል ቴሌቪዥን ስርጭት ኘሮጀክት ከተያዘው ብር 30,742,788.75 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለፈርኒቸር፣ ለቁሳቁስና ተገጣጣሚ ዕቃዎች መግዣ በ15/9/08 መዞሩ፡

- በተጨማሪም በትምህርት ሚኒስቴር በ2007 በጀት ዓመት ለአፍሪካ አቅም ግንባታ ኢንስቲትዩት ፕሮጀክት ግንባታ ብር 51,153,091 ሚሊዮን /ሃምሳ አንድ ሚሊዮን መቶ ሃምሳ ሦስት ሺ ዘጠና አንድ ብር/ለግንባታው አቅዶ የያዘ ቢሆንም ጨረታው ዘግይቶ ግንቦት መጨረሻ ወር ላይ በመውጣቱ ምክንያት በጀት ዓመቱ አለቀ በሚል ሃሳብ ለፕሮጀክቱ የተመደበውን ገንዘብ ወደ ሌላ ፕሮጀክት ዝውውር መደረጉና ይህም በተያዘው ኘሮግራም መሠረት ሥራዎች

አለመከናወናቸውን ከውጤት አንጻር ለመመዘን የማያስችል ሲሆን ይህ ፕሮጀክት በ2008 በጀት ዓመትም አፈጻጸሙ እጅግ አዝጋሚና 0.3% መሆኑ፤

282. በዚሁ መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10/3-ለ ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ በዝርዝር በመሙላት በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፊርማ በማረጋገጥ ከበቂ ማብራሪያና ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መያያዙን መረጋገጥ አለበት ቢልም ከመጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ጋር ማብራሪያና ደጋፊ ማስረጃ አለመያያዙን ከተከለሱ የመ/ቤቶች ማህደር ለማየት የተቻለ ሲሆን ከአንድ ፕሮግራም ወደ ሌላ ፕሮግራም የበጀት ዝውውር በተለያዩ ወጪ መደቦች መካከል በስፋት የሚያደርጉ መ/ቤቶች በመኖራቸው በውጤቶች፣ በዋና ዋና መደበኛ ተግባራት ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ በአግባቡ አለመታየቱ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህ አሰራር በፕሮግራም ወይም በውጤት ላይ የተመሰረተ አሰራር አለመኖሩን አመላካች ነው፡፡ ለአብነት ያህል፡-

- በፕሮግራም በጀት መሰረት የተፈቀደው በጀት ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ ሳይውል ዝውውር የሚከናወን ሲሆን፤
- በኦዲቱ በታዩት በዲላ በጀት በጸደቀ በ23ተኛው ቀን ማለትም በ23/11/2007 ከበላይ አመራር ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፣ ከመማር ማስተማር እንዲሁም ከምርምርና ስርፀት ጽ/ቤት ለፕላንት ማሽነሪ መሣሪያዎች መግዣ በጠቅላላው ብር 82,906,605/ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስድስት ሺህ ከስድስት መቶ አምስት ብር/፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በ17/12/2008 ዓ.ም. ከመኖሪያ ሕንፃዎች ግንባታ ወደ ኮንትራት ሠራተኞች አበል እና ለጭነትና በጀት ላልተመደበለት የወጪ መደብ፣ ለኮንትራት ሰራተኞች አበል፣ ለኪራይ ብር 4,417,047.00/አራት ሚሊዮን አራት መቶ አሥራ ሰባት ሺህ ከአርባ ሰባት/፣
- የውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በነሐሴ 24 ቀን 2008 ዓ.ም. ከመሰረተ ልማት ግንባታ መኖሪያ ያልሆኑ ህንጻዎች ግንባታ ብር

56,028,000.00 /ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ሃያ ስምንት ሺህ ብር/ ዝውውር መደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- እንዲሁም በአመቱ መጨረሻ የበጀት ዓመቱ ማለቂያ አንድ ወር ሲቀረው የበጀት ዝውውር የሚደረግ ሲሆን፣
  - በኦዲቱ ወቅት ከታዩት በትምህርት ሚኒስቴር በ2008 በጀት ዓመት ከሰኔ 13/08-27/08 ድረስ ከቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልገሎት፣ ከሕንፃ ቁሳቁስ እና ከተገጣጣሚዎች መግዣ፣ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ፣ ከደን እና ለባህር ግብዓቶች ክፍያ፣ ወደ ለደንብ ልብስ፣ ለፍራሽና አልጋ ልብስ፣ ለሕንፃ ለቁሳቁስ እና ለተገጣጣሚዎች፣ ለአላቂና የቢሮ ዕቃዎች መግዣ፣ ለተሽከርካሪ እና ለሌሎች መጓጓዣዎች ዕድሳት እና ጥገና፣ ለተለያዩ ክፍያዎች ለመስተንግዶ አጠቃላይ ብር 30,235,261.45 /ሰላሳ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/፣
  - እንዲሁም በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ከግንቦት 15 እስከ ሰኔ 29 ቀን ባሉት የተለያዩ ቀናት ውስጥ በ2008 ዓ.ም. ብር 28,116,891/ሃያ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ አሥራ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር/፣ በ2007 በጀት ዓመት 79,114,843/ሰባ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ አሥራ አራት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሦስት ብር/፣ በ2006 በጀት ዓመት 2,263,205.57 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ አምስት ብር ከሃምሳ ሰባት ሳንቲም/ የበጀት ዝውውር ያደረጉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ዝውውሩ የተደረገው ከደሞዝና የሥራ ማስኬጃ መጠባበቂያ ለደንብ ልብስ/ሰኔ 29/፣ ለቀን ሰራተኛ ክፍያ፣ ለጡረታ መዋጮ ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታ፣ መዋጮና ድጎማ እና ለቋሚ ሰራተኞች ደሞዝና መዋጮ ዝውውር መደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም ዓመቱን ሙሉ የበጀት ዝውውር የሚያደርጉ መ/ቤቶች /የከተማ ልማትና መ/ቤቶች፣ የጤና ጥበቃና ውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር መ/ቤቶች/ያሉ ሲሆን ይህ ደግሞ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል መሆኑ፣

  ዝውውሮቹ ከላይ ባየነው መመሪያ መሰረት ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በስተቀር ደጋፊ ሰነድ ወይም ማብራሪያ አብሮ አልተያያዘም፡፡

ሚኒስትር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡

283. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀትን በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም.ጀምሮ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በሁሉም ክልል ፕሮግራም በጀት እየተሰራበት አለመሆኑ፣ በፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በማንዋሉ መሰረት እየተተገበረ አለመሆኑና የፕሮግራም በጀት ትግበራ አሁን የደረሰበትንና ከተጀመረበት ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ ያመጣው ውጤት /ለውጥ/ አለመገምገሙ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ተከታታይ ሥልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤

284. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የፕሮግራም በጀትን አፈፃፀምን በሚመለከት ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለባለበጀት መ/ቤቶች ከ2006-2008 ዓ.ም. በየዓመቱ ለ3 ቀን የሚሰጠው ስልጠና ፕሮግራም በጀትን ለመተግበር በቂ ያልሆነና ገለጻ /orientation/ እንጂ ስልጠና አለመሆኑ፣ የፕሮግራሙ ባለቤት ለሆኑ የሥራ አመራሮች ስልጠናውን እንዲያገኙ አለመደረጉ፣

የማሻሻያ ሐሳቦች

285. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በማያቀርቡ መ/ቤቶች ላይ አስገዳጅ የሆነ ሁኔታ በማስቀመጥ እንዲያቀርቡ ሊያደርግና የሪፖርት አቀራረብ ማንዋል ከመላክ ባሻገር በአቀራረቡ ላይ የታዩ ክፍተቶች ላይ ስልጠና ሊሰጥ፣ እንዲሁም በተላኩ ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ የሪፖርት አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የታዩ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ በመስጠት በተሰጡ ሐሳቦች ላይ ማሻሻያ መደረጋቸው በቀጣይ ሪፖርት ላይ በማየት ሊያረጋግጥ እና የአፈጻጸም ግምገማው ከተጠያቂነት አንጻር እንደ በጀቱ በምክር ቤት እንዲታይ ሊያደረግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራው በሚፈልገው መልኩ በሰው ኃይል ሊደራጅና ከሪፖርት በዘለለ የካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ አስፈላጊውን የመስክ ጉብኝትም ሆነ ክትትል በማድረግ በጀቱ በትክክል ለተፈለገለት ዓላማ መዋሉንና በመርሐ ግብሩ መሰረት መሄዳቸውን በማየት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለየፕሮግራሞች የተመደበው በጀት ምን ያህል ውጤታማ መሆኑን ለማወቅ ባለበጀት መ/ቤቶች ፕሮግራሞችን ካስቀመጡት ግብ ስኬት አንጻር ያመጡትን ውጤት በመገምገም ለባለበጀት መ/ቤች ሊያሳውቅ እንዲሁም የፕሮግራም በጀት በፌዴራል ደረጃ የተደረሰበትንና ያመጣውን ውጤት በሌላ አካል ሊገመገም ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ በሚፈቅደው ማለትም አንድ መ/ቤት የማይጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ ወደ ሌላ መ/ቤት የበጀት ዝውውር ሲያደርግ የፕሮግራም በጀትን ዓላማ መሰረት ባደረገ መልኩ የበጀት ዝውውሩ እንዲከናወን በሌላው ፕሮግራም ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ አስፈላጊውን ማብሪሪያ እንዲያቀርቡ በማድረግና የበጀት አጠቃቀምና ዕቅድ ላይ መ/ቤቶች ያለባቸውን ክፍተቶች ለመሙላት አስፈላጊውን ስልጠና በመስጠት የበጀት ዝውውሩ በአግባቡ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በዓመቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ

ያሉትን የበጀት ዝውውሮች ለማስቀረት የበጀት ዝውውሮችን የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥ የማያቋረጡ ዝውውሮችን ሊያስቀር ይችላል፡፡

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፕሮግራም በጀት ወደ ክልል ለማውረድ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ እና ወደ ትግበራ መገባቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስቀድሞ በመ/ቤቶች ላይ የፕሮግራም በጀት አሰራር ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የመ/ቤቶችን ፍላጎት በመጠየቅ ስልጠና ሊሰጥና በፕሮግራም በጀት ላይ የተሻለ አሰራር እንዲመጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የክዋኔ የክትትል ኦዲት

18. <u>በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በተመለከተ</u>

286. በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

287. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ አገርቱ ያወጣችውን አገር አቀፍ የሪፈራል ስርአት ደንብ እና ጤና ጥበቃ ሚንስቴር ያዘጋጀውን የሪፈራል መመሪያ (ዳይሬክትሪ) በመጠቀም እንደሚሰሩ፣
- የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ስዓት የሚቀበሉ እና የሀኪሞች የጠዋት ስብሰባ ከሁለት ሠዓት ከሠላሣ(2፡30) ደቂቃ

በፊት ተጠናቆ ከሁለት ሠዓት ከሠላሣ ደቂቃ በኃላ ሁሉም ሀኪሞች ሥራቸው ላይ እንዲገኙ የሚያደርግ በጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ መመሪያ ውስጥ ተካቶ የተዘጋጀ እና በሦስቱም ሆስፒታሎች ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ፣

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒተል በሁሉም የህክምና ክፍሎች አካባቢ በግልፅ የሚታይ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች መኖራቸው፣
- የክትትል ኦዲት በተደረገባቸው በሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የራሳቸው የሆነ ቦርድ ያቋቋሙ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ሪፖርቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን እና የማስተማርና የምርምር ስራውን በቅንጅት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የመግባቢያ ስምምነት (memorandum of understanding) የተፈራረሙ መሆኑን፣
- የክትትል ኦዲት ከተደረገባቸው ሦስት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በትምህርት ሚኒስቴር በቅንጅት ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙ መሆኑ፣
- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ችግሩን ለመቅረፍ በተቋቋመው በደጀን ላብራቶሪ (በጋራ የሚያገለግል ላብራቶሪ) አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን፣
- በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሦስቱም ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን፣ ምቹ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ የኬሚስትሪ ማሽንና ባክ-አፕ (Back Up) በየክፍሉ የተዘጋጀ መሆኑን እና የላብራቶሪ ውጤት መጥፋትና የታካሚን ሙሉ መረጃ ያለመሙላት ችግሮችን መሻሻል መታየቱ፣

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል እና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሁለቱም ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች የተሟላላቸው በመሆኑ በመጣሪያ እጦት አጥረት ወደ ውጭ የሚላኩ ተመላላሽ ታካሚዎች የሌላቸው መሆኑ፣
- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በብሔራዊ የስነልክ ኢንስቲትዩት አማካኝነት መሳሪያዎችን ዓመታዊ ፍተሻ (Calibration) የሚያደርግ መሆኑን፣
- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመብራት ችግር ስታንድ ባይ ጄኔሬተርና የፒ-ኤስ በየክፍሉ በማዘጋጀት ችግሩ የተስተካከለ መሆኑ፣
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የውሃ እጥረት ችግር ለመቅረፍ ሥራዎች የተሰሩ መሆኑን፣
- የመፀዳጃ ክፍሎችን በተመለከተ፡- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለተመላላሽ ታካሚዎች ለብቻ አስራ ስድስት (16) መፀዳጃ ቤቶችን በማስገንባት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ባሰራው ሕንጻ ውስጥ ተጨማሪ የመጸዳጃ ቤቶች የሰራ መሆኑ፣
- በሦስቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የመድኃኒትና ቴራፒዩትክ ኮሚቴዎች (DTCs) ተቋቁመው አስፈላጊ የሆኑ የመድኃኒቶችን ዝርዝር መዘጋጀቱና ኦዲተብል ፋርማሲ ተግባራዊ ተደርጎ ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑን፣

ታውቋል፡፡

288. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉት ሦስቱም የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ

ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስዱበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ያልላኩ መሆኑ፣

- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያለሪፈራል ወረቀት ተመላላሽ ታካሚዎችን የማይቀበል ቢሆንም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን በሚመለከት የወጣውን ደንብ ግን የማያውቀው መሆኑ፣
- በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የህክምና ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል አመላካች ምልክቶች በድንገተኛ ክፍል ፊት ለፊት ያለ ቢሆንም የላብራቶሪ፣ የራዲዮሎጅ እና የምርመራ ክፍሎች ለመለየት የሚያስችል መለያ ምልክት አለመኖሩ፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የድንገተኛና የላብራቶሪ ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት የሚያስችሉ በትልልቅ የተፃፉ አማላካቾች ያሉ ቢሆንም ሌሎች የምርመራ ክፍሎችን ለማግኘት የሚያስችል አማላካች ምልክቶች አለመዘጋጀታቸው፣
- በክትትል ኦዲት ወቅት በሦስቱም ሪፈራል ሆስፒታሎች በሪኤጀንት አቅርቦትና በመለዋወጫ ዕቃ እጥረት ምክንያት የህክምና መሳሪያዎች አገልግሎት የቆሙ መሆናቸው፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የደጀን ላብራቶሪ የማያገኝ መሆኑ፣
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላዝድ ሆስፒታል አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መሣሪያዎች ማላትም፣-ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሚጅንግ (MRI)፣ ዘመናዊ ሲቲስካን ግዥ የተፈፀመ ቢሆንም በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ባለመኖሩ መሳሪያዎቹ ሥራ አለመጀመራቸው፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅና ጅማ ዩኒቬርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በገለልተኛ አካል የሚገለገሉባቸውን የህክምና መሳሪያዎች ፍተሻ (Calibration) የማያስደርጉ መሆኑ፣

- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አዲስ ወደ ሰራው ህንፃ ለመግባት ዘመናዊ የህክምና እና ላውንደሪ ማሽኖችን ለመጠቀም የሚያስችል የመብራት ጉልበት አለመኖሩ፣
- በጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተበላሽቶ እስከ ግንቦት 2004 ድረስ ያልተጠገነው የላውንደሪ ማሽን የክትትል ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተጠግኖ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- ጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከህንፃ ግንባታ አሰራር ችግር የተነሳ እስከ ስድስተኛ ፎቅ ድረስ ውሃ የማይሄድ መሆኑን፣
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚልኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ የመፀዳጃ ቤቶች እጥረት እስከአሁን መኖሩን ታውቋል፡፡

በመሆኑም

289. በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት በሚመለከታቸው አካላት (የጤና-ጥበቃ ሚኒስቴር እና በናሙና በታዩ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች)

- የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለባቸው፣
- ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁሉም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ እና
- የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ እንዳለበት

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

19. <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ላይ የክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ሪፖርት</u>

290. በመንግስት የልማት ድርጅቶች በኣለአደራ ቦርድ የሚከናወኑ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናውኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ባለአደራ ቦርዱ በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶችንና የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማስተካከልና ተግባራዊ ለማድረግ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርዱ ሁሉም ውሳኔዎች እንዲያጸድቁ ለሥራ አመራራ ቦርዱ ይላክ የነበረውን አሠራር በመቆም በመንግሰት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት እየተሠራ በመሆኑ በሥራ ላይ ይደረስ የነበረውን መዘገየት የቀነሰ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርድ የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፡-
    - ➢ በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት ከባለአደራ ቦርድ የሥራ በህሪ አንፃር የማያሰሩትን አንቀፆች በመለየት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (አሁን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር) ጥያቄ አቅርበው በማስፈቀድ ተግበራዊ ያደረገ መሆኑን፣
    - ➢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርበው ያልተፈቀደላቸው አንቀፆች በመመሪያ ቁጥር 9/20003 መሠረት እየሠሩ መሆኑን እና

- ባለአደራ ቦርድ የሚረከባቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረት የዋጋ ክለሳ ሳይደረግ ይከራይ የነበረው አሠራር ተሻሽሎ ያለጨረታ የሚከራይ ምንም ዓይነት ንብረት የሌለ መሆኑን፣

- ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) የሚረከበውን ንብረቶች በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ለይተው በዝርዝር የመረከቡ ሥራ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርዱ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የንብረት ወጪ ማዘዣ የሚያዘጋጀው እና ንብረቱን የሚይዘው በተለያየ ሰው ሲሆን የምዝገባ ሥራና የንብረት ገቢና ወጭ ደረሰኞችን የሚያዘጋጀው አንድ ባለሙያ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርድ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጪ ውል በተፈራረሙ መሠረት ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣
- የአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጭና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበርና የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን ድርጅት ባለአደራ ቦርድ ከተረከባቸው ንብረቶች ጋር በአንድነት በአንድ መጋዘን ውስጥ የነበሩት ንብረቶች ወደ ላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስቱሪ ድርጅት በመጓጓዝ በመ/ቤቱ ህንፃ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው ኮንትነሮች ውስጥ እንድቀመጥ የተደረገ መሆኑን፡
- ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር አዋጅን መነሻ በማድረግ የባለአደራ ቦርድ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ፡

- ባለአደራ ቦርዱ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች መተዳደሪያ የሚሆኑ መመሪያዎችን ያስተላለፈላቸው በመሆኑ በዚያ መመሪያ እየሰሩ መሆኑን፣
- ለሊኩዴሽን ቡድን አባላት ይከፈል የነበረው የትራንስፖርት አበል፣ የአቧራ አበል እና የትርፍ ሠዓት ክፍያዎች ከህዳር 1/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆሙ የተደረገ መሆኑን፣
  - የሹፌርና የጥበቃ ሠራተኞች የትርፍ ሠዓት ክፍያዎችን በተመለከተ ማቆም አስቸጋሪ በመሆኑ ክፍያዎቹ እንዲፈቀዱላቸው ለሰቪል ሠርቨስ ሚኒስቴር አቅርበው በማስፈቀድ ክፍያ እየተፈፀመ መሆኑን፣

- ሂሳቡን ለማጣራት የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ጨምሮ የ263 የልማት ድርጅቶች የ20 ዓመት ሂሳብ ተጠቃሎ የተሰራ መሆኑ፣

እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው

- ባለአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሰት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (አሁን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር) ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያሰችል የመግባቢያ ሠነድ ጥናትም ሆነ የተዘጋጀ የመግባቢያ ሠነድ የሌለ መሆኑን፣
- ባለአደራ ቦርዱ ተረክቦ በመጋዘን የሚያስቀምጣቸው ንብረቶች ስለመኖራቸው (Existance) ለማወቅ የንብረት ቆጠራ ቢያንስ በአመት አንዴ ቆጠራ በማድረግ የማያረገግጥ መሆኑ፣
- የፈረሱ የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ለማጣራት ለልኩዴሽን ቡድን ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሆነ /ለደመውዝ፣ ለነዳጅ፣ ለመስተንግዶና ለሌሎች ወጪዎች/በወጪ አርዕስቶች መሠረት በዝርዝር ተዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርድ እንድቀርብ የሚደረግ መሆኑን በላኩልን

የድርጊት መርሃ-ግብረ የገለፁልን ቢሆንም ለሥራ አመራር ቦርዱ የቀረበት የወጭ ሪፖርትና በሥራ መራር ቦርዱ የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑን፣

- ከ2001-2003 በጀት ዓመት ድረስ የሂሳብ ማስመርመር ሥራ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ መረሃ-ግብር ተዘጋጅቶ የቀርባል ተብሎ ለመ/ቤታችን በተላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ላይ ይዘጋጃል ተብሎ በተገለጸው መሠረት ሂሳቡን ለማስመርመር የተዘጋጀ የድርጊት መርሃ-ግብር የሌለ መሆኑን፣

በመሆኑም

291. በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ

- በአብዛኞቹ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለባቸው
- ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አሁንም የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ፣
- የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ እንዳለበት

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

20. <u>በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ሪፖርት</u>

292. የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የሚከናወኑ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናውኖ

በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የእርምት እርምጃ የሚወስድበት ጊዜ የሚያመላክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ ቢሆንም የድርጊት መርሃ ግብር ያልወጣላቸው ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች መኖራቸው፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን እና የኦሮሚያ የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችን ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወሳኝ የሥራ ሂደት በ2007፣ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በእቅዳቸው ወስጥ አካቶ በማቀድ በእቅዱ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን፣
- በናሙና የታዩት የግል የጤና ተቋማት ከህክምና ክፍሎች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በሴፍቲ ታንከር በማጠራቀም ስሞላ የሚያስመጥጡ በመሆኑ የታዩት ተቋማት በሙሉ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ፈሳሽ ቆሻሻ የሌለ መሆኑን፣

<u>እርምጃ ያልተወሰደባቸውና መሻሻል ያልታየባቸው</u>

293. የምግብ፣ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ለሚመለከተው አካላት ያሰራጩበትና ያስተዋወቁበትን ጊዜ የሚያመለክት የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላኩ ቢሆንም፡-

- በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ የሌለ መሆኑን፤

- ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የጤና ተቋማት በቁጥር ተቆጥሮ በብዛታቸው ልክ ተዘጋጅተው ለሁሉም ክልሎች የተሰራጫ የሆስፑታሎች ስታንደርድ (Comprehensive Specilaizede Hosiptal Requirements Ethiopian standard) ያለ ቢሆንም ለግል የጤና ተቋማት ያልደረሱ መሆኑን፤

- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች ሥልጠና ሥለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርግት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላኩ ቢሆንም፡

- በናሙና ተመርጠው የክትትል ኦዲት በተደረገባቸው በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከስድስቱ /6/ በስተቀር አስራ ሁለት/12/ ተቋማት ሲቀጠሩ ኦረንቴሽን ከመስጠት ወጭ በራሳቸው ሥልጠና ለፅዳትና አስተዳደር ሠራተኞች የማይሰጡ መሆኑን፣

- በባለሥልጣን መ/ቤቱም ለፅዳትና ለአስተዳደር ሠራተኞች ስለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ በተቀናጀ መልኩ ሥልጠና ስለመሰጠቱ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑን፣

- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ ደረጃውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅተው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ ቢሆንም፡-

- በክትትሉ ወቅት በናሙና ተወሰደው ከታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከአዳማ ጀኔራል ሆስፒታል፣ አሰላ ሮሆቦት ሀስፒታል፣ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል የእናቶችና ህፃናት ስፔሻሊቲ ሴንተር እና አሰላ መነሃሪያ ክልንክ በስተቀር አስራ አራቱ/14/ የጤና ተቋማት ለቆሻሻ

ማቃጠያ የሚጠቀሙት ኢንስኒሬተር በስታንዳርዱ መሠረት የህክምና አገልግሎት ከሚሰጥበት ክፍሎች 30 ሜትር ያራቁ መሆኑን፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ያላቀረቡ መሆኑን፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ስምንቱ/8/ በከለር በተለየ ዕቃ የሚጠቀሙ ሲሆን አስሩ/10/ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) በማለት በፅሑፍ ፅፎ በመለጠፍ እየተጠቀሙ መሆኑን፣
- የምግብ፣ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ ልውውጥ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መረሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለመስሪያ ቤታችን ያላቀረቡ መሆኑን፡፡
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታየው የቆሻሻ አያያዝና አወገገድን በተመለከተ የግል የጤና ተቋማት ከጤና ቢሮዎች እና ከተቆጣጣሪ አካላት ጋር ምንም አይነት የመረጃ ልውውጥ የሌላቸው መሆኑን፣
- የምግብ የመድኃኒት እና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት የሣንቴሽንና ሃይጅን ባለሙያ መኖሩን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅተው ያልቀረቡ መሆኑን፣
- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተወሰደው በታዩት 18 የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ከስድስቱ በስተቀር 12ቱ የግል የጤና ተቋማት የሳንቴሽንና የሃይጅን ባለሙያ ቀጥረው በዚህ ባለሙያ ቆሻሻ እንዲለይ ያላደረጉ መሆኑን፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ከማዘጋጃ ቤቶች እና ከሌሎች ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ለማድረግ በ2007 እቅድ የሚያሳይ የድርጊት መረሃ-ግብር ቢዘጋጁም ስለመከናወኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- በአገሪቱ ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የህክምና ቆሻሻ የሚወገድበት ሥፍራ የሌለ መሆኑ፣

በመሆኑም

294. በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ

- በተወሰኑት ግኝቶች የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለባቸው፣ ነገር ግን
- ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አሁንም የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ፣
- የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ እንዳለበት፣

በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

21. <u>በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ የክትትል ኦዲት የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት/data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤

295. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ ሥርዓት ያልተዘረጋ ፤ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችለ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ ያልዋሉ እና የመረጃ ቋት (data base) የሌለ መሆኑን ፤ እየሠሩ ያሉት በማንዋል መሆኑን ፤
- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት እና በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና የሚያግዝ Government Customs Ware house Control /GCWCS/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ከሐምሌ 1 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሙከራ ላይ ያለ እና ወደ ስራ ያልተገባ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

296. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በጉምሩክ እዳ የተወረሱ በእቃዎቹ ላይ የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያልተቀመጠባቸው እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ ሲሆን በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ በሞዴል 265 የሚመዘገብ መሆኑን፣ በተለያየ ስሌት ሲወገዱ ደግሞ በሞዴል ቁጥር 266 ወጪ እንደሚደረግ፣
- በተለይ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የሚገኙ የውርስ እቃ የመጋዝን የእቃዎች ቢን ካረድ እና ስቶክ ካረድ በትክክል አለመዳረጀት እና በስነ ስርአት አለመጠቀም፣ በሞዴል /265 በሞ/266 በሞዴል /270

ገቢና ወጭ ሲደረግ የቁጥጥር ስርአት በጣም ደካማ መሆኑ፣ እቃዎች ሲገቡ የ ስሪት አገር ማርክ በትክክል አለመፃፍ እና አለመመዝገብ፣ አንድ የመጋዝን ሰራተኛ በርክክብ ጊዜ ሲያስረክብ እና ሲረከብ በልዩነት ርክክብ እንዲያደርግ ማድረግ፣ በርክክብ ጊዜ የውስጥ ኦዲተር አለመኖረ፣ የውርስ እቃ መጋዝን ገቢ ሲደረግ ትክክለኛ የሆነ መለኪያ /size/ ወይም /standared/ አለመኖር፣ በየቀኑ ገቢ የሚደረጉ እቃዎች ከፍተኛ ቦታ የሚመጡ እቃዎች በትክክል አለመመዝገቡ እና መቼ እና ማን ገቢ እንዳደረጉ የቁጥጥር ስርአት ክፍተት መኖር፣ ተሰባሪ የሆኑት እቃዎች በአንድ ላይ በጥንቃቄ ባለመቀመጣቸው የተሰበሩ እቃዎች እና የተበላሹ መኖራቸው፣ ሁሉም አይነት እቃዎች ተደራርበው እና ተደባልቀው ከመቀመጣቸው የተነሳ በቆጠራ ጊዜ እንዳይገኙ ማድረጉን ፤

- ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ደግሞ በሁለቱም በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ተሽከርካሪዎች በሚያዙበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ያልተመዘገቡ መሆናቸውን እና በሞዴል 265 ውርስ ሆነው ገቢ አለመደረጋቸውን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ መያዙን እና በየበጀት አመቱ ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ

297. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይቶ ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትል እንደማይደረግ፣ መጋዘኖች እቃዎችን እንደዓይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ የሌላቸው ፣ እቃዎቹ ሊበላሹ በሚችሉበት

መልኩ እርስ በርስ ተደራርበው እና በየዓይነታቸው ሳይሆን አንድ ላይ ተከማችተው መቀመጣቸውን እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶችን በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በአግባቡ መያዙን ቢገልፁም የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶችን በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በአግባቡ አለመያዙን ለመመልከት ተችሏል፡፡
- የንብረት ቆጠራን በተመለከተ በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ2007 ዓ.ም እና በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ መደረጉን ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ ሲሆን በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ የተደረገ መሆኑን ፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የ2008 ዓ.ም. የንብረት ቆጠራ የተደረገ ሲሆን ፣ የ2007 ዓ.ም የተደረገው የንብረት ቆጠራ ጥራት የሌለው መሆኑን እና መረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከቆጠራ ሪፖርት ማስረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ባለሙያተኞችን በማዋቀር በ 2007 ዓ.ም እና በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ የተደረገ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠየቅ ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡
- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በ2008 ዓ.ም የንበረት ቆጠራ የተደረገ ሲሆን የ2007 ዓ.ም ቆጠራ ስለመደረጉ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣
- እንዲሁም በአዋሽ ጉ/መቅ/ጣቢያ በተደረገ ጨረታ እቃዎች በጨረታ መሸጣቸውን፣ ነገር ግን አንድ አንድ እቃዎች እቃዎች ርክክብ ሲደርጉ በመጋዘን ውስጥ ማግኘት አለመቻሉን፣ በመሆኑም አስወጋጅ ኮሚቴ እቃውን ያሸነፋት ተጫራቾች ብር ቀድሞ ገቢ ያደረጉ በመሆኑ

እቃቸውን ማስረከብ የመስሪያ ቤቱ ግዴታ መሆኑ ታውቆ ያሸነፉት እቃ በመጋዘን ውስጥ ባይገኝም ተመሳሳይ እቃዎች እንዲተካላቸው በመስማማት የዋጋ ጥናት ሳምፕል በአዋሽ ከተማ በመዘዋወር መረጃ ተሰብስቦ እቃዎቹ እንዲተኩ የተደረገ ሲሆን በጨረታ ተሸጦ በርክክብ ወቃት በመጋዝን ውስጥ ያልተገኘው/የጎደለው የእቃው አይነት ፡-

የተለያዩ ዓይነት ሞባይሎች፡-

298. የሞባይል ብዛት gt-I8852 Vetnam 55 ፍሬ ሲሆን በተደረገው የአካባቢው የገበያ ጥናት የአንዱ ዋጋ 1,700 ብር ሲሆን ኮሚቴው እንዲተካላቸው የወሰናቸው ሞባይሎች ፡ Samsung gm-G360 የአንዱ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 5፣ Samsung sm-J500 HIDS የአንዱ የአካባቢው የገበያ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 20፣ Samsung sm-J110 HIDS የአንዱ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 30 አጠቃላይ በርክክብ ወቅት የጎደሉት 55 ሞባይሎች ጨረታውን ላሸነፉት ግለሰቦች እዲተካላችው መደረጉን፣

ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

299. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በየቅርንጫፉ ወጥ የዋጋ አተማመን አለመኖሩንና በአሰራር ላይ ቅሬታ ማስነሳቱን፤
- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ዋጋ እየተመኑ ያሉት በ 16ኛው ሲዲ መሆኑን፣ የዋጋ መተመኛው ወቅታዊ ባለመደረጉም ዋጋ ለመተመን እየተቸገሩ መሆኑን፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአሁኑ ጊዜ ሲዲ የቀረ መሆኑን እና ECVS እና አሲኩዳ መስመር አለመዘርጋቱን፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የተተዉና የተወረሱ ንብረቶች የሥራ ክፍል የዋጋ ትመና አደረጃጀት የሌለው በመሆኑ የዋጋ ትመና ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን፣ በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የዋጋ ትመና ባለሞያ የሌለ እና የዋጋ ትመና እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

የተወረሱ መድሀኒቶች፣ ምግቦችና አደገኛ ዕቃዎች አጠባበቅን በተመለከተ፣

300. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያልተዘጋጀ መሆኑን እና እቃዎች ሊበላሹ በሚችሉበት ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑን፣ ሁለት መጋዘን ብቻ ያለ ሲሆን መጋዘኖቹ መደርደሪያ የሌላቸው መሆኑን፣
- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ ካለው የኮንትሮባንድ ብዛት አንፃር በቂ መጋዘን የሌለ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ ንብረቶቹ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን የማይከታተል እና የማይቆጣጠር እንደሆነ፣ በየጊዜው ለሚያዙ እቃዎች በቂ መጋዘን ባለመኖሩም እቃዎች ከመጋዘን ውጪ ሲቀመጡ የሚጠፉበት ሁኔታ መኖሩን፣
- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን፣ በፀሀይ እና በዝናብ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው የተበላሸ፣ እንዲሁም አንዳንድ አንዳንድ የውስጥ እቃዎቻቸው የጎደሏቸው መሆናቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች /እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል

የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን የሌለ መሆኑን፣ የተለያዩ አልባሳት፣ ጨርቃጨርቅ፣ ዘይት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ስኳር፣ ሳሙና እና የተለያዩ እቃዎች በኮንቴይነር መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፣ አንደኛው መጋዘን ሰፊ እና አብዛኛው የተወረሱ እቃዎች የተወገዱ ቢሆንም መደርደሪያ የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን፣ በፀሀይ እና በዝናብ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው በዝገት እና በአፈር ከመበላሸቱም በተጨማሪ የተሽከርካሪዎች አንዳንድ የውስጥ እቃዎቻቸው የጎደሉ እና የተሰበሩ መሆኑን፣ /ለምሳሌ እንደ ቴፕ፣ ስኮርት ጎማ፣መስታወት፣ ስፖኪዮ/፣ 21 አዲስ የነበሩ ተሽከርካሪዎች የላይኛው አካላቸው በዝገት እና በአፈር ለብልሽት መዳረጋቸውን እና ተሽከርካሪዎች የቆሙበት ቦታ ላይ ሰዎች እንደሚፀዳዱበት ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን በፀሀይ፣ በዝናብ እና በአቧራ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው እየተጎዳ የሚገኝ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡
- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች /ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች /እንደአይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዘታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘኖቹ አለመዘጋጀታቸውንና ያሉትም ምቹ አለመሆናቸውን፣
- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በመጋዘን ቁጥር 5 ውስጥ መጋዘኑ ሙሉ ለሙሉ ቆርቆሮ ሲሆን ጣሪያው ውሃ የሚያስገባ /የሚያፈስ/ ሲሆን ወለሉ አቧራ መሆኑን፣ እንዲሁም ፀሀይ የሚያስገባ መሆኑን፣ የህግ ሒደት ላይ ያሉት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጣቸው/ እቃዎች በማቆያ ሞዴል 270 ያልተያዙ መሆኑን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት፣ ኮስሞቲክሶች፣ መድሃኒቶች እና ሌሎች እቃዎቹ

ተዘበራርቀው እርስ በርስ ለመለየት በማያስችል መልኩ እና ሊሰበሩ በሚችሉበት ሁኔታ እርስበርስ ተደራርበው መቀመጣቸውን፣

የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በእስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዙንና በክንውን ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ መውሰደን በተመለከተ

301. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤቶች መካከል በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የሚወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ እስትራቴጅክ ዕቅድ የሌለ /ያልተዘጋጀ/ ሲሆን ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን እና ለችግሮች የመፍትሔ እርምጃ እንደሚወሰድ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ፣ ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻል ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

302. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 56/2003 ለሁሉም የተሰራጨ ሲሆን መመሪያው ላይ ክፍተት በመኖሩ መሻሻል ያለበት መሆኑን፣ የመመሪያው አንቀፅ 10 ላይ የጨረታ አወጋገድ ላይ በዝግ ጨረታ ለሚሸጡ እቃዎች የ C.I.F. ዋጋ የጨረታ መነሻ ዋጋ ሆኖ የሚያገለግለው ለሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን በእቃው ላይ ለ ሶስተኛ ጊዜ ዝግ ጨረታ የተደረገ እንደሆነ ግን የእቃው መነሻ ዋጋ የእቃው F.O.B.

ይሆናል የሚለው እቃዎች ቶሎ እንዳይሸጡ ያደረገ መሆኑን፣ ሌላው መመሪያው እቃዎች በሲዲ ዋጋ ይሸጥ የሚለው ሲሆን፣ በኮንትሮባንድ የተወረሱ ንብረቶች አብዛኛዎቹ መረጃ ስለማይገኝላቸው በ ሲዲ ዋጋ ትመና ለመሸጥ የማይመች መሆኑን እና በኮንትሮባንድ ለተወረሱ ንብረቶች የተለየ የዋጋ መተመኛ ሊኖረው እንደሚገባ፣

የባለስልጣን መ/ቤቱ የተሟላ የሰው ሃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ

303. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስተዳደርና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሃይል የሌለ መሆኑን በመዋቅሩ መሰረት የሚያስፈልገው 13 ባለሞያ ሲሆን አሁን ያለው 8 ባለሞያ መሆኑን እና እንርሱም በሙያው የሰለጠኑ አለመሆናቸውን፣ የዋጋ ትመና ባለሞያ የሌለ መሆኑን፣
- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በመዋቅሩ መሰረት የተፈቀደው የሰው ሃይል ብዛት አስራ ስምንት (18) ሲሆን፣ አሁን አምስት መደቦች ክፍት መሆናቸውን፣

የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ስለመቋቋሙና ክትትል ስለማድረጉ በተመለከተ

304. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን በታክስ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን እቃዎችን የሚያስወግደው ኮሚቴው መሆኑን፣ ነገር ግን የተወረሱ ንብረቶች

በፍጥነት እየተወገዱ አለመሆናቸውን፣ አስወጋጅ ኮሚቴ ቀልጣፋ ስራ እየሰራ አለመሆኑን፣

- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ እዳና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ ሁለት ዓይነት ኮሚቴዎች ማለትም የአስወጋጅ እና የጨረታ ኮሚቴ መኖሩ፣ አብዛኛው ሥራ መሰራት ያለበት በኮሚቴው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 56/2003 ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በአብዛኛውን የኮሚቴው ሥራዎችን የሚያከናውነው የተተዉና የተወረሱ ንብረቶች ቡድኑ መሆኑን፣
- በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴውም አፈፃፀሙን የሚከታተል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ዕቃዎች እና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

305. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኬሚካል እየተወገደ አለመሆኑን፣ ይህንን በተደጋጋሚ ለዋናው መ/ቤት በደብዳቤ ቢያሳውቁም ምላሽ ያላገኙ ሲሆን በተጨማሪም በ2003 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር ተይዞ የተወረሰ የዝሆን ጥርስ ቢኖርም በማን እና እንዴት መወገድ እንዳለበት መመሪያ የሚሰጥ አካል በመጥፋቱ እስካሁን የተቀመጠ መሆኑን፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኮንቴነር የተያዙ ያልተወገዱ ኬሚካሎች መኖራቸውን እነሱን ለማስወገድ ለዋናው መ/ቤት በተደጋጋሚ ደብዳቤ ያሳወቁ መሆኑን፤
- በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በህገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ሲል ተይዞ የነበረ በቁጥር 3,546,000 ወይም 591 ካርቶን ቢክ እስኪርቢቶ ሳይወገድ ከ 6 ዓመት በላይ በኮንቴይነር ውስጥ መቀመጡ፣

በ06/06/2008 ዓ.ም ለጨረታ ቀርቦ የቀረበው ዋጋ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ የተሰረዘ መሆኑን፣ በ 22/07/2008 ዓ.ም በድጋሚ ጨረታ ወጥቶበት የተሻለ ዋጋ የተገኘበት ቢሆንም እስኪብርቶዎች ሲሞከሩ ለብዙ ዓመታት በኮንቴይነር ውስጥ የቆዩ በመሆናቸው አብዛኛው የማይሰራ፣ የደረቀና አንዳንዱ ደግሞ የሚያቆራርጥ መሆኑን፣ በዚሁም መሠረት የእቃውን ጥራት ለማረጋገጥ ለኢትዮጵያ ተስማሚነት እና ምዘና ድርጅት በቁጥር 2.23/117/08 በቀን 22/09/2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ 100 የእስኪርቢቶ ናሙና ይዘው ያቀረቡ ሲሆን ድርጅቱም በቁጥር 2/15/6-2/900/08 በቀን 15/10/2008 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ መሰረት የጥራት ደረጃው ለፅሁፍ አገልግሎት የማይውል መሆኑን ያሳወቃቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በቁጥር 2.16/57/09፣ በቀን 01/03/2009 ዓ.ም ለተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ቡድን በፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ያልተወገዱ ኬሚካሎችና መድሃኒቶች መኖራቸውንና እንዲወገዱ ለምግብና መድሐኒትና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተደጋጋሚ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ሊወገድላቸው አለመቻሉን፣ ግቢው ውስጥ ሶስት ኮንቴነር ያልተወገደ አደገኛ ኬሚካል መቀመጡን እንዲሁም ባዶ ቦታ ላይ ያለምንም ከለላ ከአይሮፕላኑ ማቆሚያ በግምት 30 ሜትር ላይ ሳይወገዱ የተቀመጡ ተቀጣጣይ ኬሚካሎች መኖራቸውን ከቃለ-መጠይቅ እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ላይ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከአዲስ አበባ ውጪ እና አዲስ አበባ የሚገኙ ተሸከርካሪዎች ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ

306. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ተሸከርካሪዎችን በተመለከተ የመነሻ ዋጋ የሚወስዱት ከቀረጥ እና ታክስ ዋጋ ሲሆን ቀጥሎ ወደ C.I.F. የሚመጣ

መሆኑን ተሽከርካሪው ካልተሸጠ ወደ መንገድ ትራንስፖርት ትመና የሚሔዱ መሆኑን፣ አምስት ጊዜ ጨረታ ወጥቶባቸው በተሽከርካሪው ላይ ያሉ የተለያዩ ለሽያጭ የሚሆኑ ማስረጃዎች ባለመኖራቸው ያልተሸጡ ተሸከርካሪዎች መኖራቸውን፣

- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በታክስ እዳ የተወረሱ ተሸከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ መነሻ ዋጋ የሚሆን የንብረት ዋጋ ግምት ከመንገድ ትራንስፖርት እና አግባብነት ካላቸው የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር በትብብር የማይሰራ መሆኑን፣ ተሽከርካሪ በጣቢያቸው ተወግዶ እንደማያውቅ እና ተሽከርካሪ ለማስወገድ ባለሞያ የሌላቸው መሆኑን፣

22. <u>የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ</u>

የመንግስት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ የክትትል ኦዲት

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥናት ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

307. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ መ/ቤቶች መካከል በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በማዕድን፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ የማያውቅ ሲሆን፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት

የሚያስችል ጥናት በሒደት ላይ ያለና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

308. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በቤተመንግስት አስተዳደር የቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገላቸውና ቦሎ የሌላቸው ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት የተሽከርካሪዎች የጥገና ድግግሞሽ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፣ በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት የጥገና ድግግሞሽ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገላቸው 12 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኦዲት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በፌዴራል መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት መጠቀምን በተመለከተ፤

309. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) እና በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በጋራ በማቀናጀት እንደሚጠቀሙ ቢገልጹም ፣በጋራ ስለመጠቀማቸው የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑን እንዲሁም ተሽከርካሪ የሚጠየቀው በተዘጋጀ ፎርም ሳይሆን በቃል መሆኑን ፤
- በአካባቢና ደን ጥበቃ ሚ/ር ለበላይ ኃላፊዎች፣ ለከተማ ሥራ፣ ለሰርቪስ ስራ አገልግሎትና ለሌላ ተብለው በየደረጃው ተሽከርካሪ የመመደብ ሥርዓት አለመኖሩን፣

ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ እደላ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ የሚወሰን መሆኑን በተመለከተ፤

310. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ ለተሽከርካሪዎች የሚሰጥ የነዳጅ እደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ አለመሆኑን ፤
- በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር የፑል ተሽከርካሪዎች ስራ ስለሚበዛባቸው ኮታ የሌላቸው ሲሆን በኮታ የነዳጅ እደላ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ነገር ግን የተሽከርካሪ እጥረት ስላለበቸው በኮታው መሰረት እንደማይሄዱ፣

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታን በተመለከተ፤

311. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በሊትር የተወሰነ የነዳጅ ኮታ የሌላቸው መሆኑን፣በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት የበላይ ኃላፊዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለዋና ዳይሬክተር በሳምንት 50 ሊትር፣ ለምክትል ዋና ዳይሬክተር በሳምንት 60 ሊትር የሚቀዳላቸው መሆኑን፣
- በጤና ጥበቃ ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-15034 የሆነ የበላይ ሃላፊ ተሽከርካሪ በወር የተተመነለት ኮታ 165 ሊትር ሲሆን፣ በመስከረም 2006 ዓ.ም 583.99 ሊትር፣ በጥቅምት 2006 ዓ.ም 590 ሊትር፣ በህዳር 2006 ዓ.ም 339 ሊትር፣ በሚያዚያ 2006 ዓ.ም 440 ሊትር ፤ በሰኔ 2006 ዓ.ም 526.45 ሊትር፤ በሀምሌ 2006 ዓ.ም 490 ሊትር ሲሆን፣ በ2007 ዓ.ም ደግሞ በመስከረም 2007 ዓ.ም 441.06 ሊትር፣ በየካቲት 2007 ዓ.ም 589.52 ሊትር፣ በሚያዚያ 2007 ዓ.ም 440 ሊትር፤ በሀምሌ 2007 ዓ.ም 589.91 ሊትር፤በነሀሴ 2007 ዓ.ም 570.62 ሊትር

እንዲሁም በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም 575 ሊትር፣ በጥቅምት ወር 2008 ዓ.ም 550.87፣ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም 690 ሊትር፣ በታህሳስ 2008 ዓ.ም 528 ሊትር፤በሚያዚያ 2008 ዓ.ም 590 ሊትር፣ በግንቦት 2008 ዓ.ም 694 ሊትር ናፍጣ የተቀዳለት መሆኑ፣

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ስለመኖሩ በተመለከተ፤

312. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በፍትህ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ስምሪት አጠቃቀም ቅፆች 04፣ 05፣ 09፣ 12 እና 13 ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ አባሪ ላይ ያሉትን ቅፆች ማለትም ቅፅ 01፣02፣05፣እና 12 ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑን፣በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት በተሽከርካሪ ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ አባሪ ላይ ያሉትን ቅፆች ማለትም ቅፅ 02፣07፣እና 08 ስራ ላይ አለመዋላቸው፣
- እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት እንደቻለው በናሙና በታዩ መ/ቤቶች ማለትም በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ ኤፍ ቢ ፣ ዘንዘልማ ፣ ይባብ ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር፣ በማዕድን፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በስታትስቲክስ ባህርዳር ቅርንጫፍ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር እና በግገርና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ የሌለ ሲሆን በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ምንም ዓይነት ቅፅ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎችን በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚጓዙትን ኪሎ ሜትር መጠን በተመለከተ፤

313. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት ለመመልከት እንደተቻለው በናሙኑ የተወሰዱ መ/ቤቶች ያሉ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ ልኬት የማይደረግላቸው ሲሆን በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል ልኬት የተደረገው በ 2004 ዓ.ም መሆኑን አሁን ተሽከርካሪዎች ልኬት በምርታማነት ኤጀንሲ እየተደረገላቸው መሆኑን የቀድሞው ልኬት ማስረጃም ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑን፣ በማዕድን ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው እድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ/ናፍጣ/ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል በቃል ደረጃ የሚታወቅ ሲሆን በሰነድ ልኬት የተደረገበት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተሽከርካሪዎቹ ልኬት እየተደረገላቸው እንደሆነ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት ለተሽከርካሪዎች ልኬት /ኖርማላይዜሽን/ አለመደረጉን፣ በኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣ በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በከፊል ብቻ ለተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ኖርማላይዜሽን የተሰራ መሆኑን እና ለሁሉም ተሽከርካሪዎች በተሟላ ሁኔታ አለመሰራቱን፣ በሰመራ ዩኒቨርስቲ አንድ ተሽከርካሪ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር ሊጓዝ እንደሚችል የሚያሳይ /ኖርማላይዜሽን/ የሰነድ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑን፤
- በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ደግሞ ፡-
- /3266/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /476.15/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 113.3 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤

- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-13317 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በኅዳር /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 300 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.1620 መሆኑ ፣ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /1620/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /300 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 120 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 4-1077 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 7ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 420 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ /1180/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /420/ ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 7ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 251.4 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07633 የሆነው ተሽከርካሪ በአማካይ በ1 ሊትር እንዲጓዝ የተተመነው 9ኪ.ሜ. መሆኑ፣ ተሽከርካሪው በጥቅምት /08 ዓ.ም. የወሰደው የነዳጅ መጠን 341.17 ሊትር ሲሆን፣ የተጓዘው ኪ.ሜ.2410 መሆኑ ነገር ግን ተሽከርካሪው የተጓዘው ኪ.ሜ /2410/ የተጠቀመው ነዳጅ በሊትር /341.17 / ሲሰላ፣ በ1 ሊትር እንዲጓዝ ከተተመነለት 9ኪ.ሜ በማነስ መጓዙን ወይም 73.3 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን የሚያሳይ መሆኑ፤
- በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥሩ 4- 04206 የሆነው ተሽከርካሪ 34 ሊትር፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 4-05633 የሆነው ተሽከርካሪ 47.7 ሊትር፣
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሰሌዳ ቁጥሩ 4 -20494 የሆነ ተሽከርካሪ በህዳር ወር 2008 ዓ.ም ውስጥ የተጓዘው ርቀት 6721.2 ኪ.ሜ ሲሆን ይህን ርቀት ለመጓዝ መቅዳት የነበረበት ነዳጅ በልኬቱ መሰረት 840 ሊትር የነበር ሲሆን ለዚህ ርቀት የቀዳው ነዳጅ 914 ሊትር መሆኑ ወይም 74 ሊትር ብልጫ መጠቀሙን፣

ጌጃቸው (የኪሎ ሜትር ቆጣሪ) ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

314. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) የሰሌዳ ቁጥር 4-2416፣ 4-08817፣ 4-07854፣ 4-10673፣ 4-09584፣ 4-02437 እና 4-2428 ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ የሰሌዳ ቁጥር 4-09583 የሆነ ተሽከርካሪ ጌጁ የማይሰራ መሆኑን ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-05450፣ 4-03448፣ 4-05948፣ 4-13223፣ 4-17128፣ 4-08495 ተሽከርካሪዎች የማይሰራ መሆኑን፣የተሽከርካሪ እጥረት ስላለባቸው ጌጃቸወው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎችን እንደማያቆሟቸው፤
- በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት የሰሌዳ ቁጥር 4-02757፣ 4-03072፣ 4-04163፣ 4-02199፣ 4-019158፣ 4-02777፣ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን፣ አብዛኛው ተሽከርካሪ 15 እና 20 ዓመት የሰሩ በመሆናቸው መለዋወጫ ጌጅ ለማግኘት እንደማይቻል፣ ተሽከርካሪዎቹ እንዳይቆሙ የተሽከርካሪ እጥረት ያለባቸው እንደሆነ፣በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የሰሌዳ ቁጥሩ 4-00109 እና 4-05708 የሆኑ የጭነት ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ ሲሆን ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሁሉም ተሽከርካሪዎች ኪ/ሜትር ቆጣሪ /ጌጁ/ የሚሠራ መሆኑን ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት መዘጋጀቱን እና መቅረቡን በተመለከተ፤

315. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር

በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲሁም ለግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን የኦዲት ቡድኑ ለመመልከት ችሏል፡፡

- በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ 2006 ዓ.ም ሁሉም ተሽከርካሪዎች እለታዊ የነዳጅ፣የዘይትና የኪ.ሜ ያልተመዘገበ መሆኑን ከተሽከርካሪዎች የግለ ማህደር ለመመልከት መቻሉን፤
- በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተሽከርካሪ ዘይትና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ መረጃዎችን ለሚመለከታቸውና ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ ተጠናቅሮ የማይላክ መሆኑን፣ በሰመራ ዩኒቨርስቲ የተሽከርካሪ የስምሪት ሁኔታ ፣ የጥገና ወጪ፣ የመለዋወጫ ግዥ በየሩብ ዓመቱ ለዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑን፣ በትምህርት ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች ስምሪት ሁኔታ፣ የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ግዢ ወዘተ. መረጃ በየሩብ ዓመቱ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይላክ መሆኑን፣
- በኢትዮጵያ እንቨስትመንት ኮሚሽን የተሽከርካሪ ነዳጅ አጠቃቀም መረጃዎች ለሚመለከታቸውና ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ እንደማይላክ ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ለዩኒቨርሲቲው ለበላይ ኃላፊ በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ ፣ በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን የተሽከርካሪ የስምሪት ሁኔታ፣ የጥገና አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ግዢ ወዘተ. መረጃ በየሩብ ዓመቱ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የማይቀርብ መሆኑን፣

የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ

316. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት የተሽከርካሪ ስምሪት ባለሞያ አለመኖሩን፣ የስምሪት ስራው እየተሰራ ያለው በፋይናንስና

ግዢ የሥራ ዘርፍ ተደርቦ መሆኑን፣ ይህ ደግሞ በስራቸው ላይ ጫና እየፈጠረባቸው ሲሆን ችግሩም ለረጅም ጊዜ ያልተቀረፈ እንደሆነ እንዲሁም በቅ/ፅ/ቤቱ እራሱን የቻለ የጥገና ባለሞያ አለመኖሩን፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ምንም ዓይነት ቅፅ የሌላቸው መሆኑን ነገር ግን አሁን ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተሽከርካሪዎች ልኬት/ ኖርማላይዜሽን/ በየዓመቱ እንደማይደረግ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ለነዳጅ የሚመደበው በጀት ዝቅተኛ መሆኑን፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ነዳጅን በሚመለከት የሚመጡ መመሪያዎች ግልፅ አለመሆናቸውን፣ የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚልኩት የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ አለመሰጠቱን፣

  የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ወጥ /standardized / እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ መኖሩን፣ ስለነዳጅ አጠቃቀም ስልጠና መሰጠቱን እና ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዘጋጀታቸውንና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፤

317. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ፣በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣(ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ አዘጋጅቶ ያልሰጣቸው መሆኑን፤
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ) ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ፣በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣

በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድን፣ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ስልጠና ሰጥቶዋቸው እንደማያውቅ፤

- እንዲሁም በፍትህ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚሰራ በቂ ባለሞያ የሌለ መሆኑን፣ በቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ በክፍሉ በተሟላ ሁኔታ የተመደቡ ሠራተኞች አለመኖራቸውና ስልጠናም ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ በሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት ጽ/ቤት የጥገና አስተባባሪና የተሸከርካሪ ስምሪት ኦፊሰር የተሟላ አለመሆኑ እና የተሸከርካሪ ስምሪትና ቁጥጥር ስልጠና አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተሽርካሪዎች በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መሆኑን፤እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ የማያደርግ

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን፣ ስለተሽከርካሪዎች ብዛት፣ ዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት እና ኦዲትን በተመለከተ፤

318. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ(ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር ፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት ፣ በማዕድ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር ፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር

ኤጀንሲ የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በዚሁ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራ አከናውኖ እንደማያውቅ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ፔዳ፣ኤፍ ቢ፣ ዘንዘልማ፣ ይባብ፣ ሜዲሰን እና ማዕከላዊ)፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ በማዕድ፣የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር ፣ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት አከናውኖ እንደማያውቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. <u>የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ</u>

የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም

የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎችና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ፡-

319. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ላይ በዓመት አንድ ጊዜ አሰሪ መ/ቤቶች ላይ ምርመራ በማድረግ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን በጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ላይ ደግሞ ለጡረታ ባለመብቶች ክፍያ ከተፈፀመ በኋል በክፍያ ፔሮሉ መሰረት ትክክለኛነቱን በማረጋገጥና መተማመኛ በመፈራረም ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ፣ በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበው በገቢዎች ባለስልጣን ሲሆን በገቢዎች ባለስልጣን ላይ ግን ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ስለመደረጉ እና ከየትኞቹስ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ ስለመታወቁ ፡-

320. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የማይደረግበት ጊዜ መኖሩን፣ በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መ/ቤቶች ከሰራተኞች የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ብሩን ባንክ በሚያስገባው በግለሰብ ስም ወይም በዝውውር ስለሚያስገቡ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የማይታወቁ መሆኑን፣ አንዳንድ ራቅ ያሉ ወረዳዎች ላይ የጡረታ መዋጮ በወቅቱ የማይሰበሰብበት ሁኔታ መኖሩን ፣ ወረዳዎች ላይ ሀላፊ ሲቀያየር ስለጡረታ መዋጮ ግንዛቤ ስለማይኖራቸው እና የግንዛቤ እጥረት ስላለባቸው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ እንደማይሰበሰብ ፣ የጡረታ መዋጮውን ለበጀት የሚጠቀሙበት መ/ቤቶችም መኖራቸውን፣
- በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ከመንግስት ሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮን በተመለከተ በደቡብ ክልል ፋይናንስ ቢሮ (በባለበጀት መ/ቤቶች) የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ የሚደረግ መሆኑን፣ ከየትኞቹ መ/ቤቶችም እንደተሰበሰበ የሚታወቅ መሆኑን፣ ነገር ግን በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበው(በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች) የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማይደረግ መሆኑን፣ ከየትኞቹ መ/ቤቶች እንደተሰበሰበ የማይታወቅ መሆኑን ፣
- በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ከመንግስት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማያደርጉ መ/ቤቶች መኖራቸውን ፣ እንዲሁም በአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ቢሮ እና ከሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና

ኢኮኖሚ ልማት ዋና ፅ/ቤት ከመንግስት ሠራተኞች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለባቸው መ/ቤቶች ላይ በኤጀንሲው ምርመራ ስለመደረጉ ፡-

321. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት፣ በአርባምንጭ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ በሶዶ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የጡረታ መዋጮ ከፋይ በሆኑ አሰሪ መ/ቤቶች መሰብሰብ የሚገባው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰቡ በዓመት አንድ ጊዜ ምርመራ የሚደረግ ሲሆን በኤጀንሲው ዋና መ/ቤት በ 2006 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመሰብሰብ ምርመራ ያልተደረገ መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ከቀረቡት የምርመራ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ያላደረገ መ/ቤት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ፡-

322. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ያላደረገ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ እንዲከፍሉ የተለያዩ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎችን ከመፃፍ ውጪ እርምጃ እንደማይወስዱ፣
- በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ከሠራተኛ ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከሆነ ከበጀታቸው እንዲቀነስ የሚደረግ ሲሆን ፣ በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶች ከሆኑ ደግሞ ከባንክ ሒሳባቸው ላይ እንዲቀነስ የሚደረግ መሆኑን፣

- በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት ከመንግስት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያላደረጉ መ/ቤቶች ክፍያውን እንዲፈፅሙ ከማድረግ ውጪ ምንም ዓይነት ቅጣት እንደማይቀጡ ፣

- በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ከሠራተኞች ደሞዝ ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት መ/ቤቶች የተወሰደባቸው እርምጃ የሌለ መሆኑን፣ ለምሳሌ :- በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ውስጥ ከሚገኙ አሰሪ መ/ቤቶች መካከል በ2008 በጀት ዓመት በወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት የሲቪል ሠራተኛ 98,790.01 /ዘጠና ስምንት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ብር ከ ዜሮ አንድ ሳንቲም/ ፣ ከወታደር 142,601.88 /አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አንድ ብር ከ ሰማንያ ስምንት ሳንቲም/ በድምሩ ብር 241,391.89 /ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም ያልተከፈለ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ እዳ ያለበት መሆኑን፣

- በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ ቀንሰው በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት መ/ቤቶች ከበጀታቸው ወይም ከአካውንታቸው እንዲቀነስ ከማድረግ ውጪ የሚወሰድባቸው እርምጃ የሌለ መሆኑን፣

- የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለበት ሲሆን ይህንን ውዝፍ ለማስከፈል ከአካውንታቸው ላይ እንዲቀነስ በተደጋጋሚ ለሆሳዕና ቅርንጫፍ ንግድ ባንክ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ባንኩ ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

- እንዲሁም የክትትል ኦዲት ቡድኑ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሪጅን ፅ/ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የምርመራ ሪፖርት ለመመልከት እንደቻለው ከሠራተኞች ሊቀነስ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በመቀነስ በወቅቱ ለፈንዱ ገቢ ያላደረጉ መ/ቤቶች ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን

ከማስከፈል ውጪ በአዋጁ መሰረት ምንም ዓይነት ቅጣት እንዲቀጡ እና ወለዱን እንዲከፍሉ የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግለውን የሂሳብ አሰራር ማንዋል (መመሪያ) ወቅታዊ / ዘመናዊ/ እንዲሆን ስለመደረጉ፡-

323. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ለጡረታ ፈንዱ የሚያገለግል በ1992 ዓ.ም የወጣ መመሪያ እና ቻርት እንዳለ እና መመሪያውን ወቅታዊ /ዘመናዊ / ለማድረግ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ (የሂሳብ መግለጫ) በየዓመቱ መዘጋጀቱን እና ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፡-

324. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የ2006 ዓ.ም እና የ2007 ዓ.ም የሂሳብ መግለጫ የተዘጋጀ ሲሆን ፣ የ2008 ዓ.ም የሂሳብ መግለጫ ያላለቀ መሆኑን ፣ የኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ ደግሞ የ2006 ዓ.ም ብቻ ያለ ሲሆን የ2007 ዓ.ም ኦዲት ስራው በኦዲት ኮርፖሬሽን እየተሰራ መሆኑን፣ በ 2008 ዓ.ም ኦዲት እንዳልተደረገ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ የኤጀንሲው ሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሒሳብ አካውንት የሌላቸው በመሆኑና ከአሰሪ የመንግስት መ/ቤቶች የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ገቢ እንዲደረግ የሚያደርጉት በዋናው መ/ቤት በተከፈተ የጡረታ ፈንድ አካውንት ስለሆነ የሒሳብ ትንታኔ/ የሒሳብ መግለጫ/ የማያዘጋጁ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአሰሪ መ/ቤቶች ስም የተከፈተው የገቢ ሂሳብ ሌጀር ወቅታዊ ስለመሆኑ፡-

325. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው የሪጅን ፅ/ቤቶች እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሂሳብ በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር ተመዝግቦ እንዲያዝ የተደረገ ሲሆን ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት የ2006 ዓ.ም እና የ2007 ዓ.ም ሌጀር ፖስት የተደረገ ሲሆን የ 2008 ዓ.ም ፖስት ያልተደረገ /ያልተመዘገበ/ መሆኑን፣ በወላይታ ሶዶ ቅ/ፅ/ቤት ከ የጡረታ መዋጮ ገቢ ሂሳብ በአሰሪ መ/ቤቶች ሥም በተከፈተ ሌጀር ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን ፣ በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት በአሰሪ መ/ቤቶች ስም የተከፈተ የ 2006 ዓ.ም ሌጀር የሌለ ሲሆን የ2007 እና የ 2008 ዓ.ም ደግሞ በተሟላ መልኩ ፖስት ያልተደረገ /ያልተመዘገበ/ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለሪል ስቴት ወጪ ተደርጎ የተከፈለው ሂሳብ የተመለሰ ስለመሆኑ እና ቦታው ለሚመለከተው የመንግስት አካል መረከቡን በተመለከተ፡-

326. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ኤጀንሲው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ህንጻዎች ለመገንባት አሰላ፤ ደሴ፤ ጅማ እና ደብረማርቆ ለሚካሄድ ሪል ስቴት ብር 5,301,741.17 ያወጣ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የደሴ ከተማ ብር 84,496 / ሰማንያ አራት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ገቢ የተደረገ መሆኑን ፣ የጅማ ብር 355,548.46 ገቢ የተደረገ ሲሆን የአሰላ እና የደብረማርቆስ ጉዳዩ በህግ የተያዘ መሆኑን ስራው ከሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ቃለ-መጠይቅ እና ከማስረጃዎች ታውቋል፡፡

የጡረታ ፈንዱ የማስረጃ አያያዝና አጠባበቅ አንድ ወጥ እና አስተማማኝ መሆኑን በተመለከተ ፡-

327. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የኤጀንሲው የሪጅን እና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በመሀል ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአዲስ አበባ ሪጅን ፅ/ቤት እና በዋናው መ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎች የመረጃ አያያዝ በባህር መዝገብ /በማንዋል/ እና በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ /በፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር/ እንደሆነ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ቢገልፁም በፔንሽን አድሚን ሶፍትዌሩ ላይ መረጃዎች ሙሉ ለሙሉ እየተመዘገቡ አለመሆናቸውን፤
- እንዲሁም በደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት ፣ በአርባምንጭ ቅ/ፅ/ቤት፣ በሶዶ ቅ/ፅ/ቤት እና በሆሳዕና ቅ/ፅ/ቤት የመንግሥት ሠራተኞችን ምዝገባ የሚመለከቱ ማስረጃዎች የመረጃ አያያዝ በባህር መዝገብ /በማንዋል/ እና በሶፍት ኮፒ / በወርድ ወይም በኤክሴል / ሲሆን ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ / ፔንሽን አድሚን ሶፍትዌር / የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለጡረታ መዋጮ ሰብሳቢዎች ፣ አበል ከፋዮች እና አሰሪ መ/ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ስለመዘጋጀቱ ፡-

328. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የጡረታ ከፋይ እና ሰብሳቢ አካላት ለመረዳት እንደተቻለው ኤጀንሲው ለደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለደቡብ ሪጅን ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት፣ ለአርባምንጭ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለአርባምንጭ ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን፣ ለወላይታ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ለሆሳዕና ከተማ አስተዳደር

ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ዋና ፅ/ቤት እና ለኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሆሳዕና ቅርንጫፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አዘጋጅቶ ሰጥቷቸው የማያውቅ ሲሆን፣ ለወላይታ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት እና ለወላይታ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ደግሞ ከ 2006 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ አንድ ጊዜ ብቻ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

III. የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያዘጋጀው የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ዝርዝር መግለጫ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ስለሂሳብ ሪፖርቶች

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 11 አንቀፅ 59 መሰረት ሚኒስቴሩ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትና የማእከላዊ ግምጃ ቤትን ሂሳብ በማጠቃለል የፌደራል መንግስትን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ ሂሳብ አቅራቢ መ/ቤቶች በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲት ተደርገው በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ ሳያቀርቡ ሂሳቡ የተጠቃለለ መሆኑ ታውቋል፡፡

2. የገቢ ሂሣብ

2.1 የ2007 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ገቢ እቅድና ክንውን

2.1.1 ግኝት

በ2008 በጀት ዓመት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች መሰብሰብ ያለበት ገቢ በታቀደው መሰረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት አመቱ የታቀደው እቅድና በትክክል የተሰበሰበው ገቢ ሲነጻጸር በሁለት ድርጅቶች በድምሩ ብር

322,846,000.00 ክንውኑ አንሶ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 41 ተመልክቷል)

ስጋት

የገቢ መሰረተ ግምቱ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ ካልሆነ ውሳኔ ሰጭውን አካል ሊያሳሳት ከመቻሉም በተጨማሪ የገቢ እቅዱ ከክንውኑ ጋር እየተመሳከረ የማይገመገም ከሆነ ወቅታዊ የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ሊያዳግት ይችላል፡፡በተጨማሪም የታቀደው ገቢ በአግባቡ ባለመሰብሰቡ ምክንያት የመንግስት የበጀት ጉድለት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ገቢ የሚያደርጉት ከሰበሰቡት ገቢ ለስራቸው ተጠቅመው የሚተርፈውን ገቢ የሚያደርጉ በመሆኑ የሰበሰቡት እቅዱን መሸፈን እንደልቻለ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለ2008 በጀት ዓመት ገቢ እንዲሆን መጀመሪያ የታቀደው 279.2 ሚሊዮን ብር ሲሆን በተጨማሪ 250.00 ሚሊዮን ብር በእቅድ እንዲያዝ የተመደበ ቢሆንም ገቢ እንዲያደርጉ ለቀረበላቸው ጥያቄ መክፈል እንደማይችሉ በደብደቤ በመግለጻቸው በበጀት ዓመቱ ለተጨማሪ በጀት የተያዘው ገቢ ሊሆን እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት በተጨማሪ እንዲያዝ የተጠየቀው የገቢ በጀት እቅድ በጸፉት ደብዳቤ መሰረት ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ተቀባይነት አግኝቶም ከሆነ ከበጀት እቅዱ ውስጥ እንዲወጣ አልተደረገም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በእቅዱ መሰረት ከእያንዳንዱ ድርጅት መሰብሰብ ያለበት ገቢ ክትትል በማድረግ እና ሊሰበሰብ ያልቻለበት ምክንያት በማጣራት የመፍትሔ አቅጣጫ ሊበጅለት ይገባል፡፡

2.2 በመልሶ ማበደር ስምምነት ከተሰጠ ብድር ያልተሰበሰበ የወለድ ሂሳብ፤

ግኝት

መንግስት ከውጭ ሀገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነት ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2008 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ ከሦስት ድርጅቶች ላይ በድምሩ ብር 184,611,464.40 የወለድ ሂሳብ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በተመሳሳይ በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 86,660,055.16 ተገኝቶ የማሻሻያ ሃሳብ የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል:: (ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል)

		ያልተከፈለ		
ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ዋና ገንዘብ	ወለድ	ጠቅላላ ድምር
1	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	0.00	174,456,726.04	174,456,726.04
2	የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን	0.00	72,259.17	72,259.17
3	ብረታ ብረትና ኢ.ጂነሪንግኮርፖሬሽን	0.00	10,082,479.19	10,082,479.19
	ጠቅላላ ድምር	**0.0**	**184,611,464.40**	**184,611,464.40**

ስጋት

የብድር ተመላሽ በወቅቱ አለመሰብሰቡ መንግስት በእቅድ የያዛቸው ስራዎች በበጀት እጥረት ላይከናወኑ ይችላሉ፡፡

የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ያለባቸውን የወለድ ክፍያ በወቅቱ እንዲከፍሉ በደብዳቤ ጥያቄ ከመቅረቡም ባሻገር ክፍያው እንዲፈፀም

በአካልም ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ ሆኖም ባለባቸው የገንዘብ እጥረት ምክንያት ክፍያውን ለመፈፀም እንደማይችሉና ለወደፊት ክፍያውን ለመፈፀም የሚያስችል ተግባራትን እያከናወኑ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመ/ቤታችን ኃላፊዎች የድርጅቱ ኃላፊዎች ተጠርተው ውይይት ተደርጎ በአስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል ማስታወሻ ቀርቦ ውሣኔ እየጠበቀ ነው፡፡

- ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ለኮርፖሬሽኑ በመልሶ ማበደር የተላለፈው ገንዘብ ብዙ ባይሆንም የወለድ ክፍያ በወቅቱ አልተፈፀመም፡፡ የሚሰጡት ዋናው ምክንያት የገንዘብ እጥረት እንዳለባቸው ነው፡፡ በስራ ክፍሉ በኩል ጠንካራ ክትትልና ወቅቱን የጠበቀ የክፍያ ጥያቄ እያቀረበ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የመ/ቤታችን ኃላፊዎች ከኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ጋር በጉዳዩ ላይ ውይይት እንዲያደርጉበት ማስታወሻ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በቅርቡ መፍትሄ እንደሚያገኝ ይጠበቃል፡፡
- የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን እጅግ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ በመልሶ ማበደር የተላለፈለት ሲሆን ወቅቱን ጠብቆ እየከፈለ የነበረ ሲሆን አሁን ባለበት የገንዘብ እጥረት ክፍያውን እንዳልፈፀመ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በቅርቡ ያለበትን ክፍያ እንደሚፈጽም መግባባት ላይ ተደርሷል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመልሶ ማበደር ገንዘብ ከወሰዱ ድርጅቶች ተመላሽ መደረግ የሚገባውን የዋና ገንዘብና ወለድ ክፍያ በቂ የሆነ ክትትል በማድረግ ተበዳሪው ዕዳውን በወቅቱ እንዲከፍል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.3 በ2008 በጀት ዓመት በአመታዊ በጀት አዘገጃጀት ላይ በእቅድ ሳይያዝ የተሰበሰበ ገቢ

ግኝት

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 5 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2ሀ መሰረት አመታዊ በጀት ሲዘጋጅ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ሊይዝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር በ2008 በጀት አመት ውስጥ ከአገር ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ ሙሉ በሙሉ በበጀት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ሳይካተት በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ብር 400,369,539.68 ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 42 ተመልክቷል)

ስጋት

ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ በአግባቡ ተለይቶ በበጀት ዝግጅት ላይ ካልተካተተና አስቀድሞ ካልታወቀ መንግስት ሌሎች ምንጮችን ተጠቅሞ ለመሰብሰብ በሚያሳልፈው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤

- በአባሪ 42 ከተራ ቁጥር 1-9 በተመለከተው መ/ቤቶች በድጋሚ በሌሎች ሂሣብ መደቦች በሚያቀርቡት ሪፖርት ማስተካከያ እንደሚሠራለት እንገልጻለን፡፡
- በተራ ቁጥር 10 የተመለከተው፡- የዲላ ዩኒቨርስቲ አላግባብ ብድር ሰጥቶ የሰበሰበሰው ወለድ ብር 58,984.80 በድጋሚ ይህንን የህግ ጥሰት እንዳይፈጽሙ እና የተሰጠው የብድር ገንዘብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ እንዲያደርጉ ደብዳቤ የተጻፈላቸው በመሆኑ ክትትል ይደረግበታል፣
- ተራ ቁጥር 11 እና 12 በሂሣብ መደብ 2275 እና 2277 በበጀት ሳይያዝ የተገኘ ገቢ ረጂዎች አስቀድመው እንደሚሰጡ ባለመታወቁ በዓመቱ መጨረሻ የተገኘ እርዳታ በመሆኑ ነው፤

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በባለፈው በጀት አመታት ከተለያዩ ምንጮች ገቢ የተሰበሰበባቸው የሂሳብ አርእስቶች ሙሉ በሙሉ በበጀት የተካተቱ ለመሆኑ እየተረጋገጠ በጀቱ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

2.4 <u>ከመንግስት ልማት ድርጅቶች ሽያጭ እና ትርፍ ድርሻ በእቅዱ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

<u>ግኝት</u>

ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መንግሥት በሽያጭ ያስተላለፋውን ድርጅቶች እና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ገቢ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ እስከ ሰኔ 30, 2008 ዓ.ም ድረስ ከሰባት የተለያዩ ድርጅቶች በድምሩ ብር 3,554,039,809.54 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ (ዝርዝሩ በአባሪ 41/ሀ ተመልክቷል)

<u>ስጋት</u>

ይሰበሰባል ተብሎ በእቅድ የተያዘው የመንግስት የ2008 በጀት ዓመት ትርፍ ድርሻና መንግስት ልማት ድርጅቶች ሽያጭ በወቅቱ አለመሰብሰቡ የበጀት እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤</u>

የ2008 በጀት አመት ያልተሰበሰበ ገቢን በተመለከተ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የልማት ድርጅቶች ዕቅድ አቅራቢ፣ የትርፍ ድርሻ፣ የብድር ተመላሽ፣ የሊዝ ክፍያና ልዩ ልዩ ገቢዎች የሚከታተልና የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ውል ተዋዋይና አስፈጻሚ ነዉ፡፡ስለዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች በተቋቋሙበት አዋጅና ደንብ መሰረት እንዲሁም የልማት ድርጅቶች ግዥ የፈጸሙ አካላት በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን እንዲወጡ የተጠያቂነት ስርዓት መጠናከር አለበት፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤታቸውም የመንግስት

የልማት ድርጅቶች ጉዳይ የሚከታተልና የሚታየውን የገቢ አሰባሰብና የመረጃ ክፍተት ችግር ለማቃለል አንድ የተጠናከረ ቡድን ተመስርቶ እየሰራ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በበጀት አመቱ ውስጥ ከተለያዩ ከመንግስት ልማት ድርጅቶች በሽያጭ የተላለፈውን እና የዓመቱ ትርፍ ድርሻ ክፍያ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5 <u>በዕቅድ ተይዞ ሙሉ በሙሉ ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 315,735,747.00 ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 10ለ የሂሣብ መግለጫው የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱን የአገር ውስጥ ገቢ በጀት ከተሰበሰበው ጋር የውጭ አገር ብድር/እርዳታ የታወጀ በጀት ከተስተካከለው በጀት እና ከወጭው ጋር ተነፃፅሮ መቅረብ እንደለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ እንደሰበሰብ ተብሎ በየገቢ አርዕስቱ በዕቅድ የተያዘው ገቢ በዕቅዱ መሠረት እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከታቀደው ዕቅድ ብር 315,735,747.00 ሙሉ በሙሉ ያልተሰበሰበ ገቢ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 42/ሀ ተመልክቷል)

<u>ስጋት</u>

ገቢው ታሳቢ በማድረግ የታቀዱ ስራዎች እንዳይሰሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

ለዕቅዱ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና ክትትል በማድረግ እያንዳንዱን ገቢ በዕቅዱ መሠረት እንዲሰበሰብ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤</u>

- በአባሪ 42/ሀ ተራ ቁጥር ከ1 - 4 የተገለጸው በእቅድ የተያዘ ገቢ ያልተሰበሰበ በተመለከተ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲሁም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ፊሲካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ማብሪሪያ እንዲሰጥ በደብዳቤ ተገልጾላቸዋል፡፡
- ተራ ቁጥር 5. በጀቱ በሂሳብ መደብ 1432 ተይዞ ገቢው በ1489 በሂሳብ መደብ የተመዘገበ በመሆኑ ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይደገም ክትትል እናደርጋለን፡፡
- ተራ ቁጥር 6 እና 7 በተመለከተ የካናዳ አለም አቀፍ ልማት ትብብር እና የዴንማርክ የልማት ትብብር በእርዳታ ሂሣብ መደብ 2256 እና 2286 በሚል እቅድ ቢያዝም እርዳታውን ለመለገስ ይሁንታ ያሳዩት ለጋሽ ድርጅቶች ገንዘቡን ያልሰጡ በመሆኑ ነው፡፡

2.6 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 5,533,492.54 እና ተንጠልጣይ የሠነድ ሂሳብ 129,535,767.84</u>

<u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 7 እንደተገለጸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በውስጥ ቁጥጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ሳያቋርጥ ክትትል ማድርግና አግባብነት በሌላቸው፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ውጤታማና ስኬታማ ባልሆኑ ግኝቶች ላይ ወቅታዊና ተገቢ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ላይ በሂሳብ መደብ 4202 ብር 5,533,492.54 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የሚታይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 4,255,538.02 ቀጥሎ በተመለከቱት 7 መ/ቤቶች ላይ የሚፈለጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 41/ለ ተመልክቷል)

በአባሪ 41/ለ ከተራ ቁጥር ከ1 እስከ 5 ያሉት መ/ቤቶች ባለፈው ኦዲት ወቅት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምት

ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሂሳብ መደብ 4201 ብር 129,535,767.84 ውዝፍ ተንጠልጣይ ሰነድ የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 78,260,406.33 ቀጥሎ በተመለከቱት 7 መ/ቤቶች ላይ የሚታዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 41/ሐ ተመልክቷል)

በአባሪ 41/ሐ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱት መ/ቤቶች ባለፈው ኦዲት ወቅት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምት ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

በጉድለት የታየው ገንዘብ በወቅቱ እንዲተካ እርምጃ አለመወሰድ ተመሳሳይ ጉድለት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ቅድሚያ ክፍያዎች በተወሰነው የግዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረዱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል።

የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤

በሂሳብ መደብ 4201 እና 4202 የተዘረዘረውን ባለበጀት መ/ቤቶችና ከሌሎች የፌደራል ባለበጀት ሂሳብ አቅራቢዎች በአጠቃላይ የተሰብሳቢና የተከፋይ የእርጅና ዘመን መቼ እንደሚወራረድ እና የተወሰዱ እርምጃዎች የምንከታተልበት ከሚያቀርቡት ሪፖርት ጋር አያይዘው የሚያቀርቡ ሲሆን ለዚህም አስፈላጊ ክትትል እና የዳሰሳ ጥናት ተደርጎበት ለማኔጅመንቱ ሪፖርት መጋቢት/2009 የቀረበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ከፍተኛ የሰነድ ክምችት በታየባቸው ባለበጀት መ/ቤቶች ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል

በማድረግ በጉድለት የታየው ገንዘብ እንዲተካ በውዝፍ የሚታየው ተንጠልጣይ ሂሳብ እንዲወራረድ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.7 ተቀጽላ ሌጀር የሌለው የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳብ

ግኝት

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 በሂሳብ መዝገብ ላይ ምዝገባ የተከናወነለት ሂሳብ በየሂሳብ መደቡ ተለይቶ በሂሳብ ሌጀር ላይ መመዝገብ እንዳለበት ያዛል፡፡በዚሁ መሰረት የበጀት ዓመቱ ሂሳብ ሪፖርት ሲዘጋጅ ለተሰብሳቢ እና ለተከፋይ ሂሳቦች ተገቢው ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶላቸው በአግባቡ የሚያዙ መሆኑን እና ተገቢው ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከ2007 በጀት ዓመት የዞረ በድምሩ ብር 41,252,909.74 በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4209፣4210 እና 4211 ለ2008 በጀት ዓመት የመነሻና የመክፈቻ ሂሳብ ተብሎ የተመዘገበ ቢሆንም ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ተሰብሳቢው ሂሳብ ከማን ላይ እንደሚሰበሰብ ባለመገለጹ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ከላይ ከተጠቀሰው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 800,000.00 ባለፈው ኦዲት ወቅት በጉዳዩ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምት ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የተከፋይ ሂሳብ ከ2007 በጀት ዓመት የዞረ በድምሩ ብር 1,801,530.99 በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5028 እና 5054 ለ2008 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳብ ተብሎ የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ ቢሆንም ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ተከፋይ ሂሳቡ የተከሰተበት፣ የቆየበት ጊዜ እና ባለጥቅሙ ባለመገለጹ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 42/ለ ተመልክቷል)

ስጋት

የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶላቸው በአግባቡ እየተመዘገቡ ካልተያዙ ከማን እንደሚሰበሰቡ እና ለማን እንደሚከፈሉ

ስለማይታወቅ ለቁጥጥር እና ለክትትል አመቺ ስለማይሆን የገንዘብ ብክነትና ጥፋት ሊከሰት ይችላል፡፡

<u>የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤</u>

በተሰብሳቢ ሂሳብ በC1 በሂሳብ መደብ 4209 የዞረዉ የተሰብሳቢ ሚዛን ብር 8,269.99 በመጣራት ሂደት ላይ መሆኑን፡ C2 በሂሳብ መደብ 4209 የተሰብሳቢ መነሻ ብር 444,185.95 በቀጣይ ተጣርቶ ተቀጽላ ሌጀር የሚከፈትለት መሆኑን፡ በC8 በሂሳብ መደብ 4209 ተሰብሳቢ መነሻ ሂሳብ ብር 40,000,453.77፤ በE2 በሂሳብ መደብ 4210 ብር 800,000.00 ወደፊት ተጣርቶ የሂሳብ ማስተካከያ የሚዘጋጅለት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054 ብር 1,801,530.99 በማኔጅመንት ውሳኔ እንዲሰጥበት የቀረበ እና ወደፊት ማስተካከያ የሚሰራለት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር በመክፈት ሂሳቡ በአግባቡ ተመዝግቦ እንዲያዝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.8 <u>ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተላቸው መ/ቤቶች በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፤</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ቢያመለክትም መስሪያ ቤቶች እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ የሚያቀርቡት ሪፖርት የሌለ መሆኑን ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ ላይደረግ ይችላል፡፡

<u>የኦዲት ተደራጊዎች ምላሽ፤</u>

መ/ቤቶች ሌተር ኦፍ ክሬዲት የከፈቱ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ክትትል በማድረግ ተራፊውን ወደ መንግስት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ለማድርግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡(ለምሳሌ የመከላከያ ሚ/ር) ስለሆነም በዳይሬክቶሬታችን በኩል ከኢትየጵያ ንግድ ባንክ በሚቀርበው መረጃ መነሻነት የተጠናቀቁ ሌተር ኦፍ ክሬዲቶችን በመከታተል ተራፊውን ገንዘብ ገቢ ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን በማለት ገልጸዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመመሪያው መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ እየተደረገ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

IV. <u>የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች</u>

1 <u>መግቢያ</u>፣

ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ት/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር (PBS III) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት

ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2008/9 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው ሲሆን ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች/ወረዳዎች ብዛትና ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

1.1 በ2008/9 የኦዲት ዘመን የታዩ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ አቅራቢዎች ብዛት

በ2008/9 የኦዲት ዘመን (ከጥር1/2008 እስከ 30፣የካቲት/2009) 300 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሶስተኛ ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶችን ለማከናወን ታቅዶ በ238 የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ላይ የተለዩት (የተገኙት) ድክመቶች/ግድፈቶች (identified internal control weakness) እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች/አስተያየቶች (Recommendation) የተላከላቸው ተጠቃሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ወጭ ተደርጎ ለሚመለከተው አከል የተላከ የስራ አመራር ሪፖርት	የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር)	በመቶኛ (%)
1	በስራ አመራሩ የተገለጹት፣ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች	238	100
	ድምር	**238**	**100**

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ለእያንዳንዱ መ/ቤት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦችን የያዘ የስራ አመራር የተላከላቸው ዝርዝር በተቀጽላ (Annex I) በአባሪ-33 ተያይዟል፡፡

1.2 <u>በ2008/9 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

በ2008/9 የኦዲት ዘመን (ከጥር1/2008 እስከ 30፣የካቲት/2009) 300 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሶስተኛ ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ላይ የተለዩት (የተገኙት) ድክመቶች/ግድፈቶች (identified internal control weakness) እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች /አስተያየቶች (Recommendation) እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ጥሬ ገንዘብ

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- ከከዝና (ከሳጥን) በተንጠልጣይ የሚከፈል የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች በወቅቱ የማይወራረድ፣ አሊያም ወደ ሂሳብ ክፍል ዞሮ በተሰብሳቢ የማይያዝ መሆኑ፣

ተሰብሳቢእና ተከፋይ ሂሳብ

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው እና አለመፈጸማቸዉ፡፡

- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ዋና እና ተቀጽላ ሌጀሮች አለመቋቋም እና የተቀጽላ ሌጄሮች ምዝገባ ወቅታዊ አለመደረግ፤
- ለተወሰኑ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀሮች በለማቋቋሙ ምክንያት ባለቤቱ የማይተወቅ መሆኑ፤

ወጪዎች

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የውሎ አበል ፎርምና ተመኑ (rate) በአግባቡ አለመሞላት፡
- ለነዳጅና ለቅባት ፍጆታ ደካማ የውስጥ ቁጥርጥር ስረዓት መኖሩን፣
- አልፎ አልፎ ግዥዎች ከደንብና መመሪያ ውጭ የሚፈጸም መሆኑ፤

የሂሳብ ሪፖርት

- ወርሃዊ እና ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ከፍ ላለው የመንግሰት አከል አለመላካቸው፣ ንብረት
- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች አለመቋቋም፣
- ለቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ አዳዲስ ማሽኖች እና የህክምና መገልገያዎች ያለሥራ ለረጅም ጊዜ መቀመጣቸው፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣
- በአብዘኛዉ መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎች አለመመዝገብ፡
- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በወቅቱ አለመወገድ እና ተለይቶ ለብቻ የማይቀመጡ መሆኑ፣

- በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች የተሽከርካሪ ፕሮፋይል፣ የባለቤትነት ደብተር ያለመኖር እና አልፎ አልፎ ታርጋ ቁጥር/ሰሌዳ ቁጥር (በአብዘኛው ሞተር ሳይክሎች) የማይሰጥ መሆኑን፣
- በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊዎች የሁሉም ተሽከርካሪ የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፣

የክትትል ኦዲት

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ፤

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣
- ተገቢው ትኩረት አለመስጠት
- የኃላፊዎችና የሥራ ሂደት ባለቤት ቶሎ ቶሎ ከቦታቸው መነሳት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የተለዩት ችግሮች ተወግደው ተገቢው ማሻሻያ እርምጃ እንዲወሰድና የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲጠናከር በተላኩት የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመሠረታዊ አገልግሎቶች 'PBS III' ፕሮጀክት የ2008 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ (Project Financial Statement) የዓለም አቀፍ የኦዲት

ደረጃዎችን በመከተልና በስምምነቱ በተቀመጠው ቢጋር (Terme of Reference) መሠረት ኦዲት ተደርጎል፡፡

የኦዲት ስራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ደረጃ በተዘጋጀው የተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የተከናወነ ዓመታዊ ኦዲት ሲሆን፣ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት “ነቀፌታ የሌለበት” (Unqualified) ነው፡፡

V. ልዩ ኦዲት

በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች ትዕዛዝ ፣ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 7/ሰባት/ የልዩ ኦዲትና አንድ ክትትል ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል። በዚህም ምክንያት በመደበኛው የኦዲት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮብን አልፏል።.

የተከናወኑትም ኦዲቶች፣

1. በቀድሞ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በፍ/ቤት የታዘዘ የአንድ ገንዘብ ያዥ ከ2002 እስከ ሐምሌ 2007 ዓ.ም ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት
2. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የንብረት ሂሳብ ልዩ ኦዲት፤
3. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት በፌዴራል ትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ የነበሩት ከግንቦት/2006 ዓ.ም እስከ ህዳር /2007 ዓ.ም ድረስ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት፤
4. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በቀረበ ጥያቄ የክልሉን ዋና ኦዲተር ጽ/ቤት የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት፤
5. የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን፣
6. የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን የፕሮጀክት ሂሳብ
7. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ልዩ ኦዲት እና
8. በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ቀደም ባሉት ኦዲቶች ስለታዩት የተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ ላይ የተደረገው የክትትል ኦዲት

ናቸው።

የኦዲት ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል።

የ2008/2009 ኦዲት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. መግቢያ

የፌዴራልዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሠት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሠት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የብድርና እርዳታ ሂሣቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጄክቶችንና የዕርዳታ ሂሣቦች በሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ያስደርጋል፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መሰረት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች እንዳስፈላጊነቱ ማሳሰቢያ በመስጠት፣ ውጤቱን ከሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2008/2009 ኦዲት ዓመት /ከሐምሌ/2007 እስከ ጥር/2009 ዓ.ም የኦዲት ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የደረሱ/ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2008 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ

2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲቋቋም፣ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ

የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው ክትትል እንዲያደርጉና አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ በግልባጭ እንዲያውቁት ያይደረጋል፡፡

2.3 የስራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2008 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘቸውና ያከናወናቸው የሂሳብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

መግለጫ	የ2008 በጀት ዓመት			የ2007 በጀት ዓመት ሲነጻጸር	የ2008 ክንውን በመብለጥ(በማነስ)
	ዕቅድ	ክንውን	ልዩነት	ክንውን	ልዩነት
ወጪ የተደረጉ ኦዲት ሪፖርቶች	260	238	22(2%)	248	(10) (4%)

ከላይ እንደተመለከተው የ2008 ክንውን ሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር በ22 ሪፖርቶች ወይም በ8% የሚያንስ ሲሆን፣ ከ2007 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነጻፀር በ10 ሪፖርቶች ወይም በ4% በማነስ አሳይቷል። ለዚህም ዋና

ምክንያቱ በቁጥር 49 ረቂቅ ኦዲት ሪፖርቶች ለደንበኞች ተልከው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምልሽ ያልተሰጠባቸው በመሆኑ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ወጪ የሆኑት 238 ሪፖርቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Clean opinion/ 152፤ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆኑም ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Except for/ 59 ፤አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው /Disclaimer/ 27 ናቸው፡፡

2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ

በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል 142 ሲሆን፣ በ2008 በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ 13 በድምሩ 155 ሰራተኞች ውስጥ በጡረታ የተገለሉ 2፤በሞት የተለዩ 1 እና በፈቃዳቸውና ልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ 9 በመሆኑ፣ በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 143 ሰራተኞች በስራ ላይ እንደነበሩ ተውቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል ሙያ ደረጃ ሲተነተን ፕሮፌሽናል /ኦዲተሮች/ 99 ፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 44 ሲሆኑ፣ በፆታም ሲታይ ወንድ 94 እና ሴት 49 በድምሩ 143 ናቸው ፡፡

2.5 የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ከሆነው የኦዲት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትንና ሀገርቱም በዚህ ሙያ ረገድ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ በመሆኑ፣በእንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው አሶሴሽን ኦፍ ሰርቲፋይድ አከውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የኮርፖሬሽኑ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ የፈተና ዝግጅት ጊዜ፣ በገንዘብና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና በደመወዝ ጭማሪና በመሳሰሉት ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት 30 ኦዲተሮች የመጀመሪያ ደረጃ/Fundamental stage/፣ 7 ደግሞ በፕሮፌሽናል ደረጃ / ትምህርቱን በተለያየ ደረጃ በመከታተል ላይ ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑን ሰራተኞች የሙያ ብቃት ከፍ ለማድረግና የስልጠናውንም ጥራት ለማገዝ ባለው ዓላማ መሰረት የኮርፖሬሽኑ ቤተ መጽሐፍት ለተጠቃሚዎች ዘወትር በስራ ቀናት ክፍት በማድረግ እና እንዳስፈላጊነቱ ከ11፡30 በኋላ፣ ቅዳሜና እሁድ እና በበኃላት ቀናት ክፍት በማድረግና የሚያስፈልጉ መጻሕፍት በማቅረብ በአገልግሎቱ ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ለአንድ ሰራተኛ የሀገር ውስጥ የስልጠና ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል::

የኦዲት ሙያ ያለቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፣ ኮርፖሬሽኒ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሰጠው ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 <u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ</u>

በኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሂሣብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡

በ2008 በጀት ዓመት በእቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፣ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2008 የፋይናንስ እቅድና ክንውን/በብር/

መግለጫ	ገቢ	ወጪ	ያልተጣራ ትርፍ /ከታክስ በፊት/	የተጣራ ትርፍ /ከታክስ በኋላ/
ዕቅድ	28,994,382.00	24,650,964.00	4,343,418.00	3,040,393.00
ክንውን	33,920,965.00	22,299,745.00	11,621,220.00	7,277,802.00
ክንውን በመብለጥ (በማነስ)	4,926,583.00	(2,351,219.00)	8,118,887.00	5,078,494.00
ልዩነት በመቶኛ/%/	17	(10)	186	167

የ2008 የእቅድ ክንውን ከ2007 ጋር ሲነጻፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ /በብር/

የበጀት ዓመት	ገቢ	ወጪ	የተጣራ ትርፍ
2008	33,920,965.00	22,299,745.00	8,118,887.00
2007	26,595,582.00	19,303,777.00	5,088,358.00
ልዩነት የ2008 ክንውን በመብለጥ (በማነስ)	7,325,383.00	2,995,968.00	3,030,529.00
ልዩነት በመቶኛ/%/	**21.59**	**13.43**	**37.32**

የ2008 የገቢና ወጪ ከ2007 ጋር ሲነጻፀር ገቢና ወጪው በሰንጠራዡ እንደሚታይ ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል።

3. <u>የ2008/2009 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች</u>

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከሐምሌ/2007 እስከ ጥር /2009 ዓ.ም አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ(ቀደም ሲል እስከ ሰኔ 30 ደረሱንን ብቻ ነበር ሲቀርብ የነበረው) ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 113 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 192 በድምሩ 305(ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡

በነዚህ ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 203፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 69 ፣አቀም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 29፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የቀረበባቸው(Adverse) 1 ፤ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 3 እና

ሌሎች 1 በድምሩ 306 ናቸው፡፡ አቀም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው መ/ቤቶች ውስጥ ዘጠኙ/9/ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በስሩ የሚገኙ የትምህርት ፋኩሊቲዎች ከ1999 አእስከ 2006 በጀት ዓመታት ኦዲት ተደርጎ የቀረቡ ሪፖርቶች ናቸው:: የ2007 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ስለቀረበ በዝርዝር አልተያዘም፡፡

4. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

በ2008/2009 ኦዲት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብለው ወይም የጎላ ችግር ስላለበት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታ እና ከአንድ በጀት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው ድርጅቶች

አቋም ሊወሰድበት ስላልተቻለ (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት መስጠት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ ያላስቻሉ ዋና ዋና ምክንያቶች/ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

4.1.1 የኢትዮጵያ ኤልክትሪክ ኃይል

እ.አ.አ. July 7/2014 የተጠናቀቀው የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ቀጥሎ በተጠቀሱት ጉልህ ጉዳዮች የተነሳ በሂሳቡ ላይ አሰስተያየት መስጠት እንደሚችሉ በሪፖርቱ ተጠቅሷል።

- ድርጅቱ የተመሠረተው እ.ኤ.አ Dec 9/2013 የቀድሞ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ለሁለት ሲከፈል ሲሆን፣ የኮርፖሬሽኑ መብትና ግዴታዎች በዚያው ዕለት ወደ ድርጅቱ እንዲተላለፉ ተደርጓል። እነዚህን

መብትና ግዴታዎች በሂሳብ መግለጫዎች ውስጥ መካተት ያለባቸው፤ ቢሆንም በሚመለከተው በተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተዘጋጀ ሪፖርት ስላልቀረበልን፣ በድርጅቱ የመነሻ ሂሳብ (Dec 9/2013) የተመለከተው ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፣ ይህ የመነሻ ሂሳብ በድርጅቱ ዓመታዊ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ላይ እና በዓመቱ መጨረሻ July 7/2014 በሚታየው ሂሳብ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡

- ከላይ እንደተገለፀው ድርጅቱ የተመሠረተው የቀድሞውን የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ለሁለት በመክፈል ሲሆን፣ የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ አያያዝ በኮምፒዩተር የታገዘ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሲሆን፤ ምንም ዓይነት ክፍፍል እንዳልተፈፀመ ሆኖ የቀጠለ ነው፡፡ በመሆኑም በድርጅቱ ከቀድሞ የተለየ የሂሳብ አመዘጋገብ ሥርዓት የለም፣ ለኦዲት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የተዘጋጁት ሂሳቡን በእጅ (Manualy) በመተንተን ከመሆኑና በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የሂሳብ እንቅስቃሴ በእጅ ተንትኖ መዘጋጀት ለስህተት የተጋለጠ ከመሆኑ አንፃር፤ እንዲሁም የሂሳብ መረጃዎቹን ከኮምፒውተር በመውሰድ ሂደት ሊታመንበት የሚችል የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ፣ የሂሳብ መግለጫዎች ከስህተት በፀዳ መልኩ ተዘጋጅተዋል ተብሎ ለማመን እንዲሁም ለማጣራት ሌላ አማራጭ ዘዴ መጠቀም አልተቻለም፣
- በገቢ ሂሳብ ላይ ሊታመንበት የሚችል የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ፣ የተጠየቁ የተለያዩ የሂሳብ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው ሌላ አማራጭ ዘዴ ስላልተገኘ በትርፍና ኪሣራ ሂሳብ የተመለከተው ገቢ ብር 1,586,218,866.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፣ በመሆኑም በዚህ ሂሳብ ላይ ሊደረግ የሚያስፈልግ ማስተካከያ ይኑር ወይም ያልተመዘገበ ገቢ ስለመኖሩ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው በቋሚ ንብረት ሂሳብ ሥር ከውጭ ምንዛሪ መዋዠቅ የተነሳ የተጠራቀመው ኪሣራ (Capitalized losses) ብር 1,241,416,980.00 መያዙ ከመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎች

ያፈነገጠ አሠራር በመሆኑና በሂሳብ መርሆዎቹ መሠረት ኪሣራው በወጪ ሂሳብ ውስጥ መካተት ነበረበት፤ይህም የዓመቱን ትርፍ በብር 1,241,416,980 ይቀንሳል/ዝቅ ያደርጋዋል።

- በክምችት ዕቃዎች ዋጋ ግምት (valuation of stock) ላይ የተዘረጋ የውስጥ፤ ቁጥጥር ስርዓት ባለመኖሩ በJuly 7/2014 የተመለከተው የክምችት ሂሳብ ብር 442,603,916.00 ትክክል ስለመሆኑ ሌላ ማረጋገጥ የሚቻልበት የኦዲት ዘዴ ባለማገኘቱ፣
- ከሕንፃ ተቋራጮች መያዣ ሂሳብ (Contractors Retation) በውጭ ምንዛሪ ተከፋይ ዕዳው በተከሰተበት ዕለት ባለው ተመን ወደ ብር ተመንዝሮ ብር 1,871,864,065.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ቢሆንም፣ ይህ ከዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ያፈነገጠ ሲሆን፤ በደረጃዎቹ መሠረት ዕዳው መሰላት የነበረበት በሀብትና ዕዳ መግለጫው ዕለት በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን ላይ ተመስርቶ መሆን ነበረበት፣ ይህም መጠን በምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መወሰን /መገመት አዳጋች በመሆኑ፣
- ከዓመቱ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ ላይ ብር 43,377,511.00 ወደ ተከፈለ ካፒታል እንደተላለፈ ተመልክቷል። ሆኖም ይህ የሂሳብ ዝውውር ሥልጣን በተሰጠው አካል ስለመፈቀዱ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ የሂሳቡ ዝውውር ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም።

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ጉልህነት የተነሳ ሂሳቡ ላይ አስተያየት ለመስጠት በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ስላልቀረበ በሂሳብ መገለጫዎቹ ላይ አስተያየት አንሰጥም በማለት ኦዲተሮቹ ገልፀዋል።

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በዝርዝር ባቀረበው የሥራ አመራር ሪፖርት መሠረት ሂሳቦቹን በማስተካከል እንደ አዲስ ለተመሠረተው ኮርፖሬሽን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር እና የሚመለከታቸውም አካላት ይኸው ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተሉት ይገባል፡፡

4.1.2 የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት

የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት ከ Dec.9/2013 እስከ July 2014 እ.አ.አ ያለው ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ በሂሳቡ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ገልጿል፡፡

- አገልግሎቱ በDec. 9/2013 እ.አ.አ የተመሠረተው ከቀድሞው የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ለሁለት በመከፈሉ ሲሆን ፣ የኮርፖሬሽኑ መብትና ግዴታዎች ለአገልግሎት ተላልፏል፡፡ ነገር ግን ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ስለመብትና ግዴታዎቹ ክፍፍል የቀረበ ሪፖርት ወይም መግለጫ ያልቀረበልን በመሆኑ፣ በDec. 9/2013 እ.አ.አ ለመነሻ የሆነው ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ይኸው የመነሻ ሂሳብ ጉዳይ በዓመቱ መጨረሻ (July 2014) በተመለከቱት ሂሳቦችና ሂሳብ አፈፃፀም ላይም ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡
- ከላይ የተመለከተው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የአገልግሎቱ ሂሳብ የኮርፖሬሽኑን በኮምፒውተር የተደገፈ ሂሳብ አያያዝ (ምዝገባ) ምንም ክፍፍል እንዳልተከናወነ አድርጐ በመውሰድ ቀጥሏል፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱ የተለየ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት የለውም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎቹ በእጅ (Manually) የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ የሂሳብ ዝውውሮቹ በጣም ከፍተኛ እና ብዛት ያላቸው ከመሆኑ የተነሳ ስለመረጃዎች አያያዝ የተዘረጋ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ባለመኖሩ ጉልፅ የሆነ ስህተት በሂሳብ መግለጫዎቹ ዝግጅት ወቅት ተከስቶ እንደሆነ ከስህተት ነጻ ነው በማለት ልናረጋግጥ የምንችልበት ሌላ አማራጭ ዘዴ አልተገኘም፡፡
- በገቢ ሂሳብ አሰባሰብ ላይ ሊታመንበት የሚችል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በትርፍና ኪሣራ የተመለከተው የገቢ ሂሳብ ብር 1,057,479,244.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ከአዳዲስ መስመሮች ዝርጋታ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ብር 54,564,593.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ሲሆን፤ ይህን ሂሳብ በሕግ በማስገደድ ሊሰበሰብ የሚችል ስለመሆኑና ሂሳቡም በትክክል ስለመሰላቱ ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂና አስተማማኝ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው ይህ ሂሳብ በትክክል የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አለመቻሉ፤
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ የተቋራጮች መያዣ/Contractors's Retation/ ብር 278,779,134 ተከፋይ ዕዳው በተከሰተበት ዕለት ባለው የውጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ብር ተመንዝሮ የተካተተ ቢሆንም፤ ይህ ከዓለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች ያፈነገጠ ሲሆን በደረጃዎቹ መሠረት ዕዳው መሰላት የነበረበት በሀብትና ዕዳ መግለጫው ቀን Dec 9/2013 እ.አ.አ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን ላይ ተመስርቶ መሆን ነበረበት፡፡
- ያልተሰበሰቡ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በሚል በሀብትና ዕዳ መግለጫው ብር ብር 2,203,977,205 የተመለከተ ሲሆን፣ በሂሳቡ ላይ እምነት ሊጣልበት የሚችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ ሂሳቡ ትክክል ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሌላ ዘዴ ባለመኖሩ፣
- በሂሳብ ዓመቱ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ላይ ብር 8,268,1498.00 ሂሳብ ወደ ተከፈለ ካፒታል እንዲዘዋወር ተደርጓል፡፡ ሆኖም ለዚህ የቀረበ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ባመኖሩ ስለ ዝውውሩ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ስለሂሳቡ የኦዲት አስተያየት መሰጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልጿል፡፡ በዚህ በጥር/2009 ዓ.ም ላይ የሂሳቡም ኦዲት በሁለት ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት እና ለአገልግሎቱ በመ/ቤታችን ለተፃፈ ደብዳቤ ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወስዱ የተገለፀ ቢሆንም የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

በመሆኑም አሁንም በቀረበው ኦዲት ሪፖርት መሠረት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግና የተቀሩት ሃሳቦችም ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

4.1.3 የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ

ሰኔ 30/2004 ዓ.ም የተጠናቀቀው የኤጀንሲው ሂሣብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ በሂሳቡ ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ገልጿል፡፡

- በተጠቃለለው ሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የክምችት ዕቃዎች (Stock) ብር 3,895,078,907.00 ሂሳብ ላይ የተዳረሰው የጤና ፕሮግራም ክምችት ዕቃዎች ብር 71,132,244.00 እና የተዘዋዋሪ መድኃኒት ፈንድ (Revolving Drug Fund) ክምችት ዕቃዎች ብር 5,881,333.00 ማስተካከያ በማድረግ ነው፡፡ ይህም ማስተካከያ የተደረገው በሂሣብ ምዝገባው በፒች ትሪ ሂሣብ አያያዝ ስርዓት (Peach tree Accounting System) እና በኤጀንሲው የክምችት አመዘጋገብ ስርዓት በቆጠራ የተገኘውን የክምችት ሂሣብ ለማስታረቅ የተደረገ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በሁለቱ በሂሣብ አያያዝ ሥርዓቶች ላይ የተፈጠረውን ልዩነት በማስረጃ ላይ የተመሠረተ አሳማኝ ምክንያት ባለመኖሩ የማስተካከያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በጤና ፕሮግራም ሂሣብ ላይ የተካተተው በጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች ብር 12,648,776.00 ለረጅም ጊዜ የቆየ እና ምንም የመጠባበቂያ ሂሳብ ያልተያዘለት በመሆኑ በሰኔ 30/2004 የተያዘውን የእርዳታ ሰጪዎች ፈንድ ሂሳብ በዚሁ ያህል የተጋነነ ሆኖ እንዲታይ ማድረጉ፣
- በተጠቃለለው የሀብት ዕዳ መግለጫ የተመለከቱት ተሰብሳቢ ብር 105,640,805.00 እና ተከፋይ ብር 99,489,376.00 በኤጀንሲው እና ቅርንጫፎቹ መካከል (Intra-branch accounts) ያለ ሂሣብ ሲሆን በመሠረቱ ይህ ሂሣብ ሲጠቃለል ምንም ቀሪ (Nill balance) ማሳየት

ነበረበት፡፡ ይህም ሂሣብ ለምን ሊታይ እንደቻለ በቂና አሳማኝ መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊቀርብ ባለመቻሉ በኤጀንሲውና ቅርንጫፎቹ መካከል የታየው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 128,657,751.00 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 153,437,700.00 በአብዛኛው የክምችት ዕቃዎች ሲሆን በሰኔ/2004 እና ቀደም ባሉት ዓመታት የታየ የቆጠራ ማነስ እና ብልጫ (shortage and overage) ተብሎ በጊዜያዊነት/Suspense/ የተያዘ ሂሳብ ነው፡፡ በመሆኑም በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 896,747,976.00 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 949,116,698.00 ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ ወይም መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አለመቻሉ ፤
- በዓመቱ መጨረሻ የልማት አጋር ድርጅቶች ፈንድ በተያዘው (donor's fund) ላይ ተሰብሳቢ በብር 65,522,764.00 እና ተከፋይ በብር 22,894,219.00 ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን፤ለማስተካከያው አስፈላጊነት እንዲሁም በቂ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፤ በመሆኑም የዚህን ማስተካከያ አስፈላጊነትና ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተዘዋዋሪ የመድኃኒት ፈንድ ሂሳብ ላይ የተካፋይ ሂሳብ ብር 205,591,699.00 በዋና መ/ቤት፤ በመቀሌ፤በጉለሌ እና ደሴ ቅርንጫፎች ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየና አሁንም ሳይጣራ ያለ ሂሳብ ነው፤ በመሆኑም ይህ ሂሳብ በእውነትም የኤጀንሲው ዕዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም::
- በተዘዋወሪ የመድኃኒት ፈንድ ሂሳብ ላይ በድምሩ ብር 22,256,882.00 ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን (Abnormal/debit balance) በተከፋይ ሂሣቡ ላይ ይታያል፡፡ ይህ ያልተገባ ሚዛን

ለምንና እንዴት ሊታይ እንደቻለ ምንም ማብራሪያ እንዲሁም ይህንን የሚያስረዳ የሂሣብ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የተከፋይ ሂሣብ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ማረጋገጥ አልተቻለም፤

- በተጠቃለለው የሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው ብር 443,867,155.00 ኤጀንሲው በሚያንቀሳቅሳቸው ፈንድ መካከል ያለ ሂሣብ (Intra-fund accounts) ተብሎ ቢያዝም፤ በመሠረቱ ይህ ሂሣብ ሲጠቃለል ምንም (Nill balance) ማሳየት ነበረበት፡፡ በፈንድ መካከል ያለው ሂሣብ ልዩነት በተመለከተ በቂ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ሊቀርብልን ባለመቻሉ ይህ ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተጠቃለለው ሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው ተከፋይ የመንግሥት ድርሻ (Dividend payable) ብር 23,711,964.00 እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብር 30,149,257.00 ለረጅም ጊዜ የቆየ ሂሣብ እና የቀድሞ የመድኃኒት እና የሕክምና መሳሪያዎች አስመጪና ጅምላ ሻጭ ድርጅት የተጣራ ትርፍ እንደነበር፤ ይህም በደንብ ቁጥር 107/1996 መሠረት የመንግሥት ዲቪደንድ 60%፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ 40% ሊከፋፈል ይገባ ነበር፡፡ ሆኖም ምንም ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ይህ ክፍፍል ለምን እንዳልተደረገ፣ የቀድሞ ድርጅት መብትና ግዴተዎች ወደ ኤጀንሲው ስለተላለፉ ይህ ዕዳ ለምን ለመንግስት እንዲከፈል እንዳልተደረገ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ በቀረቡት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት እንዳልተቻለ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ በቀረበው ሪፖርት መሠረት ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ፤ እንዲሁም የኤጀንሲው የሂሣብ ኦዲት በ4 ዓመታት ወደኋላ የቀረ በመሆኑ

መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ እንዲደረግ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለኤጀንሲውና ለሚመለከታቸው መ/ቤታችን ማሳሰቢያ ልኳል፡፡

በመሆኑም ኤጀንሲው በሂሣብ አያያዝና ንብረት አስተዳደሩ በኩል ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት በመስጠት አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.1.4 <u>ኢትዮ- ቴሌኮም</u>

ሰኔ 30/2014 እ.ኤ.አ የተጠናቀቀው የኢትዮ-ቴሌኮም ሂሣብ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ ብር 12,909,725,059.00 የቋሚ ንብረቶች ዋጋ በሚል ተመልክቷል፡፡ ሆኖም በሂሣብ መዝገቦች የተመዘገበው ዋጋ ያለውን ሁኔታ በትክክል የሚያሳይ ስለመሆኑ ሊታመንበት የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ እና በቂ እና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረቶች ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑና ማስተካከያ ያስፈልገው እንደሆነ/ በምን ያህል? እንደሆነ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው በሥራ ሂደት ላይ የሚገኙ የካፒታል ሥራዎች (Capital works in progress) ለበርካታ ዓመታት ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው ሂሣብ ሲሆኑ፣ ሥራዎቹ በርግጥም በስራ ላይ ስለመኖራቸው፣ አሁንም በስራ በሂዳት ላይ ስለመሆናቸው የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ፣ በሂደት ላይ ያሉ የካፒታል ሥራዎች የተባለው ሂሳብ በትክክል ስለመገለፁ፣ ማስተካከያ ያስፈልገው እንደሆነም/ በምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ (ለመወሰን) አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- በሀብትና በዕዳ መግለጫው ከተመለከተው የክምችት ዕቃዎች ሂሣብ ብር 6,214,746,961.00 ውስጥ ብር 5,013,931,418.00 እ.ኤ.አ. በሰኔ 30/2014 በሂሣብ ምዝገባው መሠረት ዕቃዎች (materials) በሚል

ነው፡፡ ሆኖም ለአንዳንዶቹ የዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት ወይም ሌላ የዋጋ ትመና ማስረጃ ባለመቅረቡ ወይም ሌላ አማራጭ የዕቃዎቹን ዋጋ (valuation) ማግኘት ወይም ስለመኖራቸው ማረጋገጥ የሚቻልበት ዘዴ ባለመኖሩ፤ ቀሪው የክምችት ዕቃዎች ብር 1,201,015,273.00 ረጅም ጊዜ በጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች (goods in transit) የሚል ነው፡፡ በጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች የተባለውን የሚያስረዳ፣ እነዚህ ዕቃዎች አሁንም በጉዞ ላይ ስለመሆናቸውና ስለመኖራቸው በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም የክምችት ዕቃዎች ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በተሰብሳቢ ሂሣብ ላይ የሚታይ በርካታ ያልተገባ ሚዛን (Abnormal balance - credit) የሚይ ሲሆን በሀብትና ዕደ መግለጫው በተመለከተው ተሰብሳቢ ውስጥ ብር 1,200,000,00.00 በማይገባ ሚዛን በክሬዲት ተመዝግቦ የታያል፡፡በተጨማሪም ለኦዲት ስራው ሊታመንበት የሚችል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ለሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ አልተዘረጋም፡፡ በሀብትና ዕደ መግለጫው የተመለከተው ተሰብሳቢ ብር 6,389,318,338.00 በሙሉ ሊሰበሰብ ስለመቻሉ በቂና አሰተማመኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ፤ በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ፤ በምንስ ያህል እንደሆነ ለመወሰን አልተቻለም፡፡
- በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ላይ ሊታመንበት የሚችል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ለኦዲቱ ዓላማ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ በሀብትና ዕዳ መግለጫ በተመለከተው የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ብር 6,608,082,312.00 ላይ ለመድረስ ያልተገባ ኔጌቲቭ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ሚዛን (Abnormal negative balance) ለምን እንደተቀነሰ፣ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ለማወቅ ባመቻሉ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና በባንክ ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በድርጅቱ ምስረታ ዕለት የተመለከተው የተከፈለ ካፒታል ብር 5,000,000,000.00 ሲሆን፤ በተጣራ ሀብት የተመዘገበው ግን ብር

4,749,718,661.00 ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም የብር 1,100,000,000.00 ወጪ ከተመዘገበው የተከፈለ ካፒታል ላይ ተቀናሽ ተደርጓል፡፡ ይህም ቅናሽ ለምን እንደተደረገ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም በሀብትና ዕዳ የተመለከተው የተከፈለ ካፒታል ሂሳብ በትክክለኛው ሁኔታ አልተገለጸም፡፡

- በተከፋይ ሂሣቦች ላይ በርካታ ያልተገባ ሚዛን (Abnormal debit balances) የሚታይ ሲሆን፣ በጥቅሉ ከብር 1.2 ቢሊዮን በላይ በተከፋ ሂሣብ ላይ ተመዝግቦ ይታያል፡፡ በተከፋይ ሂሣቡ ላይ በቂና አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው ተከፋይ ሂሣብ ብር 8,078,455,232.00 ትክክለኛ ተከፋይና የድርጅቱ ዕዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በሂሣቡ ላይም ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም፡፡
- በትርፍና ኪሣራ መግለጫው የተመለከተው የገቢ ትርፍ ግብር ብር 2,619,489,926.00 ሲሆን፣ በሀብትና ዕዳ መግለጫው ላይ ተመጣጣኝ ዕዳ (ተከፋይ) ተብሎ አልተገፀም፡፡ ይህም በሀብትና በዕዳ መግለጫ ላይ የተጣራ ሀብትን በዚሁ ልክ ከፍ ብሎ እንዲታይ (over state net asset) አድርጓል፡፡
- ከሂሣብ መግለጫው ጋር በተያያዘው ማብራሪያ መሠረት ኢትዮ-ቴሌኮም በሚከተለው የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲ የትርፍ ግብር ለማስላት የሚጠቀሙ፣ በሂሣብ መግለጫዎቹ ያለው ሀብትና ዕዳ መጠን እና ለታክስ መሠረት የሚሆኑትን ተመጣጣኝ ግብር የሚጣልበት ትርፍ ላይ በጊዜያዊነት የሚከሰተውን የግብር ልዩነት በመዘግየት ነው፡፡ ሆኖም በትርፍና ኪሣራ ላይ የተቀነሰው ወይም የተሰላው የዘገየ ታክስ በሂሣብ መግለጫዎቹ አልተመለከተም፡፡ የዘገየ ታክስ ዕዳ ባለበት መጠን እንዲቆይ የተደረገበት ምክንያት በበቂ ማብራሪያ የተደገፈ ወይም ያልተቀነሰበት ምክንያት ባለመጠቀሱ የዓመቱ ትርፍ ግብር እና የዘገየ ታክስ በትክክል ስለመሰላታቸው ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይም በተጠቀሱት ምክንያቶች በኢትዮ-ቴሌኮም ተዘጋጅተው በቀረቡት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የድርጅቱ ሂሣብ ኦዲት በሁለት ዓመታት ወደኋላ የቀረ ነው፡፡

እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤- በሚለው አምድ ስር የተከፈለ ካፒታል ብር 20,200,000,000.00 እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም፤ በምስረታ ወቅት የተከፈለ ካፒታል ብር 4,749,718,661.00 ብቻ በመሆኑ ትኩረት የሚሹ ጉዳይ ነው በሚል ገልጸውታል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ስለኢትዮ ቴለኮም የሂሣብናበንብረት አያያዝ፣ የሂሣቡ ወቅታዊነት በተመለከተ የተነሱት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጣቸውና በአፋጣኝ እንዲስተካከሉ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.1.5 <u>ኬሚከል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን</u>

June 30/2014 G.C የተጠናቀቀው የኬሚካል ኮርፖሬሽን ሂሣብ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ክርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የቋሚ ንብረቶች ሂሳብ

  ብር 5,278,120,786.00 ውስጥ የተካተተው የተጣራ የምዝገባ ዋጋው (Net book value) ብር14,681,879.00 የሆነ ንብረት ስለመኖሩ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተመለከተው የቋሚ ንብረቶች ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የፋብሪካ ተከላ ዋጋ (Plantation cost) ብር 64,241,019.00 የተመለከተ ሲሆን፣ ከዚህ ሌላ ስለጉዳዩ የተሰጠ ማብራሪያ (መረጃ) ባለመኖሩ ወይም በምን ሁኔታ ዋጋው እንደተጠራቀመ ወይም እንዴት የእርምጅና ተቀናናሽ ሊሰላለት እንደሚገባ የታወቀ ጉዳይ የለም፡፡ በመሆኑም የሂሣብ መግለጫዎቹን ለመረዳት የሚያስችሉ በቂ መረጃዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የተለያዩ ተሰብሳቢ ሂሣቦች በድምሩ ብር 10,118,254.00 ለረጅም ጊዜያት ሳይሰበሰብ የቆየ በመሆኑ፣ በሕግ አስገዳጅነት ሊሰበሰቡ የሚችሉበት ሁኔታ የሚያስረዳ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ስለትክክለኛነታቸው ማረጋገጫ ማግኘት አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ጥሬ ገንዘብ ብር 2,889,417.00 ሲሆን፣ በኮርፖሬሽኑ የሂሣብ ምዝገባ በሚታየው በዚህ መጠንና እና ባንክ መካከል ልዩነት እንዴት እና በምን ሁኔታ ሊከሰት እንደቻለ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የተለያዩ ተከፋይ ሂሣቦች በድምሩ ብር 16,279,515.00 ለበርካታ ዓመታት የቆየ ሲሆን ሳይከፈል የቆየበት ምክንያት የሚያሳይ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ፣ ስላልቀረበ የተመለከተው ሂሣብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በሰኔ 30/2014 እ.አ.አ በተዘጋጀው የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፣ የማሻሻያ ሀሳቦቹን ትግበራ መርሐ-ግብር በኮርፖሬሽኑ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ እንዲደረግ በማለት ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴርና ለሚመከለታቸው አካላት በቁጥር ቸከ17/2 በ07/10/2008 ዓ.ም በመ/ቤታችን ለተፃፈው ደብዳቤ የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

በመሆኑም ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ በቀረበው ኦዲት ሪፖርት መሠረት የማስተካከያ እንዲወሰድና የሚመለከታቸው ሁሉ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

4.1.6 <u>በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የብሔራዊ የኒዩክለስ ፕሮጀክት</u>

June 30/2014 G.C የተጠናቀቀው የፕሮጀክቱ ሂሣብ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ውጤት እንደሚከተለው ነው፡፡

- ለኦዲቱ ዓላማ ሊውል የሚችል በሂሣብ አያያዝ ላይ ተገቢና አስተማማኝ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ፣
- ከሂሣብ መግለጫዎች ጋር በተያያዘው ማብራሪያ መሠረት <<ከጎማ ሽያጭ የተገኘ ገቢ በተክል ልማት ወጪ የዋለ ሀብት>> ተብሎ ተመዝግቧል፡፡ በሂሣብ አያያዝ ፖሊሲ መሠረት ይህ ትክክለኛውን ገቢ እና ወጪ የሚደብቅ ሲሆን፤ ገቢዎች እንደተገኙ ወጪወዎችም እንደተከሰቱ ሊመዘገቡ ይገባል የሚለውን መሠረታዊና ዘመናዊ የሂሣብ አያያዝ (Accrual Basis of Accounting) የሚቃረን አሠራር በመሆኑ፣
- በሂሣብ ዓመቱ መጨረሻ የተደረገ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ውጤት ባለመኖሩ ሌላ ለኦዲቱ ሥራ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል አሠራር ባለመገኘቱ በሀብት ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረቶች ሂሣብ ብር 8,150,139.00 ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሀብት ዕዳ መግለጫዉ ለወደፊት የዘገዩ ወጪዎች/Deferred Expenditure/ ብር 24,255,923.00 ሲሆን የዚህ ሂሣብ የወደፊት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያሳይ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ወይም ለምን ይህ ሂሳብ በወጪ በማያዝ ፋንታ እንደሀብት (Asset) እንደተያዘ ማብራሪያ ሊሰጠን ባመቻሉ ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የተክል ልማት ወጪ ተብሎ ብር 64,241,019.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ቢሆንም፤ ይህ ሂሣብ እንዴት እንደተጠራቀመ፣ ከሂሣቡ ጋር ያለው ግንኙነት፤ ዋጋው በእርጅና እየቀነሰ ሊሄድ የሚችልበትን የሚያስረዳ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ የሂሣብ

መግለጫዎቹን ግልጽና ሊረዱት የሚቻል እንዲሆን የሚየስችሉ ማብራሪያዎች ሊደረጉበት ይገባል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 3,172,957.00 ትክክል ስለመሆኑ፣ በቂና አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በሀብት ዕዳ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ጥሬ ገንዘብ ብር 2,889,417.00 ሲሆን፣ በኮርፖሬሽኑ የሂሣብ ምዝገባ በሚታየው በዚህ መጠንና እና ባንክ መካከል ልዩነት እንዴት እና በምን ሁኔታ ሊከሰት እንደቻለ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ብር 2,202,815.00 ከFAO የተገኘ እርዳታ በሚል ተይዟል፡፡ ሆኖም ይህንን የሚያስረዳ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ተከፋይ ሂሣብ ብር 4,505,346.00 ለበርካታ በዓመታት ሳይከፈል የቆየ ሲሆን፤ሳይከፈል የቆየበት ምክንያት የሚያሳይ በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ስላልቀረበ የተመለከተው ሂሣብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በፕሮጀክቱ በተዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድና መርሃ-ግብር አዘጋጅተው እንዲልኩ ለኮርፖሬሽኑ ለፃፍነው ደብዳቤ በቀድሞ አጠራር የብሔራዊ ኒኩለስ ፕሮጀክት ይባል የነበረው በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር የጎማ ዛፍ ልማትና ምርት ፕሮጀክት ተብሎ እንደሚጠራ ገልጸው በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ

ለመውሰድ መርሀ-ግብር አዘጋጅተው በቁጥር ኬኢ.ኮ22.30/08 ጥቅምት 22/2008 ዓ.ም ልኳል፡፡

በመሆኑም በተዘጋጀው መርሀ-ግብር እና በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የማስተከከያ እርምጃዎቹ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

4.1.7 <u>የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለሥልጣን</u>

July 7/2014 እ.ኤ.አ የተጠናቀቀው የባለስልጣኑ የሂሳብ መግለጫዎች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው ምክንያቶች ኦዲተሮቹ የዘረዘሩት እንደሚከተለው ነው፡፡

- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የባለሥልጣኑ ቋሚ ንብረት ሂሳብ አያያዝ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመዘርጋቱና ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴ መጠቀም ባለመቻሉ በዓመቱ መጨረሻ የሚታየው ቋሚ ንብረት በአካል ስለመኖሩ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሳብ ሚዛን የተቀነሳውና በትርፍና ኪሳራ መግለጫው በወጪ የተመለከተው የእርጅና ተቀናናሽ ብር 63,962,671.00 ነው፡፡ ይህ ሂሳብ የተሰላው በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ በቋሚ ዕቃዎች አጠቃላይ በድፍኑ ሲሆን፤ ቀደም ባሉት ዓመታት በመግዣ ዋጋውም ሆነ በግምታዊ የቆሚ ንብረቶች ዋጋ ላይ ምንም የእርጅና ተቀናናሽ ተደርጎ አይተወቅም:: ይህም ተቀባይነት ካለው የሂሣብ አያያዝ መርሆ ያፈነገጠ ሲሆን፤ አመራሩ የዋጋ ተቀናናሽ በእያንዳንዱ የቋሚ ንብረቶች ዓይነት የእርጅና ተቀናናሽ ማስላት ነበረበት፤ ቀደም ባሉት ዓመታት የነበሩት ንብረቶች ላይም የእርጅና ተቀናናሽ ተሰልቶ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡በመሆኑም በመግለጫው የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ ወይም በሂሳብ

በመግለጫዎቹ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ለውጥ መጠን ለማወቅ ወይም በምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ሊወስን አለመቻሉ፣

- ሌሎች ንብረቶች (others assets) በሚል ብር 30,130,399.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ሲሆን ባለሥልጣኑ በቂና አስተማማኝ የሆነ ማስረጃ ሊያቀርብልን ባለመቻሉ የንብረቶቹ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እና እሴት ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

- የክምችት ዕቃዎች በሚል በሀብትና ዕዳ መግለጫው ብር 30352086.00 የተመለከተ ሲሆን፤ የዚህን ዋጋ ዝርዝር የሚገልጽ ማስረጃ ስላልቀረበልን የክምችት ዕቀዎች ዋጋ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሣብ 7 July 2013 እና July 2014 እ.አ.አ በቅደም ተከተል ብር 85,566,643.00 እና ብር 42,667,615.00 ሂሣብ ምንም የመጠባበቂያ ሂሣብ ያልተያዘበትና ማብራሪያ ያልተገኘለት በመሆኑ ትክክልኛ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴ የምንጠቀም ባለመኖሩ መጠኑ ትክክል ስለመሆኑም ሆነ ሊሰበሰብ የሚችል ሂሣብ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ሂሣብ ብር 31,080,676.00 ሲሆን በባለሥልጣኑ ምዝገባ እና በባንክ ሚዛን መካከል ብር 4,889,451.00 ልዩነት የሚታይ እና በቂ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ሊቀርብለት ያልቻለ መሆኑ ፤ በእኛ አስተያየት በሀብትና ዕዳ የተመለከተው ሂሣብ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልቻለም፡፡

- ለተከፋይ ሂሣብ አያያዝ የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ በተከፋይ ሂሣብ የተመለከተ ብር 9,316,556.00 ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል የኦዲት ዘዴ ባለመኖሩ ሂሣቡ ትክክል

ስለመሆኑ እውነተኛ ተከፋይና የባለሥልጣኑ ዕዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፤ናቸው

ከላይ በተመለከቱት መሠረታዊ የሆኑ ጉድለቶች የተነሳ በባልሥጣኑ የሂሣብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በባለሥልጣኑ ሂሣብ አያያዝ ላይ ተደጋጋሚ ችግሮች በመኖራቸው እንዲስተካከል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ተግባራዊ አለመደረጉን፤ የሂሣብ ኦዲቱም በ2 ዓመታት ወደኋላ የቀረ መሆኑ ተውቋል፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግ መ/ቤታችን ለባለሥልጣኑና ጉዳይ ለሚመለከታቸው ተገቢው እርምጃ ተወስዶ ማስተካከያ እንዲደረግ ቀደም ሲል ለፃፍነው ደብዳቤ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ባለሥልጣኑ በአስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስቧል፡፡

ባለሥልጣኑም በኦዲት ሪፖርቱ በሰጠው ምላሽ በአንድ በኩል ችግሩ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የመጣ እንደሆነና አንዳንዶቹ ደግሞ ከባለሥልጣኑ የመወሰን አቅም በላይ መሆናቸውን የገለፀ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኦዲተሮቹ ችግሮቹን አሁን አገዘፉት ይህ የአሁኑ አመራር ኃላፊነት አይደለም የሚል ምላሽ ሰጥተው እርምጃ ለመውሰድ እንቅስቃሴ መጀመሩን በነሐሴ/2007 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም የሂሣብ አያያዝ ድክመት የአሁኑም ሆነ የቀድሞ አመራር ተገቢውን ማስተካከያ የማድረጉ ኃላፊነት አሁን ያለው የበላይ አመራር በመሆኑ ተጠያቂ የሚሆን የቀድሞው አመራሩም ቢሆን፤ እንዲጠየቁ የማድረግ ኃላፊነት የሚወስደው አሁን ባለው አመራሩ መሆኑ ታውቆ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ወደኋላ የቀሩት ዓመታት ሂሣብ ለኦዲት እንዲቀርቡ ተደርጎ የኦዲቱ ውጤት እንዲገለጽ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.2. ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው

4.2.1 የግዮን ሆቴሎች ድርጅት

June 30/2016 እ.አ.አ የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሣብ በ ዘመድሁን እና ኩባንያው ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው ኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- በሀብት ዕዳ መግለጫው የተመለከተው በድምሩ ሀብት ብር 19,956,219.00 እና ዕዳዎች በድምሩ ብር 2,649,453.00 የድርጅቱ ሀብት እና ዕዳ /ግዴታ/ ያልሆነ ሂሣብ የተካተተ በመሆኑ፣ ይህም ከዓለም አቀፍ የሂሣብ ደረጃዎች ያፈነገጠ በመሆኑ፣ ሥራ አመራሩ እናዚህን ከሀብትና ዕዳው መግለጫዎች ውስጥ ቢያስወጣ ኖሮ በJune 30/2016 የተመለከተውን ሂሣብ በብር 17,306,766.00 ያነሰ ያደረገው የነበረ በመሆኑ፣
- June 30/2016 በተመለከተው ተከፋይ ሂሣብ ብር 2,998,895.26 ለበርካታ ዓመታት ሳይከፈል የቆየ እና ለዚህም በቂና አስተማማኝ ማብራሪያ ሊሰጥ ባለመቻሉ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የሂሣብ መግለጫዎቹ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ዝግጅት ደረጃዎች መሠረት ስላልተዘጋጁ የድርጅቱን ሀብትና ዕዳ የሥራ አፈፃፀም እና የገንዘብ ፍሰት በትክክል አያሳዩም በማለት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

መ/ቤታችን ድርጅቱ እና የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱና ማስተካከያ እንዲደረግ በማለት ለጻፍነው ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ለቀረበው ኦዲት ሪፖርት ለጻፍነው ደብዳቤ ድርጅቱ በሰጠው መልስ ሂሣቦቹ ቀደም ሲል በድርጅቱ ሥር ይተዳደሩ ከነበሩትና አሁን ወደግል ይዞታ የዞሩት ሆቴሎች ሂሣብ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለፅ ማስተካከያ ለመድረግ መርዓ ግብር አዘጋጅቶ የላከ ቢሆንም ተግባራዊ ስልልተደረገ በዚህ ሪፖርትም ቀርቧል፡፡

በመሆኑም የድርጅቱ ሀብት ወይም ዕዳ ያልሆኑትን ሂሣቦች በማጥራት ከሂሣብ መግለጫዎች ማውጣትና ትክክለኛ የድርጅቱን ገጽታ የሚያሳይ ሂሣብ መግለጫዎች ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

5. ስለመንግስት ልማት ድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ፣ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

5.1 <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ</u>

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ ሳይይደረግ ለሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙበት መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ ያልተካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2 <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ ክምችት እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ ሳያደርጉ በሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች/ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በጊዜያዊነት/Suspense Account/ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝገቦ መቆየት የሚቻል

ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣

- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም ለምርት ግብዓት ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይደረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2.1 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋግሩ ተሰብሳቢው እየጨመረና ጊዜው እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ባለዕዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት/ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት በአብዛኛው የማይሳካ መሆኑ፤

- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአወሳሰዱ፣ አፈ.ቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው፣ መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለዕዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛ የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

5.2.2 <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፣ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፣ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ አንዳንዶቹ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ምንም ማስረጃ የሌላቸው፣ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የተደረገው የጥሬ

ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

5.2.3 <u>ተከፋይ ሂሳቦች</u>

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ማዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በወቅቱ እንዲከፍሉና ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

5.2.4 ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉት ቁጥጥር አናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፤ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፤ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፤ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

6. በመንግሥትና የልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሲሆን፣ በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡
ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠራት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈትና በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሳብ ማሳወቂያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣

- ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽ፣
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ
- የአንዱን በጀት ዓመት ፕሮጀክት ወጪ ሂሳብ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የፕሮጀክት ሂሳብ መዝገብ ያለመቋቋማቸው፣አልፎ አልፎም ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎቹን ለኦዲት አለማቅረብ፣
- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠንና በፈፃሚ መ/ቤት ወይም ቅ/ጽ/ቤት ገቢ የሆነው/ የተመዘገበው ሂሳብ መካከል አልፎ አልፎ ልዩነት መኖሩ፣
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ንብረቶች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ ሂሳብ አያያዝ የተመለከቱት ችግሮች እንዲስተካከሉ በየኦዲት ሪፖርቶቹ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ፣የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ስለተግባራዊነቱ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።

7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

7.1 የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- በውስጥ ኦዲተሮች ስራውን በጥልቀት ያለመከታተልና በሚያቀርቡት ግኝቶች ላይም እርምጃ አለመውሰድ፣
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ለሂሳብ
- ስራው በቂ ትኩረት አለመስጠትና በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

7.2 ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣ የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ቅልጥፍናና የውጤት ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣ ያስችላል፡፡ በመሆኑም፣

- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት በተሞ፤ ሁኔታና በእንክብካቤ አመቺ በሆነ ቦታ እንዲቀመጡና በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርቡ፣
- ለማንኛውም የድርጅቱ ንብረት በማንኛውም ጊዜ ኃላፊና ጠጠያቂው ግለሰብ ማን እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅበት ዘዴ እንዲቀየስ፡ለግለሰቦች ተደራራቢ ተግባርና ሃላፊነት በመስጠት ለምዝበራ አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር በተለይ

በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፤ በንብረትና ገንዘብ አጠባበቅ ረገድ የማያሻማ ግልጽ የሆነ ስራ ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፤

- ከውስጥና፤ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም በኦዲት ሪፖርቶች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

8. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች

በመ/ቤታችን እስከ ሚያዝያ 30/2009 ዓ.ም ባለው መረጃ መሰረት ከ1 ዓመት በላይ ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ 50 የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የ4 ቱ ደግሞ በውል ያልተወቀ/ ዝርዝራቸው በአባሪ-37 ተመልክቷል/ እንዳሉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።